# እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!

## በምድረ በዳ ጉዞህ የእግዚአብሔርን ብርታትና ዓላማ በሕይወትህ መለማመድ

ጆን ቢቬሬ

እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!
የተሰኘው አጋዥ ዲቪዲ የታከለበት



የተከበርህ ወዳጄ፣

አዳጋች ፈተናዎችና ተግዳሮቶች ሲገጥሙህ፣ እግዚአብሔር ከሰጠህ ተስፋ ቃል በቀላሉ ልትዘናጋ ትችላለህ። ይህን መጽሐፍ የጻፍሁት፣ ሌላው ቀርቶ ምድረ በዳ ውስጥ እንኳ ቢሆን፣ እያንዳንዱ ወቅትና ቦታ የራሱ ዓላማ እንዳለው ላሳስብህና ላበረታታህ ነው።

እርሱ ለእኛ ላዘጋጀው ፍጻሜ ታላቅ ዕቅድ ዝግጁ ሊያደርገን እግዚአብሔር ልባችንን የሚያለሰልሰውና ባሕርያችንን የሚቀርጸው፣ በእንዲህ ዐይነት የምድረ በዳ ወቅትና ስፍራ ነው። እግዚአብሔር ዝም ያለህና ሓልዎቱ የራቀህ ሊመስልህ ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር አልተወህም — አንተ ውስጥ ሥራ እየሠራ ነው! በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ በድል ካለፍህ በኋላ በነገርህ ሁሉ ስለሚኖረው ዕድገት በሚከተሉት ገጾች ታነባለህ።

ይህ መጽሐፍ ለአንተ የተሰጠ ስጦታ ነው። ይህ ማበረታቻ ከሚያስፈልጋቸው ሌሎች አማኞች ጋር የዚህን መጽሐፍ መልእክት ለመከፋፈል ነጻነት ይሰማህ። በራስህ ቋንቋ ሌሎች ብዙ ሕይወት ለዋጭ ጠቃሚ ነገሮችን ለማውረድና ለማጥናት **CloudLibrary.Org** ጐብኝ።

አሁን ካላችሁበት የምድረ በዳ ልምምድ ውስጥ ከእርሱ ታላቅ ኀይልና ሥልጣን ጋር እንድትወጡ፣ የበለጠ ርኅራኄ እንዲኖራችሁና በትክክል ድምፁን መስማት የምትችሉበት ሁኔታ ውስጥ እንድትሆኑ ጸሎቴ ነው። ወርቅ በእሳት እንደሚጠራ፣ የእናንተም መጥራት ሂደት ንጹሑን ወርቅ እንዲያስገኝ እጸልያለሁ።

ምንጊዜም ቢሆን የእርሱ ተስፋ ፊት ለፊታችሁ ይሁን፤ የጀመራችሁትን በተገቢው ሁኔታ ፈጽሙ!

ተባረኩ!

ጆን



**ጆን ቢቨሬ**
JohnBevere@ymail.com

CloudLibrary.org
MESSENGER INTERNATIONAL
MessengerInternational.org

# እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!

በምድረ በዳ ጒዞህ
የእግዚአብሔርን ብርታትና ዓላማ
በሕይወትህ መለማመድ

# እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!

በምድረ በዳ ጉዞህ
የእግዚአብሔርን ብርታትና ዓላማ
በሕይወትህ መለማመድ



ጆን ቢቨሬ

ትርጉም ተስፋዬ መስፍን

*God, Where Are You?!. Amharic, by john P.Bevere*
*MessengerInternational.org*
*© 2019 Messenger International*
*Originally published in English as God, Where Are You?!*
*A previous version of this title was published in 1992 under the title:*
*Victory in the wilderness.*
*This updated version offers new and revised content from the author.*

*Additional resources in Amharic and many other languages by*
*John and Lisa Bevere are available for free download at:*
*CloudLibrary.org*

*To contact the author: JohnBevere@ymail.com*
*This book is a gift from messenger International and is*
*NOT FOR SALE*

*Translated by – Tesfaye Mesfin*
*Origination by – Betelhem Minas*

*Printed in Ethiopia*

**እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?! በጆን ቢቨሬ**
*MessengerInternational.org*
*© 2019 Messenger International*
**መጀመሪያ** *God, where Are You?!* **በተሰኘ ርዕስ በእንግሊዝኛ ታተመ**
**ቀደም ሲል በ1992 ይኸው ቅጂ**
*Victory in the Wilderness.* **በሚል ርእስ ታትሞ ነበር።**
**ይህ አዲስ ቅጂ ከደራሲው ተጨማሪና ወቅታዊነት ያላቸው ሐሳቦች ያቀርባል።**

**በጆንና ሊዛ ቢቨሬ የተጻፉ ተጨማሪ ጠቃሚ ነገሮችን በአማርኛ ከ***CloudLibrary.org* **ማውረድ ይቻላል።**

**ደራሲው ጋር ለመገናኘት** *JohnBevere@ymail.com*
**ይህ መጽሐፍ የሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ስጦታ ነው፤**
**አይሸጥም**

**ትርጉም — ተስፋዬ መስፍን**
**የኮምፒውተር ዝግጅት — ቤተልሔም ሚናስ**

**በኢትዮጵያ ታተመ**

# ማውጫ


መግቢያ ........ Vii

መቅድም ........ 1

1 ‹‹የት ነው ያለሽው?!›› ........ 5

2 ሌሎች ብዙዎች በዚያ አልፈዋል ........ 19

3 የምድር በዳ አስፈላጊነት ........ 31

4 ግንኙነታችን ........ 43

5 አዲስ ወይን ጠጅ ........ 57

6 ሰማያዊ ሽልማት ........ 77

7 የእግዚአብሔር አውራ መንገድ ........ 91

8 የውሃ ጉድጓድ አዘጋጁ ........ 111

9 ብርቱ ሆኖ ለመገኘት አስቀድሞ መሰልጠን ........ 129

10 ውሃ በምድረ በዳ ውስጥ ........ 145

11 የጌታ መንገድ አዘጋጁ ........ 161

12 ድል በምድረ በዳ ውስጥ ........ 179

የውይይት ጥያቄዎች ........ 201

ተጨማሪ ........ 207

# መግቢያ

እግዚአብሔር ጽዮንን በእርግጥ ያጽናናታል፤ ፍርስራሾቿንም በርኅራኄ ይመለከታል፤ ምድረ በዳዋን እንደ ኤደን፣ በረሓዋንም እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል፤ ተድላና ደስታ፣ ምስጋናና የዝማሬ ድምፅ በእርሷ ይገኛሉ።

- ኢሳይያስ 51፥3

ትንቢተ ኢሳይያስ ከብሉይ ኪዳን ነቢያት መጻሕፍት በጣም የምወደው ነው፡፡ ከላይ በተመለከትነው ምንባብ እግዚአብሔር ደረቅ ነገሮቻችንን ወደ ኤደን የአትክልት ቦታ መለወጥ እንደሚፈልግ እርግጠኛ እንድንሆን ኢሳይያስ ምሳሌያዊ አገላለጽ ይጠቀማል፡፡ ደረቁ አፈርና የምድረ በዳው ጠፍ ቦታ፣ እኛን እንደ ገና ለመሥራት የሚጠቀምበት መሣሪያ መሆኑንም ግልጽ ያደርጋል፡፡ ቀድሞ የነበረው ነገር መወገድ ወደ ፊት የሚሆነውን የሚያመላክት መገለጥ ይሆናል፡፡ እርሱ ወዳዘጋጀልን ተስፋ ቦታ ሊያደርሰን አባታችን በምናልፍባቸው ወቅቶች ውስጥ እኛን ያዘጋጀናል፡፡

በተስፋ መቁረጥ በረሓዎች ውስጥ ከባሌቤቴ ጆን ጋር አብሬ የማለፍ ክብር አግኝቻለሁ፤ በዚያ ጊዜ የምድረ በዳው አሸዋ ብዛትና ቃጠሎ ውጦ የሚያስቀረን መስሎ ነበር የታየን፡፡ በዚያ ወቅት ባለቤቴ አጥብቆ ሲጸልይ፣ ምክንያቱን ለማወቅ ጥረት ሲያደርግና አንዳንዴም ምርር ብሎ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!›› በማለት ሲጠይቅ በቅርብ ሆኜ የመታዘብ ዕድል አግኝቻለሁ፡፡

ስሕተታችን ምኑ ላይ እንደ ነበር ለማወቅ፣ የተለያዩ ሐሳቦችን በማውጣትና በማውረድ አብዛኛውን ሌሊት ያለ እንቅልፍ እናሳልፍ ነበር፡፡ ምናልባት እኛ የወሰድነው የተሳሳተ እርምጃ ወይም ማስተካከል ያለብን ጥፋት ይኖር ይሆን? በማለትም ራሳችንን እንጠይቅ ነበር፡፡

ገና ጠዋት በማለዳ ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት፣ ከእግዚአብሔር ለመስማትና መልስ ለማግኘት ጆን ለጸሎት ወደ ውጭ ይወጣ ነበር... ምናልባት ይህ ቀን ነገሮች ጥርት ብለው የሚወጡበትና ሁኔታዎችም

የሚለወጡበት ቀን እንደሚሆን ተስፋ በማድረግ ይጠባበቅ ነበር፡፡ እኔም እርሱ ወደ ቤት እስኪመለስ ድረስ በጉጉት እጠባበቅ ነበር፤ እርሱ በሚመለስበት ጊዜ እንቅልፍ ላይ የነበሩ ልጆቻችን ሙሉ በሙሉ ነቅተው ከመኝታቸው ይነሡ ነበር፡፡

‹‹ለመሆኑ፣ ከእግዚአብሔር የሰማኸው ነገር አለ?›› በማለትም ዘወትር እጠይቀው ነበር፡፡

ጆን ምንም እንዳልሰማ ራሱን በመነቅነቅ ይነግረኛል፡፡ በዚህ ጊዜ ልቤ በሐዘን ይሞላል፤ የነበረኝም ተስፋ ይጨልማል፡፡

ለመሆኑ ባለ ማወቅ የፈጸምነው ጥፋት ይኖር ይሆን? መጀመሪያውኑ በእርግጥ በእግዚአብሔር ምሪት መሠረት ነበር የተንቀሳቀስነው? ታዲያ፣ ይህ አሁን እየሆነ ያለው እንዴት ሊሆን ቻለ? ወደዚህ ቦታ የመራን እግዚአብሔር ቢሆን ኖሮ በእንዲህ ዐይነት አዳጋች ሁኔታ ውስጥ ግራ ስንጋባ ለምን ዝም ይለን ነበር?

አዎን፣ ያለነው ምድረ በዳ ውስጥ ነው፡፡

ዛሬ የተረዳሁትን ያኔ ተረድቼ ቢሆን ኖሮ፣ ነገሮች የተለየ ገጽታ ይኖራቸው ነበር፡፡ ያንን ጊዜ ልቤ ሳይዝልና እምነቴም ሙሉ እንደ ሆነ አልፈው ነበር፡፡ በዚያ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር እያጠራኝና ለበለጠው ነገር እያዘጋጀኝ መሆኑንም እገነዘብ ነበር፡፡

ከዚህ ግንዛቤ አንጻር ይህ መጽሐፍ መንገድ መሪና የተለየ የእግዚአብሔር ስጦታ ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡ በእንዲህ ዐይነት ወቅት የምትማሩትን በማስተዋል ተቀበሉ፤ ወደ ፊት ለሚገጥማችሁ ማንኛውም ሁኔታ ይበልጥ ንቁዎችና ዝግጁዎች ያደርጋችኋል፡፡ ልባችሁ ይበርታ፤ አይዞአችሁ፤ ብቻችሁን አይደላችሁም፡፡

— ሊዛ ቢቨሬ
በ New York Times ከፍተኛ ተነባቢነት ያላቸው መጻሕፍት ደራሲና
የ Messenger International ተባባሪ መሥራች፡፡

# መቅድም

ይህ መጽሐፍ የእኔን የራሴንና ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሌሎች ብዙ ሰዎች የምድረ በዳ ጕዞ ይናገራል፡፡ መጨረሻው ግብ ላይ፣ ‹‹ደርሻለሁ›› ወይም እግዚአብሔር ለእኔ ያለውን ዓላማ ሁሉ ፈጽሜአለሁ ብዬ አላስብም፤ ይሁን እንጂ፣ ቀጥሎ በምታነቧቸው ገጾች ያሉት መልእክቶች እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላችሁ ፍጻሜ በመገሥገሥ ረገድ፣ ብርታትና ጉልበት እንዲሆኑዋችሁ ጸሎቴ ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ ሁሉን ያሚላና ያካተተ ጥናት ነው ብዬ አላስብም፡፡ በዚህ መጽሐፍ ያልተዳሰሱ ሌሎች ብዙ ነገሮች ይኖራሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ያለፍሁበት ልምምድና የምድረ በዳ ጉዞን በተመለከተ ዋና ዋና ነጥቦችን እንደሚሸፍን አስባለሁ፡፡ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለእናንተ ግልጽ ማድረግና መልእክቱ የእናንተም እንዲሆን፣ ለሕይወታችሁም ተግባራዊ ያደርገው ዘንድ ለመንፈስ ቅዱስ ተገቢውን ስፍራ መስጠት ነው፡፡

ይህ መጽሐፍ መንፈሳዊ ምድረ በዳ ወይም በረሓ ምን ማለት እንደ ሆነና ምን ማለት እንዳልሆነ፣ ዓላማና ጥቅሙ ምን እንደ ሆነ ይገልጻል፡፡ በምድረ በዳ በምታሳልፉት ወቅት እነዚህ ምሳሌዎች፣ ምክሮችና ትምህርቶች በጥበብና በማስተዋል የመመላለስን አስፈላጊነት ግልጽ እንዲያደርጉላችሁ ጸሎቴ ነው፡፡

ይህን መጽሐፍ ስታነቡ ምሳሌ ሊሆኑ የሚችሉ አብዛኞቹ ግላዊ ነገሮቼ የተፈጸሙት በመጀመሪያዎቹ ሁለት ኀላፊነቶቼ ወቅት ዓመቶች መሆኑን ትረዳላችሁ፡፡ የመጀመሪያው፣ ፓስተሬንና ወደ እርሱ የሚመጡ እንግዶቹን በዳላስ ቴክሳስ ያገለገልሁበትን አራት ተኩል ዓመቶች ያካትታል፡፡ የምድረ በዳ ጉዞዬ የጀመረው ይህ አገልግሎቴ ከማብቃቱ በፊት በነበሩት የመጨረሻዎቹ አሥራ ስምንት ወሮች ነበር፡፡ ሁለተኛው፣ በፍሎሪዳ አንድ ቤተ ክርስቲያን የወጣቶች ፓስተር በነበርሁበት ሁለት ዓመት ተኩል ውስጥ ነበር፡፡ ይህ የምድረ በዳ ጕዞዬ በጣም ከባድ ነበር፤ በዳላስ በነበርሁ ጊዜ ያለፍሁበትን ከዚህኛው ጋር ሳነጻጽረው የሽርሽር

ጉዞ ያህል ቀላል ያደርገዋል፡፡ ምናልባት ያልተለመደ ቢመስል እንኳ ይህኛው ከባድ የምድረ በዳ ጉዞዬ የወሰደው ጊዜም አስራ ስምንት ወሮች ነበር፡፡

ከዚያ ወዲህ በሕይወቴ ያለፍሁባቸው የምድረ በዳ ወቅቶች ይኖሩ ይሆን? አዎን ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያሉ ወቅቶች በሚመጡበት ጊዜ ስለ ምንነታቸውና ምክንያታቸው የበለጠ ማስተዋልና መረዳት ነበረኝ፡፡ ስለዚህም እንደ መጀመሪያው ጊዜ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ምን እየሆነ ነው?›› ወይም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?›› በማለት በተደጋጋሚ አላለቀስሁም፤ ምን እየሆነ እንደ ነበርና የእኔም ምላሽ ምን መሆን እንደ ነበረበት ካለፈው ጊዜ ልምምዴ በሚገባ ተምሬ ነበር፡፡

በእንዲህ ዐይነት አዳጋች ወቅት ውስጥ እያለፉ ካሉት በጣም ብዙ ወንዶችና ሴቶች ጋር ተነጋግሬአለሁ፡፡ ብዙውን ጊዜ በንግግራችን ውስጥ የምሰማው ግራ መጋባትንና ተስፋ መቁረጥን ነው፡፡ ብዙዎቹ ምን እየሆነ እንዳለ ፍንጭ እንኳ የላቸውም፡፡ በቅርቡ እኔና ሚስቴ ሊዛ በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ሁለት የኢንተርኔት ስርጭቶች (ፖድካስቶች) አዘጋጅተን ነበር፤ ያገኘነውም ምላሽ በፍጹም ከጠበቅነው በላይ ነበር፡፡ ይህም መጀመሪያ የጻፍሁትንና Victory in the wilderness (ድል በምድረ በዳ ውስጥ) በሚል ርዕስ ታትሞ የነበረውን መጽሐፍ እንደ ገና እንድመለከት አደረገኝ፡፡

ያንን መጽሐፍ የጻፍሁት ከሰላሣ ዓመት በፊት ነበር፡፡ እንደ ገና በጥንቃቄ ሳነበው አሁን ላለንበትም ዘመን የሚሆን ትክክለኛ ትንቢታዊ መልእክት እንደ ነበር ተረዳሁ፡፡ ስለዚህም እኔና መጽሐፉን ያሳተመልኝ ድርጅት እነዚያ ዘመን የማይሽራቸው እውነቶች ላይ፣ ካለፉት ሰላሣ ዓመታት ወዲህ የተረዳኋቸውን አያሌ ግንዛቤዎች በመጨመር መጽሐፉን እንደ ገና ማዘጋጀት ጀመርሁ፡፡ ስለሆነም ይህ መጽሐፍ እንደ ገና ተሻሽሎ የቀረበ የቀድሞው መጽሐፍ ሳይሆን፣ ትኩስና አዲስ መልእክት ነው፡፡ ይህ አሁን እጃችሁ ውስጥ ያለው መጽሐፍ አሁን ያለውም ሆነ ወደ ፊት የሚመጣውን ትውልድ በእንዲህ ያለው ሁነኛ ወቅት እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ዘመን የማይሽረው መልእክት መሆኑን በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡፡

‹‹ለሁሉም ጊዜ አለው፤ ከሰማይ በታች ለሚከናወነው ለማንኛውም ነገር ወቅት አለው›› ተብሎ ተነግሮናል (መክብብ 3፥1 አመት)፡፡

በሕይወታችን የተለያዩ ወቅቶች ይኖራሉ፤ እያንዳንዱ ወቅት የራሱ ዓላማ አለው፡፡ በትክክልና በተገቢው ሁኔታ ለመንቀሳቀስ የወቅቱ ዓላማ ምን እንደሆነ መረዳት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አንድ ሰው በብርድ ጊዜ የሚለብሰውን በሙቀት ጊዜ አይለብስም፤ በበጋ ጊዜ የሚለብሰውንም በክረምት ጊዜ አይለብስም፡፡ አለባበሱን ከወቅቱ ጋር ማስማማት ይኖርበታል፡፡

በምድረ በዳ የምታሳልፉት የመጥራትና የመበርታት ወቅት ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን እንድትገነዘቡ በዚህ መጽሐፍ አማካይነት እናንተን መርዳት እፈልጋለሁ የዚህም ዓላማ እናንተን ማዘጋጀት ነው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የምንነጋገረው ከአገልግሎት ጋር የተያያዘ መሆኑን ብዙም ሳትቆዩ ትረዳላችሁ፡፡ በመሠረቱ፣ ሁላችንም የተለያየ ጥሪ አለን፤ አንዳንዶቻችን ለነጋዴነት፣ አንዳንዶቻችን ለምሁራዊነት፣ አንዳንዶቻችን ለጤና ባለ ሙያነት፣ አንዳንዶቻችን ለመንግሥታዊ ሥራ ተጠርተናል፤ ዝርዝሩ ማለቂያ የለውም፡፡ የእኔ ጥሪ አምስቱ የአገልግሎት መስኮች ናቸው፤ ታሪኮቼ የሚሽከረከሩትም በእነዚሁ ዙሪያ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ መርሖዎቹ እግዚአብሔር እናንተን ለጠራበት ማንኛውም የሕይወት ገጽታ ተግባራዊ መሆን ይችላሉ፡፡ ለንግድ ሥራ የተጠሩትም እንደ ወንጌል አገልጋዮች ሁሉ ለተጠሩበት መስክ ዝግጅት ያስፈልጋቸዋል፡፡ ይህ የትኛውንም የሕይወት አቅጣጫ ይመለከታል፡፡

መጽሐፉ ውስጥ፣ ‹‹ጒዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች›› የሚል አንድ ለየት ያለ ክፍል ጨምሬአለሁ፡፡ ይህ ክፍል በጣም አጭር፣ በግል የምታደርጉትና በተቻለ መጠን የምድረ በዳ ጊዜያችሁ ውጤታማ እንዲሆን የሚረዳችሁ ጠቃሚ ዕይታዎችና ማበረታቻዎች የያዘ ነው፡፡ መጀመሪያ እኔ ላይ እንደ ደረሰው እናንተም ወቅቱን ባለ ማወቅ እንዳትጒዱ፣ ብቻውን የእርካታ ምንጭ ወደ ሆነው ወደ እርሱ በምታደርጉት ጒዞ እንድትበረቱ ይህ መልእክት ነገሮችን ግልጽ እንደሚያደርግላችሁ አምናለሁ፡፡

እጅግ አክባሪያችሁ

ጆን ቢቨሬ

ጃንዋሪ 2019

# 1

# ‹‹የት ነው ያለኸው?!››

*በትዕግሥትና በተረጋጋ ሁኔታ በድርቅና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ስናልፍ፣ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር እንመሰክራለን፤ ጣፋጭ በሆነው መገኘቱ እኛን በሚጎበኝበት ጊዜ ግን እርሱ ለእኛ ያለውን ፍቅር ይመሰክራል።*

— Madame Guyon

... ወደ ምሥራቅ ብሄድ በዚያ የለም፤ ወደ ምዕራብም ብሄድ እርሱን አላገኘውም፤ በሰሜን እየሠራ ሳለ አላየውም፤ ወደ ደቡብ በሚዞርበትም ጊዜ ደብዛው አይገኝም።

— ኢዮብ 23፥8-9



ሰው ሁሉ ላይ እየተቆጣሁ ነበር፤ ምክንያቱ ግን ለእኔም ለራሴ ግልጽ አልነበረም። በዚያ ላይ ነገር ሁሉ የተበለሻሸ ነበር የሚመስለኝ።

ወንዱ ልጃችን ኤዲሰን ገና አስራ ስምንት ወሩ ነበር፤ ሌላው ቀርቶ ለእርሱ እንኳ ትዕግሥት አልነበረኝም።

ሚስቴ ሊዛ ላይ እጮኸባታለሁ።

በፓስተሬም ተስፋ ቆርጫለሁ።

አብረውኝ በሚሠሩ ሰዎች እበሳጫለሁ።

በጣም ግልጽ ለመሆን፣ በራሱ በእግዚአብሔር እንኳ ሳልበሳጭና ሳልሰናከል አልቀረሁም፤ አልፎ አልፎም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ለመሆኑ ምን እያደረግህ ነው?›› እላለሁ።

‹‹በሕይወቴ ስትሠራ የማላየው ለምንድነው?››

‹‹የሰጠኸኝ ተስፋ የማይፈጸመው ለምንድነው?››

‹‹ነገሮች እንዲህ የተበለሻሹት ለምንድነው?››

‹‹አንተ ስትናገረኝ የማልሰማው ለምንድነው?›› እላለሁ።

ደጋግሜም፣ ‹‹ለመሆኑ፣ የት ነው ያለኸው?›› በማለት አጉረመርማለሁ።

እናንተስ ብትሆኑ፣ እግዚአብሔር በጣም ቅርባችሁ እንደ ነበርና በሹክሹክታ ዐይነት ድምፅ ስሙን ስትጠሩ፣ ወዲያው ይመልስላችሁ እንደ ነበር የምታስታውሱት ጊዜ ሳይኖር ይቀራል?

ግን ውሎ አድሮ፣ ደጋግማችሁ ብትጠሩትም ከእርሱ ምንም መልስ የማትሰሙበት ጊዜ መጣ። እርሱ ከሕይወታችሁ ጨርሶ የጠፋ ያህል ይሰማችኃል። ምናልባት አሁን እንኳ፣ እንደዚያ ያለ ሁኔታ ውስጥ ልትሆኑ ትችላላችሁ፤ ከዓመታት በፊት እኔ አድርጌ እንደ ነበረው እናንተም፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ የት ነው ያለኸው?!›› በማለት እየጠየቃችሁ ይሆናል።

መንፈሳዊ ምድረ በዳ ውስጥ ብሆንም፤ ያንን አላወቅሁም ነበር። በዚያ ዘመን የምኖረው በዳላስ ቴክሳስ ነበር፤ እግዚአብሔር ኀጢአቱን ይቅር ያለለት ጥሩ የኢየሱስ ተከታይ መሆኔን ነበር

የማውቀው፡፡ ሆኖም እንደ አንድ አዲስ ክርስቲያን የመጀመሪያው የምድረ በዳ ሕይወት ውስጥ ገና መግባቴ ነበር፡፡

ይህ ከመሆኑ በፊት እኔ ወደ እርሱ ስጮኽ፣ ጌታ ወዲያውኑ እንደሚመልስልኝ ነበር የማስበው፡፡ በጣም ጥቃቅን ለሚመስሉ ጥያቄዎቼ እንኳ፣ ከእርሱ መልስ ማግኘቴንም አስታውሳለሁ፡፡ ሓልዎቱ ቅርቤ ነበር፤ በግልጽ መረዳት የምችለውና ብርቱ ነበር፡፡ አሁን ግን ምን እየሆነ እንደ ነበር ማሰብ እንኳ አልቻልሁም፡፡ በየቀኑ በጉልበቴ በመንበርከክ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ምን እየሆነ ነው? አንተ ሚሊዮን ኪሎ ሜትሮች ያህል ከእኔ እንደ ራቅህ ነው የሚሰማኝ!›› በማለት ያለ ማቋረጥ እጸልይ ነበር፡፡ አንድ ባንድ ሕይወቴን በመመርመር፣ ‹‹ለመሆኑ፣ ምን ዐይነት ከባድ ኀጢአት አድርጌ ይሆን?›› በማለት አስብ ነበር፡፡

አዎን፣ እንደ ማንኛውም ሰው ኀጢአት አደርጋለሁ፤ ሆኖም፣ ወዲያውኑ ንስሓ በማድረግ ጌታ ይቅር እንዲለኝ እጠይቃለሁ፡፡ እኔ እስከማውቀው ድረስ፣ ሆን ብዬና ተዘጋጅቼበት ዘወትር የምለማመደው ኀጢአት በሕይወቴ አልነበረም፡፡

እያለፍሁበት በነበረው ደረቅ የምድረ በዳ ልምምዴ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ስትናገረኝ የማልሰማው እስከ መቼ ነው?›› በማለት ደጋግሜ ጠይቄአለሁ፡፡

ከታላቁ የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከኢዮብ ጋር ራሴን አላስተካክልም፣ ይሁን እንጂ፣ በዚያ ወቅት የነበረኝ ምላሽ ከብዙ ዘመን በፊት ኢዮብ የነበረው ዐይነት ነበር፡፡ ከዚያ በፊት አጉል ድፍረት የሚመስለኝ አነጋገሩ አሁን ለእኔ የተለየ ትርጒም ይሰጠኝ ጀመር፡፡ አንዳንድ አነጋገሩ ጭው ያለ ምድረ በዳ ውስጥ ብቻውን የቀረ ሰው የሚሰማውን ዐይነት ጥልቅ ስሜት ያመለክታል፡፡

> <<...ወደ ምሥራቅ ብሄድ፣ በዚያ የለም፤
> ወደ ምዕራብም ብሄድ፣ እርሱን አላገኘውም፤
> በሰሜን እየሠራ ሳለ አላየውም፤
> ወደ ደቡብ በሚዞርበት ጊዜ ደብዛው አይገኝም፡፡>>
> (ኢዮብ 23፥8-9)

መጸለይ ቀጠልሁ፤ ግን ሰማይ ናስ የሆነ ያህል ነበር፡፡

ከዚያም የክርስትና ሕይወት አንድ ሕፃን ከሚያድግበት መንገድ ጋር እንደሚመሳሰል አንድ ቀን ጌታ አሳየኝ፡፡ ገና መንፈሳዊ ሕፃን ነበርሁ፤ አሁን ግን ወደ አዲስ ዕድገት እየተሻገርሁ ነበር፡፡ በዚያ ጊዜ ቤቴ ውስጥ ለዚህ ምሳሌ የሚሆን ነገር ነበረኝ፡፡ ኤዲሰን አስራ ስምንት ወሩ ነበር፡፡ እንደ አንድ ጥሩ እናት በሚያስፈልገው ሁሉ እርሱን ለመርዳት ሊዛ ሁሌም አጠገቡ ነበረች፡፡ ትንሽ ማለቃቀስ ሲጀምር፣ ወዲያውኑ ዕቅፏ ውስጥ አስገብታ ጡት በማጉረስ ምቾት እንዲጠበቅ ታደርጋለች፡፡

ኤዲሰን እንደ ማንኛውም ጤናማ ሕፃን ማደግ ጀመረ፡፡ በኋላ ግን እንደ ሌሎች አራት ልጆቻችን እርሱም ራሱን መመገብ መቻል ያለበት ጊዜ መጣ፡፡ መቼም በዚህ ጊዜ የሚኖረውን መዝረክረክ ሳትመለከቱ አልቀራችሁም፡፡ ሕፃናት በእጃቸው እያነሡ መመገብ ሲጀምሩ፣ ራሳቸውንና ያሉበትን ቦታ ሁሉ ያበለሻሹታል፡፡

እንደ በፊቱ እነርሱን መመገብ ስታቋርጡ ሕፃናት ይናደዳሉ፤ እናንተ ግን እንደ መልካም እናት ወይም አባት ኀላፊነታችሁን እየተወጣችሁ ነው፡፡ ራሳቸውን ለመመገብ ልጆቻችን በሚያደርጉት ጥረት አካባቢውን ሁሉ ማዝረክረክ ሲጀምሩ በፊት እንደምናደርገው እኛ ልንመግባቸው እንፈልጋለን፤ ይህ ግን ዕድገታቸውን እንደሚያሰናክል እናውቃለን፡፡ ልጆቻችን እንዲያድጉ መፍቀድ ነበረብን፡፡ መቼም፣ አስራ ስምንት ዓመት የሞላውን ልጅ በማንኪያ እያነሣን አንመግበውም!

ሕፃናት እያደጉ ሲሄዱ፣ እናንተ የምታደርጉላቸውም ድጋፍ መልኩን እየለወጠ ይመጣል፤ እንዲህ የምታደርጉት እንዲያድጉና በሳሎች እንዲሆኑ ለማበረታታት ነው፡፡ እግዚአብሔርም እንድናድግና መንፈሳዊ ብስለት እንዲኖረን በእያንዳንዳችን ተመሳሳይ ነገር ያደርጋል፡፡ ዳግም በተወለድን ጊዜ መንፈሳዊ ሕፃናት እያለን ስናለቃቅስ፣ ለተወሰነ ጊዜ ቶሎ ይደርስልን ነበር፡፡ በዚህ መሐል ጊዜ እያለፈ ሄዶ ወተት ብቻ የምንመገብበትን ጊዜ ስንሻገር፣ (ዕብራውያን 5፥12) እንድናድግና በሳሎች እንድንሆን በአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ እንድናልፍ ያደርጋል፤ እዚያ ሁኔታ ውስጥ ስንሆን ባለቃቀስን ጊዜ ሁሉ መልስ አይሰጠንም፡፡

መንፈሳዊ ዕድገትና በሳልነት ከሕፃንነት ጀምሮ እስከ ጉልምስና

ድረስ፣ አንድ ሰው ከሚያልፍበት ሂደት ጋር እንደሚመሳሰል እንዳስተውል ጌታ ከረዳኝ ወዲህ ነገሮችን በተለየ ሁኔታ ማየት ጀመርሁ፤ ያጠፋሁት ነገር ይኖር ይሆን? አሁን እያለፍሁበት ያለው ሁኔታ ለፈጸምሁት ኀጢአት ቅጣት እየተቀበልሁ ያለሁበት ጊዜ ይሆን? ወይስ በበለጠ ሁኔታ ኢየሱስን ለመከተልና ለማገልገል ዝግጁ እንድሆን እንዳች የምማረው ስላለ በምድረ በዳ ሕይወት እያለፍሁ ይሆን? በማለት ራሴን መጠየቅ ጀመርሁ፡፡

ኢየሱስ ላይ ተመሳሳይ ዐይነት ነገር ደርሶ እንደ ነበረም አስታወስሁ፡፡ በዮሐንስ ከተጠመቀና እግዚአብሔር አብም ስለ ማንነቱ ከመሰከረለት በኋላ፣ ወዲያውኑ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ወደ ምድረ በዳ ሄደ፡፡ በዚያ ጊዜ ኢየሱስ ለበደሉ እየተቀጣ አልነበረም፤ እንዲያውም እርሱ ምንም ዐይነት ኀጢአት አልነበረበትም፡፡

ስለዚህም በሁኔታው በጣም ተቆጥቼና ለራሴም እያዘንሁ በነበረበት በዚያ ወቅት፣ ምናልባት'ኮ ይህ የምድረ በዳ ልምምድ ለእኔ መስሎ እንደ ታየኝ መጥፎ ላይሆን ይችላል? በማለት አሰብሁ፡፡

## ለምድረ በዳ ሕይወት ያለን አስተሳሰብ

ኢየሱስን እየመሰልን መሄድ ከፈለግን፣ ፀባያችን እየተለወጠ መሄድ አለበት፡፡ ይህን ለማድረግ አብዛኛውን ጊዜ እግዚአብሔር የሚመርጠው ቦታ መንፈሳዊ ምድረ በዳ ነው፡፡ እዚያ በምንሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር በጣም የራቀን ይመስለናል፤ የገባልን ተስፋ ቃልም ባዶ ይሆንብናል፡፡ ሆኖም፣ ይህ የእኛ ስሜት እንጂ፣ እውነታው እንደዚያ አይደለም፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ እርሱ ምንጊዜም ቅርብ ነው፤ ምክንያቱም እርሱ እንደማይጥለንና እንደማይተወን ቃል ገብቷል (ዕብራውያን 13÷5)

የምድረ በዳ ሕይወት ነገሮች ስታልሙት ከነበረውና በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ቃል እንደ ገባላችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁበት በተቃራኒው እየሄዱ የሚመስልበት ጊዜ ነው፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ ምንም ዐይነት መንፈሳዊ ዕድገትና ብስለት አይሰማችሁም፡፡ እንዲያውም ቀድሞ ከነበራችሁበት ደረጃ እንኳ እንደ ወረዳችሁና ዝቅ እንዳላችሁ ነው የሚሰማችሁ፡፡ በዚያ ጊዜ የእርሱ መገኘት (ሓልዎት) የበለጠ

እውን ሊሆንላችሁ ሲገባ እንዲያውም ይደበዝዝባችኋል፡፡ የማትወደዱና ችላ የተባላችሁ ይመስላችኋል፡፡ ያ ግን እውነት አይደለም፡፡

መንፈሳዊ ምድረ በዳ ማንኛውም እውነተኛ የክርስቶስ ተከታይ የሚያልፍበት ሕይወት ነው፤ ሆኖም፣ እዚያ ውስጥ ስትሆኑ ብቻችሁን እንደ ሆናችሁ ይሰማችኋል፡፡ እያንዳንዱ የእግዚአብሔር ልጅ የምድረ በዳ ሕይወት መለማመዱ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እንደ አንድ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ጤናማ ዕድገት እንዲኖራችሁ ከተፈለገ በተደጋጋሚ በምድረ በዳ ውስጥ ታልፋላችሁ፡፡

ከዚያ ደረቅና ጠፍ ቦታ ቶሎ የምትወጡበት ሁኔታ ወይም የምታመልጡበት አቋራጭ መንገድ ባሳያችሁ ደስ ባለኝ ነበር፤ ግን በፍጹም እንዲህ ያለ ነገር የለም፡፡ ወዳጄ፣ እንዲህ መሆኑ መልካም ነው፤ ምክንያቱም ወደ ተስፋው ምድር የምንደርሰው በምድረ በዳ አልፈን ነው፤ ያንን ጊዜና ወቅት በመቀበልም ነው፡፡

## ምድረ በዳ ምንድነው?

ብዙዎቻችን በጣም ጥቂት ውሃ ባለበትና ከፀሐዩ ሐሩር መከለያ የሚሆን ምንም ነገር በማይገኝበት ጭው ያለ በረሓ ውስጥ አልነበርንም፡፡ በረሓ ቀኑ በጣም ይሞቃል፤ ሌሊቱ በጣም ይቀዘቅዛል፤ በዚህ ላይ ብቸኝነት ይሰማናል፤ ይጠማናል፤ ይርበናል፡፡ ይህም አልበቃ ብሎ ያለንበት ቦታ ሊጠፋን ይችላል፤ ከዚያ የምንወጣበትን መንገድ እንዴት እንደምናገኝም አናውቅም፡፡ ምናልባት በእንዲህ ዐይነት ልምምድ ውስጥ ገና አላለፍንም ይሆናል፤ ምድረ በዳ ምን ሊሆን እንደሚችል ግን ስሜቱ አለን፡፡ በዚህ መጽሐፍ ስላለፍሁባቸው የምድረ በዳ ጉዞዎች አንዳንድ ዋና ዋና ነጥቦች አካፍላችኋለሁ፤ በተደጋጋሚ እንዲህ ያለ ሕይወት ውስጥ ገብቼ አውቃለሁ፤ የሽርሽር ያህል ምቹ አይደለም!

ደስ የሚለው ግን ለእግዚአብሔር መታዘዝ እስከ ፈለግን ድረስ፣ የምድረ በዳ ወቅት ይህን ያህል መጥፎ አይሆንም፡፡ እንዲህ ማለቱ ከሰው አስተሳሰብ ጋር እንደማይጣጠም አውቃለሁ፤ ሆኖም፣ የምድረ በዳ ዐላማ አዎንታዊ እንጂ፣ አሉታዊ አይደለም፤ ዓላማው በመንፈስ መሪነት አዲስ እንቅስቃሴ እንድናደርግ እኛን ማስተማር፣ ማንጻት፣ ማበርታትና ማዘጋጀት በኋላም የበለጠ ውጤታማ ማድረግ ነው፡፡

ብዙዎች ወደ ምድረ በዳ በሚገቡበት ጊዜ ባለ ማወቅ በጣም ይታወካሉ፤ ይቅበጠበጣሉ፡፡ የተሳሳተ ነገር ያደርጋሉ ወይም ማድረግ ይፈልጋሉ፡፡ የሥራ መስካቸውን በተመለከተ ሥር ነቀል ለውጥ ያደርጉ ይሆናል፤ አባልነታቸውን ከአንዱ ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን ይለውጡ ይሆናል፤ ደስታ የሚያስገኝላቸው ወይም ሁኔታዎችን የሚለውጥላቸው ስለሚመስላቸው በየጊዜው የሕይወታቸውን አቅጣጫ ይለውጣሉ፡፡ ገና ትዳር ያልያዙ ከሆኑም ከደረሰባቸው ጉዳት ለመላቀቅ አዲስ ጓደኛ ይይዛሉ፡፡

መጀመሪያውኑ እግዚአብሔር ለምን በዚያ ደረቅ ቦታ እንድታልፉ እንዳደረገ በሚገባ ሳትረዱ ከዚያ መውጫ መንገድ የምትፈልጉ ከሆነ፣ የምድረ በዳ ጊዜያችሁን ታረዝሙታላችሁ፡፡ ይህም የበለጠ ችግር፣ የበለጠ ተስፋ መቁረጥ ያመጣባችኋል፤ ወቅቱን ወይም እግዚአብሔር እናንተን እየመራ ያለበትን ቦታ በሚገባ ባለ መረዳታችሁ ተሸናፊዎች ትሆናላችሁ፡፡

አርባ ዓመት በምድረ በዳ በሚጓዙበት ጊዜ የእስራኤል ልጆች ላይ የደረሰውም ይኸው ነበር፡፡ የነበሩበትን ቦታና ሁኔታ መረዳት ባለ መቻላቸው አንድ ትውልድ ሙሉ ወደ ተስፋው ምድር ሳይገባ ቀረ፡፡ ምንኛ አሳዛኝ ነው! እነርሱን ወደ ምድረ በዳ ሲመራቸው እግዚአብሔር የነበረው ዓላማ እነርሱን መፈተን፣ ማስተማርና መለኮታዊ ተስፋቸውን ማለትም አዲስ ርስት መውረስ እንዲችሉ ብርቱ ጦረኞች እንዲሆኑ ማዘጋጀት ነበር፡፡ ከዚያ በተሳሳተ መልኩ እስራኤላውያን ግን ምድረ በዳ የእነርሱ መቀጫ ቦታ እንደ ሆነ አሰቡ፤ ስለዚህም አጉረመረሙ፤ ተነጫነጩ፤ አዘውትረው ክፉ ነገር ተመኙ፡፡

ከምድረ በዳ በመነሣት ውጊያ በመግጠም የተስፋውን ምድር የሚይዙበት ጊዜ ሲመጣ ተመልሰው የመጡት ሰላዮች ያዩትንና ያስተዋሉትን ሲናገሩ፣ የአጉረምራሚዎቹንና ተነጫናጮቹን ክፉ ወሬ አደመጡ፡፡ ከእግዚአብሔር ተስፋ ቃልና ችሎታ፣ ወይም ከሰው አስተሳሰብና ችሎታ አንዱን እንዲመርጡ ዕድል ሲሰጣቸው፣ ከእግዚአብሔር ይልቅ በሰው መተማመንን መረጡ፡፡ ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር እንደሚወርሱ ቢነገራቸውም፣ እነርሱ ግን ያ እንደማይሆን የተነገራቸውን ሐሰት ተቀበሉ፡፡ የእግዚአብሔርን

ማንነትና ባሕርይ አለማወቃቸው የተሳሳተ ርምጃ እንዲወስዱ አደረጋቸው፡፡

ስለዚህም ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር፣ ‹‹እንደዚያ ከሆነ፣ የራሳችሁን መንገድ ያዙ›› አላቸው፡፡ ግፋ ቢል አንድ ዓመት የሚወስደው አጭሩ የምድረ በዳ ጉዞ የዕድሜ ዘመን ልምምድ ሆነባቸው፡፡

እኔና እናንተ ግን የዚያ ዐይነት ውሳኔ ማድረግ የለብንም፤ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹ይህ ሁሉ ምሳሌ ይሆን ዘንድ በእነርሱ ላይ ደረሰ... እኛን ለማስጠንቀቅም ተጻፈ›› እንዳለው እኛ ከእነርሱ ስሕተት መማር እንችላለን (1 ቆሮንቶስ 10÷11)፡፡

ከማጉረምረምና ከመነጫነጭ ይልቅ የምድረ በዳ ልምምድ ውስጥ መሆናችንን ብንገነዘብ፣ ከዚህ ባሻገር ወደ አዲስ ዕድገት፣ የኃይል፣ የበረከትና የተለያዩ ዕድሎች እንዲሁም የተገባልን ቃል እውን የሚሆንበት፣ ‹‹የተስፋ ምድር›› መኖሩን በማወቅ አመስጋኞች እንሆን ነበር፡፡ እንዲህ ቢሆን ኖሮ፣ ከባድ የተባለው ነገር ወይም ሁኔታ ይህን ያህል ከባድ ሊሆንብን እንደማይችል አታስቡምን? እንደዚያ ከሆነ፣ ቀጥሎ ባለው ጥቅስ ሐዋርያው ያዕቆብ ከሚነግረን ጋር እንስማማለን ማለት ነው፡-

> ወንድሞች ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት... ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ሙሉአን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጸም፡፡ (ያዕቆብ 1፥2፣4)

## ምድረ በዳ ሕይወት ውስጥ
## መግባቴ አንድ ዐይነት በደል ፈጽሜአለሁ
## ማለት አይደለምን?

ጥሩ ጥያቄ ነው!

ምድረ በዳ ሕይወት ውስጥ ስንሆን ብዙዎቻችን፣ ‹‹ጥፋቴ ምንድነው? እግዚአብሔርን ያሳዘንሁበት ነገር ይኖር ይሆን?›› በማለት መጠየቃችን የተለመደ ነው፡፡ በመሠረቱ ግን ይህ የምድረ በዳ ሕይወትን ዓላማ አለመረዳት ነው፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናያቸውና በታሪክ የነበሩ ወንዶችና ሴቶች ምድረ በዳ እግዚአብሔር ወዳቀደላቸው ፍጻሜ ለመድረስ ዝግጅት የሚያደርጉበት ቦታ መሆኑን ነበር የተረዱት፡፡

## ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 1 ያለህበትን ወቅት ተረዳ

ብዙዎቻችን በምድረ በዳ ውስጥ ስንሆን ለምን እንደዚያ እንደሆነ እንገረማለን፡፡ እግዚአብሔር በጣም መልካም ነው፤ ከበረከቶቹ፣ ከመገኘቱና በሕይወታችን ከሚፈጸሙት ተስፋዎቹ ጋር ተላምደናል፡፡ ያ መልካም ጊዜ ያበቃል ብለን አንጠብቅም፡፡ አንድ ቀን ግን ነገሮች ቀድሞ በነበሩበት ሁኔታ እንዳይደሉ እናያለን፡፡ እንዲህ በሚሆንበት ጊዜ በሁኔታው ግራ ከመጋባት ይልቅ፣ ቆም ብለን ማስተዋልና ዕይታችንን ማስፋት በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ እያለፋችሁበት ያለውን ሁኔታ አስተውሉ፤ ምክንያቱም ወቅቱንና ያላችሁበትን ቦታ ካልተረዳችሁ፣ ለሁኔታው የምትሰጡት ምላሽ የተሳሳተ ይሆናል፡፡

ነገሩ ከአንድ በጣም ሞቃት አገር በጣም ቀዝቃዛ ወደ ሆነ አገር ከመሄድ ጋር ይመሳሰላል፡፡ አንዳንዴ እጅግ በጣም ከመቀዝቀዙ የተነሣ ቴርሞሜትሩ ከዜሮ በታች ሊያመለክት ይችላል፡፡ ያላችሁበትን ቦታ ማወቅ መልካም ነው፤ አለበለዚያ የሚያስፈልገውን ልብስ ማዘጋጀት ልትረሱ ትችላላችሁ!

መንፈሳዊ ምድረ በዳን በተመለከተ ተመሳሳይ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ በዚያ ጠፍ ቦታ ሁኔታዎችን ካላስተዋላችሁ ግራ መጋባት ሊገጥማችሁ ይችላል፤ ምናልባትም ከፍ ያለ ዋጋ የሚያስከፍላችሁ ስሕተት ልትፈጽሙ ትችላላችሁ፡፡ የይሳኮር ልጆች፣ ‹‹ዘመኑን የተረዱና እስራኤላውያንም ምን ማድረግ እንደሚገባቸው የተገነዘቡ›› እንደ ነበሩ ከብሉይ ኪዳን እናነባለን፡፡ (1 ዜና መዋዕል 12፥32)

እናንተም ምድረ በዳ ውስጥ ያላችሁበትን ዘመን ከተረዳችሁ ምን ማድረግ እንደሚገባችሁ በሚገባ ታውቃላችሁ፡፡

ስለሆነም ምድረ በዳ የዝግጅት ቦታ እንጂ፣ በእግዚአብሔር የመጣል ወይም የመረሳት ቦታ አይደለም፡፡

ከምናደርገው የተሳሳተ ምርጫ የተነሣ በደረቅ ቦታ ወድቆ መቅረት ሊኖር እንደሚችል አስባለሁ፡፡ በክርስትና ሕይወታችን የቱንም ያህል አድገናል ብለን ብናስብም፣ ምንጊዜም ቢሆን በሕይወታችን መፍትሔ የሚያሻው ኀጢአት መኖሩንና በተሳሳተ አቅጣጫ የመሄድ ዝንባሌ እንዳለን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለሆነም አንድ ትልቅ መጥፎ ውሳኔ ወይም ተከታታይ የተሳሳቱ ምርጫዎች አጉል ቦታ ሊጥሉን ይችላሉ፡፡

ሆኖም፣ አንድ መዘንጋት የሌለብን እውነት አለ፡- ይቅር ባይ አምላክና ድካማችንን ሁሉ የሚረዳ ሊቀ ካህን አለን፡፡ ስለዚህም ከወደቅንበት ለመነሣትና ራሳችን ላይ ካመጣነው መዘዝ ለመውጣት የመጀመሪያው ርምጃ ወደሚወደን አባታችን በመመለስ፣ ‹‹አባት ሆይ፣ ይህንና ያንን በማድረጌ ኀጢአት ፈጽሜአለሁ፤ ይቅር በለኝ፡፡ ይህን ኀጢአት እናዘዛለሁ፤ አሁን ደግሞ በአንተ ጸጋ የልዩነት ሕይወት እኖራለሁ›› ማለት ይኖርብናል፡፡

እናንተ ራሳችሁ በፈጸማችሁት ስሕተት በሕይወታችሁ ደረቅ ምድር ውስጥ ከገባችሁ፣ ከጌታ ጋር ያላችሁን ግንኙነት አስተካክሉ፤ መማር ያለባችሁን እንዲያስተምራችሁ ፍቀዱለት፤ በተቻለ መጠን ቶሎ ከዚያ ቦታ ውጡ፡፡ እርግጥ ነው፤ ጊዜ በጌታ እጅ ነው፤ ዘማሪው፣ ‹‹ዘመኔ ያለው በእጅህ ነው›› ይላል (መዝሙር 31፥15)፡፡ እስከ አሁን የተነጋገርነው እውነት ቢሆንም፣ ምድረ በዳ ውስጥ የገባችሁት እግዚአብሔር አሁን እናንተን የሚያስተምርበት ትክክለኛ ቦታ ያ በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ መሆኑ በአንድ ወይም በሌላ መልኩ ሁኔታውን ለመረዳት አዳጋች እንደሚያደርገው አውቃለሁ፡፡ ይህን መጽሐፍ የጻፍሁበት ምክንያትም ይኸው ነው - እግዚአብሔር ምድረ በዳን እንዴት እንደሚመለከተውና በዚያ ተጠቅሞ ኢየሱስን መሰል ሕይወት እንዲኖረን እኛን ማስቻል መሆኑን እንድትገነዘቡ መርዳት ነው!

አንድ በግልጽ መረዳት ያለባችሁ ነጥብ፣ እግዚአብሔር ወደ ምድ በዳ ያመጣችሁ ለሰይጣን ተንኮል አሳልፎ ሊሰጣችሁና ጨርሶ እናንተን ለመርሳት አለመሆኑን ነው፡፡ ከግብፅ የወጡት

እስራኤላውያን ሁለተኛ ትውልድ ወደ ተስፋው ምድር ከመግባታቸው በፊት እግዚአብሔር እንዲህ በማለት ነግሮአቸው ነበር፡-

> <<አምላክህ እግዚአብሔር ትእዛዞቹን መጠበቅህንና በልብህ ያለውን ለማወቅ፣ ትሑት ሊያደርግህና ሊፈትንህ በእነዚህ አርባ ዓመታት በዚህ ምድረ በዳ ጉዞህ ሁሉ እንዴት እንደ መራህ አስታውስ>> (ዘዳግም 8፥2)

ስለዚህም ምንም እንኳ እስራኤላውያን በደል ቢፈጽሙም በሞኝነታቸው፣ በምስጋና ቢስነታቸውና በዐመፃቸው ምክንያት ምድረ በዳ ውስጥ አያሌ ዓመታት ቢያሳልፉም፣ እግዚአብሔር ያንን ለመልካም ሊለውጥላቸው እንደሚችል ነው የምንመለከተው! በእርግጥ ያደረገውም ያንኑ ነበር፤ በዚህ በጣም ደስ ይለኛል! እናንተስ?

እንዳትሳሳቱ - ምድረ በዳ ውስጥ ስለሆንን ጌታ በሕይወታችን መሥራቱን አያቆምም፡፡ ይልቁን በዚያም ውስጥ ይመራናል፤ ያለ እርሱ በዚያ ውስጥ ማለፍ አንችልም፡፡ ከዚያም በላይ እርሱ በሕይወታችን አንዳች ነገር ለማድረግ እስኪነሣሣ ድረስ አስታዋሽ አጥተን በዚያ ቦታ ያለ አንዳች ዓላማ እንኖራለን ማለትም አይደለም፡፡ የሚራራልን አባታችን እግዚአብሔር በፍጹም እንደዚያ አያደርግም፡፡ በዚያ ውስጥ እያለን እንኳ፣ እርሱ ድንቅ ሥራውን በሕይወታችን ይፈጽማል፡፡

ምናልባትም፣ ‹‹ዛፎቹን እንጂ፣ ጫካውን ማየት አትችልም›› ሲባል ሰምታችሁ ይሆናል፡፡ ምድረ በዳን በተመለከተም ነገሩ ተመሳሳይ ነው በዚያ ውስጥ እያላችሁ እግዚአብሔር ሲንቀሳቀስ ማየት ያስቸግራል፡፡

ይህ በጣም ጠቃሚ እውነት በግልጽ መታወቅ አለበት - ምድረ በዳ የሽንፈት ቦታ አይደለም፤ ሌላው በቀር፣ ለእግዚአብሔር ለሚታዘዙ ሰዎች እንደዚያ አይሆንም፡፡ በራብ ሰውነቱ የደከመው፣ የልቡን የሚያካፍለውና የሚያጽናናው ያልነበረው ኢየሱስ አርባ ቀን በምድረ በዳ እየተፈተነ ነበር፡፡ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ቃል ሰይጣንን አሸነፈ! ምድረ በዳ ለእግዚአብሔር ልጆች የሽንፈት ቦታ አይደለም፤ ‹‹ነገር ግን በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት እያዞረ ለሚመራን… ምስጋና ይሁን›› (2 ቆሮንቶስ 2፥14)፡፡

እስራኤላውያን በምድረ በዳ በነበሩ ጊዜ በዚያ አካባቢ በነበሩ

ሕዝቦች ጥቃት እየደረሰባቸው ነበር፣ ጠላቶቻቸውን እንዲወጉ እግዚአብሔር ለእስራኤል ተናገረ፡፡ የእስራኤል ልጆች አሞራውያንን (ዘኁልቁ 21፥21-25)፣ ሜዶናውያንን (ዘኁልቁ 31፥1-11) የባሳን ሰዎችን (ዘኁልቁ 21፥33-35) አሸነፉ፡፡ የእግዚአብሔር ዓላማ እንዲሸነፉ ቢሆን ኖሮ፣ ለያዙት ቦታ እንዲከላከሉ ወይም መልሰው እንዲዋጉ አይነግራቸውም ነበር፡፡ ምንም እንኳ ያ የሽንፈት ጊዜ እንዲሆን ባይታሰብም፣ አብዛኞቹ ሰዎች ወደ ተስፋው ምድር ሳይገቡ ሞተዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ይህ ያለ መታዘዛቸው አሳዛኝ ውጤት እንጂ፣ የእግዚአብሔር ዓላማ እንደዚያ እንዲሆን አልነበረም፡፡

ከምድረ በዳ ሕይወት ባሻገር ያለው ምክንያት በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ማጣት ወይም በእርሱ መቀጣት ማለት አለመሆኑን ይህ ግልጽ ሊያደርግላችሁ እንደማይችል አስባለሁ፡፡ ምድረ በዳ እግዚአብሔር እናንተን የሚጥልበት ወይም የሚረሳበት ቦታም አይደለም፡፡ እጃችሁን ወደ ላይ አንሥታችሁ የምትማረኩበት ቦታም አይደለም!

## እግዚአብሔር አንዳች መልካም ነገር እያደረገ ነው !

ምድረ በዳ ምልክቶችን፣ በረከቶችን፣ በሚያስፈልጋችሁ ነገር መትረፍረፍን ወይም ተአምርን የምትጠብቁበት ቦታ ሳይሆን፣ ለሕይወታችሁ የእግዚአብሔርን ሐሳብ የምትፈልጉበት ቦታ ነው፤ ትክክለኛ ፀባይንና ብርታትን የሚሰጣችሁም ይኸው ነው፡፡ ራእይ ሊኖራችሁ ይገባል፤ ልባችሁ ውስጥ ያለውን ተስፋ በተመለከተ ጥርት ያለ ዕይታ ከሌላችሁ፣ ወደ ማጉረምረምና ተስፋ ወደ መቁረጥ ልታመሩ ትችላላችሁ፡፡

በሕይወት ውስጥ ትክክለኛ ቦታችሁን ከተረዳችሁ፣ በዚያው ልክ ሕይወታችሁን በተመለከተ ትክክለኛ ዕይታ ይኖራችኋል፡፡ ምንም እንኳ ሲዳስሳችሁ ባይሰማችሁም፣ በሁኔታዎች ውስጥ የእግዚአብሔርን እጅ ታያላችሁ፡፡ ለእርሱ ያላችሁ ፍቅር ስለሚያድግ፣ ‹‹ከዚያ ውስጥ የሚገኘው ጥቅም ምንድነው?›› ከማለት አልፋችሁ፣ ‹‹እግዚአብሔር ምን እንዳደርግ ወይም እንድሆን ነው የሚፈልገው?›› ወደ ማለት ትሸጋገራላችሁ፡፡

ቀደም ሲል የጥንቱ ኢዮብን ገጥሞት ስለ ነበረው ግራ መጋባትና እግዚአብሔር እያደረገ የነበረውን መረዳት አለመቻሉን አንሥቼ ነበር፡፡ በየትኛውም አቅጣጫ የእግዚአብሔርን ነገር ማየት አልቻለም ነበር! የኢዮብ ሕይወት በዚያ አብቅቶ ቢሆን ኖሮ፣ በእርግጥ አሳዛኝ ይሆን ነበር፡፡ ኢዮብ ግን ተስፋ ለመቁረጥ እጁን አልሰጠም፤ በእምነትና በተስፋ ተሞልቶ እንዲህ አለ፡-

> <<ግን እኔ፣ የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኃላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ>> (ኢዮብ 23፥10)

እንዴት የሚገርም መረዳት ነው! እግዚአብሔር ወዴት እየወሰደን እንደሆነ መረዳት ለእኛ ከባድ ቢሆንም፣ እርሱ ግን መንገዱን ያውቃል፡፡ ስለዚህ ሙሉ በሙሉ በእርሱ መተማመን እንችላለን፤ ሐዋርያው ጳውሎስም ይህን አስመልክቶ ሲጽፍ፣ ‹‹በእናንተ መልካምን ሥራ የጀመረው እርሱ፣ እስከ ክርስቶስ ኢየሱስ ቀን ድረስ ከፍጻሜው እንደሚያደርሰው እርግጠኛ ነኝ›› ይላል፡፡ (ፊልጵስዩስ 1፥6)

ምድረ በዳ ውስጥ ብንሆን እንኳ... ይህ እውነት መሆኑን እናውቃለን፡፡

# 2

# ሌሎች ብዙዎች በዚያ አልፈዋል

ክርስቲያኖችን የተለያየ የመከራ ማዕበል ቢገጥማቸውም፣ ከዚያ ውስጥ የበለጠ ውበት ተላብሰው ይወጣሉ፡፡ ተራራ አናት ላይ እንደሚያድጉ ዛፎች ነፋስ ቢያናውጣቸውም ጠንካራ እንጨት እንደሚያስገኙ ዛፎች ይሆናሉ፡፡

— ቢሊ ግራሐም

ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ እንደ ተመለሰ... መንፈስ ወደ በረሓ ወሰደው፡፡

— ሉቃስ 4፥1 (አ.መ.ት)



እንኳን ወደ ምድረ በዳ ልምምድ መጣችሁ! መቼም፣ እንዲህ ያለው የመልካም ምኞት መግለጫ ሳይገርማችሁ አልቀረም፡፡ በመሠረቱ ማንኛችንም ብንሆን፣ መንፈሳዊ ምድረ በዳ ውስጥ ጥቂት ጊዜ ማሳለፍ ጥሩ ነገር ይሆናል በማለት አናስብም፤ ይሁን እንጂ፣ የሚወደን አምላካችን እንዲህ ላለው ጊዜ ላቅ ያለ ግምት እንዳለው መገንዘብ ይኖርባችኋል፤ ብቻችሁን አይደላችሁም፡፡

በእምነት ጉዞአችሁ የምታልፉበት ምድረ በዳ መልካም ቦታ እንዳልሆነ የምታስቡ ከሆነ፣ ረጋ ብላችሁ እንድታስቡ እነግራችኋለሁ! እውነቱ ከዚያ የተለየ ነው፤ ምድረ በዳ ውስጥ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ቅዱሳንን ዱካ እናገኛለን፤ ሌላው ቀርቶ የእግዚአብሔር ልጅ እንኳ ምድረ በዳ ውስጥ ሁነኛ ጊዜ አሳልፎአል፡፡

በሌላ አነጋገር በምድረ በዳ ውስጥ ስናልፍ ሌሎችም ከእኛ ጋር አሉ፤ ...ብቻችንን አይደለንም ማለት ነው፡፡

ደጋግሜ የሰዎችን ስም በማንሣቴ አትገረሙ፤ በምድረ በዳ ያለፉ ሰዎች ዝርዝር ስፍር ቁጥር የለውም፡፡

ቀደም ሲል መጽሐፍ ቅዱስ፣ ‹‹በምሥራቅ አገር ከሚኖሩትም ሰዎች ሁሉ ይልቅ እጅግ ታላቅ ሰው ነበረ›› የሚልለትን ኢዮብን አንሥቻለሁ (ኢዮብ 1፥3)፡፡ ይህ ሰው ንብረቱን፣ ልጆቹን፣ ጤናውንና የሚስቱን ድጋፍ እንኳ ሳይቀር ማንኛውንም ነገር አጣ፡፡ መልካሙና ጻድቁ ሰው ኢዮብ፣ የተሰወረ ኀጢአት ሳይኖርበት እንዳልቀረ የቅርብ ጓደኞቹ ነግረውት ነበር፡፡ በምድረ በዳው በጣም ከመመረሩ የተነሣ ኢዮብ ባይወለድ ኖሮ ይሻለው እንደ ነበር ተናግሮም ነበር፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ ሁሉንም ነገር ትቶ አዲስ የተስፋ ምድር የማግኘት ጉዞ እንዲጀምር እግዚአብሔር የተናገረውንና ትውልድ አገሩ ዑር ውስጥ ተመችቶት ይኖር የነበረው አብርሃም ባለፈበት መንገድ ታልፋላችሁ፡፡ በጉዞው ሁሉ ሚስቱ ሣራ አጎኑ ነበረች!

አብዛኛውን ሕይወታቸውን ያሳለፉት ምድረ በዳ ውስጥ ነበር፡፡

ሙሴም የምድረ በዳ ሕይወትን የተለማመደ ሰው ነበር፡፡ እንደ አንድ ልዑል፣ ፈርዖን ቤተ መንግሥት ውስጥ ነበር ያደገው፤ አንድ ግብፃዊ ከገደለ በኃላ ግን፣ በጎች እየጠበቀ ዐርባ ዓመት በምድረ በዳ ኖረአል፤ እግዚአብሔር በእሳቱ ቁጥቋጦ ውስጥ ራሱን በገለጠለት ጊዜ ሙሴ እዚያው ነበር፡፡

> አንድ ቀን ሙሴ የምድያም ካህን የሆነውን የአማቱን የዮቶር በጐችና ፍየሎች እየጠበቀ ሳለ፣ መንጋውን እየነዳ ወደ ምድረ በዳው ዳርቻ አምርቶ የእግዚአብሔር ተራራ ተብሎ ወደሚጠራው ወደ ኮሬብ ቀረበ። እዚያም የእግዚአብሔር መልአክ በቁጥቋጦው ውስጥ በሚንቀለቀል የእሳት ነበልባል መካከል ተገለጠለት። ሙሴም ቁጥቋጦው በእሳት ቢያያዝም እንኳ፣ አለመቃጠሉን አየ። ሙሴም ቁጥቋጦው ለምን እንደማይቃጠል ቀረብ ብዬ ይህን አስገራሚ ነገር ልመልከት አለ። ሙሴ ሁኔታውን ለመመልከት መቅረቡን እግዚአብሔር ባየ ጊዜ፣ ከቁጥቋጦው ውስጥ እግዚአብሔር፣ <<ሙሴ፣ ሙሴ፣>> ብሎ ጠራው፤ ሙሴም እነሆኝ አለው። (ዘፀአት 3፥1-4)

ከዚያም ሁላችንም ታሪኩን እንደምናውቀው ሙሴ ወደ ግብፅ ተመልሶ ሕዝቡን ከግብፅ አወጣ፤ የሄደው ወደ ምድረ በዳ ነበር!

ምድረ በዳ ውስጥ አባቱ በጣም ይወደው የነበረውንና በገዛ ወንድሞቹ ጉድጓድ ውስጥ የተጣለውን፣ ከዚያም በባርነት ወደ ግብፅ የተሸጠው ዮሴፍን ታገኛላችሁ፡፡ በሐሰት በተቀነባበረ ክስ ወህኒ ቤት ገባ፡፡ ፈርዖን ወህኒ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ለዮሴፍ ገለጠ፤ የእንጀራ ቤቱና መጠጥ አሳላፊውን ሕልም መተርጐም ቻለ፡፡ ይህም እርሱ ሳያውቀው፣ የራሱ የፈርዖንን ሕልም ለመተርጐም አዘጋጀው፡፡

ከዚያም ንጉሥ ዳዊትን እናገኛለን፡፡ ቀጣዩ የእስራኤል ንጉሥ እርሱ እንደሚሆን ሳሙኤል ትንቢት ተናግሮለት ነበር፤ ከዚያ በኃላ ብዙ ሳይቆይ ዋሻ ውስጥ በመኖርና ምድረ በዳ ውስጥ በመንከራተት ለዙፋን ሲዘጋጅ ራሱን አገኘው፡፡ እርሱ እረኛው፤ ጉልበቱ፣ ጋሻውና

መጠጊያው መሆኑን እግዚአብሔር ራሱን የገለጠለት እዚያ ነበር፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ታላቅ ነቢይ እንዲሆን ተጠርቶ ነበር፤ አባቱ ዘካርያስ ይህን ስለሚያመለክት ራእይ ነግሮት ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ራሱን ለዮሐንስ የገለጠለት ምድረ በዳ ውስጥ እንጂ፣ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ውስጥ አልነበረም፤ ከግመል ጠጉር የተሠራ ልብስ እየለበሰ፣ አንበጣና የበረሓ ማር እየበላ፣ ብዙ ዓመት በይሁዳ ምድረ በዳ ኖረ፡፡ ሉቃስ 3፥2-3፣ ‹‹…የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ፤ እርሱም ለኀጢአት ስርየት የሚሆን የንስሐን ስብከት እየሰበከ በዮርዳኖስ ወንዝ አካባቢ ወዳሉት ስፍራዎች ሁሉ መጣ›› ይላል፡፡

አብዛኛውን የአዲስ ኪዳን ክፍል እግዚአብሔር ለሐዋርያው ጳውሎስ የገለጠለት በአረቢያ በረሓ ነበር፤ እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለው ዓላማ የተገለጠለት እዚያ ነበር፤ እርሱ ራሱ፣ ‹‹በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ እንድሰብክ ልጁን በእኔ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ ከማንም ሥጋ ለባሽ ጋር አልተማከርሁም፤ ከእኔ በፊት ሐዋርያት ወደሆኑትም ወደ ኢየሩሳሌም አልወጣሁም፤ ነገር ግን ወዲያው ወደ አረብ አገር ሄድሁ…›› በማለት ጽፎአል (ገላትያ 1፥16-17)፡፡

ለመሆኑ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ራእይ በተቀበለ ጊዜ ሐዋርያው ዮሐንስ የት የነበረ ይመስላችኋል?

> እኔ ወንድማችሁ ዮሐንስ ከእናንተ ጋር አብሬ በኢየሱስ መከራውንና መንግሥቱን፣ ትዕግሥቱንም ተካፋይ የሆንሁ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ኢየሱስ ምስክርነት ፍጥሞ በምትባል ደሴት ነበርሁ፡፡ (ራእይ 1፥9)

ፍጥሞ ለምድረ በዳ ልምምድ ጥሩ ምሳሌ የምትሆን፣ በረሓ ውስጥ የነበረች ደሴት ናት፡፡

ከሁሉም የበለጠ ደግሞ የአባቱንና የመንፈስ ቅዱስን ቡራኬ ሕዝብ ፊት ከተቀበለ በኋላ በሰይጣን እንዲፈተን መለኮት ራሱ ወደ ምድረ በዳ የላከው ኢየሱስም አብሮን ይሆናል፡፡

ብዙ ጊዜ ይህ አርአያነት እንዳለው አስተውያለሁ፡- በእኛ አማካይነት ወደ ፊት ማድረግ የፈለገውን ታላቅ ነገር ያሳየናል፣ ከዚያም እኛን ለዚሁ ለማዘጋጀት በቀጥታ ወደ ምድረ በዳ ይመራናል፡፡

እንግዲህ በምድረ በዳ ውስጥ ማለፍ ለታላላቅ ቅዱሳንና ለጌታችን ለኢየሱስም አስፈላጊ ከነበረ፣ ምንም እንኳ እኔ ቀላሉን መንገድ ብመርጥም፣ ምድረ በዳ ውስጥ ጥቂት ጊዜ ማሳለፍ ለእኔም መልካም እንደሚሆን እገነዘባለሁ፡፡ ምድረ በዳ እግዚአብሔር እኛን የሚፈትንበት፣ ትሑት የሚያደርግበት፣ የሚያበረታበትና የሚያጠራበት ስፍራ ነው፡፡ እኛ ውስጥ መንፈሳዊ ባሕርይ የሚቀርጸው እዚያ ነው፡፡ ወደ ፊት በእርሱ መንግሥት ለሚኖረን ውጤታማ ሥራ የምንሠለጥንበት ቦታ ነው፡፡

ምድረ በዳን በተመለከተ ከሁሉም የበለጠው አጓጊ ጉዳይ፣ እግዚአብሔር በአዲስ ሁኔታ ራሱን ለእኛ የሚገልጥበት ቦታ መሆኑ ነው! ነቢዩ ኢሳይያስ እንዲህ ሲል ጽፏል፤

> እግዚአብሔር ጽዮንን በእርግጥ ያጽናናታል፤ ፍርስራሾቿንም በርኅራኄ ይመለከታል፤ ምድረ በዳዋን እንደ ዔድን፣ በረሓዋንም እንደ እግዚአብሔር ተክል ቦታ ያደርጋል፤ ተድላና ደስታ፣ ምስጋናና የዝማሬ ድምፅ በእርሷ ይገኛል። (ኢሳይያስ 51፥3)

የዔደን አትክልት ቦታ እግዚአብሔር ራሱን ለአዳም የገለጠበት ቦታ ነው፤ አዳም ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ያደርግ የነበረው እዚያ ነበር፡፡ በምድረ በዳ ጌታን ትራባላችሁ፤ ጌታን ትጠማላችሁ፡፡ ስለሆነም ባላችሁበት ጒስቋላና ይበልጥ ትኩረቱን በሰበሰበ ሁኔታ ውስጥ እግዚአብሔር ራሱን ሲያሳያችሁ፣ ከዚህ ዓለም ሕይወት ነገሮች ወደ እርሱ ዘወር ትላላችሁ፡፡ እግዚአብሔር ለሕይወታችን ላለው ጥሪ በጐ ምላሽ የምንሰጥ ከሆነ፣ ልምምዳችን ይህን ይመስላል፡፡ ጌታ በአዲስ ሁኔታ ራሱን የሚገልጥልን ምድረ በዳ ውስጥ ነው፡፡ ኢሳይያስ 45÷15፣ ‹‹አዳኙ የእስራኤል አምላክ ሆይ፣ አንተ በእውነት ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ›› ይላል፡፡ እርሱን አጥብቀው

የሚፈልጉት የበለጠ እርሱን እንዲራቡና እንዲጠሙ፣ ከእርሱም ጋር የጠበቀ መቀራረብ እንዲኖራቸው እርሱ ይህን ያደርጋል፡፡ እርሱን ከማይራቡና ከማይጠሙ ሰዎችም ጌታ ራሱን ይሰውራል፡፡ እርሱ በዋዛ ፈዛዛ አይገኝም፤ እንደ ተራ ነገር አይቆጠርም፡፡

### ጉዞውን በድል ለመውጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 2 የቱንም ያህል ብቸኝነት ቢሰማህ

እግዚአብሔር ከአንተ ጋር አለ

ሁነኛ የምድረ በዳ ሕይወት ውስጥ ስንሆን፣ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር አብሮነት ጨርሶ ይጠፋብናል! መገኘቱ እንዲሰማችሁ የቻላችሁትን ያህል ጥረት ብታደርጉም ሚሊዮን ማይሎች የራቀን ይመስለናል፡፡

ሁለት የእግዚአብሔር ሓልዎት መገለጦች መኖራቸውን መረዳት በጣም ይጠቅማል፡፡ የመጀመሪያው፣ ‹‹አልጥልህም ከቶም አልተውህም›› (ዕብራውያን 13÷5) የሚለው ቃል ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ ይህ እግዚአብሔር ምሉዕ በኩለሔነት (ሁሉም ቦታ መገኘት) ነው፡፡ ንጉሥ ዳዊት፣ ‹‹ወደ ሰማይ ብወጣ፣ አንተ በዚያ አለህ፤ መኝታዬንም በሲኦል ባደርግ በዚያ ትገኛለህ›› በማለት ያመለከተው ይህንን ነው (መዝሙር 139÷8)፡፡ የቅዱሳት መጻሕፍትን ቃል ብታምኑና በእግዚአብሔር ብትደገፉ፣ ስሜታችሁ ወይም እየሆነ ያለው ምንም ይሁን ምን፣ እግዚአብሔር ሁሌም ከእናንተ ጋር ነው፡፡

ሌላው ሁላችንም የምንወደውና የክርስትና ሕይወት አካል የሆነው የእግዚአብሔር አብሮነት እርሱ በወደደ ጊዜ የሚገለጸው ሓልዎቱ ነው፡፡ ‹‹መገለጥ›› ማለት ከማይታየው ወደሚታየው፣ ከማይሰማው ወደሚሰማው፣ ከማይታወቀው ወደሚታወቀው ማምጣት ማለት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው እግዚአብሔር ለሥጋዊ ስሜቶቻችን ራሱን

እውን ሲያደርግልን ነው፡፡ እንዲህ ያለው ልምምድ እጅግ አስደናቂ ሲሆን አምልኮ ውስጥ እያለን፣ በግል እየጸለይን እያለ፣ ፀጥ ያለ ደን ውስጥ ወዲያ ወዲህ በምንልበት ጊዜ በዕለት ተዕለት ተግባራችን፣ ምናልባትም በሌሎች አያሌ መንገዶች ሊከሰት ይችላል፡፡

ስለዚህ ምድረ በዳ ውስጥ መንፈሳዊ ራብና ጥማት ሲገጠማችሁ እግዚአብሔር በአስደናቂና ውብ መገኘቱ ባይባርካችሁ እንኳ፣ ዘና ብላችሁ በተስፋ ቃሎቹ ተደገፉ፤ ከእነዚህም ዋናው፣ ‹‹አልተውህም ከቶም አልጥልህም›› የሚለው ነው፡፡ መገኘቱ በማይሰማን ጊዜ እንኳ፣ በእርሱ ደስ ስንሰኝ ለእርሱ ያለን ፍቅር በሁኔታዎች የማይደበዝዝ መሆኑን በጉልህ ያመለክታል፡፡

## እግዚአብሔርን መራብ

በፍጹም ልባቸው እግዚአብሔርን ለሚፈልጉ ሰዎች እርሱ ራሱን ይገልጣል፡፡

የእስራኤልን ልጆች ወደ ምድረ በዳ ያመጣቸው ትሑት ሊያደርጋቸውና ሊያስርባቸው እንደ ነበር እግዚአብሔር መናገሩን አስታውሱ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ኢያሱ እንዳደረገው እግዚአብሔርን ከመራብ ይልቅ፣ ሕዝቡ ጌታ ከእነርሱ ያራቃቸው ነገሮችን መራብ ጀመሩ፡፡ ስለዚህ ለሙሴ እንዳደረገው ራሱን ሊገልጥላቸው ወደ እነርሱ ሲመጣ ለእርሱ ምንም ፍላጐት አልነበራቸውም እንዲያውም ችላ አሉት፡፡

ዘዳግም ውስጥ ይህን እናነባለን፡-

<<ተራራው በእሳት ሲቃጠል ከጨለማው ውስጥ ድምፁን በሰማችሁ ጊዜ እናንተ የነገዶቻችሁ አለቆችና ሽማግሌዎቻችሁም በሙሉ ወደ እኔ ዘንድ መጣችሁ፤ እንዲህም አላችሁ፣ <አምላካችን እግዚአብሔር ክብሩንና ግርማውን አሳይቶናል፤ ከእሳቱም ውስጥ ድምፁን ሰምተናል፡፡ እግዚአብሔር አነጋግሮትም እንኳ፣ ሰው

በሕይወት ሊኖር እንደሚችል በዛሬው ቀን አይተናል። ከእንግዲህ የአምላካችን እግዚአብሔርን ድምፅ ብንሰማ እንሞታለን፤ ይህችም ታላቅ እሳት ፈጽማ ታጠፋናለች። ታዲያ ለምን እንሙት? ለመሆኑ ከእሳት ውስጥ ሆኖ ሲናገር እኛ እንደ ሰማነው ሁሉ፣ የሕያው እግዚአብሔርን ድምፅ ሰምቶ በሕይወት ለመኖር የቻለ ከሥጋ ለባሽ ማን አለ? አንተ ቀረብ አምላካችን እግዚአብሔር የሚለውን ሁሉ አዳምጥ፤ ከዚያም አምላካችን እግዚአብሔር የሚነግርህን ሁሉ ንገረን፣ እኛም እንሰማለን፤ እናደርገዋለንም።>> (ዘዳግም 5፥23-27)

እዚህም ላይ ለሙሴ እንዳደረገው ሁሉ እግዚአብሔር ለእነርሱም በምድረ በዳ ራሱን ሊገልጥላቸው የነበረውን ፍላጐት እናያለን፣ እነርሱ ግን ፈቃደኛ አልሆኑም፤ ሙሴን፣ ‹‹ሂደህ ከእግዚአብሔር ጋር ተነጋገር፤ መጥተህ የነገረህን ንገረን፤ እኛም ያንን እናደርጋለን›› አሉት፡፡

በሚያሳዝን ሁኔታ ሕዝቡ ስለ እግዚአብሔር እንጂ፣ እግዚአብሔር ራሱን አላወቁትም፡፡ ስለሆነም እርሱ ያዘዛቸውን ማድረግ አልቻሉም፡፡ እርሱን ባለ ማወቃቸውም ቃል የተገባላቸውን ምድር ሳያዩ በምድረ በዳ ሞቱ፡፡

በዮሐንስ፣ በሙሴ፣ በዳዊት፣ በዮሴፍ፣ በጳውሎስና በሌሎች ሕይወት እንዳደረገው እግዚአብሔር እኛንም ወደ ምድረ በዳ የሚያመጣን የምንራበው እርሱን መሆኑን ለማየት ወይም ያመለጠንን ምቾትና ደስታ መሆኑን ሊፈትነን ነው፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡-

ትለምናላችሁ ግን አትቀበሉም፤ ለራሳችሁ ሥጋዊ ደስታ በማሰብ በክፉ ምኞት ትለምናላችሁና። አመንዝሮች ሆይ፣ ከዓለም ጋር ወዳጅ መሆን የእግዚአብሔር ጠላት መሆን እንደ ሆነ አታውቁምን? ስለዚህ የዓለም ወዳጅ መሆን የሚፈልግ ሁሉ የእግዚአብሔር ጠላት ሆኖአል። ወይስ በውስጣችሁ ያሳደረው መንፈስ አብዝቶ ይቀናል በማለት መጽሐፍ የተናገረው በከንቱ ይመስላችኋልን? ነገር ግን ጸጋን አብዝቶ ይሰጠናል፤ መጽሐፍም፣ <<እግዚአብሔር ትዕቢተኞችን

ይቃወማል፤ ለትሑታን ግን ጸጋን ይሰጣል>> ያለው ለዚህ ነው። እንግዲህ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አስገዙ፤ ዲያብሎስን ተቃወሙት ከእናንተም ይሸሻል። ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል። እናንተ ኀጢአተኞች እጃችሁን አንጹ፤ እናንተ በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉ ልባችሁን አጥሩ። (ያዕቆብ 4፥3 - 8)

በፍጹም ልባችን እርሱን ለመፈለግ ወደ እርሱ ስንቀርብ፣ እርሱም ወደ እኛ ይቀርባል፡፡ የእስራኤል ልጆች ትኩረት ከእግዚአብሔር ይልቅ እነርሱ የሚፈልጉት ነገር (ፍትወት) ላይ ነበር፡፡ በዓለም መንገድ የሚገኘውን ምቾትና ደስታ በመፈለግ አመነዘሩ፡፡ ብዙም ሳይቆዩ፣ ያ ሁሉ ምቾትና ድሎት ግብፃውያንንና ሰራዊታቸውን ማዳን አለመቻሉን ረሱ፡፡

ወደ እርሱ ለመቅረብ ሁለት ነገሮች ማድረግ እንዳለብን እግዚአብሔር ይናገራል፡፡ በመጀመሪያ፣ እጆቻችንን ማንጻት አለብን፡፡ ሁለተኛ ቆሮንቶስ 7÷1፣ ‹‹እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፣ ይህ የተስፋ ቃል ስላለን፣ ሥጋንና መንፈስን ከሚያረክስ ነገር ሁሉ ራሳችንን እናንጻ፤ እግዚአብሔርንም በመፍራት ቅድስናችንን ፍጹም እናድርገው›› ይላል፡፡ ኀጢአት ከእግዚአብሔር ይለየናል፤ ‹‹ነገር ግን በደላችሁ ከአምላካችሁ ለይቶአችኋል፤ ኀጢአታችሁ ፊቱን ከእናንተ ሰውሮታል፤ በዚህም ምክንያት አይሰማም›› (ኢሳይያስ 59÷2)፡፡

በሁለተኛ ደረጃ፣ ልባችንን ማንጻት አለብን፡፡ ለዚህ ቁልፉ ያዕቆብ፣ ‹‹እናንተ በሁለት ሐሳብ የምትዋልሉ ልባችሁን አጥሩ›› የሚለው ነው፡፡ (ያዕቆብ 4÷8)፡፡ በሁለት ሐሳብ የሚዋልሉ ሰዎች ከመንፈስ ወደ ሥጋ፣ ወደ ፊትና ወደ ኃላ ይሄዳሉ፡፡ ልባቸውንና ሐሳባቸውን የእግዚአብሔር ነገሮች ላይ አያደርጉም፡፡ ቈላስይስ 3÷1-2፣ ‹‹እንግዲህ ከክርስቶስ ጋር ከተነሣችሁ፣ ክርስቶስ በእግዚአብሔር ቀኝ በተቀመጠበት በላይ ያሉ ነገሮችን እሹ፤ ሐሳባችሁም በላይ ባለው ላይ እንጂ፣ በምድራዊ ነገር ላይ አይሁን›› ይላል፡፡

አጥብቃችሁ የምትፈልጉት በጣም የምትወዱትን ነው፡፡ ቁልፉ ቃል፣ ‹‹ይሁን›› የሚለው ነው፡፡ አንድ ሴት ጠጉርዋን ፐርም ስትደረግ

እያንዳንዱ ጠጉር በኬሚካሉ ስለሚለወጥ ይጠቀለላል፡፡ አሁን እያንዳንዱ ጠጉር በዚያ መልኩ እንዲሆን ስለ ተደረገ ጥቅልል ጠጉር ይኖራታል፡፡ ያንን ጠጉር ስባችሁ ቀጥ ልታደርጉት ትችላላችሁ፤ ሆኖም፣ ስትለቁት ወደ ነበረበት ይመለሳል፡፡

ሰዎች ወደ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳሉ፤ አምልኮ ቡድን ውስጥ ይዘምራሉ፤ ክርስቲያናዊ ተግባሮች ውስጥ ይሳተፋሉ፤ ከዚያ ውጭ አንዳች፣ ‹‹ክርስቲያን›› ያልሆነ ነገር ሲያደርጉስ ልባቸው ምን ላይ ነው የሚሆነው? እነርሱ እንዲሆን ያደረጉት ላይ ነው፡፡ ከቤተ ክርስቲያኑ ሕንፃ ወይም አካባቢ እንደ ወጡ አእምሮአቸው ወዲያውኑ ቀድሞ ወደ ነበሩበት ቦታ ወይም ነገር ይመለሳል፡፡ ፐርም የተደረገው ጠጉር ወደ ቦታው እንደሚመለሰው ማለት ነው፡፡ የአምልኮ መዝሙሮች የሚዘምሩ፣ መልእክቶችን በማስታወሻ ደብተራቸው የሚያሰፍሩ፤ ጊዜያቸውን ለተለያዩ የቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎቶች የሚሰጡ ሰዎች ባሉበት ብዙ ቤተ ክርስቲያኖች ሰብኬአለሁ፤ በመሠረቱ እነዚህ ነገሮች ሁሉ መልካም ናቸው፤ ይሁን እንጂ፣ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቶች መካከልና ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ የሚያወሩት ስለ ገንዘብ፣ ስለ ስፖርት ልብስ፣ ማኅበረ ሰብ ሜዲያ ላይ ስለ ወጡ አዳዲስ ወሬዎች፣ ስለ ጋዜጦችና ስለ ሌሎች የዚህ ዓለም ነገሮች ነው፡፡ ስለ እነዚህ ነገሮች ሲያወሩ ፊታቸው ይፈካል፤ ይሁን እንጂ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያነቡት፣ የሚጸልዩት፣ ሌሎችን የሚያገለግሉትና ሌላው ቀርቶ፣ ወደ ቤተ ክርስቲያን የሚሄዱት ያንን ማድረግ ስላለባቸው ብቻ ነው፡፡

አንድ ወጣት ከአንድ ልጃገረድ ጋር ፍቅር ከያዘውና ለመጋባት ከተጫጬ ስለ እርሷ እንዲያስብና እንዲያወራ አትነግሩትም፡፡ ዘወትር ልቡ ውስጥ ናት፤ ስሟ ሲጠራ ፊቱ ይፈካል፡፡ ምክንያቱም ፍቅሩ ወይም ልቡ እርሷ ላይ በመሆኑ ነው፡፡ እርሷን በተመለከተ ሐሳቡ አይዋልልም፤ ስለ ሌሎች ልጃገረዶች አያስብም፤ እርሷን አፍቅሮአል!

መዝሙር 16÷8 ላይ ዳዊት፣ ‹‹እግዚአብሔርን ሁልጊዜ በፊቴ አድርጌአለሁ›› ይላል፡፡ ሐሳቡ እየዋለለ አይደለም፡፡ ልቡ ንጹሕ ነው፡፡ ጌታን እንደሚወድ አድርጎ የሚወዳቸው ሌሎች

ነገሮች ልቡ ውስጥ የሉም፡፡ ለእግዚአብሔር ያለው ፍቅር ዓለም ከምትሰጠው ማንኛውም መልካም ነገር ይበልጣል፡፡ ከኢየሱስ ይበልጥ የምንወዳቸው ወይም የምንፈልጋቸው ነገሮች ጣዖት ተብለዋል፡፡ ዳዊት እንዲህ ይላል፣

> ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ሊወጣ ይችላል?
> በተቀደሰ ስፍራውስ ማን ይቆማል? ንጹሕ እጅና
> ቅን ልብ ያለው፣ ነፍሱን ለሐሰት ነገር የሚያስገዛ፣
> በውሸት የማይምል፡፡ (መዝሙር 24፥3-4)

ንጹሕ ልብ ያለው ሰው ከኢየሱስ ይበልጥ የሚወደው፣ የሚፈልገው ወይም የሚተማመንበት የሌለው ሰው ነው፡፡ ማቴዎስ 10፥37 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹ከእኔ ይልቅ እናቱን ወይም አባቱን የሚወድ፣ ለእኔ ሊሆን አይገባም፤ ከእኔ ይልቅ ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን የሚወድ ለእኔ ሊሆን አይገባም›› ይላል፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ፣ ምድራዊ ሕይወታቸውን በጣም ከመወደዳቸው የተነሣ እግዚአብሔርን የማወቅ ዕድል እንዳመለጣቸው የእስራኤል ልጆች መሆን የለብንም፡፡

ኢሳይያስ 35፥1-2 እንዲህ ይላል፡-

> ምድረ በዳውና ደረቁ ምድር ደስ ይላቸዋል፤ በረሓው ሐሤት ያደርጋል፤ ይፈካል፤ እንደ አደይም ያብባል፡፡ በደስታና በዝማሬ ሐሤት ያደርጋል፤ የሊባኖስ ክብር ይሰጠዋል፤ የቀርሜሎስንና የሳሮንን ግርማ ይለብሳል፡፡ የአምላካችንን ታላቅ ግርማ፣ የእግዚአብሔርን ታላቅ ክብር ያያሉ፡፡

የእግዚአብሔር ክብር የሚገለጠው ምድረ በዳ ውስጥ ነው! ከእኛ በፊት ካለፉት ታላላቅ ቅዱሳን ሁሉ ጋር እንሁን! ዳዊት፣ ሙሴ፣ ጳውሎስ፣ ዮሴፍ እና ሌሎች ብዙዎች ታላላቅ ወንዶችና ሴቶች እንዳደረጉት ንጹሕ እጆችና ንጹሕ ልብ ይዘን ወደ እግዚአብሔር እንቅረብ!

# 3

# የምድረ በዳ አስፈላጊነት

ወደ ኋላ ዘወር ብላችሁ ልምምዶቻችሁን አስቡ። ጌታ በምድረ በዳ እንዴት በየዕለቱ እንደ መራችሁ፣ እንደ መገባችሁና እንዳለበሳችሁ አስታውሱ። ክፉ ምግባራችሁንና <<የግብፅን ደስታ>> በመናፈቅ ማጉረምረማችሁን መታገሡን አስቡ! በመከራችሁ ሁሉ የጌታ ጸጋ ለእናንተ ብቁ የነበረበትን ወቅት አትርሱ።

- ቻርለስ ኤች ሰፐርጂን

አምላክህ እግዚአብሔር... በልብህ ያለውን ለማወቅ፣ ትሑት ሊያደርግህና ሊፈትንህ... በምድረ በዳ ጉዞህ ሁሉ እንዴት እንደ መራህ አስታውስ...

- ዘዳግም 8፥2

በኩሌ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ምድረ በዳ ሕይወት ስገባ በጣም ነበር የደነገጥሁት፡፡ ኢየሱስ ክርስቶስን በመከተል ያሳለፍሁቸው የመጀመሪያዎቹ ዓመቶች የጫጉላ ሽርሽር ያህል ደስ የሚሉ ነበሩ፡፡ እኔና ሊዛ መኖሪያችንን በዳላስ ቴክሳስ አድርገን ነበር፤ በመሐንዲስነት ጥቂት ጊዜ ከሠራሁ በኋላ ቤት ክርስቲያናችን ውስጥ የአገልግሎት ቦታ ያዝሁ፡፡ የተሰጠኝ፣ ‹‹ሥራ›› ፓስተራችንንና ሚስቱን ማገልገል፣ በጣም ትልቅ የነበረው ቤተ ክርስቲያናችንን ለማገልገል የሚመጡ እንግዶችን ማስተናገድ ነበር፡፡ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበር! በዚያ ዘመን ቤተ ክርስቲያናችን በአሜሪካ በጣም ከታወቁት አንዱ ስለ ነበር ቤተ ክርስቲያናችን ውስጥ አገልግሎት ለመስጠት የሚመጡ የዓለማችን ትልልቅ የወንጌል አገልጋዮችን አስተናግድ ነበር፡፡

እነዚያ ታላላቅ አገር አቀፍና ዓለም አቀፍ መሪዎች አውሮፕላን ማረፊያ ሲደርሱ የምቀበላቸው እኔ ነበርሁ፤ ከዚያም ወደ ቤተ ክርስቲያን ወይም ማረፍ ወደሚፈልጉበት ቦታ እወስዳቸው ነበር፡፡ አንዳንድ ቦታዎችን መጐብኘት ሲፈልጉ መኪና እነዳላቸው ነበር፤ አብሬአቸውም እመገብ ነበር፡፡ ከአንዳንድ የዘመናችን ታላላቅ አገልጋዮች ጋር ለብዙ ሰዓቶች የመጨዋወት ዕድል ነበረኝ፡፡ በዚህ ሁኔታ ያሳለፍሁት የመጀመሪያ ዓመት በጣም ደስ የሚል ሕይወት ነበር፡፡

በኋላ ግን ነገሮች ከባድ እየሆኑ መጡ፡፡ ያንን በተመለከተ ከእግዚአብሔር የሰማሁት ምንም ስላልነበረኝ ወደ ምድረ በዳ ሕይወት እየገባሁ መሆኑን አላወቅሁም ነበር፡፡ እግዚአብሔር የሚያስተምረን እንዲህ ያለው ቦታ ውስጥ ነው፤ ፀባያችን የሚቀረጸውና እምነታችንም የሚያድገው እዚያ ነው፡፡ የሚያስፈልግ ምድረ በዳ፡፡

እስቲ እንዲህ አስቡ፤ በቅርቡ ከዕድሜ ልክ የባርነት ሕይወት

ነጻ የወጣችሁ እስራኤላውያን እንደ ሆናችሁ አስቡ፡፡ ከግራና ከቀኝ እያጓራ የነበረው ባሕር ተከፍሎ በውስጡ በማለፍ በሰላም ወደ ደረቅ ምድር የተሻገራችሁት በቅርቡ ነበር፤ ነገሩ አስፈሪ ልምምድ ቢሆንም፣ የከፍተኛ ደስታም ጊዜ ነበር፡፡ ወደ ኋላ ዘወር ስትሉ ለእናንተ መከላከያ የሆናችሁ የውሃ ግድግዳ ጠላቶቻችሁ ላይ ሲከደን ዐይታችሁ ነበር፡፡ ሲያሰቃዩዋችሁ የነበሩ ተደምሰሰዋል፤ አዎን ለዘላለም ጠፍተዋል! እግዚአብሔር ባደረገላችሁ ታላቅ ማዳን በጣም ደስ አላችሁ፤ ፈነጠዛችሁ፤ በፊቱ አሸበሸባችሁ! እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር መሆኑን ስላወቃችሁ፣ ከእንግዲህ እፊታችሁ መቆም የሚችል ኃይል እንደሌለ አሰባችሁ፡፡ ከእንግዲህ ኃይሉን ወይም ታማኝነቱን አስመልክቶ በፍጹም ጥርጥር እንደማይኖራችሁ አስባችሁ ነበር!

አሁን ግን ሁኔታዎች ሁሉ ተለዋውጠዋል፤ ደክሞአችኋል፤ ጠምቷችኋል፤ ሰውነታችሁ በበረሓው ሙቀት እየነደደ ነው፡፡ ገና ወደ ‹‹ተስፋው ምድር›› ድንበር እንኳ አልደረሳችሁም፤ እባቦችና ጊንጦች በሞሉበት ምድረ በዳ ያለ ዓላማ እየተንከራተታችሁ ነው፡፡ አሁን ባሕር ውስጥ ሰጥመው ስለ ቀሩት ፈረሶችና ፈረሰኞች በዝማሬና በሽብሸባ ጌታን እያመሰገናችሁ አይደለም፤ ይልቁንም፣ ‹‹ከግብፅ ያወጣኸን ለምንድነው? እኛንና ልጆቻችንን፣ እንስሶቻችንንም ጭምር በውሃ ጥም ልትገድለን ነው?›› በማለት እያማረራችሁ ነው፡፡

እስቲ አንዳንድ ጥያቄዎች እናንሣ... እግዚአብሔር በታላቅ ክንድ ከጠላት ኃይል ያዳናችሁ በዚህ ግራ መጋባትና አስፈሪ ፀጥታ ባለበት ምድረ በዳ ውስጥ ሊተዋችሁ እንደ ሆነ ነው የምታምኑት? የእርሱ ዓላማ ይህ ነውን? በፍጹም አይደለም - ይህ ወደ ተስፋው ምድር በምታደርጉት ጉዞ የምታልፉበት በጣም አስፈላጊ ቦታ ነው፡፡

የእስራኤልን ልጆች ጌታ ከግብፅ ወደ ምድረ በዳ እንደ መራቸው ሁሉ፣ እናንተንም ወደዚያው ይመራችኋል፡፡ ወደዚህ ቦታ የመራችሁ እግዚአብሔር እንጂ ሰይጣን አይደለም፡፡ ይህን ደረቅ ቦታ በተመለከተ ራሱን የቻለ ዓላማ አለ፤ መለኮታዊ ዕቅድ አለ፡፡ በመጀመሪያ ትሑት ያደርገናል፤ ከዚያ ይፈትነናል፡፡ ይህን የሚያደርገው የልባችንን

እውነተኛ ባሕርይ ማወቅ እንድንችል ነው፡፡

ትሑት የሚያደርገን እንዴት ነው? ‹‹በልብህ ያለውን ለማወቅ፣ ትሑት ሊያደርግህና ሊፈትንህ አስራበህ መና መገበህ›› (ዘዳግም 8፥3)፡፡ እንዲራቡ በማድረግ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ትሑት አደረጋቸው፡፡ ቀጥሎ ደግሞ መና እንደመገባቸው ይናገራል፡፡ እርስ በርሱ የሚጋጭ አባባል ይመስላል፡፡ መና እየመገባቸው ከነበረ እንዴት ሊራቡ ይችላሉ?

መና በጣም ምርጥ ምግብ ነው፤ የመላእክት ምግብ ነው! ኤልያስ አርባ ቀን ለተጓዘበት መንገድ ኃይል ያገኘው በሁለት እንጀራ ነበር፡፡ እስራኤላውያንም ይህን ምግብ በብዛት ሲያገኙ ነበር፡፡ በሳምንቱ ውስጥ ስድስት ቀን ሙሉ ጠዋት ጠዋት ከሰማይ የሚወርደውን ትኩሱን መና ይቀበሉ ነበር፤ በስድስተኛው ቀን የሚቀበሉት ግን በተአምር ለሰባተኛውም ቀን የሚበቃቸውን ጭምር ነበር፡፡ መጀመሪያ መና ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ የተስፋው ምድር ድንበር ላይ እስከ ሰፈሩበት ቀን ድረስ አንድ ቀን እንኳ ጐድሎባቸው አያውቅም፡፡

ታዲያ፣ እግዚአብሔር፣ ‹‹አስራብሁህ›› የሚለው ለምንድነው? ስለ ምን ዐይነት ራብ ነው የሚናገረው? ይህን ለመረዳት የነበሩበትን ሁኔታ አገናዝቡ፡፡ ጧት ቁርስ የምትበሉት፣ ማታም ራት የምትበሉት ዳቦ ብቻ ነበር እንበል፤ ማባያ የሚሆን ቅቤ፣ ለውዝ፣ እንቁላል ወይም ማርማላታ አልነበረውም፤ ዳቦ ብቻ፡፡ ይህ ደግሞ ለጥቂት ቀኖች ወይም ሳምንቶች ብቻ ሳይሆን አርባ ዓመት ሙሉ የቀጠለ ነበር!

የወጣቶች ፓስተር በነበርሁ ጊዜ ሃምሳ ስድስት ወጣቶች ይዘን ለስምንት ቀን ሚሲዮናዊ አገልግሎት ትሪኒዳድ ወደሚባል አገር ሄደን ነበር፡፡ ምግባችንን የምታዘጋጅልን የትሪኒዳድ ቤተ ክርስቲያን ነበረች፤ በእንግድነት የተቀበሉን በጣም ደጐች ነበሩ፡፡ በየቀኑ የምንመገበው የዶሮ ሥጋ ነበር፡፡ በተለያዩ መንገዶች አዘጋጅተው ከሩዝና ከአትክልት ጋር ያቀርቡልን ነበር፤ ግን ሁሌም የዶሮ ሥጋ ብቻ፡፡

ስምንት ቀን ሙሉ የዶሮ ሥጋ ከበላን በኋላ፣ ከዚያ የተለየ ምግብ አስፈለገን፡፡ ወደ አገራችን ስንመለስ ከወጣቶቹ አንዱ በዚያ ምሽት ራት ምን እንደሆነ እናቱን ሲጠይቅ፣ ‹‹የዶሮ ሥጋ!›› አለችው፤ እርሱም እባክሽን ሽሮ ወጥ አዘጋጂልኝ በማለት ለመናት

ለስምንት ቀን ብቻ ትሪኒዳድ ስለ ነበርን ሁላችንም በየግላችን እንነጫነጭ ነበር፤ በዚያ ሁኔታ አርባ ዓመት ሙሉ መኖር ምን ማለት እንደሆነ ይታያችኋል? አራት ዓመት ሳይሆን፣ አርባ ዓመት ሙሉ አንድ ዓይነት ምግብ መብላት! እግዚአብሔር ያስራባቸው እንዴት እንደ ነበር አሁን ግልጽ የሆነልን ይመስለኛል፡፡ እርሱ የሰጣቸው ሆዳቸው የፈለገውን ሳይሆን፣ በሕይወትና በጤና ለመኖር የሚያስችላቸውን ነበር፡፡

በነበሩበት አካባቢ እንዲራቡና የጐደላቸውን እንዲፈልጉ ያደረጋቸው ሌላ ምን ሊኖር ይችላል? ይህን ታሪክ ስናነብ ልብሳቸውና ጫማዎቻቸው አለማለቃቸው በጣም ሊያስገርመን ይችላል፤ ሁሌም እንዲህ ቢሆን፣ ቤተ ሰብ ከወጪ አረፈ ማለት ነበር! ግን አርባ ዓመት ሙሉ አንድ ዐይነት ልብስ ብትለብሱ፣ አንድ ዐይነት ጫማ ብቻ ብታደርጉ፣ ወደ ገበያ ወጥታችሁ የምትገዙት ነገር ባይኖር፣ ምን ይሰማችኋል? እጅግ አሰልቺ ነው የሚሆነው!

አዎን፣ መሠረታዊ ፍላጐቶቻቸው ተሟልተውላቸው ነበር፤ ከፀሐይ ቃጠሎ ጥላ፣ ከብርድም መጠለያ ነበራቸው - ግን አንድ በጣም የጐደላቸው ነገር ነበር፡፡

አንድ ዐይነት አካባቢ ብቻ ማየት በጣም አሰልቺ ነበር፤ ይህ ደግሞ ለጥቂት ሳምንቶች ሳይሆን፣ አርባ ዓመት ሙሉ የቀጠለ ነበር፡፡ በየቀኑ ንጹሕ የምንጭ ውሃ፣ የለመለመ መስክ፣ ጥቅጥቅ ያለ ደን፣ የሚያምር ሐይቅ ወይም ባሕር በሌለበት፣ ተመሳሳይ የግራር ዛፎች፣ ከሰል የመሰለ ደረቅ ተራራ፣ ብዛት ያለው የአሸዋ ክምር፣ የተሰነጣጠቀ መሬት ብቻ በሚታይበት ቦታ ብትኖሩ ምን ይሰማችኋል?

ለሕይወት የሚያስፈልጋቸው ሁሉ ነበራቸው፤ እነርሱ የሚፈልጉት ግን አልነበራቸውም፡፡ ይህን በአእምሮአችን ይዘን ቀጥሎ

ያለውን ጥቅስ እናንብብ፡-

> ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምርህ ትሑት ሊያደርግህ አስራበህ... መና መገበህ። (ዘዳግም 8፥3)

ምንም እንኳ መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸውን ሁሉ ቢያሟላም፣ የሥጋቸውን ምኞትና ፈቃድ እንዳያገኙ በማድረግ እግዚአብሔር አስራባቸው፡፡ ያ ራብ ደግሞ ለፈተና ምቹ ሁኔታ ፈጠረ፤ የሚፈልጉት በእርግጥ እርሱን ሳይሆን ወደ ኃላ ጥለውት የመጡትን ነገር መሆን አለመሆኑን ሊያሳያቸው እግዚአብሔር ፈለገ፡፡ በእርግጥ የፈለጉት እርሱን ይሆን ወይስ የሥጋቸውን ምኞት? ጽድቅን ይራቡና ይጠሙ ይሆን ወይስ ምቾትና ደስታን? በጣም የሚያሳዝነው የእስራኤላውያን ልብ እርካታ ሊሰጣቸው በሚቻለው በእግዚአብሔር ላይ ብቻ አልነበረም፤ ስለዚህ ፈተናውን ሳያልፉ ቀሩ፤

> ድብልቁ ሕዝብ ሌላ ምግብ ጐመጀ፤ እስራኤላውያንም እንዲህ እያሉ ያጉረመርሙ ጀመር፣ <<ምነው የምንበላው ሥጋ ባገኘን ኖሮ! በግብፅ ያለ ምንም ዋጋ የበላነው ዓሣ፣ እንዲሁም ዱባው፣ በጢኹ፣ ኩራቱ፣ ነጭ ሽንኩርቱ ትዝ ይለናል። አሁን ግን የምግብ ፍላጐታችን ጠፍቶአል፤ ከዚህ መና በስተቀር የምናየው የለም!>> (ዘኁልቁ 11፥4-6)

**ጉዞን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች**

# 3 ነገሮችን በራሳችን መንገድ እንዳናደርግ እንጠንቀቅ

የራሳችንን ሐሳብና ፍላጐት መከተል ለለመድን ሰዎች ምድር በዳ ውስጥ ከሚገጥሙን ታላላቅ ፈተናዎች አንዱ በራሳችን መንገድ አንዳች ነገር እንዲሆን ለማድረግ መሞከር

ነው፡፡ የተጀመረው ነገር አልጠናቀቅ ሲል፣ እግዚአብሔር እጅግ የራቀ ሲመስል፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት ማድረግ የፈለግነው መጠነኛ ነገር እንኳ አልሳካ ሲል፣ ለጸሎት መንበርከካችን ጉልበታችንን ከማሳመም ውጪ ሌላ ምንም ጥቅም የሌለው ሲመስል፣ ያኔ ግራ በመጋባት አንዳች ነገር ለማድረግ ማንኛውንም ርምጃ እንወስዳለን፡፡ ይህ ግን ትክክል አይደለም፤ በመሠረቱ ምድረ በዳ ይህን ያህል እንቅስቃሴ የሚታይበት አይደለም፤ እዚያ ጥቂት ውሃና አሰልቺ ምግብ ነው የሚገኘው፡፡ ምድረ በዳ ጠፍ ቦታ ነው፡፡ ሕይወት እኛ ከምናደርገው ወይም እኛ አለን ከምንለው በላይ ነው፡፡ ይልቁንም ወሳኙ ነገር ሕይወት በቅርበት የምናውቀው ማን መሆኑና በእያንዳንዱና በየዕለቱ የእርሱን ፈቃድ መፈጸማችን ነው፡፡

በአንዱ የምድረ በዳ ቆይታዬ እያንዳንዱ ቀን እንደ ሳምንት ረዝሞብኝ ነበር፤ ጥቂት ራእይ፣ ፍላጎትና ጥቂት ተነሳሽነት ብቻ ስለ ነበረኝ እያንዳንዱ ሳምንት የወር ያህል ረዝሞብኝ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ግን ጕዞዬን መቀጠል ነበረብኝ፡፡ ወደ ፊት መግፋት፣ ልቤ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ቃል ምንጭ መቅዳት፣ የምችለውን ያህል ጌታንና ሕዝቡን ማገልገል፣ ነበረብኝ፤ ትዕግሥት በማጣት አንዳች ነገር በችኮላ ከማድረግ መታቀብ ነበረብኝ፡፡ አሁን ያለሁት እኔ ሳልሆን እግዚአብሔር በፈለገው ቦታ መሆኑን፣ በየጊዜው ራሴን ማሳሰብ ነበረብኝ፡፡ እርሱ በፍጹም ጊዜ አያባክንም፤ የሰጠውንም ተስፋ በትክክል ይፈጽማል፡፡

በእርግጠኝነት የምናገረው ምድረ በዳ፣ ‹‹ልታይ ልታይ›› የምንልበት ቦታ አለመሆኑ ነው! ንቁዎች እንድትሆኑና ማንኛውንም የኀጢአት ፈተና መቃወም እንድትችሉ በምድረ በዳ ቆይታችሁ አስፈላጊ ከሆኑ ነገሮች እየጠራችሁና ለበለጠ ዓላማ እየተዘጋጃችሁ መሆኑን

አትርሱ፡፡
እግዚአብሔር ራሱ በሚሠራው ምድረ በዳ ውስጥ ባለው አውራ መንገድ ዘወትር ከእርሱ ጋር ተመላለሱ፡፡ እርሱ የዘገዬ ቢመስላችሁ እንኳ፣ ከእርሱ ቀድማችሁ ለማለፍ አትሞክሩ!

በግብፅ ጥለው የመጡትን አስታወሱ፤ ሌላው ቀርቶ፣ በእግዚአብሔር ምሪት አሁን ካሉበት ደረቅ ምድረ በዳ ይልቅ፣ የባርነት ሕይወት የተሻለ መስሎ ታያቸው፡፡ አጉረመረሙ፤ ተነጫነጩ ሥጋ እንዲሰጣቸውም አጥብቀው መጮኸ ጀመሩ፡፡ እግዚአብሔርም ጩኸታቸውን ሰማ፡፡

> እርሱም የለመኑትን ሰጣቸው፤ ዳሩ ግን የሚያኮስምን ሕመም ሰደደባቸው... እነርሱ እስኪጠግቡ ድረስ በሉ፤ እጅግ የጐመጁትን ሰጥቶአቸዋልና፡፡ ነገር ግን ገና ምኞታቸውን ሳያረኩ፣ ምግቡ ገና በአፋቸው ውስጥ እያለ፣ የእግዚአብሔር ቁጣ በላያቸው መጣ፡፡ (መዝሙር 106፥15፤ 78፤29-30)

የተመኙትን አግኝተዋል፤ ሆኖም ከሚገባ በላይ ከፍ ያለ ዋጋ ከፍለውበታል፡፡ ከዚህ ምግብ ጋር ነፍስን የሚያከሳ ነገር መጣ፡፡ ይህ ከሳት መታገሥ እንዳይችሉ፣ ፈተናውን ማለፍ እንዳይችሉ አደረጋቸው፤ በመጨረሻም ወደ ተስፋው ምድር ሳይገቡ ቀሩ! ኀጢአት የሆነው ያቀረቡት ጥያቄ የወከለው እንጂ፣ ሥጋ መጠየቃቸው አልነበረም፡፡ ልባቸው በእግዚአብሔርና እነርሱን በሚመራበትና በሚመግበት መንገድ የረካ እንዳልነበር ያሳያል፡፡ በግብፅ ጥለውት የመጡትን ሕይወት አጥብቀው እየፈለጉ እንደ ነበረም ያሳያል፤ እዚያ የነበሩት በባርነት መሆኑን ዘንግተው፣ አሁን ያ ሕይወት አስደሳች እንደ ነበር ነው እያሰቡ የነበረው፡፡

ይህ ለሁላችንም የሚጠቅም ትምህርት አለው፤ የምንፈልገው ተስፋ የሰጠውን ጌታ ሳይሆን፣ ከዚያ ተስፋ የምናገኘውን ጥቅም

ብቻ ከሆነ፣ በምድረ በዳ ለሚኖረን ሕይወት ብርታት እናጣለን፡፡ ከትክክለኛ ዕይታ አንጻር ብንመለከተው ኖሮ፣ የባርነት ዘመን እንኳ መልካም ያልነበረውን ሕይወት በትዝታ እናሰላስላለን፡፡

እርሱ ለሚሰጣችሁ ወይም ለሚያደርግላችሁ ነገር ጌታን መፈለግ አንድ ነገር ነው፡፡ ስለ ማንነቱ ወይም ስለ እርሱነቱ ብቻ ጌታን መፈለግ ደግሞ ፍጹም ሌላ ነገር ነው፡፡ የመጀመሪያው ለራሳችሁ ጥቅምና ራስ ወዳድ ዓላማችሁ ሲሆን፣ ግፋ ቢል ውጤቱ ከእግዚአብሔር ጋር ብስለት የሌለው ግንኙነት እንዲኖራችሁ ማድረጉ ነው፡፡ ስለ ማንነቱና እርሱነቱ ጌታን መፈለግ ግን ውጤቱ ከእርሱ ጋር የጠበቀና ዘላቂ ግንኙነት እንዲኖረን ማድረጉ ነው፡፡

## እንደ ፈቃዱ የሆነ እጦት

ማንኛችንም መረዳት እንደምንችለው ጠፍ በሆነ ምድረ በዳ ውስጥ ስንኖር የአቅርቦት እጥረት ያጋጥማል፤ እዚያ የሚገኘውን እኛ የምንፈልገው ሳይሆን፣ የሚያስፈልገን ስሜታዊ፣ አካላዊ ወይም ቁሳዊ ነገሮች ብቻ ናቸው፡፡ መሠረታዊ ፍላጎታችንን በተመለከተ እንደሚጠነቀቅልን እግዚአብሔር ቃል ገብቷል፤ ስለዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ነገሮችን አትረፍርፎ ሳይሆን፣ የዕለት እንጀራችንን ብቻ ይሰጠናል፡፡

በምንኖርበት አገር ኑሮ ምቹ ከሆነ፣ ኑሮዬ ገነት ውስጥ ነው እንላለን፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ ግን ገነት የሚባል ነገር አይገኝም፡፡ በዚያ ስናልፍ የሚኖረን ልምምድ የተለያዩ ነገሮች እጥረት መኖሩን ያሳየናል፡፡ በማኅበረ ሰብ ደረጃ የሚያስፈልጋችሁን እንጂ፣ የምትፈልጉትን አታገኙም፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን መንፈሳዊ ነገር ያውቃል፤ ያ ግን እኛ ያስፈልገናል የምንለው ላይሆን ይችላል! በዚህ ጊዜ እርሱ የምንፈልገውን ይሰጠናል፤ ያ ማለት ግን የግድ እንደ እኛ ፍላጐት ላይሆን ይችላል፡፡

የምድረ በዳ ዓላማ እኛን ከተለያዩ አላስፈላጊ ነገሮች ማጥራትና ማበርታት ነው፡፡ መፈለግ ያለብን የእርሱን ፈቃድ እንጂ፣ ከእርሱ የሚገኘውን ስጦታ መሆን የለበትም፡፡ እንዲህ ከሆነ ሁሉም ነገር ወደ ተትረፈረፈበት ጊዜ ስንመጣ፣ ኪዳኑን ለእኛ ለማጽናት አብዝቶና አትረፍርፎ የሰጠን አምላካችን እግዚአብሔር መሆኑን አንዘነጋም (ዘዳግም 8፥2-18)፡፡

መሠረታዊው ችግር ፍላጐትንና ምኞትን በተመለከተ እኛ የምንሰጠው ገለጻ ከእውነታ የተለየ መሆኑ ነው፡፡ እኛ የምንፈልገውን ሁሉ የግድ ለሕይወት ወሳኝ እንደ ሆነ እናስባለን፤ በመሠረቱ ግን እንደዚያ አይደለም! ምናልባትም ብዙዎቻችን ቀጥሎ ባለው ክፍል ጳውሎስ ምን ማለቱ እንደ ሆነ በሚገባ መረዳት ያለብን ይመስለኛል፣

> ይህን የምለው ስለ ቸገረኝ አይደለም፤ ምክንያቱም በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ያለኝ ይበቃኛል ማለትን፣ ማጣትን ዐውቀዋለሁ፤ ማግኘትንም ዐውቀዋለሁ። ብጠግብም ሆነ ብራብ፣ ባገኝም ሆነ ባጣ፣ በማንኛውም ሆነ በየትኛው ሁኔታ ያለኝ ይበቃኛል የማለትን ምስጢር ተምሬአለሁ። ኀይልን በሚሰጠኝ በክርስቶስ ሁሉን ማድረግ እችላለሁ። (ፊልጵስዩስ 4፥11-13)

ሁሉም በበዛበትና በተትረፈረፈበት ጊዜ ብቻ ሳይሆን በጉድለቱም ጊዜ ቢሆን ክርስቶስ በሚሰጠው ኀይል እንደሚረካ ጳውሎስ ተምሯል፡፡ ምንም ነገር እንደሌላቸው ችግረኞች ሁሉ፣ በምዕራቡ ዓለም የተትረፈረፈ ሀብት ያለን ብዙዎች ባለን ነገር መርካትን የተማርን አይመስልም፡፡ በመብት ደረጃ ማግኘት ያለብን የመሰለንን ሁሉ ካላገኘን፣ ምንም የሌለን ይመስለናል፡፡ የሰዎችን እምነት በሀብታቸው እንለካለን፤ መንፈሳዊነታቸውንም በንብረታቸው እንመዝናለን፤ እውነተኛው መለኪያ ፀባያቸውና እምነታቸው መሆን ሲገባው፣ ምን ያህል ስኬታማ መሆናቸውን የምንለካው ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ባላቸው ማንነት ወይም ደረጃ ነው፡፡

የእስራኤል ልጆች ከግብፅ የወጡት ከግብፃውያን የዘረፉትን

ብዙ ሀብት ማለትም ከብርና ከወርቅ የተሠሩ ዕቃዎችና ንጹሕ ጌጣ ጌጦች ይዘው ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያንን የከበረ ነገር ምድረ በዳ ውስጥ ጣዖት ለመሥራት ተጠቀሙበት፤ በእነዚያ ንጹሕ ጌጣ ጌጦች ተውበውም ጣዖቶቹ ፊት አሸበሸቡ፡፡ በመሠረቱ እነዚህ ነገሮች መንፈሳዊነትን ሳይሆን ተቃራኒውን ነበር የሚያመለክቱት፡፡ ዘፀአት ውስጥ ከተጠቀሱ መካከል ወደ ተስፋው ምድር ለመግባትና ርስታቸውን ለመያዝ የሚያበቃ ፀባይ ያላቸው ሆነው የተገኙት ሁለት ሰዎች ብቻ ነበሩ፡፡ የተለየ መንፈስ ስለ ነበራቸው መግባት የቻሉት፣ ኢያሱና ካሌብ ብቻ ነበሩ፤ እነዚህ ሰዎች በፍጹም ልባቸው እግዚአብሔርን ተከትለው ነበር (ዘኁልቁ 14፥24)፡፡

አንዳችን ሌላውን የምንመዝነው በትክክለኛ ማንታችን ሳይሆን፣ ባለን ሀብትና ንብረት መጠን ከሆነ፣ መለኪያ እሴቶቻችን ተዛብተዋል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች ገንዘብ ሲያገኙ ወይም የመሪነት ወይም ሌሎች ላይ ተፅዕኖ ማድረግ ወደሚችሉበት ደረጃ ሲመጡ፣ እንደ ፈለጋቸው እንዲኖሩ እግዚአብሔር የፈቀደላቸው ይመስላቸዋል! ገንዘባቸውን ለምኞታቸው ፈቃድ በማዋል የፈለጉትን ሁሉ ይገዛሉ፤ ተፅዕኖ የማድረግ ዐቅማቸውንም ራሳቸውን ለመጥቀም ያውሉታል፡፡ ብዙ ጊዜ እንዲህ ያሉት ሰዎች የምድረ በዳ ሕይወታቸውን በአግባቡ ያልተጠቀሙበት ናቸው፡፡ በመሠረቱ ግን፣ በገንዘብ መባረክና ከፍ ያለ ሥልጣን ዓላማውንና የእርሱን ምሪት በተመለከተ የበለጠ በእግዚአብሔር ወደ መተማመን ሊያመጣን ይገባ ነበር፡፡

በአገልግሎት ዘመኑ ኢየሱስ የነበረውን ዝንባሌ ልብ በሉ፤ በራስ ወዳድነት ስሜት እየተንቀሳቀሰ አልነበረም፡፡ ኀጢአታችንን፣ ደዌያችንንና የሞት ቅጣታችንን በራሱ ወሰደ፡፡ ምንም እንኳ እርሱ ኀጢአት ባይኖርበትም፣ ከራሱ ይልቅ የበለጠ ቅድሚያ የሰጠው ለእኛ ጥቅም ነበር፡፡ ለሕይወቱና ለአገልግሎቱ የነበረው ዓላማ ራስን ማገልገል ሳይሆን፣ ራስን መስጠት ነበር! ራሱን በመካድ ከማንኛውም

የበለጠውን ስጦታ ማለትም የዘላለምን ሕይወት ለሰዎች ሰጠ፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር እንዲህ ያለውን ባሕርይ እኛ ውስጥ ይሠራል፡፡ ምድረ በዳ የመንፈስ ፍሬ የሚመረትበት ቦታ ነው፡፡ እርሱን በማወቅ ጽኑ ፍላጐት ውሃ ስንረሰርስ እርሱ እንደ ተመላለሰ መመላለስን እንማራለን፡፡

# 4

# ግንኙነታችን

ውስጣዊ ሕይወታችን ከተስተካከለ ይህን ያህል ጥረት ባናደርግም አስቸጋሪ ነገሮቻችን መወገዳቸው በጣም የሚገርም ነው፡፡

- ኤ.ደብልዩ ቶዘር

<<ብትወዱኝ ትእዛዛቴን ትጠብቃላችሁ>>

- ዮሐንስ 14፥15

እግዚአብሔር እኛን በምድረ በዳ ሲያሳልፍ ለራሱ የሚፈልገው ምንድነው? በምድረ በዳ በማለፋችን እኛ ከምናገኛቸው ጥቅሞች ጥቂቶቹን ዳስሰናል፤ አንዳንድ ተጨማሪ ነገሮች ማየታችንንም እንቀጥላለን፤ ግን ለእግዚአብሔር የሚሆኑ ነገሮችስ ይኖሩ ይሆን? አዎን፣ አሉ፡፡ ከእርሱ ጋር ያለንን ግንኙነት ደረጃ ማሳደግ ይፈልጋል፡፡ እኛ ከእርሱ ጋር በጣም እንድንቀራረብ ይፈልጋል፡፡ የሚያሳዝነው ግን ብዙዎቻችን ከጌታ ጋር የሚኖረንን ግንኙነት ለራሳችን መጠቀሚያ ብቻ ልናውለው እንፈልጋለን፤ ይህ ምኞትና ፍላጐታችንም ማነቆ ይሆንብናል፡፡

ከሚስቴ ከሊዛ ጋር በተጫጨሁበት ዘመን ለእርሷ ካለኝ ፍቅር የተነሣ አጥብቄ እከታተላት ነበር፤ ዘወትር ስለ እርሷ አስብ ነበር፡፡ የሚቻለውን ያህል ከእርሷ ጋር ብዙ ጊዜ ለማሳለፍ ማንኛውንም ነገር አደርግ ነበር፡፡ እርሷ አንድ ነገር ከፈለገች፣ የምሠራውን ሁሉ ትቼ በመኪናዬ ወደ እርሷ እበርር ነበር፡፡

ቤተ ሰቦቿ ቤት ውስጥ ከእርሷ ጋር አምስት ሰዓት ሙሉ ያሳለፍኩትን ጊዜ አስታውሳለሁ፡፡ ያም ሆኖ፣ ቅር እያለኝ ነበር ተለይቻት የሄድሁት፡፡ የምኖርበት ቦታ እንደ ደረስሁ ወዲያውኑ ስልኩ አቃጨለ፤ ሊዛ ነበረች፤ በጣም በሚጣፍጥ ድምፅ፣ ‹‹ማሬ፣ ጃኬትህን ረስተህ ሄደሃል›› አለችኝ፡፡

ድምጿ የሙዚቃ ያህል ጣፋጭ ነበር፡፡ ወዲያውኑ፣ ‹‹እንግዲያውስ ተመልሼ መጥቼ እወስደዋለሁ›› አልኳት፡፡

ወደዚያ ተመልሼ፤ እንደ ገና ሦስት አራት ሰዓት አብረን አሳለፍን፤ በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን፣ እኩለ ሌሊት ላይ፣ ‹‹ማሬ፣ አይስ ክሬም ይዘህልኝ እንድትመጣ እፈልጋለሁ›› ብትለኝ፣ ያለ አንዳች ማመንታት፣ ‹‹በአሥር ደቂቃ ውስጥ እደርሳለሁ፤ ምን ዐይነት ጣዕም ያለውን ነው የምትፈልጊው?›› እላት ነበር፡፡

ከእርሷ ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ምክንያት እፈልግ ነበር፡፡ ለእርሷ ከነበረኝ ከባድ ፍቅር የተነሣ፣ ማንኛውንም የምትፈልገውን ነገር ማድረግ ደስታዬ ነበር፡፡ እንዲህ የማደርገው ስለምወዳት እንጂ፣ ምን ያህል እንደምወዳት ለማሳየት አልነበረም፡፡

ስለ እርሷ ለሰዎች ተናግሬ አይበቃኝም፤ እንዲያውም፣ የሚሰማኝ ባገኝ ኖሮ ስለ እርሷ ለመዘመር እንኳ ወደ ኋላ አልልም ነበር፡፡ ከሰዎች ጋር እየተነጋገርሁ እያለ ጥቂት ክፍተት ካገኘሁ ጣልቃ አስገብቼ ስለ ሊዛና በቅርቡ ስለምናደርገው ጋብቻ አወራለሁ፤ ከባድ ፍቅር ውስጥ ነበርሁ!

ከተጋባን ጥቂት ዓመት በኋላ ግን ትኩረቴን ስፖርት ላይ፣ ከጓደኞቼ ጋር የማደርገውን በተለይም የአገልግሎት ሥራዬን የመሳሰሉ ነገሮች ላይ ማድረግ ጀመርሁ፡፡ ከእርሷ ጋር ምርጥ ጊዜ ማሳለፍ ወይም ለእርሷ አንድ ነገር ማድረግ አሰልቺ እየሆነ መጣ፡፡ እንደ ድሮው ስለ ሊዛ ብዙ አላስብም፡፡ ስጦታ ይገዬላት የምመጣው ለልደት በዓል (ገና)፣ ለሌሎች በዓላትና ለእርሷ ልደት ቀን ብቻ ሆነ፤ ያም ቢሆን ከሞላ ጐደል ነበር፡፡ አንድ ጊዜ የፍቅረኞች ቀን በሚከበርበት ቀን ለእርሷ ስጦታ ማምጣትን እንኳ ረስቼው ነበር፡፡ በጣም ቅር አላት፤ ሌላ ምርጫ ስላልነበረኝ ይቅርታ ጠየቅኋት፡፡ በጣም አሳዛኙ እውነታ ስንጋባ የነበረውን ሁኔታ አለማስታወሴ ነበር፡፡ ኅብረታችን ጥላ አጠላበት፤ የመጀመሪያ ፍቅሬ ቀዘቀዘ!

የኋላ ኋላ እግዚአብሔር ማስተዋሌንና ልቤን በመመለሱ በጣም አመሰግነዋለሁ፡፡ ምን ያህል ራስ ወዳድ መሆኔን እንዳይ አደረገ፡፡ ከችሮታው የተነሣ ፍቅራችንን እንደ ገና አቀጣጠለ፤ ትዳራችንንም ፈወሰ፡፡

ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነትም እንዲህ ያለ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ ብዙ የክርስቶስ ተከታዮች የራሳቸውን ምቾት ብቻ የሚፈልጉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ፤ ተጨማሪ ነገር ከመፈለግ ይልቅ በደረሱበት ደረጃ ላይ ብቻ ይወሰናሉ፡፡ እንደ ቀድሞው እግዚአብሔርንና የእግዚአብሔርን ነገር አጥብቀው አይፈልጉም፡፡ መንፈሳዊ ደረጃቸውን

ራሳቸውን ከሌሎች ጋር ወይም ብቁ ነው ከሚሉት ነገር ጋር ያወዳድራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ አጥብቀው እግዚአብሔርን መፈለግ ያቆማሉ፡፡ ትኩረታቸው ሁሉ ዕለታዊ ሥራቸው ላይ፣ ስኬታቸው ላይ፣ በዚህ ሕይወት ነገሮች ላይ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ከእርሱ ስለሚያገኙት በረከት እንጂ፣ እርሱ ራሱን አይሆንም፡፡ ከእግዚአብሔር ይልቅ ወደ ራሳቸው ዘወር በማለት በልባቸው ይስታሉ፡፡ ‹‹ክርስቲያናዊ›› ወዳጅነትን ሊያጠብቁ ይችላሉ፤ በማኅበረ ሰቡ ወይም ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሰሚነት ያላቸው ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁን እንጂ፣ ሕይወት የሰጣቸውን ጌታ አይናፍቁትም፡፡

ከእርሱ ጋር ሊኖረን የሚገባውን ጥብቅ ግንኙነት ሳይሆን፣ ለጥቅም ወይም ለበረከቶቹ ብቻ እግዚአብሔርን የምንፈልግ ከሆነ፣ በቀላሉ እንስታለን፡፡ እውነተኞች እንሁን፤ በእግዚአብሔር ፊት ረጅም ጊዜ በጸሎት የምናሳልፈው ለምን እንደ ሆነ ልብ እንበል፤ ያንን ከእርሱ ዕይታ አንጻር ከመዘንነው መጠቀሚያ ልናደርገው እየሞከርን እንደሆነ እንገነዘባለን፡፡ እግዚአብሔርን ችግር በገጠመን ጊዜ መፍትሔ የምናገኝበት ምንጭ ወደ መሆን ደረጃ ዝቅ እናደርገዋለን፡፡ እርሱ ግን እጅግ ስለሚወደን በዚያ ስሕተት ውስጥ አይተወንም፡፡ ኢየሱስን ይፈልጉ ለነበሩ አያሌ ሰዎች ያደረገውን ለእኛም ያደርግልናል፡፡

> በማግሥቱ ሰዎች… ኢየሱስ ወይም ደቀ መዛሙርቱ በዚያ አለመኖራቸውን እንዳወቁ ኢየሱስን ፍለጋ በጀልባዎች ወደ ቅፍርናሆም ሄዱ። በባሕሩ ማዶ ባገኙትም ጊዜ፣ <<ረቢ መቼ ወደዚህ መጣህ?>> አሉት። ኢየሱስም እንዲህ ሲል መለሰላቸው፤ <<እውነት እላችኋለሁ፤ የምትፈልጉኝ እንጀራ ስለ በላችሁና ስለ ጠገባችሁ ነው።>> (ዮሐንስ 6፥22-26)

ኢየሱስ ከእያንዳንዱ ተግባራችን በስተ ጀርባ ያለውን እውነተኛ ዓላማ ያውቃል፡፡ ሕዝቡ እርሱን ፍለጋ የመጡት ተጨማሪ በረከት (ነጻ ምግብ) ፈልገው እንጂ፣ ምልክቶችን ስላዩና የምልክቶቹን

ምንነት ስለ ተረዱ እንዳልነበር አውቋል፡፡ ምልክት አቅጣጫ ወይም መረጃ ይሰጣል እንጂ፣ ወደ ራሱ አያመለክትም፡፡ ሕዝቡ በእውነት እርሱን እየተከተሉ የነበረው ሆዳቸው ስለ ሞላ እንጂ፣ ምልክቶቹ የገለጡትን ጌታ በመፈለግ እንዳልነበር አውቋል፡፡

አንድ ነገር ሲያጣ ወይም ሲፈልግ ብቻ ወደ እናንተ የሚመጣ ሰው ታውቃላችሁን? እንዲያውም ከዚያ በከፋ ደረጃ ወዳጆቻችሁ መስለው የነበሩ፣ በኋላ ግን የፈለጉት እናንተን ሳይሆን ከእናንተ ገንዘብ ወይም ሌላ ነገር ፈልገው እንደ ነበር የተረዳችሁበት ጊዜ አለ? እነዚህ ሰዎች እናንተን የዓላማቸው ማሳኪያ ማድረግ እንጂ፣ በእርግጥ ስለ እናንተ የሚያስቡ ወይም እናንተን የሚወዱ አይደሉም፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ መጠቀሚያ መሆን በጣም ይጐዳል፡፡

እንዲህ ያለው ራስ ወዳድ ዝንባሌ ማኅበረ ሰቡ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፣ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ ሞልቷል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያሉ ብዙዎች በጌታ ብቻ ያረፉ አይደሉም፤ በአንድ ወቅት ለኢየሱስ የነበራቸው ፍቅር ቀዝቅዟል፡፡ ጌታን የሚያገለግሉት ለግል ጥቅማቸው እንጂ በማንነቱ እርሱን በመውደዳቸው አይደለም፡፡ ስለዚህም እግዚአብሔርን የሚፈልጉት ወይም በእርሱ ደስ የሚሰኙት የሚፈልጉትን እስከ ሰጣቸው ድረስ ነው፡፡ አስቸጋሪ ሁኔታዎች ሲመጡ ግን እውነተኛ ዓላማቸው ይገለጣል፡፡

ትኩረታችን እኔነት ላይ ከሆነ፣ ውሎ አድሮ ችግር ወይም አዳጋች ሁኔታ ሲመጣ ማጉረምረም መነጫነጭም ይኖራል፡፡ አንዴ እንደዚያ ከሆነ ደግሞ ራስ ወዳድነትን መሠረት ያደረገው ማጉረምረም ይበልጥ እያደገ ይመጣል፤ ችግሩ በጨመረ ቁጥር መነጫነጩም ይቀጥላል፡፡ ይህን የእስራኤል ልጆች ከነበሩበት ሁኔታ ማየት ይቻላል፡፡ በፈርዖን አገዛዝ ግብፅ ውስጥ ከነበረው አስጨናቂ ሕይወት ጌታ ነጻ ሲያወጣቸው ሕዝቡ ደስ ተሰኙ፡፡

> ከዚያም የአሮን እኅት ነቢይቱ ማርያም ከበሮዋን አንሥታ ያዘች፤ የቀሩትም ሴቶች ሁሉ ከበሮ ይዘው እያሸበሸቡ ተከተሏት፡፡ ማርያምም፣ <<ፈረሱንና ፈረሰኛውን በባሕር ውስጥ ጥሎአል፤

ለእግዚአብሔር ዘምሩ፤ እጅግ ከፍ ከፍ ብሎአልና!>> እያለች ዘመረችላቸው። (ዘፀአት 15፥20-21)

ሕዝቡ እንደዚያ ቀን ተደስተው አያውቁም፡፡ ከአሳዳጆቻቸው እነርሱን ለማዳን እግዚአብሔር ባሳየው ታላቅነቱ፣ ተአምራዊ ኃይሉና መልካምነቱ በጣም ተደንቀው ነበር፡፡ ከሦስት ቀን በኃላ በሱር ምድረ በዳ መራራ ውሃ ሲገጥማቸው ግን፣ ማጉረምረም ጀመሩ፤ ሙሴንም፣ ‹‹ምን እንጠጣ›› በማለት ጠየቁት (ዘፀአት 15፥24)፡፡ በመሠረቱ ይህ አስፈላጊ አልነበረም፤ ቀይ ባሕርን ከፍሎ ያሻገራቸው አምላክ የሚጠጡት ጥሩ ውሃ ሊሰጣቸው ይችል አልነበር? ከሦስት ቀን በፊት እንደ ነበረው ሙሴ አሁንም መልካም መሪ አልነበረምን?

እርግጥ ነው፤ እግዚአብሔር፣ ‹‹መራራውን ውሃ ጣፋጭ›› አድርጎታል፡፡ የዚያ ተአምር ትውስታ ግን ቶሎ ከልባቸው ደበዘዘ፡፡ ከጥቂት ቀን በኃላም ሕዝቡ ማጉረምረማቸውን ቀጠሉ፤ በዚህ ጊዜ ያጉረመረሙት፣ ምግብን በተመለከተ ነበር፡፡ ‹‹ምነው በእግዚአብሔር እጅ ሞተን ባረፍነው ኖሮ!›› በማለት አጉረመረሙ፡፡ በእርግጥ ያ ይሻል ነበር? በጠባቂዎች እየተገረፉ ጡብ መሥራት ይሻላቸው ነበርን?

በምድረ በዳውም መላው ማኅበር በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ። እስራኤላውያንም እነርሱን እንዲህ አሏቸው፤ <<ከሥጋ መቀቀያው ምንቸት ዙሪያ ተቀምጠን የፈለግነውን ያህል ምግብ መመገብ በምንችልበት በግብፅ ሳለን ምነው በእግዚአብሔር እጅ ሞተን ባረፍነው ኖሮ!>> (ዘፀአት 16፥2-3)

ሁሉም ድርቅ በሆነበት ከባድ ጊዜ ማጉረምረም ሲጀመር፣ ብዙውን ጊዜ የሚያነጣጥረው መሪዎች ላይ፣ የቤተ ሰብ አባሎች ላይ፣ ወዳጆች ወይም ጠላቶች ላይ፣ ከዚያም አልፎ መንግሥት ላይ ነው፡፡ ብዙዎቻችን የችግር የመከራችን ምንጭ እግዚአብሔር ነው ብለን አንናገርም (ስለምንፈራ)፡፡ ስለዚህም እስራኤላውያንም

ሙሴና አሮን ላይ ቢያጉረመርሙም ልባቸው ውስጥ ግን፣ ‹‹ለዚህ ሁሉ መከራ የዳረገን እግዚአብሔር ራሱ ነው!›› የሚል ሐሳብ እንደ ነበር ግልጽ ነው፡፡ ይህን በሚገባ የተረዳው ሙሴ፣ ‹‹ያጉረመረማችሁት እኛ ላይ ሳይሆን፣ እግዚአብሔር ላይ ነው›› አላቸው (ዘፀአት 16፥8)፡፡

## ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

### # 4 አጀንዳችሁን ግልጽ አድርጉ

ቀደም ባሉት የምድረ በዳ ልምምዶቼ ምንም የሚለወጥ ነገር የሌለ ይመስለኝ ስለ ነበር፣ በተቻለ መጠን ቀና ዝንባሌ እንዲኖረኝ ጥረት አደርግ ነበር፡፡ እኔን የሚያሳስበኝ ብዙ መጠበቄ ሳይሆን፣ እየጠበቅሁ እያለ የሚሰማኝ ሕመም ነበር፡፡ ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርሁ በስብከት እንዳገለግል እግዚአብሔር ወደ ሰጠኝ ራእይ እንዳልገባ መንገዱን የዘጋ በመሰለኝ ረባሽ ሁኔታ፣ በጣም እየተበሳጨሁ ነበር፡፡ የምድረ በዳ ልምምዴን እኔን ለማጥራት እንደሚጠቀምበት ጌታ ተናግሮኝ ነበር፡፡ ዘወትር አደርግ እንደ ነበረው አንድ ቀን ይህ፣ ‹‹የምድረ በዳ ጉዞ›› ለምን ይህን ያህል ጊዜ እንደ ወሰደ ግልጽ እንዲያደርግልኝ አጥብቄ እየጸለይሁ ነበር፤ ጌታም፣ ‹‹የምታገለግለው እኔን ወይም ራእይህን መሆን አለመሆኑን ለማየት ነው›› አለኝ፡፡

ከዚያ ጊዜ ወዲህ እውነተኛ አጀንዳዬ በመላው ዓለም ወንጌል እንድሰብክ እግዚአብሔር የሰጠኝ ራእይ ወይም እርሱ እስኪናገረኝ በትዕግሥትና በታዛዥነት መጠበቅ መሆን አለመሆኑን ለማጣራት በጥንቃቄ ማሰብና መጸለይ እንዳለብኝ ወሰንሁ፡፡ ከእርሱ ዓላማ ጋር ተስማማሁ ማለት የምችለው ያኔ ብቻ ነው፡፡

ስለሆነም የእኔ ምክር፡- እግዚአብሔር የሰጣችሁ

ራእይ የቱንም ያህል ድንቅ ቢሆንም፣ በእርሱ ሓልዎት ውስጥ የእርሱን ፈቃድ መፈጸም እንጂ፣ እርሱ የሰጣችሁ ራእይ ከፍተኛውን ስፍራ እንዲይዝ አትፍቀዱ፡፡

ምድረ በዳ ልባችሁ ውስጥ ያለውን ዓላማ – ራስ ወዳድ መሆን አለመሆናችሁን ይገልጣል፡፡ ልቦናችሁ ውስጥ ያለውን እንዲያሳያችሁ መንፈስ ቅዱስን ለምኑት፤ እውነተኛ ዓላማችሁ ምንድነው? እስከዚህ ጊዜ ድረስ የ‹‹ግብፅ›› ባርያዎች ያደረጋችሁና በምድረ በዳ ጉዞአችሁ እንድታጉረመርሙ ያደርጋችሁ ምንድነው? እርሱ በፍቅር የሚያቀርብላችሁን እርምት ቅንና ግልጽ ሆናችሁ መቀበል ለወደ ፊቱ መንፈሳዊ ጤንነታችሁ እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

በጣም ደስ የሚለው እያንዳንዳችን ንስሐ እንዳንገባና የልባችንን ዝንባሌ እንዳንለውጥ የማያስቆመን ምንም ነገር አለመኖሩ ነው! ከእርሱ ለሚገኘው መልካም ነገር ብቻ እርሱን መጠቀሚያ ከማድረግ ይልቅ፣ አሁኑኑ ቆም ብለን ንስሓ መግባትና የልባችንን ሁኔታ መለወጥ እንችላለን፡፡

እግዚአብሔር በምድረ በዳ የሚያሳልፈን ለእኛ ካለው የላቀ ዓላማና ታላቅ ፍቅሩ የተነሣ ሊሆን ይችላል፡፡

## እግዚአብሔር ከእኛ ስሌት በላይ ነው

የእስራኤል ልጆች ራሱ እግዚአብሔርን እየፈለጉ ስላልነበር የእርሱን መንገድ ማወቅ አልቻሉም፡፡ ታላላቅ ሥራዎቹን በአድናቆት እያዩ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ተአምር ካልተደረገ ግን ከእርሱ ወደ ኋላ ይሉ ነበር፡፡ ሙሴ ተራራው ላይ በነበረ ጊዜ እነርሱ ከእግዚአብሔር መንገድ ወጡ፤ መዳናቸው ባስገኘላቸው ጥቅም ብቻ ረክተው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ራሱን በቅርበት የማወቅ ናፍቆት አልነበራቸውም፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ እያሉ አንድ ቀን ቀደም ሲል እግዚአብሔር

ለሙሴ እንደ ተናገረ፣ ለእነርሱም ለመናገር ወደ ሲና ተራራ እንደሚመጣና ሕዝቡ ራሳቸውን እንዲቀድሱ እንዲናገር እግዚአብሔር ለሙሴ ተናገረ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጊዜው ደርሶ እግዚአብሔር በግርማውና በአስፈሪነቱ ኃይሉን በገለጠ ጊዜ ሕዝቡ ያንን መቋቋም አልቻሉም፡-

> ሕዝቡም መብረቁንና ነጐድጓዱን፣ የተራራውን መጤስና የመለከቱን ድምፅ ባዩና በሰሙ ጊዜ፣ በፍርሃት ተንቀጠቀጡ፤ በርቀትም ቆሙ፤ ሙሴንም፣ <<አንተ ራስህ ተናገረን፤ እኛም እናደምጥሃለን፤ እግዚአብሔር እንዲናገረን አታድርግ አለበለዚያ መሞታችን ነው አሉት። (ዘፀአት 20፥18-19)

‹‹አንተ ለእግዚአብሔር ተናገርልን፤ ከዚያም እርሱ የሚልህን መልሰህ ንገረን፤ እኛም ያንን እናደርጋለን›› በማለት አጥብቀው ሙሴን ለመኑት፤ እዚህም ላይ ቢሆን፣ የሚፈልጉት ከእግዚአብሔር የሚገኘውን ጥቅም እንጂ፣ ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራቸው የማይፈልጉ ምን ያህል ራስ ወዳድ መሆናቸውን እያሳዩ ነበር፡፡ ምናልባት ዓላማቸው ጥሩ ሊሆን ይችላል፤ ከእርሱ ጋር የጠበቀ ግንኙነት ሳይኖራቸው የእግዚአብሔርን ቃል መጠበቅ ፈልገዋል፤ ግን አልሆነላቸውም፡፡

እስራኤላውያን ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረብን ሳይሆን፣ ለችግሮቻቸው መፍትሔ ማግኘት ነበር የፈለጉት፤ እግዚአብሔርም አሥሩን ትእዛዞች ሰጣቸው፤ ያም ቢሆን መፍትሔ አልሆናቸውም፡፡ ቀጥሎ የመጡት ትውልዶችም ቢሆኑ፣ እነዚህን ትእዛዞች መፈጸም አለመቻላቸው ግልጽ ሆኖአል፡፡

አሁን ያለው የእኛ ትውልድስ? የተፈለገውን ያህል ጥረት ብናደርግ የእግዚአብሔርን መንገዶች መፈጸም የምንችል ስንቶቻችን ነን? ከእርሱ ጋር ሕይወት ሰጪ ግንኙነት ሳይኖረን፣ እኛም እንደ እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል ማለትም ሕጐቹን መፈጸም እንሞክራለን፡፡ ዮሐንስ 14፥21 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹የሚወደኝ ትእዛዜን ተቀብሎ የሚጠብቅ ነው፤ የሚወደኝንም አባቴ ይወደዋል፤ እኔም

እወደዋለሁ፤ ራሴንም እገልጥለታለሁ›› ብሏል፡፡

ይህን ጥቅስ ብዙ ጊዜ አንብቤ የነበረ ቢሆንም ጌታ፣ ‹‹ሕጌን ከጠበቃችሁ እኔን መውደዳችሁን ታሳያላችሁ›› በማለት እንደ ተናገረ ነበር የምረዳው፡፡ አንድ ቀን ግን ይህን ጥቅስ እንደ ገና እንዳነብ አሳሰበኝ፡፡ እኔም እንደገና አነበብሁት፤ በዚህ ጊዜ፣ ‹‹ምን ማለቴ እንደ ነበር አሁንም መረዳት አልቻልህም አይደል – እንደ ገና አንብበው!›› አለኝ፡፡ ዘጠኝ ወይም አሥር ጊዜ ያህል ጥቅሱን ደጋግሜ ባነብም፣ ቀድሞ ከነበረኝ የተለየ መረዳት ላገኝበት አልቻልሁም፡፡

በመጨረሻ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ዐላዋቂነቴን ይቅር በል፤ እስቲ፣ ምን ማለትህ እንደ ነበር አንተ አሳየኝ!›› አልሁ፡፡

‹‹ጆን፣ ትእዛዜን ከጠበቃችሁ እኔን መወደዳችሁን ታሳያላችሁ አላልሁም›› አለኝ፡፡ ‹‹እኔን መውደድ አለመውደዳችሁን አስቀድሜ ዐውቃለሁ፤ እኔ እያልሁ ያለሁት አንድ ሰው አጥብቆ እኔን ከወደደ፣ ለእርሱ ትእዛዞቼን የመጠበቅ ችሎታ ይሰጠዋል ነው!››

አሁን ገና ገባኝ! ጉዳዩ ግንኙነትን ማጥበቅ እንጂ፣ ሕግን የመጠበቅ ጉዳይ አይደለም፡፡ ይህን እንደ ትእዛዝ እንደ ተናገረ አስብ ነበር፡፡ እርሱ ግልጽ ያደረገው የጠበቀ ግንኙነትን አስፈላጊነት ነበር፡፡

- ሕግና ደንቦችን በመጠበቅ እግዚአብሔር አይታወቅም፡፡
- እግዚአብሔር በተለያዩ ዘዴዎች አይገኝም፡፡
- ሁሉን ቻዩ መንፈስ ቅዱስን ሰዎች ወደ ፈጠሩት ስሌት ዝቅ ማድረግ አይቻልም!

ይሁን እንጂ፣ ጌታን በተመለከተ ብዙዎቻችን ያለን አስተሳሰብ ይህን ነው የሚመስለው፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር መቀራረብ የሚለውን፣ ‹‹በሕጎችና በስሌቶች›› መተካት እንሞክራለን፡፡ ለደስተኛ ሕይወት የሚያበቁ ሰባት እርምጃዎች፤ ድነት ለመቀበል አራት ነጥቦች፣ ከሰዎች ጋር ያለንን ግንኙነት ማሻሻል የሚረዱ አምስት ነጥቦች፣ የጸሎት መልስ ለማግኘት አስተማማኝ ዘዴዎች የተሰኙትን የመሳሳሉ ስሌቶች ሰምተናል ወይም አንብበናል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር ሊኖረን

ስለሚገባው መቀራረብም እነዚህን የመሳሰሉ ሰው ሠራሽ ዘዴዎች መጠቀም እንሞክራለን፡፡ እግዚአብሔር ባስፈለገን ቁጥር አንዱን እንደምንፈልገው የምንጠቀምበት የተለያዩ ተስፋ ቃሎች የሞሉበት ሳጥን እንደ ሆነ እናስባለን፡፡ እግዚአብሔርን የምንቀርበው በዚህ መንገድ ከሆነ፣ ለኀጢአት መፍትሔ ማግኘት ምን ያህል ከባድ ሊሆን እንደሚችል ይታያችኋል?

እግዚአብሔር ልጆቹ ውስጥ ማለት እኔና እናንተ ውስጥ የሚኖር ሕያው አምላክ እንጂ፣ መፍትሔ ፍለጋ ሰዎች የሚያዘጋጁት ስሌት አይደለም፡፡ እርሱ ከእኛ ጋር መቀራረብና በእኛነታችንም ሆነ በምናደርገው ሁሉ ውስጥ ተሳትፎ ማድረግ ይፈልጋል! ይህ ደግሞ ልባዊ ግንኙነት ወይም እውነተኛ ቅርርብ ይጠይቃል፡፡ እንግዲህ ፍቅራችንን ከሚያደበዝዝ ከእንዲህ ያለው ጉዳይ አንጻር ኢየሱስ የሚከተለውን የተናገረው ለምን እንደ ነበር ግልጽ ይሆንልናል፤

> <<ይሁን እንጂ የምነቅፍብህ ነገር አለኝ፤ ይኸውም የቀድሞውን ፍቅርህን ትተሃል፤ እንግዲህ ከየት እንደ ወደቅህ አስብ፤ ንስሐ ገብተህ ቀድሞ ታደርገው የነበረውን ነገር አድርግ፤ ንስሐ ካልገባህ መጥቼ መቅረዝህን ከቦታው እወስድብሃለሁ፡፡>> (ራእይ 2፥4-5)

እንደ ሌሎቹ እስራኤላውያን ሙሴ በሩቅ ሆኖ እግዚአብሔርን በማምለክ አልረካም፡፡ የእግዚአብሔርን ሓልዎት መገለጥ ሲያይ፣ ይበልጥ ወደ ፊት ገፋ እንጂ ወደ ኋላ አላለም፡፡ ዘፀአት 20፥21፣ ‹‹እግዚአብሔር ወዳለበት ጥቅጥቅ ወደ ሆነው ጨለማ ሙሴ ቀርቦ ሳለ ሕዝቡ በርቀት ቁመው ነበር›› ይላል፡፡ ምንም እንኳ፣ ሙሴ ከፍ ያለ ተፅዕኖና ሥልጣን የነበረው ሰው ቢሆንም፣ ሦስት ሚሊዮን ሰዎች እየመራ የነበረ ሰው ቢሆንም፣ ብሉይ ኪዳን ውስጥ በተፈጸሙት እጅግ አስገራሚ ድንቆችና ምልክቶች እግዚአብሔር የተጠቀመበት ታላቅ አገልጋይ ቢሆንም፣ እነዚህ ነገሮች እርሱ ማርካት እንደማይችሉ ተረድቶአል፡፡ እነዚህን አስገራሚ ምልክቶችና ድንቆች ከተለማመደ በኋላ እንኳ ለእግዚአብሔር ያቀረበውን ልመና ልብ በሉ፤

<<በእኔ ደስ ተሰኝተህ ከሆነ፣ አንተን ዐውቅህና ያለ ማቋረጥ በፊትህ ሞገስ አገኝ ዘንድ መንገድህን አስተምረኝ... ሐልዎትህ ከእኛ ጋር ካልሄደ ከዚህ አትስደደን... እባክህን ክብርህን አሳየኝ።>> (ዘፀአት 33፥13-18)

እግዚአብሔር ለሙሴ ትልቅ ምርጫ አቅርቦለት ነበር፡፡ በዚያ ቃጠሎ ምድረ በዳ መካከል ሄዶ ሕዝቡን ወደ ተስፋው ምድር እንዲያመጣ እግዚአብሔር ነግሮት ነበር፡፡ በሰላም ወደዚያ እንዲገቡ የሚረዳቸው መልአክ እንደሚልክ ነግሮትም ነበር፡፡ ምድሪቱ መልካም፣ ወተትና ማር የምታፈስ፣ ያማሩ ዕይታዎች፣ ውብ አትክልት ቦታዎችና ታላላቅ የዝግባ ዛፎች የሞሉባት መሆንዋንም ነግሮት ነበር፡፡ ከዚሁ ጋር አያይዞም እርሱ ግን ከእነርሱ ጋር እንደማይሄድ ነግሮት ነበር፡፡ ሙሴ ይህን ሲሰማ እግዚአብሔር ያቀረበለትን አማራጮች ሁሉ መቀበል አልፈለገም፡፡ ሙሴ፣ ‹‹ሐልዎትህ አብሮኝ ካልሆነ ቃል የገባህልኝ ነገሮች ሁሉ ይቅሩብኝ፤ ከማንኛውም መልካም ነገር ይበልጥ እኔ የምፈልገው አንተን ራስህን ነው›› ነበር ያለው፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ እርሱን በሚፈልግ ሰው እግዚአብሔር እጅግ ደስ ይሰኛል፡፡

ሙሴ ከዚያም የበለጠ ፈልጐአል፤ ‹‹አንተን ዐውቅህና ያለ ማቋረጥ በፊትህ ሞገስ አገኝ ዘንድ መንገድህን አስተምረኝ›› በማለት እግዚአብሔርን አጥብቆ ለምኖአል፡፡ (ዘፀአት 33፥13)፡፡ እግዚአብሔርን ለማወቅ፣ የእርሱን መንገድ ማወቅ አለብን! ከእርሱ ኀይልን ወይም በረከትን ሳይሆን፣ ፈቃዱን ለማወቅ ለሚፈልጉ እርሱ መንገዱን ያሳያቸዋል፡፡ ‹‹አምላካቸውን የሚያውቁ ሕዝብ ግን ይበረታሉ›› (ዳንኤል 11፥32)፡፡

አገልግሎት በጀመርሁ ዘመን በየጠዋቱ ከአንድ እስከ ሁለት ሰዓት ያህል በጸሎት አሳልፍ ነበር፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ሰዎች እንዲድኑ ተጠቀምብኝ፤ በሽተኞች እንዲፈወሱ ተጠቀምብኝ፤ አጋንንት እንዳስወጣ ተጠቀምብኝ›› በማለት አጥብቄ እጸልይ ነበር፡፡ ደግሜ ደጋግሜ ይህንኑ እጸልይ ነበር፤ የተለያዩ ቃላት ብጠቀምም እንኳ፣ አንኳር ነጥቡ ከዚህ የተለየ አልነበረም፡፡

እየጸለይሁ የነበረው ስለ አገልግሎቴ መስፋፋት ስለ ነበር ራስ ወዳድ ነኝ ብዬ አስቤም አላውቅም ነበር፡፡

አንድ ቀን ግን፣ ‹‹ልጄ፣ ጸሎቶችህ ራስ ወዳድና ዒላማ የሳቱ ናቸው›› በማለት ጌታ ተናገረኝ፡፡ በሰማሁት በጣም ነበር የደነገጥሁት፡፡

‹‹እነዚህን ነገሮች ለማድረግ ያነሳሳህ ዓላማ ምንድነው?›› አለኝ፡፡ ‹‹ሁሌም ከአንተ የምሰማው ‹...ተጠቀምብኝ› ስትል ነው፤ የጸሎትህ ትኩረት አንተ ራስህ ላይ ነው፡፡ እኔ አንተን የፈጠርሁህ ሰዎችን እንድታድን፣ በሽተኞችን እንድትፈውስ፣ አጋንንትን እንድታስወጣ አይደለም፤ አንተን የፈጠርሁህ ከእኔ ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖርህ ነው፤ ዓላማህ መሆን ያለበትም ይኸው ነው፡፡››

ይህ ለእኔ አስደንጋጭ ነበር፡፡ ከዚያም በፍጹም የማልረሳውን ነገር አሳየኝ፤ ይሁዳ ሰዎችን ነጻ አውጥቶአል፤ በሽተኞችን ፈውሶአል፤ አጋንንት አስወጥቶአል፤ ይህን ሁሉ ያደረገው በኢየሱስ ስም ነበር፡፡ ኢየሱስ አሥራ ሁለቱን ሲልክ በኃላ ላይ አሳልፎ የሰጠው ይሁዳም ከእነርሱ ጋር ነበር፡፡ የትኩረት አቅጣጫዬ ተሳስቶ ነበር፤ እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ግብ ማለትም እርሱ ያዘጋጀልን ሰማያዊ ሽልማት – ኢየሱስ ክርስቶስን ማወቅ ነው፡፡ (ፊልጵስዩስ 3፥10)፡፡

ከጥቂት ዓመታት በኃላም ሊዛ ለአገልግሎት እየተዘጋጀች እያለ ይህንኑ እኔ ስጸልይ የነበረውን እየጸለየች ነበር፤ ጌታ ለእርሷም እየተናገራት ነበር፤ ‹‹ሊዛ፣ እኔ ሰዎችን አልጠቀምባቸውም፤ እነርሱን፣ እቀባለሁ፤ እፈውሳለሁ፤ የእኔን መልክ እንዲመስሉ እለውጣቸዋለሁ እንጂ አልጠቀምባቸውም›› አላት፡፡ በማያያዝም፣ ‹‹ሰዎች ተጠቅመውብሽ ያውቃሉን?›› አላት፡፡

‹‹አዎን ጌታ ሆይ፣››

‹‹ታዲያ፣ ምን ተሰማሽ?››

‹‹እንደ ተካድሁ ነበር የተሰማኝ!››

በመቀጠል ጌታ፣ ‹‹ብዙ አገልጋዮች እንድጠቀምባቸው ብቻ ወደ እኔ ይጮኻሉ፡፡ ‹‹እንድፈውስ ተጠቀምብኝ፤ ተፅዕኖ እንዳሳድር ተጠቀምብኝ፤ ሰዎች እንዲድኑ ተጠቀምብኝ›› ይሉኛል፤ እኔም እንደ

ልባቸው መሻት ተጠቀምሁባቸው፤ ትኩረታቸው ሁሉ አገልግሎት ላይ ሆነ፤ የሰጠኋቸውን ስጦታ የራሳቸውን መንግሥት ለመገንባት ተጠቀመበት እንጂ፣ የእኔን መንገድ ለመማር ደንታ አልነበራቸውም፡ ፡ ችግር ሲገጥማቸው ወደ እኔ ይጮኻሉ፤ እነርሱ በፈለጉት መንገድ ለጸሎታቸው መልስ ባለመስጠቴም በእኔ ተሰናከሉ፡፡ መጠቀሚያ እንዳደረግሁዋቸው ተሰማቸው፤ እኔ ላይ ተቆጡ፡፡ ቀድሞኑ እኔን በሚገባ አውቀውኝ ስላልነበር ወድቀው ተለዩ፡፡››

ፍላጐቷ ሁሉ ከባልዋ የወለደቻቸውን ልጆች ማሳደግ እንጂ፣ በግል እርሱን ለማወቅ ደንታ ስለሌላት ሴት ምን ታስባላችሁ? እንዲህ ዐይነቷ ሴት ባልዋ እግር ላይ ወድቃ፣ ‹‹ባሌ ሆይ፣ ልጆች እንድወልድልህ እባክህ ተጠቀምብኝ! ልጆች ስጠኝ፤ አለበለዚያ እሞታለሁ!›› ትላለች፡፡ ነገሩ ግራ የሚያጋባ ይመስላል፤ እኛ ራሳችን ከእርሱ ጋር ተገቢ ግንኙነት ሳይኖረን፣ ‹‹ሰዎች እንዲድኑ ተጠቀምብን›› እያልን እግዚአብሔርን መለመናችን ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ አንዲት ሴት ከባልዋ ጋር በምታደርገው ግንኙነት ልጅ እንደምትወልድ ሁሉ፣ እኛም ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነትና ኅብረት ካለን ልጆች ይወለዳሉ፡፡

እስራኤላውያን ትክክለኛውንና ተገቢ የሆነውን እየፈለጉ ወይም እየተከታተሉ አልነበረም፡፡ ፈጣሪን ሳይሆን፣ ፍጡሩን ነበር የፈለጉት፤ ውጤቱ ምን እንደ ነበር ሁላችንም እናውቃለን፡፡ ምድረ በዳ ፊት ለፊታቸው ላለው ተግዳሮት ጥበብና ብርታት የሚገኝበት የዝግጅት ቦታ ሳይሆን፣ የከንቱነት ቦታ ሆነባቸው፤ በመጨረሻው አንድ ትውልድ ሙሉ በዚያ ሞተው ቀሩ፡፡ እንዴት ያለ ውድመት ነው! የተስፋው ምድር’ኮ ይህን ያህል ሩቅ አልነበረም፡፡

ከዚህ ለሁላችንም የሚሆን ትምህርት ማግኘት ይቻላል! ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የጠበቀ ግንኙነትና ኅብረት እየተለማመድን በምናደርገው ጉዞ ምድረ በዳ በደስታ ልንቀበለው የሚገባ የሕይወት ገጽታ ነው፡፡

# 5

# አዲስ ወይን ጠጅ

<<ፍጥረትን ሁሉ የሚያድስ የአንተ አዲስ ወይን ጠጅ መያዣ ዕቃዎች አድርገን።>>

- ኤፍሬም ሶርያዊ

<<የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውን እርሱ። እነሆ አዲስ ነገር አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፤ አታስተውሉትምን? በምድረ በዳ መንገድ አዘጋጃለሁ፤ በበረሓም ምንጭ አፈልቃለሁ።>>

- ኢሳይያስ 43፥18-19



እግዚአብሔርን በጥብቅ ሁኔታ ማወቅ ከፈለግን፣ ለውጥን በደስታ መቀበል አለብን፡፡ ይህን ለመለማመድ ደግሞ ከምድረ በዳ የተሻለ ቦታ የለም፡፡ በዚህ ጠፍ በሆነ ቦታ፣ ምንም ልምላሜ በሌለበት፣ አስታወሽ በማይገኝበት ቦታ የመንፈሱን መንቀሳቀስ በአዲስ ሁኔታ እንለማመዳለን፡፡

ብዙዎችን ግራ የሚያጋባው ጥያቄ፡- ለውጥን ለማምጣት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ወይም ደረቅ የሆኑ ጊዜዎች መኖር ያለባቸው ለምንድነው? የሚለው ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ፣ የምንመለከተው ይህንን አስመልክቶ ይሆናል፡፡

ለአስራ ስምንት ወሮች ያህል በመንፈሳዊ ምድረ በዳ ካሳለፍሁ በኋላ የወጣቶች አገልግሎት መሪ እንድሆን ተመርጬ ነበር፡፡ በዚያ ዘመን በፍሎሪዳ የነበረው ያ ቤተ ክርስቲያን በመላው አሜሪካ በፍጥነት እያደጉ ካሉት አንዱ ነበር፤ ስለዚህም ከዚያ በፊት የወጣቶች ፓስተር የመሆን ልምዱ ስላልነበረኝ ሥራው ከዐቅሜ በላይ ሆነብኝ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ወደዚያ ያመጣኝ እግዚአብሔር መሆኑን አውቅ ነበር፤ አጥብቄ ፊቱን ብፈልግ መፍትሔ እንደሚኖር አውቅ ነበር፡፡

ይህ የወጣቶች አገልግሎት ባሕላዊ ዐይነት ሲሆን፣ ለልጆቹ ቀለል ያሉ ተግባራዊ ነገሮች መስጠት ላይ ያተኮረ ነበር፤ ብዙዎቹ ወጣቶች በመንፈሳዊ ሕይወታቸው እያደጉ አልነበረም፡፡ ብዙዎቹ ልቅ ዐይነት ሕይወት ነበር የሚኖሩት፡፡ ያንን ኀላፊነት ስቀበል መንፈስ ቅዱስ፣ ‹‹የንስሓን፣ የቅድስናን፣ የመታዘዝንና የክርስቶስን ጌትነት መልእክት ስበክ›› በማለት እየተናገረኝ እንደ ሆነ ይሰማኝ ነበር፡፡ ስለዚህም ይህንኑ ማስተማርና መስበክ ጀመርሁ፤ የወጣቶቹም ሕይወት በሚገርም ሁኔታ ይለውጥ ጀመር፡፡

ውጤቱ የሚደንቅ ነበር፡፡ በጥቂት ወሮች ውስጥ የወጣቶቹ ቁጥር በሦስት እጥፍ አደገ፡፡ የተደባዳቢ ቡድን አባሎች፣ ከእግዚአብሔር በጣም

ርቀው የነበሩ፣ በሐሰተኛ ትምህርት የተጠመዱ ወጣቶች በብዛት በኢየሱስ ወደ ማመን መጡ፡፡ ከእምነት ወደ ኋላ አፈግፍገው የነበሩ ወጣቶችም በእምነታቸው ይታደሱ ጀመር፡፡ ብዙዎቻችን የእግዚአብሔርን ሓልዎት በመለማመድና በፍቅር ማደግ ጀመርን፡፡ እግዚአብሔር እኛንም ሆነ አገልግሎታችንን በሚገርም በሁኔታ እየባረከ ነበር፡፡

በዳላስ የተለማመድሁት የመጀመሪያው የምድረ በዳ ጉዞዬ ያበቃው በቅርቡ ስለ ነበር፤ ከእንግዲህ የዚያ ዐይነት ሁኔታ እንደማይገጥመኝ አስቤ ነበር፡፡ የወንጌል መስበክ ጥሪዬን እያከናወንሁ ነበር፡፡ ኢየሱስ በምድረ በዳ ያለፈው አንድ ጊዜ ብቻ ስለ ነበር የእኔም ከዚያ የተለየ እንደማይሆን ጠብቄ ነበር፡፡ ግን ብዙም ሳይቆይ መሳሳቴን ተረዳሁ፡፡ በሕይወቴ መንጻትንና መንፈሳዊ ብርታትን መሞላት በተመለከተ ገና ብዙ የሚቀረኝ ነገር ነበር፤ በምድረ በዳ ስለምናሳልፈው ወቅት ገና ብዙ መማር ነበረብኝ፡፡ በቅርቡ የምገባበት የምድረ በዳ ጊዜ የመጀመሪያው የአሥራ ስምንት ወሮች ልምምዴን እንደ ሕፃናት ጨዋታ እንድመለከተው የሚያደርግ ነበር፡፡

መንፈስ ቅዱስ ለቤተ ክርስቲያናችን አመራሮች ብዙ አዳዲስ ሐሳቦች እየሰጠ ነበር፡፡ ብዙውን ጊዜ የምድረ በዳ ዝግጅት ካደረግን በኋላ ለአንዳች ተልዕኮ ‹‹በእግዚአብሔር ስንላክ›› እግዚአብሔርም አዲስ ወይን ጠጅ ከሰማይ ሲሰጠን እንዲህ ያለ ነገር ይሆናል፡፡ እንደ ሙሴ፣ እንደ ዳዊት፣ እንደ ዮሴፍና እንደ ሌሎቹ ውጤታማና ፍሬያማ የምንሆንበትን መንገድ ያሳየናል፡፡

እየተለማመድን የነበረው የወጣቶቹ አገልግሎት ዕድገት በእርግጥም ልዕለ ተፈጥሯዊ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ በዚህ ስኬትና መከናወን መሓል ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናችን አልፈን፣ ሌሎችንም የማገልገል ከባድ ሸክም ነበረኝ፡፡ በማዕከላዊ ፍሎሪዳ ያሉ ወጣቶችን ሁሉ መድረስ እንዳለብን ይሰማኝ ነበር፡፡ ስለዚህ በጸሎት ውስጥ የወጣቶቹ አገልግሎት በቴሌቪዥን ቢሰራጭ መልካም አይደለም ወይ? የሚል ሐሳብ መጣ፡፡ በዚያ ዘመን ማለት በ1980ዎቹ ዓመታት ሰዎችን በመድረስ ረገድ ይህን ማድረግ ትክክለኛ መንገድ ነበር፡፡

በዚያ ዘመን ኢንተርኔት፣ ማኅበራዊ ሚዲያ፣ ዩቲዩብ፣ ስማርት ፎን የሚባሉ ነገሮች አልነበሩም፡፡ በአካባቢያችን የነበረ አንድ ግዙፍ ቴሌቪዥን ጣቢያ አራት ሚሊዮን ሰዎች የመድረስ ዐቅም እንደ ነበረው ተረዳሁ፡፡ በጣም የሚገርመው ደግሞ ይህ ጣቢያ ቅዳሜ ምሽት አራት ሰዓት ላይ ያልተያዘ ጊዜ ነበረው፤ ፕሮግራማችንን በዚህ ሰዓት ማስተላለፍ ብዙ ወጣቶችን ለመድረስ እንደሚያስችለን አስቤ ነበር፡፡

ይህን ሐሳብ ለዋናው ፓስተር ብነግረውም ለዚህ የሚሆን በጀት የለንም አለኝ፡፡ ስለዚህም ወጣቶቻችን ለቴሌቪዥን ፕሮግራሙ የሚያስፈልገውን ገንዘብ ለማሰባሰብ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ባበረታታቸው ፈቃደኛ ይሆን እንደሆነ ጠየቅሁት፡፡ እርሱም ያንን ማድረግ እንደምንችል ነገረን፤ ስለዚህም በአደገኛ ዕፅ ሱሰኝነት፣ በአልኮል መጠጥ፣ የተጠመዱትን ወይም የተለያዩ ችግሮች ያሉባቸው በማዕከላዊ ፍሎሪዳ ያሉ ወጣቶችን በወንጌል ለመድረስ ያለኝን ራእይ ለወጣቶቻችን አካፈልሁዋቸው፡፡ ወጣቶቹም ራእዩን በመካፈል ከቤተ ሰብ ከሚሰጣቸው የኪስ ገንዘብ፣ ጋዜጦችን በመሸጥና ሌሎች የትርፍ ሰዓት ሥራ በመሥራት በየቅዳሜ ምሽት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለማሰራጨት የሚያስችለንን በቂ ገንዘብ ማሰባሰብ ቻሉ፡፡

ዋናው ፖስተር በጣም ተገረመ፤ በዚያ ሥራ የእግዚአብሔር እጅ እንዳለበት ተረዳ፡፡ ይህ የአዲስ ወይን ጠጅ ጅማሬ ነበር፤ በየሳምንቱ ቅዳሜ ከምሽቱ አራት ሰዓት ላይ የሚተላለፍ የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለማሰራጨት ያን ያህል ገንዘብ ማሰባሰብ ስለ ቻሉ ወጣቶች ከዚያ በፊት ተሰምቶ አያውቅም ነበር፤ እኛ ግን ያንን እውን አደረግነው፡፡ ብዙ ወጣቶች ጌታን መቀበል ጀመሩ፣ ‹‹የአዲስ ወይን ጠጅ›› ራእይን ባንቀበል ኖሮ፣ እነዚያ ወጣቶች ወንጌልን የሚሰሙበት ዕድል ላይኖራቸው ይችል ነበር፡፡ የወጣቶች ፓስተርነት ሥራዬን ከተውሁ ከብዙ ዓመቶች በኃላ እንኳ፣ በዚያ ስርጭት ሕይወታቸው የተለወጠ ብዙ ወጣቶችን ምስክርነት እየሰማሁ ነበር፡፡

## ለውጥ መልካም ነው

ስለ ወጣቶቹ ፕሮግራም መናገር ከመቀጠሌ በፊት፣ በመጀመሪያ አዲስ ወይን ጠጅ ምን ማለት እንደ ሆነና ለምን አስፈላጊ እንደ ሆነ ጥቂት ማብራሪያ መስጠት እፈልጋለሁ፡፡

እግዚአብሔር የሚያነሣሣውን ለውጥ እውን ማድረግ ሁሌም ቀላል አይደለም፤ ይሁን እንጂ፣ የኃላ ኃላ ሁሌም መልካምና ፍሬያማ ነው የሚሆነው፡፡ ካለንበት ምቾትና የተደላደለ ሁኔታ ስለሚያወጣን ብዙ ጊዜ ለውጥን እንቃወማለን፡፡ በተፈጥሮአችን የለመድናቸው አሠራሮችና ሁኔታዎች እስረኞች ነን፡፡ የለውጥን መንገድ ብንቀበል እንኳ፣ የለመድነውን ምቾት ስለሚነሣን ከዚያ ጋር መጣጣም ያቅተናል፡፡ ሆኖም፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ በተመለከተ ውጤታማ እንድንሆን ከተፈለገ፣ ለውጥን ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለብን፡፡

ተወልደን ያደግነው በመንፈሳዊ ቤተ ሰብ ውስጥ ከሆነ የእምነት ልምምዳችንና አሠራራችን፣ እንዲሁም ባሕላችን የሚቀረጸውና ሥር የሚሰድደው በመጀመሪያዎቹ የዕድሜ ዘመናችን ይሆናል፡፡ በመሠረቱ፣ ባሕልም ሆነ ነገሮችን የምናደርግበት መንገድ ሁሌም ስሕተት አይደሉም፤ ይሁን እንጂ፣ ሰዎች ምላሽ የሚሰጡት ልባቸው ውስጥ ላለው ምሪት ሳይሆን፣ ከባሕል ለወረሱት አስተሳሰብ ብቻ ከሆነ እምነት የሚገለጥበት መንገድ ሕይወት የለሽና የልማድ ብቻ ይሆንብናል፡፡

እንዲያውም፣ እንዲህ ያለው ልማድ ሃይማኖታዊ ማነቆ ሊሆንብን ይችላል፡፡ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብን ብቻ የሚከተል ሰው፣ ከዚህ ቀደም እግዚአብሔር ያደረጋቸውን ነገሮች አጥብቆ የመያዝ ዝንባሌ ቢኖረውም፣ አሁን እግዚአብሔር እያደረገ ያለውንና ወደ ፊትም የሚያደርገውን ግን ይቃወማል፡፡

ኢየሱስ በዚህ ምድር ባገለገለበት ዘመን የነበሩ ፈሪሳውያንና ሌሎች የሃይማኖት መሪዎች የዚህ ዐይነት ዝንባሌ ነበራቸው፡፡

የአብርሃም ልጆች፣ የቃል ኪዳኑ ሕዝብና የሙሴ ደቀ መዛሙርት ነን በማለት ሁሌም ይኩራሩ ነበር፡፡ ከዚያ ቀደም እግዚአብሔር ባደረገው ሁሉ ጠንካራ እምነት ቢኖራቸውም፣ በመካከላቸው የነበረውን የእግዚአብሔር ልጅ ግን ተቃወሙት፡፡ ለባሕላቸውና ለለመዱት የአምልኮ መንገድ ቅጥ ያጣ ቅንዓት ነበራቸው፤ ኢየሱስ መጥቶ ምቾትና መረጋጋታቸውን ሲነካባቸው፣ ያንን መቀበል አልፈለጉም፡፡ ከእግዚአብሔር አሠራር ጋር መጣጣም ሲኖርባቸው፣ እነርሱ ግን በራሳቸው ባሕላዊ ገደብ... መወሰን ሞከሩ፡፡ ባሕላቸውን አጥብቀው ለመያዝ ሲሉ እርሱ ያመጣውን ለውጥ አንቀበልም አሉ፡፡

የእናት አባቴ ሃይማኖት የሚለውን ከመጠን በላይ የሚያከርሩ ወገኖች ሰው – ‹‹እግዚአብሔር የሚሠራው በእኛ ቤት ክርስቲያንና የሃይማኖት አባቶች ብቻ ነው!›› የሚል አጉል ትምክህት ያዳብራሉ፤ በጊዜው መፍትሔ ካልተገኘለትም ወደ ትችት፣ ስድብ፣ ጥላቻና ሌሎችን አሳልፎ ወደ መስጠት ሊያደርሳቸው ይችላል፡፡ ኢየሱስ በዚህ ምድር ባገለገለበትም ዘመን ሆነ በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሲሆን የታየውም ይኸው ነበር፡፡

ለመለወጥና ከአንዱ የእምነት ደረጃና ክብር ወደ ሌላው ለመሸጋገር ከፈለግን የራሳችንን ምቾት በመተው የእግዚአብሔርን መንፈስ ምሪት መከተል አለብን፡፡ ብዙ ጊዜ ይህ መንገድ ወደ ምድረ በዳ ልምምድ ሊወስደን ይችላል፤ እግዚአብሔር የታደሰና የተነቃቃ ሕይወት የሚሰጠን በዚያ ውስጥ ስናልፍ ነው፡፡

ከመጥምቁ ዮሐንስ ሕይወት የምናየው ይህንኑ ነው፡፡ አባቱ ካህን ነበር፤ እንዲያውም በአንድ ወቅት ሊቀ ካህንም ነበር፡፡ ዮሐንስም እንደ አባቱ ካህን መሆን ይችል ነበር፡፡ ኢየሩሳሌም ወዳለው ትምህርት ቤት ሄዶ ከታዋቂው መምህር ከገማልያል እግር ሥር ተቀምጦ ካህን ለመሆን የሚያበቃውን ዕውቀት የመማር ሰፊ ዕድል ነበረው፡፡ አንድ ቀን ግን የጌታ መንፈስ ዮሐንስን ወደ ምድረ በዳ ይጠራው ጀመር፡፡ ብዙ ጸለየ፤ ሆኖም ወደ ምድረ

በዳ እንዲሄድ ውስጡ የነበረው ግፊት ይበልጥ እየጠነከረ መጣ፡፡ ውስጡ ግጭት ሳይፈጠር አልቀረም፤ እንዲያውም እንዲህ በማለት ሳያስብ እንዳልቀረም መገመት ይቻላል፡፡

አብሮ አደጎቹ በሙሉ ወደ፣ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት›› ሄደዋል፡፡ ዲፕሎማና ዲግሪ ሲያገኙ እንደ መሪ ተቀባይነት ይኖራቸዋል፡፡ ክህነት ይቀበላሉ፤ በአገሩ ውስጥ ባሉ የተለያዩ ምኩራቦች የመስበክ ዕድል ይሰጣቸዋል፡፡ ታዲያ፣ እኔን በተመለከተ የሚኖራቸው ግምት ምንድነው የሚሆነው? በጊዜ ወደ፣ ‹‹መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት›› ካልሄድሁ መጨረሻዬ ምን ሊሆን ነው?

እግዚአብሔር እንደ ጠራኝ አውቃለሁ፡፡ አንድ ጊዜ አንድ ታላቅ መልአክ ተገልጦ እኔ እንደምወለድና አገልጋይ እንደምሆን እንደ ነገረው አባቴ አጫውቶኛል፡፡ ወደ ምድረ በዳ ከሄድሁ ግን፣ ማን እንደሆንሁ ማንም አያውቅም፡፡ በምኩራባቸው እንድሰብክም አይጋብዙኝም፡፡

ይሁን እንጂ፣ በአእምሮው የሚመላለሱትን ጥያቄዎች በመተው፣ ዮሐንስ ወደ ምድረ በዳ ለመሄድ የእግዚአብሔርን መንፈስ ምሪት ተከተለ፡፡ ‹‹ሕፃኑም አደገ፤ (ዮሐንስ) በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእስራኤል ሕዝብ በይፋ እስከ ታየበት ቀን ድረስ በበረሓ ኖረ›› የሚል እናነባለን (ሉቃስ 1÷80)፡፡ ዮሐንስ ያገለገለው ስድስት ወር ብቻ ቢሆንም፣ ለዚህ አገልግሎት ከልጅነቱ አንሥቶ ለዓመታት በምድረ በዳ ዝግጅት ሲያደርግ እንደ ነበር መረዳት ትኩረት የሚያሻው ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ከሴቶች ከተወለዱት›› መካከል እርሱ ታላቅ ነቢይ መሆኑን ኢየሱስ ራሱ መስክሮለታል፡፡

ዮሐንስ ምን ያህል ጊዜ በበረሓ እንደ ኖረ፣ በስንት በረሓዎች እንደ ተንከራተተ፣ የገጠሙትን አዳጋች ሁኔታዎች በተመለከተ መጽሐፍ ቅዱስ አልነገረንም፡፡ ሉቃስ 3÷2፣ ‹‹ሐናና ቀያፋም ሊቃነ ካህናት ሳሉ፣ የእግዚአብሔር ቃል ወደ ዘካርያስ ልጅ ወደ ዮሐንስ በምድረ በዳ መጣ›› ይላል፡፡ ሐናና ቀያፋ በነባሩ ሃይማኖታዊ ሥርዐት እያገለገሉ በነበረ ጊዜ፣ በደረቁና አዳጋቹ ምድረ በዳ ውስጥ

አዲስ የእግዚአብሔር መሣሪያ ለአገልግሎት እየተዘጋጀ ነበር፡፡ አዲሱ የወይን ጠጅ የሚፈልቀውም ከዚያ ውስጥ ነው፡፡

ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 5 በድንኳን ኑር - ቤት አትሥራ

ምድረ በዳ የምታልፍበት ጊዜያዊ ቦታ መሆኑን አትርሳ፡፡ በምድረ በዳ ቆይታህ በድንኳን ኑር፡፡ በእርግጠኝነት የምነግርህ ቤት መሥራት እንደሌለብህ ነው!

ምንም እንኳ እስራኤላውያን አያሌ ዓመታት በምድረ በዳ በመንከራተት ቢያሳልፉም፤ ያ የእግዚአብሔር ዕቅድ አልነበረም፡፡ የተመቻቸ ቦታ ፈልገው ተደላድለው እንዲቀመጡ፣ ወይም ዓላማው ያ ይመስል ቤት ሠርተው እንዲኖሩ አልነገራቸውም፡፡ ደመናው በሚንቀሳቀስበት ጊዜ እነርሱም ጓዛቸውን ሸክፈው ለመነሣት ዝግጁ እንዲሆኑ በድንኳን መኖር ነበረባቸው፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ምድረ በዳ ጊዜያዊ ቦታ ነው፤ መድረሻ ፍጻሜ አይደለም፡ ፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹ሰዎች! ይህ ምድረ በዳ እስከዚህ መጥፎ አይደለም፤ የተስፋ ምድር ብሎ ነገር አያስፈልግም፡፡ ይልቁን መሠረት ቆፍራችሁ ለእኔም ሆነ ለእናንተ ቤቶች ሥሩ አላላቸውም፡፡›› በምድረ በዳ ጉዞ ዘመናቸው ሁሉ እግዚአብሔር ራሱ የሚኖረው በድንኳን ነበር፡፡

ለአጭር ጊዜ እስከሆነ ድረስ ድንኳን ተክሎ ውጪ መኖር አስደሳች ሊሆን ይችላል፤ ብዙዎቻችን ግን ያንን ትተን እዚያ መኖር እንፈልጋለን፡፡ ከአግባቡ ወጥተን ምድረ በዳ ውስጥ መሠረት እንጣል፡፡ ምንጊዜም ቢሆን ሸክምህን ሸክፈህ ለመንቀሳቀስ፣ የኃላ ኃላም አሮጌውን ድንኳን እስከ ወዲያኛው ለመጣል ዝግጁ ሁን፡፡

እግዚአብሔር ዮሐንስን ያዘጋጀው ምድረ በዳ ውስጥ እንጂ፣ በዘመኑ ተቀባይነት በነበረው ‹‹የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት›› አልነበረም! በጣም ብዙ ሰዎች በምድረ በዳ ዮሐንስ የሚናገረውን የእግዚአብሔር ቃል ለመስማት ከመላው ይሁዳና ከኢየሩሳሌም መጥተው ነበር፡፡ ትኩስ የመንፈስ ነፋስ እየነፈሰ ነበር፤ አዲስ ወይን ጠጅ እየፈለቀ ነበር፤ ያ የሆነው ምድረ በዳ ውስጥ እንጂ፣ ከሃይማኖታዊ ቦታዎች በአንዱ አልነበረም፡፡ በሃይማኖታዊው ግብዝነትና በሰዎች አጉል ባሕል የተሰላቹ ሰዎች፣ ከዚያ ወጥተው ለሚመጣው የእግዚአብሔር ልጅ ዝግጁ ለመሆን ወደ ዮሐንስ ሄዱ፡፡

ይህ ከሆነ በኋላ ወዲያውኑ፣ በዮሐንስ አማካይነት በዮርዳኖስ ወንዝ ለመጠመቅ ኢየሱስ መጣ፡፡ ምንም እንኳ፣ እርሱን ለማጥመቅ ብቃት እንደሌለው ዮሐንስ ቢያስብም፣ ኢየሱስ ግን ያ እንዲሆን አጥብቆ ተናገረ፡፡ የኢየሱስ አገልግሎት እግዚአብሔር በዚያ ወቅት በዚህ ምድር እያደረገ ከነበረው መጀመሩ አስፈላጊ ነበር፡፡ ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላ፣ ወዲያውኑ እርሱንም መንፈስ ወደ ምድረ በዳ መራው፡፡

ኢየሱስ ወደ ምድረ በዳ በተመራ ጊዜ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ የነበረ ቢሆንም፣ ከአርባ ቀን መፈተን በኋላ፣ ከምድረ በዳ የተመለሰው በመንፈስ ኃይል እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ይናገራል፡፡ ከእንግዲህ ወደዚህ ምድር ለመጣበት አገልግሎት ዝግጁ ሆኗል፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ ጥቂት ወሮች ብቻ ካገለገለ በኋላ ሌላ አዲስ ነገር ከምድረ በዳ በቀለ፤ ይኸውም የኢየሱስ ክርስቶስ አገልግሎት ነበር፡፡

## አዲስ የወይን ጠጅ መያዣ (አቁማዳ)

ኢየሱስ አገልግሎት ከጀመረ ብዙም ሳይቆይ፣ አንዳንድ ሰዎች ወደ እርሱ መጥተው፣ ‹‹የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት አብዛኛውን ጊዜ ይጾማሉ፤ ይጸልያሉ፤ የፈሪሳውያን ደቀ መዛሙርትም እንደዚሁ

ያደርጋሉ፤ የአንተዎቹ ግን ዘወትር ይበላሉ፤ ይጠጣሉ›› አሉት የሚል እናነባለን (ሉቃስ 5፥33)፡፡ ለመሆኑ፣ ‹‹አንዳንድ ሰዎች›› የተባሉት እነማን ነበሩ? መልሱን ከማቴዎስ ወንጌል እናገኛለን፤ ‹‹የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ወደ ኢየሱስ ቀርበው፣ ...ጠየቁት›› (9፥14)፡፡ እነዚህ ሰዎች ፈሪሳውያን እንደ ሆኑ ለዓመታት ተቀብዬ ኖሬአለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ የመጥምቁ ዮሐንስ ደቀ መዛሙርት መሆናቸውን በተገነዘብሁ ጊዜ ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በአዲስ ብርሃን ግልጽ አድርጐልኛል፤ እነዚህ ሰዎች አብዛኛውን ጊዜ ከምግብ በመጾምና ረጅም ሰዓት በመጸለይ ተሰላችተዋል፤ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ግን እንዲህ እያደረጉ አልነበረም፡፡ የዮሐንስ ተከታዮች የሚፈለገውን መሥዋዕት ሁሉ ከፍለዋል፤ የኢየሱስ ደቀ መዛሙርት ግን ትኩረትን ሁሉ ስበዋል፡፡

በዮሐንስ ዘመን የእግዚአብሔር መንፈስ ሲንቀሳቀስ ከነበረበት መንገድ አንዱ አብዛኛውን ጊዜ በመጾም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እነዚህ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ከዮሐንስ አገልግሎት አሠራር፣ የእግዚአብሔር መንፈስ አሁን እየሠራ ወደ ነበረው ሽግግር ወይም ለውጥ አላደረጉም፡፡ ፍሬውን ያስገኘው የእነርሱ አገልግሎት ዘዴ ወይም የአምልኮ መንገድ እንደ ሆነ አምነው ነበር፡፡ መጥምቁ ዮሐንስን ለመከተል ትልቅ ዋጋ ከፍለዋል፤ ቤተ ሰቦቻቸውን ትተው ምድረ በዳ ውስጥ አንበጦች እየበሉ ኖረዋል፤ አሁን ግን መሪያቸው እስር ቤት ውስጥ ነው፡፡ ይህ አዲሱ ሰው (ኢየሱስ) እነርሱ በነበሩበት ደንብና ሥርዐት የማይኖሩ ደቀ መዛሙርት አፍርቶአል፡፡ እንዲህ በመሆኑ የዮሐንስ ደቀ መዛሙርት ሳይከፋቸው አልቀረም፤ ሃይማኖታዊ መንፈስ ሳያዳብሩም አልቀረም፡፡

ልብ በሉ፤ ሃይማኖታዊ መንፈስ እግዚአብሔር በቀደመው ዘመን ያደረገውን አጥብቆ ያምናል፤ አሁን እያደረገ ያለውን ግን ይቃወማል፡፡ የዮሐንስ ተከታዮችን በጣም ያሳስባቸው የነበረው አሁን እግዚአብሔር እየተናገረና እያደረገ ያለው ሳይሆን፣ ለመሪያቸው ታማኝ መሆንና የእርሱ ተከታዮች እንዴት መኖር እንዳለባቸው

ነበር፡፡ ዋናው ትኩረታቸው ይከተሉት የነበረው አሠራር ላይ እንጂ፣ አሁን እየተፈጸመ ያለው የእግዚአብሔር ፈቃድ ላይ (ልብ) አልነበረም፡፡ ትኩረታቸው በአንድ ወቅት ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ መርቶአቸው የነበረው አሠራር ወይም መንገድ ላይ ነበር፡፡

ትዕቢትና ቁጣ የበላይነቱን መያዝ ጀመረ፡፡ ከዮሐንስ ጋር የነበሩት ጊዜያቸውንና ምናልባትም ገንዘባቸውንም ለአገልግሎቱ አውለዋል፡፡ አሁን ግን ሲከተሉት የነበረውን፣ ሲያራምዱት የነበረውን ወይም አግኝተነዋል ብለው አስበው የነበረውን እንዳያጡ ስጋት ገብቶአቸዋል፡፡ ስለዚህ የመጣውን ለውጥ ተቃወሙ፤ መሪያቸው ራሱ፣ ‹‹እርሱ ሊልቅ፣ እኔ ግን ላንስ ይገባል›› በማለት የተናገረለትን መቀበል አቃታቸው (ዮሐንስ 3፥30)፡፡

ኢየሱስ የሰጣቸውን መልስ ተመልከቱ፤ ‹‹ሙሽራው አብሮአቸው እያለ ዕድምተኞቹ እንዲጾሙ ማድረግ ይቻላልን? ‹‹ፍጹም አይቻልም›› (ሉቃስ 5፥34)፡፡ የእግዚአብሔር ልጅ በመካከላቸው ተገልጦ እያለ፣ መጾም ለምን ያስፈልጋቸዋል? ከእግዚአብሔር የሆነውን ነገር መቀበል ከፈለጉ፣ ማድረግ ያለባቸው ወደ እኔ መምጣት ብቻ ነው›› በማለት ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ መንገዳቸውን አጋለጠ፡፡ ሃይማኖታዊ አመለካከታቸው በመጾምና ሌሎች ሃይማኖታዊ ነገሮችን በማድረግ፣ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እናገኛለን በማለት እንዲያስቡ አደረጋቸው፡፡ የእነርሱ መጾም ከማይጾሙት ወይም የእነርሱን መንገድ ከማይከተሉት ይበልጥ ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርባቸው መስሎ ታያቸው፡፡ በዚህ መልኩ ትዕቢት አቆጠቆጠ፤ ባሕል ከዋናው ጉዳይ የበለጠውን ቦታ ያዘ፡፡

ከምግብ መጾም ጥቅም ቢኖረውም፣ እግዚአብሔር የሚናገረውን በተሻለ ሁኔታ ለመስማት ወደሚያስችለን ሁኔታ የሚያመጣን እንጂ፣ እግዚአብሔር ላይ ተፅዕኖ የምናደርግበት መንገድ አይደለም፡፡ ታዲያ፣ እርሱ በመካከላቸው እያለ፣ የእግዚአብሔርን ድምፅ ለመስማት ደቀ መዛሙርቱ መጾም ለምን ያስፈልጋቸዋል? እንደገና ሉቃስ 5፥34-35 ተመልከቱ፣ ‹‹ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፤ ሙሽራው አብሮአቸው

እያለ ዕድምተኞቹ እንዲጾሙ ማድረግ ይቻላልን? ነገር ግን ሙሽራው ከእነርሱ የሚወሰድበት ቀን ይመጣል፤ በዚያ ጊዜ ይጾማሉ፡፡›› ‹‹ይጾማሉ›› አለ እንጂ፣ ‹‹ምናልባት ይጾሙ ይሆናል›› አለማለቱን ልብ በሉ፡፡ እነዚያ ሰዎች የሚናገሩት ከምግብ ስለ መጾም ብቻ ነበር፤ ኢየሱስ ግን ስለ ሌላ ዐይነት ጾም እየነገራቸው ነበር፡፡ ይህ ጾም የሚደረገው ሙሽራው ከእርሱ በሚወሰድበት ጊዜ መሆኑን ልብ በሉ፡፡ እየተናገረ ያለው ከምግብ ስለ መጾም ብቻ ሳይሆን፣ የእርሱን ሓልዎት መገለጥ ስለ መፈለግ ጾም ነው፡፡ ይህ እውነት መሆኑን ቀጥሎ ከነገራቸው ምሳሌ መረዳት ይቻላል፡፡ የምድረ በዳ ሕይወት መገለጫ ከሆኑ ነገሮች አንዱ፣ የእግዚአብሔር ሓልዎት ከእኛ በጣም የራቀ መስሎ መታየቱ ነው፡፡

እየተናገረ የነበረውን ምሳሌ ለማብራራት የሰጠውን ገለጻ ተመልከቱ፡፡

> <<አዲስ የወይን ጠጅም በአሮጌ አቁማዳ ጨምሮ የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል፤ የወይን ጠጁ ይፈስሳል፤ አቁማዳውም ከጥቅም ውጪ ይሆናል፡፡>> (ሉቃስ 5፥37)

በመጽሐፍ ቅዱስ ወይን የእግዚአብሔር ሓልዎት ወይም መገኘት ምልክት ነው፡፡ ኤፌሶን 5÷18 ላይ ጳውሎስ፣ ‹‹በመንፈስ ተሞሉ እንጂ፣ በወይን ጠጅ አትስከሩ፤ ይህ ብክነት ነውና›› ይላል፡፡

በአዲሱ ወይን ጠጅ ማለትም በእግዚአብሔር ሓልዎት መሞላት አለብን፡፡ አዲስ ወይን ጠጅ፣ ትኩስ የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ነው፡፡

እስቲ፣ አሁን ይህን ጠቃሚ ጥያቄ በአጭሩ እንደገና ላንሳው፡፡ መጀመሪያ በመንፈስ ቅዱስ ስትሞሉ ምንኛ ደስ ይል እንደ ነበር ታስታውሳላችሁ? የእግዚአብሔር ሓልዎት በጣም ጣፋጭና ብርቱ ነበር፡፡ በጸለያችሁ ጊዜ ወዲያውኑ ሓልዎቱ ይሰማችሁ ነበር፤ ቀኑን በሙሉ እርሱ ከእናንተ ጋር መሆኑ ይሰማችሁ ነበር፡፡ በዚያ

ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስትቀመጡ እርሱ ለእናንተ በጣም ቅርብ ከመሆኑ የተነሣ በደስታ ታለቅሱ ነበር፡፡

ውሎ አድሮ ግን የእርሱ ሓልዎት እንደ ቀድሞው በቀላሉ በጉልህ ላይሰማችሁ ይችላል፡ አሁንም እንደ ቀድሞ እየጸለያችሁ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው? በማለት ትጠይቃላችሁ፤ ምናልባት የምድረ በዳ ጉዞ መጀመሩ ይሆናል!

ያ ምድረ በዳ ወይም የእግዚአብሔር ሓልዎት ጾም ራሱን የቻለ ምክንያት አለው፡፡ አዲስ አቁማዳ እንድትሆኑ እግዚአብሔር እያዘጋጃችሁ ነው፡፡ አዲሱን የወይን ጠጅ ማለት ትኩስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንቅስቃሴን በአሮጌው አቁማዳ ውስጥ ማኖር አትችሉም፡፡

ኢየሱስ ባገለገለበት ዘመን አቁማዳ የሚባለው ከበጎች ቆዳ የሚሠራ መያዣ ነበር፡፡ ወይን ጠጁ መጀመሪያ ሲያዝበት ቆዳው ተላጣጭና ተጣጣፊ ነበር፡፡ በቀላሉ ይለጠጣል፤ ወይን ጠጅ በተጨመረ መጠን ያለ ምንም ችግር ይሰፋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዓመታት እየተቆጠሩ ሲሄድ የመካከለኛው ምሥራቅ የአየር ሁኔታ ቆዳውን ያደርቀዋል፤ ቆርፋዳና በቀላሉ የሚጐዳ ይሆናል፡፡ ውስጡ ያለው ወይን ጠጅ ወጥቶ አዲስ የወይን ጠጅ ሲገባበት አቁማዳው በጣም ቆርፋዳና ለአደጋ ተጋላጭ ስለሆነ፣ የአዲሱን ወይን ጠጅ ክብደት መሸከም ወይም መብላላቱን ማስተናገድ አይችልም፤ ስለዚህ በቀላሉ ይሰነጠቃል ወይም ይቀደዳል፡፡ ይህን ችግር ለማስተካከል አሮጌው አቁማዳ ለተወሰነ ቀን ውሃ ውስጥ ይዘፈዘፋል፤ ከዚያም በወይራ ዘይት ይታሻል፡፡ ያ መደረጉ አቁማዳውን ተለጣጭና ተጣጣፊ ወደ መሆን ይመልሰዋል፡፡

ይህ እኛ ውስጥ የሚፈጸመው ሁኔታ ምሳሌ ነው፤ ምክንያቱም፣ እኛ የአዲሱ መንፈሳዊ ወይን ጠጅ መያዣ አቁማዳዎች ነን፡፡ የእግዚአብሔር ሓልዎት በውስጣችን እንዲኖር ተጠርተናል፡፡ የምናልፍበት ወይም የምንኖርበት ሁኔታ ለእግዚአብሔር አሠራር ምቹና ዝግጁ እንዳንሆን ያደርገናል፡፡ የምንኖረው ዓለም በሚባል ብልሹ ሥርዐት ውስጥ እንጂ፣ መንግሥተ ሰማይ ውስጥ አይደለም፡፡ አእምሮአችን በየጊዜው

መታደስ ይኖርበታል፡፡ አቁማዳችን ምቹና – ሁሌም ለትኩሱ የወይን ጠጅ ዝግጁ እንዲሆን በእግዚአብሔር ቃል መረስረስ አለበት፡፡ ኤፌሶን 5÷26 ላይ ጳውሎስ፣ ‹‹እርሱ (ኢየሱስ) በቃሉ አማካይነት በውሃ አጥቦ (ቤተ ክርስቲያንን) በማንጻት (ቤተ ክርስቲያንን) እንዲቀድሳት…›› በማለት ጽፏል፡፡ አቁማዳው በወይራ ዘይት መቀባቱ፣ እኛን በተመለከተ በጸሎት እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጊዜ መስጠት ማለት ነው፡፡ ቃሉን በማንበብና በጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ስናሳልፍ አእምሮአችን ይታደሳል፤ በመንገዳችንና በአሠራር ዘዴያችን ግትሮች አንሆንም፡፡

ሆኖም፣ አሮጌውን አቁማዳ ለማደስ መጀመሪያ ውስጡ ያለው አሮጌው የወይን ጠጅ መፍሰስ አለበት! ያ ማለት ዕቃው ውስጥ ምንም ወይን ጠጅ የለም፤ በጉልህ የሚታይ የእግዚአብሔር ሓልዎት የለም ማለት ነው! ያ የእግዚአብሔርን ሓልዎት ጾም ወይም ደጋግመን እንዳልነው ደረቅ ጊዜ ማለት ነው! እንግዲህ ለመለወጥ ዝግጁ የምንሆነው በዚህ ዐይነቱ ወቅት ውስጥ ነው!

ለመሆኑ እግዚአብሔር ሓልዎቱን የሚወስደው ለምንድነው? ተስፋ ሊያስቆርጠን ነውን? በፍጹም አይደለም፤ ያ የሚሆንበት ሁኔታ ግን ይኖራል! እርሱ እስኪፈልጋችሁ ድረስ ከፊቱ ገለል እንድትሉለት ነውን? በፍጹም አይደለም! እርሱ ሓልዎቱን የሚወስደው በበለጠ ትጋት እርሱን እንድትፈልጉና እንድትናፍቁ ለማድረግ ነው፡፡ መፈለግ እንደ ገና ተለጣጭና ተጣጣፊ ያደርጋችኋል፡፡ ግትርና ተጣጣፊ ያልሆኑ ሰዎች እግዚአብሔርን መፈለግ የተዉ ሰዎች ናቸው፡፡ የራሳቸውን መንገድ የሙጥኝ ብለው ይዘዋል፡፡ ያለፈው ጊዜ ልምምዳቸውን መሠረት በማድረግ የራሳቸውን አሠራርና ስሌት እንደ ቋሚ ነገር ወስደዋል፡፡

የእነዚያ ዮሐንስን ይከተሉ የነበሩ ሰዎች ሁኔታም ይህን ይመስላል፡፡ በእርሱ በኩል እግዚአብሔር በኃይል ሲሠራ አይተው ስለ ነበር፣ ራሳቸውን ከእርሱ ጋር አቆራኝተዋል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔርን በቅርበት የማወቅን ሰማያዊ ዋጋ ለመያዝ ወደ ፊት ከመዘርጋት ይልቅ በእምነት ይዞታቸውና አሠራራቸው ግትሮች

ሆነዋል፡፡

በማንኛውም የእግዚአብሔር እንቅስቃሴ በአዲስ ሁኔታ የምንማረው ትምህርት ይኖራል፡፡ ትምህርትና ጤናማ አስተምህሮ እኛን ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሚያመጡ መንገዶች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለትምህርቱ ወይም ትክክል ነው ብለን ይዘነው ለነበረው አስተምህሮ ተገቢ ያልሆነ ትኩረት የምንሰጥ ከሆነ፣ ውሎ አድሮ ለሃይማኖታዊ ቀንበር ወይም ለወግ አጥባቂነት ወይም ለስሕተት አስተሳሰብ ወይም ለእነዚህ ሁሉ ሊዳርገን ይችላል፡፡

በያዛችሁት ግትር የአምልኮ መንገድ እግዚአብሔርን ማወቅ አትችሉም፤ ይሁን እንጂ፣ ብዙ ክርስቲያኖች ሳያውቁት እንዲህ ባለው አኗኗር ውስጥ ናቸው፡፡ የሙጥኝ ብለው የያዙዋቸው አመለካከቶች፣ አካሄዶችና የአምልኮ መንገዶች መሥርተዋል፡፡ ውሎ አድሮ አርአያነት ያለው ክርስቲያን የሚያደርጋቸው ዕውቀት ሲገጥማቸው ፍለጋቸውን ያቆማሉ፤ ወደ ለመዱት አመለካከት ወይም ባሕል ይመለሳሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እየኖሩ ያሉት የተሟላውን ወንጌል ቢመስላቸውም አሁንም ባዶነት ይሰማቸዋል፡፡

ኤርምያስ 29፥12-13 እንዲህ ይላል፤

> ‹‹እናንተም ትጠሩኛላችሁ፤ ቀርባችሁ ወደ እኔ ትጸልያላችሁ፤ እኔም እሰማችኋለሁ። እናንተ ትፈልጉኛላችሁ፤ በፍጹም ልባችሁ ከፈለጋችሁኝ ታገኙኛላችሁ።››

እግዚአብሔርን በማግኘት ረገድ ጸሎት ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ የሃይማኖታዊ ልማድና ወግ እስረኞች ቢሆኑም፣ በታማኝነት ጸሎት የሚያደርሱ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡ እግዚአብሔር ግን በፍጹም ልባችን እርሱን መፈለግ እንዳለብን ነው የሚናገረው፡፡ እንዲህ ዐይነት ፍለጋ ከተለምዷዊ ጥሪት ያለፈ ነው፡፡ አጥብቆ እርሱን መፈለግና ፈቃዱን መናፍቅን ይጠይቃል፡፡ ዕብራውያን 11፥6፣ ‹‹…ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብ ሁሉ እግዚአብሔር መኖሩንና ከልብ ለሚሹትም ዋጋ እንደሚሰጥ ማመን አለበት›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

እስቲ አሁን ደግሞ ኢየሱስ ያለውን እንደ ገና እንይ፤

<<አዲስ የወይን ጠጅም በአሮጌ አቁማዳ ጨምሮ የሚያስቀምጥ ማንም የለም፤ እንዲህ ቢያደርግ አዲሱ የወይን ጠጅ አቁማዳውን ያፈነዳዋል፤ የወይን ጠጁም ይፈስሳል፤ አቁማዳውም ከጥቅም ውጪ ይሆናል። ስለዚህ አዲስ የወይን ጠጅ በአዲስ አቁማዳ መጨመር አለበት፤ እንግዲህ አሮጌ የወይን ጠጅ ከጠጣ በኋላ፣ አዲሱን የሚሻ ማንም የለም፤ ምክንያቱም <አሮጌው የተሻለ ነው> ስለሚል ነው። >> (ሉቃስ 5፥37-39)

አሮጌውን ወይን ጠጅ የለመደ ሰው፣ በድንገት ተነሥቶ አዲሱን ወይን ጠጅ አይፈልግም፡፡ ምክንያቱም የልማድ ተገዢዎች የሆንን ፍጡራን በመሆናችን ነው፡፡ አሮጌውን ወይን ጠጅ አውጥቶ በመድፋት፣ አዲሱን የወይን ጠጅ እንድንጠማ ደረቅ በሆነ የዝግጅት ጊዜ እኛን በማሳለፍ ተመቻችተን የተቀመጥንበትን ልማዳችንን እግዚአብሔር መስበር አለበት፡፡ በጣም ከተጠማችሁና ምንም የምትጠጡት ከሌላችሁ፣ ‹‹አዲሱን ወይን ጠጅ አልፈልግም፤ እኔ የምፈልገው አሮጌውን ነው›› በማለት አታማርሩም፡፡ የእግዚአብሔርን ሓልዎትና ኃይል የምትፈልጉ ከሆነ፣ በሕይወታችሁ ለሚሆነው ትኩስ የእግዚአብሔር መንፈስ እንቅስቃሴ ዝግጁ ትሆናላችሁ፡፡ በምድረ በዳ ልምምዱ ጊዜ ዳዊት እንዳለው፣ እኛም እንዲህ እንላለን፤

እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ አምላኬ ነህ፤  
አንተን ከልብ እሻለሁ፤  
ውሃ በሌለበት፣ በደረቅና በተራቈተ ምድር  
ነፍሴ አንተን ተጠማች  
ሥጋዬም አንተን ናፈቀች።  
ስለዚህ በመቅደስህ ውስጥ አየሁህ  
ኀይልህንና ክብርህንም ተመለከትሁ። (መዝሙር 63፥1-2)

ዳዊት የእግዚአብሔርን ኀይልና ሓልዎት ተጠምቶአል፡፡

ስለዚህም ወደ ተጠራበት ሥራ ሲመጣ፣ የእግዚአብሔርን ሳይሆን የገዛ ራሱን መንገድ ከተከተለው ከሳኦል በተለየ መልኩ ጌታ ለሚፈልገው ሁሉ ተጣጣፊ (የተመቸ) ሆኗል፡፡

## ሌላ የምድረ በዳ ቆይታ

ቀደም ሲል በዚህ ምዕራፍ እንዳመለከትሁት የማስተማር አገልግሎት የጀመርሁት የወጣቶች ፓስተር በመሆን ነበር፡፡ በቴሌቪዥን የምናስተላልፈው ስብሰባ ትልቅ ስኬት ሆኖልን ነበር፡፡ በአካባቢያችን በነበረ በጣም ተወዳጅ ዓለማዊ ሬዲዮ ጣቢያም ወንጌል እናሰራጭ ነበር፡፡ ሁሉም ነገር በመልካም ሁኔታ እየሄደ ነበር፡፡ አንድ ቀን እየጸለይሁ እያለ እግዚአብሔር ለውጥ እየመጣ እንደሆነ ነገረኝ፣ ‹‹ከወጣቶች ፓስተርነት ተነሥተህ፤ ከአሜሪካ ምሥራቅ የባሕር ዳርቻ እስከ ምዕራብ ዳርቻ፣ ከካናዳ እስከ ሜክሲኮ ድንበር፣ ወደ አላስካ፣ ሐዋይ... ከተሞች ወዳሉት ቤተ ክርስቲያኖችና ኮንፈረንሶች እልክሃለሁ›› አለኝ፡፡

መንፈስ የነገረኝን ለሊዛ ነገርኋት፤ በሌላ ከተማ ለነበረ አንድ ፓስተር ወዳጃችን በቀር ነገሩን ለማንም ሳናካፍል ሁለታችንም ይህን በልባችን እናሰላስለው ነበር፡፡ እግዚአብሔር ያንን እንደሚያደርግ ተናገረ፤ እኔም የተናገረው በእርግጥ እርሱ እንደ ነበር አውቃለሁ፤ የተናገረውን እንዲያደርግ እግዚአብሔርን መርዳት እንደማልችል አውቃለሁ፡፡

ለአንድ ዓመት ያህል ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፡፡ በዚያ የቆይታ ጊዜ በፍጹም የማይቻል እስኪመስል ድረስ፣ ወደ እግዚአብሔር ሓልዎት ውስጥ መግባት በጣም አዳጋች እየሆነብኝ መጣ፡፡ ከምንጊዜውም በላይ ብዙ ጊዜ በጸሎት አሳልፍ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን የተለወጠ ነገር አልነበረም፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ ቀደም ሲል ለወጣቶች የነበረኝ ራእይ እየደበዘዘ መጣ (በአሮጌው ወይን ጠጅ መደፋት ልንመስለው እንችላለን)፡፡ ብዙ በጸለይሁ መጠን ራእዩም የበለጠ ያሽቆለቁል ነበር፡፡ በውጭ በኩል ምንም የተለወጠ ባይኖርም፣

እኔ ውስጥ ግን ፍላጐቴ እየደከመ ነበር፡፡

የወጣቶች አገልግሎት ከመጀመሩ በፊት ለሰዓቶች ያህል እጸልይ ነበር፤ ሌላ ሰው እንዲሰብክ እግዚአብሔርን የጠየቅሁበት ብዙ ጊዜ እንደ ነበረም አስታውሳለሁ፡፡ ወደ አገልግሎት የምሄደው ባዶነት እየተሰማኝ ነበር፤ እያገለገልሁ እያለ ግን የእግዚአብሔር ሐልዎት ሲመጣ ይታወቀኛል፡፡ አገልግሎቴን ፈጽሜ ወደ ቤት እየሄድሁ እያለ እስከሚቀጥለው ሳምንት የእግዚአብሔር ሐልዎት ከእኔ ይለይ ነበር!

ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ፣ ከዚያ በፊት አይተነው በማናውቀው ውስጣዊና ውጫዊ ፈተና ውስጥ እያለፍን ነበር፡፡ ምናልባት አንድ የፈጸምሁት ከባድ ኀጢአት ሳይኖር እንደማይቀር አሰብሁ፤ ኀጢአት ነው ብዬ ያሰብሁትን ሁሉ ተናዘዝሁ፤ ግን ከነበርሁበት ደረቅ ጊዜ እፎይታ አላገኘሁም፡፡

አንድ ቀን የፈጸምሁት ኀጢአት የትኛው ሊሆን እንደሚችል እያሰላሰልሁ ሳለ ጌታ፣ ‹‹እዚህ ምድረ በዳ ውስጥ ያለኸው ኀጢአት ስላደረግህ አይደለም! እየመጣ ላለው ለውጥ እያዘጋጀሁህ ነው›› አለኝ፡፡

እየመጣ ያለውን አገልግሎት ለማስተናገድ የሚያስፈልገኝን ባሕርይ እኔ ውስጥ እየሠራ ነበር፡፡ እስቲ፣ ኢሳይያስ 43፥18-19 እናንብብ፤

> <<የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውን እርሱ፡፡ እነሆ አዲስ ነገር አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፤ አታስተውሉትምን? በምድረ በዳም መንገድ አዘጋጃለሁ፤ በበረሓም ምንጭ አፈልቃለሁ፡፡>>

‹‹እየመጣ ስላለው ለውጥ›› በራሱ ጊዜ እግዚአብሔር በተአምራዊ መንገድ ስለ ገለጠው ዝርዝር ሁኔታ ቆየት ብዬ በዚሁ መጽሐፍ እነግራችኋለሁ፡፡ በዚያ ከባድ የምድረ በዳ ሕይወቴ ለአሜሪካ፣ በኋላም ለአገሮች የሚሆነውን አገልግሎታችንን ለመውለድ እግዚአብሔር ሁኔታዎችን እያዘጋጀ ነበር፡፡

ወዳጄ፣ አዲሱ ሲመጣ፣ ከእርሱም ጋር ፈተናዎች ሲመጡ፣ ወደ አሮጌው የመመለስ ፍላጐት እንዳይኖርህ እግዚአብሔር አሮጌው የወይን ጠጅህን ያደርቀዋል፡፡

# 6

# ሰማያዊ ሽልማት

አንዳንድ ሰዎች ወደ ኃላ ተመልሰው ያለፉበትን መከራ ሁሉ ይጐለጉላሉ፤ ፊት ለፊታቸውም ሌሎች ተጨማሪ መከራዎች እንደሚኖሩ ይጠብቃሉ፤ ዕድሜ ዘመናቸውን በድንጋጤና በመርበትበት ያሳልፋሉ።

- ዲል. ሙዲ

ወንድሞ ሆይ፣ እኔ ገና እንዲያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቆጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኃላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ።

- ፊልጵስዩስ 3፥13-14

ከአዲስ ኪዳን ሁለት ሦስተኛውን የጻፈው ሐዋርያው ጳውሎስ ነው፡፡ ብዙ አብያተ ክርስቲያናትንም ተክሏል (መሥርቶአል)፡ ፡ አገልግሎቱ በመላው ዓለም ተስፋፍቶ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን ሕይወቱ ማብቂያ ላይ፣ ‹‹እንደ ያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቆጥርም›› ብሎአል፡፡ በደረሰበት ደረጃ አልረካም፤ ሩጫው መጨረሻ ላይ ደርሶ ሽልማት እስኪቀበል ድረስም አይረካም፡፡

ሩጫችንን እንድንጨርስና ሽልማታችንን እንድንቀበል ከተፈለገ፣ ልባችን ውስጥ መያዝ ያለብን የመጀመሪያ ነገር፣ ገና እንዳልያዝነው ወይም ገና እንዳልደረስንበት መገንዘብን ነው፡፡

ፍጹማን አይደለንም፤ ስለዚህ በየጊዜው መለወጥና ማደግ አለብን፡፡ ሙሴ አስደናቂ ጥሪ ያለው ሰው ነበር፤ ሦስት ሚሊዮን ሕዝብ መርቷል፤ ብሉይ ኪዳን ውስጥ ከነበሩት ሁሉ የበለጠ ተአምራዊ ምልክቶችና ድንቆች በአገልግሎት ዘመኑ ተደርገዋል፡፡ ያ ሁሉ ሆኖ ግን ሙሴ በምድር ላይ እጅግ የዋህ (ለመማር ዝግጁ የሆነ) ሰው መሆኑን እግዚአብሔር ተናግሮአል፡፡ ሩጫውን ለመጨረስና ሰማያዊ ሽልማትን ለመቀበል በመገሥገሥ ላይ ያለ እንደሆነ ራሱ እንጂ፣ ግቡ ላይ እንደ ደረሰ ወይም በእጁ እንደ ያዘ ራሱን አልቆጠረም፡፡ መለወጥና ማደግ ከፈለግን፣ ለመማር ዝግጁ መሆን አለብን፡፡

ለእግዚአብሔር ሩጫችንን መፈጸም ከፈለግን፣ ማድረግ ያለብን ሁለተኛ ነገር፣ ከኃላ ያለውን ነገር (ድልም ሆነ ሽንፈት) መርሳት ነው! በኢሳይያስ 43፥18-19 ላይ እግዚአብሔር የሚናገረውን እንደ ገና እንመልከት፤

> ‹‹የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውን እርሱ፡፡
> እነሆ አዲስ ነገር አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን
> ይበቅላል፤ አታስተውሉትምን?
> በምድረ በዳ መንገድ አዘጋጃለሁ፤ በበረሓም
> ምንጭ አፈልቃለሁ፡፡››

ያለፈ ዘመን ውድቀትን፣ በሌሎች መገፋትን ወይም ኀጢአትን ሁሉ የምናሰላስል ከሆነ፣ ለክርስቶስ ወደ ፊት ከመገሥገሥ ያሰናክሉናል፡፡ ያም ሆኖ፣ ያለፈው ዘመንም ድል እንዲሁ ወደ ኃላ ሊይዘን ይችላል፡፡ ከሚገባ በላይ በራሳችን የምንመካና በእኛነታችን እርግጠኞች በመሆን ባለፈው ዘመን ስኬታችን የምንደገፍ ከሆነ፣ እግዚአብሔር ለእኛ ያዘጋጀው ነገር ሊያመልጠን ይችላል፡፡ ኢሳይያስ 43 ላይ እግዚአብሔር የሚለውም ይህንኑ ነው፡፡ ያለፉት ነገሮች በእርሱ የሆኑ ነበሩ፤ ይሁን እንጂ፣ ወደ ፊት መገሥገሣችንን እንድንቀጥልና እግዚአብሔር ያቀደልንን እንድንፈጽም ባለፈው ዘመን እርሱ በእኛ ውስጥ የሠራበትን መንገድ ለመተው ዝግጁ መሆን አለብን፡፡ ያን የማናደርግ ከሆነ ግን፣ እንደ አሮጌው አቁማዳ የመሆን ችግር ሊገጥመን ይችላል፡፡

ጳውሎስም ይህንን እውነት አጠንክሮ ተናግሮአል፤

> ልጅ ሳለሁ እንደ ልጅ እናገር ነበር፤ እንደ ልጅ አስብ ነበር፤ እንደ ልጅም አሰላ ነበር። ከጐለመስሁ በኃላ ግን፣ የልጅነትን ነገር እርግፍ አድርጌ ትቻለሁ። አሁን የምናየው በመስተዋት ውስጥ እንደሚታይ በድንግዝግዝ ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን ፊት ለፊት እናያለን። አሁን የማውቀው በከፊል ነው፤ በዚያን ጊዜ ግን እኔ ራሴ ሙሉ በሙሉ የታወቅሁትን ያህል ዐውቃለሁ። (1 ቆሮንቶስ 13፥11-12)

አንድ ሕፃን ገና አላደገም ይባላል እንጂ፣ ተሳስቶአል አይባልም፡፡ የአምስት ዓመት ልጅ እያለሁ ዓለም ሁሉ እኔ እንደምጫወትበት አሻንጉሊት ይመስለኝ ነበር፡፡ ፊደል ማወቅ ለእኔ እጅግ በጣም ትልቅ ስኬት ነበር፡፡ በጣም ውስብስብና ታላላቅ የሕይወት ገጽታዎችን ለማስተናገድ ብስለት ይጐድለኝ ስለ ነበር በዚያ ጊዜ ሕይወትን የማየው በጨለመ መስተዋት ውስጥ ነበር፡፡

አሥራ ስምንት ዓመት ሲሆነኝ ግን በአሻንጉሊቶች መጫወት ሌጐስ ያለፈ ዘመን ትዝታዎች ሆኑ፡፡ በሕይወት እየበሰልሁ ከመጣው

ብዙ ዓመታት ወዲህ ነገሮችን የማይበት መስተዋት እንደ በፊቱ የጨለመ ወይም የደበዘዘ አይደለም፡፡ የመረዳት ደረጃዬና መጠን እያደገ መጥቷል፡፡ የአሥራ ስምንት ዓመቱ ልጅ እንደ አምስት ዓመቱ ልጅ ልሁን ካለ ጤናማ አይደለም ማለት ነው፡፡ እያደግን ስንሄድ የድሮውን የልጅነት አስተሳሰብና መረዳት እየተውን እንመጣለን፤ አብዛኞቹ የልጅነት ነገሮች አሁን ለደረስንበት ደረጃ የሚጠቅሙም የሚመጥኑም አይሆኑም፤ ተግባራዊም አይደሉም፡፡

## ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

### # 6 ‹‹መደረግ የሌለባቸው ነገሮች›› ዝርዝር

ስለ አሳዛኙ የእስራኤል ልጆች ልምምድ መጽሐፍ ቅዱስ የሚነግረንን መሠረት በማድረግ በደረቁ ምድር በሚኖረን ጊዜያዊ ቆይታ በዚያ ቦታ ማድረግ የሌለብን አንዳንድ ነገሮች አሉ፡፡ እውነት ነው፤ በክርስትና ሕይወታችን ማድረግ ለሌለብን ነገሮችን በተመለከተ ይህ ጥሩ ዝርዝር ሊሆነን ይችላል፤ ይሁን እንጂ፣ በበረሓ ውስጥ በሚገጥመን ውጣ ውረድ እነዚህን ኀጢአቶች የማድረግ ፈተና ይበረታል፡፡ ቀጥሎ ያሉት ከዋና ዋናዎቹ ዝርዝሮች ጥቂቶቹ ናቸው፤

1. ክፉውን ነገር መመኘት፡፡ ሁሉንም ነገር በምናጣበት ጊዜ አንዳንዴ አንዳንድ ትክክል ያልሆኑ ነገሮችን ብናደርግ ጥሩ ስሜት እንደሚኖረን እንዲያውም ደስተኛ ልንሆን እንደምንችል እናስባለን፡፡
2. ጣዖቶችን መከተል፡፡ እንዲህ ሲባል ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የሚጋጭ መሆኑን እያወቅን የራሳችንን ፍላጐት ለማሳካት የምናደርገው ጥረት ማለት ነው፡፡ ከኢየሱስ የበለጠ ወይም ከእርሱ አስቀድመን ፍቅራችንን ለሰዎች

ወይም ለነገሮች መስጠት ማለት ነው፡፡
3. ለዝሙት ኀጢአትና ርኩሰት መሸነፍ፡፡
4. ጌታን መፈታተን፡፡
5. ማጕረምረም፤ ማጕረምረም፤ ማጕረምረም፡፡

በቆሮንቶስ ለነበሩ አማኞች በጻፈው የመጀመሪያ መልእክቱ ጳውሎስ አባቶቻችን በምድረ በዳ ከፈጸሙት ስሕተት ብዙ መማር እንደምንችል ይናገራል፡፡

ወንድሞች ሆይ፣ አባቶቻችን ሁሉ በምድረ በዳ እንደ ነበሩ… ታውቁ ዘንድ እፈልጋለሁ፡፡ እግዚአብሔር በብዙዎቹ ደስ ስላልተሰኘ በበረሓ ወድቀው ቀሩ፡፡ እነርሱ ክፉ እንደ ተመኙ እኛም ደግሞ እንዳንመኝ እነዚህ ነገሮች ምሳሌ ሆነውናል፡፡ (1 ቆሮንቶስ 10፥1፤5-6)

እስራኤላውያንን ትልቅ ዋጋ አስከፍሎአቸዋል፤ እኛ ከእነርሱ ምሳሌ መማር አለብን፡፡

ወዳጄ፣ ምድረ በዳ ውስጥ የእግዚአብሔርን መንገድ፣ እንዲያውም ጥልቅ ፈቃዱን መረዳት ትችላለህ፤ ይሁን እንጂ፣ ዐቋምህ አንድ መሆን አለበት፤ ምን ጊዜም ቢሆን በልብህ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ አሁን ባለሁበት ሁኔታ መልካምነትና ፍቅርህ ባይሰማኝ እንኳ፣ አንተ መልካም መሆንህንና እኔንም እንደምትወደኝ አምናለሁ›› በል፡፡

በተመሳሳይ መንገድ በእግዚአብሔር ነገሮች እያደግን፣ በሕይወት ደረጃዎች ወደ ላይ እየወጣን ስንሄድ፣ ብስለት የሌላቸው የድሮ ነገሮችን መተው አለብን፡፡ አሁን የእግዚአብሔርን መንገድና ክብር በድንግዝግዝ እያየን መሆኑን ጳውሎስ ይናገራል፤ ሆኖም፣ ወደ ሰማያዊው ሽልማት እየገሠገሥን ስንሄድ፣ እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እስክናይ ድረስ የበለጠ አጥርተን እናያለን፡፡ በሌላ አነጋገር እርሱ እኛን እንደሚያውቀን እኛም እርሱን እናውቀዋለን!

ጳውሎስ የጠቀሰው ሰማያዊ ሽልማት ምንድነው? ይህን

ቀደም ባለው ጥቅስ መልስ ሰጥቶበት ነበር፡፡ ፊልጵስዩስ 3፥10፣ ‹‹ክርስቶስንና የትንሣኤውን ኀይል እንዳውቅ፣ የሥቃዩ ተካፋይ እንድሆንና በሞቱም እርሱን እንድመስል እመኛለሁ›› ይላል፡፡ የእግዚአብሔር ሰማያዊ ሽልማት የልጁን የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ መምሰል – እርሱ እንደሚያውቀን እኛም እርሱን ማወቅ ነው! እዚያ ግብ ላይ እስክንደርስ መርካት የለብንም፤ ስለዚህም የእግዚአብሔርን ልብ መፈለግን ማቋረጥ የለብንም፡፡

ሰማያዊውን ሽልማት ለማግኘት ማድረግ ያለብን ሦስተኛው ነገር፣ ‹‹ወደ ግቡ መፍጠን›› ነው፡፡ መፍጠን የሚለው ቃል ተቃውሞ ወይም ተፅዕኖ መኖሩን ያመለክታል፡፡ ጌታን ለማወቅ ስንነሣ ምንጊዜም ተቃውሞ ይኖራል፡፡

ለዲያብሎስ ትልቁ ስጋት የኢየሱስ ክርስቶን መልክ እየመሰለ በመሄድ ላይ ያለ ሰው ነው፤ የጨለማ ኀይሎች ያንን ሰው ከምንም ነገር ይልቅ ጠንክረው ይዋጉታል፡፡ አማኞች የክርስቶስን መልክ እየመሰሉ ሲሄዱ፣ ከእንግዲህ በውስጣቸው ለሚኖረው ለእርሱ እንጂ፣ ለራሳቸው አይኖሩም፡፡ ያኔ በክርስቶስ ያላቸው ሕይወት ይበልጥ ጉልበት እያገኘና እየፈካ በሙላት ይገለጣል፡፡ እርሱን ለማወቅ ከመከራው ጋር ኅብረት ማድረግን ማወቅ አለብን በማለት ጳውሎስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ በሥጋችን የምንቀበለው ይህ መከራ ለራስ መሞት ማለት ነው፤ ይህ ደግሞ የትንሣኤውን ሕይወት ያስገኛል! ጴጥሮስ እንዲህ በማለት ይጽፋል፤

> እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ፣ እናንተም በዚሁ ዐላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኀጢአትን ትቶአል። ከዚህም የተነሣ ከእንግዲህ በሚቀረው ምድራዊ ሕይወት እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንጂ እንደ ሥጋዊ ምኞት አይኖርም። (1 ጴጥሮስ 4፥1-2)

በሥጋችን መከራ ተቀብለን ከሆነ፣ ትኩረታችን የራሳችን መንገድ ላይ አይሆንም፤ ከእንግዲህ ለዚያ አንገዛም፤ የዓለምን

ኀጢአት አንከተልም፡፡ ይልቁን፣ የክርስቶስ ማንነት በውስጣችን ይሠራል! እንግዲህ የሕይወታችን ግብ አድርገን መነሣት ያለብን ይህን ነው፡፡

## ከክርስቶስ ጋር መከራ መቀበል

ለመሆኑ የክርስቶስ መከራ ሲባል ምን ማለት ነው? አንዳንድ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች ይህን መጽሐፍ ቅዱሳዊ አባባል ስላጣመሙት ብዙዎች ይህን በተሳሳተ መንገድ ተረድተውታል፡፡ እዚህ ላይ መከራ የሚለው በበሽታ መሠቃየትን ወይም ለዕዳ የሚከፈል ገንዘብ በማጣት መጨነቅ አይደለም፡፡ በከፈልነው መሥዋዕት ልክ እግዚአብሔርን ለማራራት ለሳምንቶች ምግብ ሳይበሉ መኖር ማለት አይደለም፡፡ እዚህ ላይ መከራ የሚለው መሥዋዕትን ሳይሆን መታዘዝን ነው፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ የክርስቶስ መከራ ምን እንደ ሆነ ግልጽ አድርጎታል፤

> **ኢየሱስ በዚህ ምድር በኖረበት ዘመን ከሞት ሊያድነው ወደሚችለው ጸሎትንና ልመናን፣ ከታላቅ ጩኸትና ከእንባ ጋር አቀረበ፤ … የእግዚአብሔር ልጅ ቢሆንም እንኳ ከተቀበለው መከራ መታዘዝን ተማረ። (ዕብራውያን 5፥7-8)**

ኢየሱስ መታዘዝን እዚሁ ተማረ እንጂ፣ ከሰማይ ወደ ምድር ይዞት አልመጣም፡፡ ላለመታዘዝ አማራጭ ቢኖረውም ለአባቱ በመታዘዝ ተማረ፡፡ እርሱ እግዚአብሔርን እንጂ፣ ሰውን ደስ ማሰኘት አልፈለገም፡፡ በእርሱ መታዘዝ የሰው ልጆች ዘላቂ ጥቅም እንደሚያገኙ አውቆአል፡፡ ጴጥሮስ እውነተኛ መከራን ሰውን ደስ ከማሰኘት ተቃራኒ በሆነ መልኩ እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ከመኖር ጋር አመሳስሎታል፡፡ (1 ጴጥሮስ 4፥2)

‹‹የክርስቶስ መከራ›› አእምሮአችን፣ ስሜታችን ወይም አካላዊ ጥቅሞቻችን የማስመሰልን ወይም የደስታ ሕይወት መኖርን እንድንመርጥ ቢፈታተኑንም በእግዚአብሔር መንገድ መሄድ ማለት

ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ ይህ በተግባር የሚታየው እግዚአብሔር በአንድ መንገድ እንድንሄድ ሲነግረን ወዳጆቻችን፣ ቤተ ሰቦቻችን፣ የሥራ ባልደረቦቻችን ወይም ሌሎች ሰዎች በሌላ መንገድ እንድንሄድ ሲፈልጉ በሚገጥመን ግጭት ውስጥ ነው፡፡ እንዳለመታደል ሆኖ ብዙውን ጊዜ እንዲህ ያለው ተቃውሞ የሚገጥመን በጣም ከሚቀርቡን ሰዎች መሆኑ ነው፡፡ ለዚህ ዐይነተኛ ምሳሌ የሚሆነን የኢየሱስን መሞትና መቀበር በተመለከተ ጴጥሮስ ያሰማው ተቃውሞ ነው፡፡

> ኢየሱስ ከዚያ ጊዜ ጀምሮ ወደ ኢየሩሳሌም ይሄድ ዘንድ፣ በዚያም በሽማግሌዎች፣ በካህናት አለቆችና በኦሪት ሕግ መምህራን እጅ መከራን ይቀበልና ይገደል ዘንድ፣ በሦስተኛው ቀን ከሞት ይነሣ ዘንድ እንደሚገባው ለደቀ መዛሙርቱ ይገልጽላቸው ጀመር። ጴጥሮስ ኢየሱስን ወደ ጐን ሳብ አድርጐ፣ <<ጌታ ሆይ፣ እንዲህ ያለ ነገር ፈጽሞ አይድረስብህ>> እያለ ይገሥጸው ጀመር። ኢየሱስም ወደ ጴጥሮስ ዘወር ብሎ፣ <<አንተ ሰይጣን ሂድ ከዚህ! የሰው እንጂ የእግዚአብሔር ነገር በሐሳብህ ስለሌለ መሰናክል ሆነህብኛል!>> አለው። (ማቴዎስ 16፥21-23)

ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ ወደ ኢየሩሳሌም መሄድ እንዳለበት፣ መከራ መቀበልና መገደል እንዳለበት፣ ከዚያም በሦስተኛው ቀን ከሞት እንደሚነሣ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ በግልጽ ተናገረ፡፡ ምናልባት ከሞት እንደሚነሣ ኢየሱስ የተናገረውን ጴጥሮስ አልሰማም፤ በሚገባ ሰምቶ ቢሆን ኖሮ፣ ኢየሱስ እንደሚሞት መናገሩ ይህን ያህል አይረብሸውም ነበር፡፡

ጴጥሮስ ምን እያለ እንደ ነበር መረዳት ችላችኃልን?

> *ቆይ፣ ቆይ፣ አንተ'ኮ መሲሑ ነህ፤ [ይህን ቀደም ሲል ተናግሮ ነበር] መንግሥት መመሥረትና እስራኤልን ነጻ ማውጣት አለብህ፡፡ እንደምታውቀው አንተን ለመከተል ስል ሥራዬን፣ ሚስቴንና ቤተ ሰቤን ትቼ መጥቻለሁ፡፡*

*አንተን ለመከተል ወዳጆቼን አጥቻለሁ፡፡ ለዚህ ጉዳይ ጊዜዬን ሁሉ ሰጥቻለሁ፤ ከዚህ ጋር በተያያዘ መታወቅ አትርፌአለሁ፡፡ አንተ ከሞትህ የምኩራብ መሪዎች ትክክል እንዳልነበርህ ያስባሉ፡፡ ጋዜጦችና መጽሔቶች አንተ ምን ያህል አወዛጋቢ ሰው እንደ ሆንህ በስፋት ይጽፋሉ፡፡ አንተን ለሚተቹ ማኅበራዊ ሚዲያዎች መነጋገሪያ ትሆናለህ፤ ብዙ ታዋቂ የነገረ መለኮት ምሑራንና መሪዎችም አንተ ቀድሞውኑ ሐሰተኛ እንደ ነበርህ ሲናገሩ ነበር፡፡ አሁን ደግሞ እንደምትገደል አንተ ራስህ እየነገርኸን ነው፡፡ እንደዚያ ከሆነ የእኔስ መጨረሻ ምን ሊሆን ነው? አንተን በመከተል ይህን ሁሉ ጊዜ አጥፍቻለሁ፤ አንተ ከሞትህ ባዶ መቅረቴ'ኮ ነው፤ በዚያ ላይ ስሜ ይጠፋል፡፡*

ይህን ሁሉ ከዘረዘረ በኋላ ጴጥሮስ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ በፍጹም መሞት የለብህም!›› በማለት ደመደመ፡፡

የጴጥሮስ አስተሳሰብ ራስ ወዳድና የዚህ ዓለም አመለካከት እንደ ነበረ ኢየሱስ ያመለከተው ወዲያውኑ ነበር፡፡ ነገሮችን ከእግዚአብሔር አንጻር እያየ አልነበረም፡፡ ነገሮችን ከራሱ ጥቅም አንጻር ማየትን ዓለም የተማረው ‹‹የዚህ ዓለም አምላክ›› ከተባለው ከሰይጣን ነበር፡፡ (2 ቆሮንቶስ 4፥4)፡፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ግን የዚያ ተቃራኒ ነው፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ምንም እንኳ ዓላማዊ አመለካከት ካላቸው፣ ‹‹ወንድሞችና እኅቶች›› ጋር የማይስማማ ቢሆን እንኳ፣ ከባሕላዊው አስተሳሰብ በታቃራኒ መሄድ ይኖርብናል፡፡ በመሠረቱ ጴጥሮስ ክፉ ሰው አልነበረም፤ ይሁን እንጂ፣ የአስተሳሰቡ አዝማሚያ የክርስቶስ ሳይሆን የዓለምን አስተሳሰብ የተከተለ ነበር፡፡ ነገሮች እንዴት መከናወን ወይም ወዴት አቅጣጫ መሄድ እንዳለባቸው አስቀድሞ ከነበረው አስተሳሰብ ለውጥ ማድረግን እየተቃወመ ነበር፡፡

ለዚህ ሌላ ምሳሌ የሚሆኑን የከነዓንን ምድር ለመሰለል ተልከው የነበሩት እስራኤላውያን ናቸው፡፡ እንዲወርሱ የሚፈልገውን

የተስፋ ምድር በተመለከተ መረጃ የሚሰበስቡ ሰዎችን እንዲልክ እግዚአብሔር ለሙሴ በነገረው ጊዜ ከአንድ ዓመት ለበለጠ ጊዜ በምድረ በዳ እየኖሩ ነበር፡፡ ሙሴ ከእያንዳንዱ ነገድ አሥራ ሁለት ሰዎች መረጠ፡፡ ከእነዚያ ሁለቱ ኢያሱና ካሌብ ነበሩ፡፡

ሰላዮቹ ምድሪቱን ሰልለው ሲመለሱ ያዩትንና መወሰድ የነበረበትን እርምጃ በተመለከተ ያቀረቡት ሪፖርት እርስ በርሱ የሚጋጭ ነበር፡፡ ከእነርሱ አሥሩ እንዲህ አሉ፤

> <<በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ግን ኀያላን ሲሆኑ፣ ከተሞቹም የተመሸጉና ትላልቅ ናቸው፤ እንዲያውም የዔናቅን ዝርያዎች በዚያ አይተናል። አማሌቃውያን የሚኖሩት በኔጌብ፣ ኬጢያውያን፣ ኢያቡሳውያንና አሞራውያን በኮረብታማው አገር፣ ከነዓናውያን የሚኖሩት ደግሞ በባሕሩ አቅራቢያና በዮርዳኖስ ዳርቻ ነው። ... ከእኛ ይልቅ ብርቱዎች ስለሆኑ ልናሸንፋቸው አንችልም!>> አሉ፡ ፡ እነዚህም ስለ ሰለሏት ምድር በእስራኤላውያን መካከል እንዲህ የሚል መጥፎ ወሬ አሰራጩ፤ <<ያየናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ናት፤ እዚያ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ግዙፎች ናቸው።>> (ዘኁልቁ 13፥28-29፤ 31-32)

ካሌብና ኢያሱ ግን የተለየ ሪፖርት ነበር ያቀረቡት፤

> ከዚያም ካሌብ ሕዝቡን በሙሴ ፊት ጸጥ አሰኝቶ፣ <<እንውጣ! ምድራቸውንም እንውረስ፤ ማሸነፍም እንችላለን።>> አላቸው። ... እግዚአብሔር በእኛ ደስ ከተሰኘብን ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደዚያች ምድር መርቶ ያገባናል፤ ለእኛም ይሰጠናል። ብቻ በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ፤ እንደ እንጀራ እንጐርሳቸዋለንና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሩአቸው። ጥላቸው ተገፎአል፤ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነውና አትፍሩአቸው።!>> (ዘኁልቁ 13፥30፤ 14፥8-9)

ምድሪቱን ለመሰለል አሥራ ሁለቱም የሄዱት አብረው ነበር፡፡ ተመሳሳይ ምድር፣ ከተሞችና ሕዝብ ነበር ያዩት፡፡ ታዲያ፣ አሥሩ ሰዎች ሌላ ሪፖርት፣ ሁለቱ ደግሞ የዚያ ተቃራኒ ሪፖርት ይዘው

የተመለሱት ለምንድነው? የዕይታ ጉዳይ ነው!

እርሱን የተከተሉት በፍጹም ልባቸው ስለ ነበር፣ ኢያሱና ካሌብ የተለየ መንፈስ እንደ ነበራቸው እግዚአብሔር ተናግሮአል፡፡ (ዘኁልቁ 14÷24)፡፡ በሌላ አነጋገር በሰው ፍላጐት ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ፈቃድ ተንቀሳቅሰዋል፡፡ ለራሳቸው ሕይወት ከመሳሳት አንጻር ሳይሆን፣ ነገሮችን ያዩት በእግዚአብሔር ዐይን ነበር፡፡ አሥሩ ሰላዮች ሁሉም በአንድነት ከኢያሱና ከካሌብ የተለየ ነገር ያዩት ለምን እንደ ሆነ በመረዳት ረገድ ይህ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡ አሥሩን ሰዎች ይበልጥ ያሳሰባቸው የእግዚአብሔር ፍላጐት ሳይሆን፣ የራሳቸው ምቾት፣ ዋስትናና የቤተ ሰባቸው ጉዳይ ነበር፡፡ ሕይወታቸው የሚመራው ለእነርሱ ጥቅም በሚያስገኝ ነገር እንጂ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማስቀደም አልነበረም፡፡ እግዚአብሔር እንደማይተዋቸውና በሚገጥማቸው ማንኛውም ነገር መሳካትን እንደሚሰጣቸው አልተረዱም፡፡ የተቀሩትም ሰዎች ይህን የተሳሳተ አስተሳሰብ ነበር የያዙት፤ ምክንያቱም እነርሱም እንዲህ ነበር ያሉት፤

> እስራኤላውያን በሙሉ በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ፤ ማኅበሩም ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ <<ምነው በግብፅ ወይም በዚህ ምድረ በዳ ሞተን ባረፍነው ኖሮ! እግዚአብሔር ወደዚች ምድር የሚያመጣን ለምንድነው? በሰይፍ እንድንወድቅ ነውን? ሚስቶቻችንና ልጆቻችንም ይማረካሉ፤ ታዲያ ወደ ግብፅ መመለሱ አይሻለንምን?>> (ዘኁልቁ 14፥2-3)

የእስራኤል ልጆች ወደ ኋላ ተመልሰው እንደ ልባቸው የሚበሉበትን፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የተረጋጋ ኑሮ የሚኖሩበትን በድሮ ዘመን በግብፅ ያሳለፉትን፣ ‹‹ደግ ጊዜ›› እያሰቡ ነበር፡፡ ምንም እንኳ፣ በግብፅ ባርያዎች የነበሩ ቢሆንም አሁን የገጠማቸው ሁኔታ ከባርነት እንኳ የከፋ ሆኖባቸው ነበር፡፡ ሁሉም በአንድነት የሚያስፈልገውን ለውጥ እየተቃወሙ ነበር፡፡ ምንም እንኳ፣ የዘላንነት አኗኗራቸውና የአመጋገብ ምርጫቸው ይህን ያህል ደስ የሚል ባይሆንም ከምድረ

በዳ ሕይወት ጋር በመላመዳቸው ደኅንነት ተሰምቷቸዋል፡፡ ከዚህም የተነሣ የተስፋውን ምድር በዐይናቸው ማየት አልቻሉም እግዚአብሔር ለሕይወታቸው የነበረውንም ፈቃድ አልፈጸሙም፡፡

ኢያሱና ካሌብ ግን ያለ ምንም ማመንታት ወደ ፊት ገሥግሠዋል፤ የገጠማቸው ፈተና እነርሱን ፀጥ ለማሰኘት ከሚፈልጉት፣ ‹‹ወንድሞቻቸው›› የመጣ ነበር፤ ‹‹መላው ማኅበር ግን በድንጋይ ሊወግሯቸው ተነጋገሩ›› (ዘኍልቍ 14፥10)፡፡ ኢያሱና ካሌብን የተቃወሙ ሰዎች አእምሮአቸው አልታደሰም፤ ስለዚህም ነገሮችን የሚያዩት ዓለም በሚያይበት መንገድ ነበር፡፡ በመንገዳቸው ተሰናከሉ፤ በምድረ በዳ አስተሳሰብ ተጠመዱ፡፡

ሐዋርያው ጳውሎም ከእርሱ በፊት እንደ ነበሩት ኢያሱና ካሌብ ሁሉ ከኋላው ያለውን ነገር እየረሳ ወደ ሰማያዊው ሽልማት እንደሚገሠግሥ ተናግሮአል (ፊልጵስዩስ 3፥14)፡፡

እንደ ገና ኢሳይያስ 43፥18-19ን ብንመለከት፣ በዚህ ዘመን ብርታት የሚሰጠንን መመሪያ እናገኝበታለን፤

> <<የቀደመውን ነገር አታስቡ፤ ያለፈውን እርሱ፡፡
> እነሆ አዲስ ነገር አደርጋለሁ፤ እርሱም አሁን ይበቅላል፤ አታስተውሉትምን? በምድረ በዳ መንገድ አዘጋጃለሁ፤ በበረሓም ምንጭ አፈልቃለሁ፡፡>>

በጣም የሚያሳዝነው በዚህ መንገድ እንኳ፣ እግዚአብሔር ለእነርሱ ያለውን ፈቃድ በመፈጸም ወደ ፊት ወደ ነጻነት ከመገሥገሥ ይልቅ፣ አሁን ባሉበት ባርነት፣ ‹‹ምቾት›› ውስጥ መኖር የሚፈልጉ ብዙዎች መሆናቸው ነው፡፡ እነርሱ ከለመዱት ሆኖም አስከፊ ከሆነው ሕይወታቸው ይበልጥ ወደ ፊት የሚመጣውን ለውጥ ይፈሩታል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ ባለፈው ጊዜ እግዚአብሔር ባደረገው በመርካታቸው ወደ ፊት በመራመድ አዳዲስ ተግዳሮቶችን ለመጋፈጥ ፈቃደኞች አይደሉም፡፡ እርግጥ ነው፣ እግዚአብሔር በእነርሱ በኩል ታላላቅ ነገሮች አድርጎአል፤ ይሁን እንጂ፣ ባለፈው ዘመን ስኬቶቻቸው ላይ

ተደላድለው ተኝተዋል፡፡

ለእግዚአብሔር ፈቃድ መታዘዝ፣ ሕይወትና ነጻነት ይሰጣል፤ እውነተኛ ፍጻሜ የሚገኘውም በዚያ መንገድ ብቻ ነው፡፡ አሁን ካላችሁበት ሁኔታ አንጻር ወደ ሰማያዊው ሽልማት መገሥገሥ በፍጹም የማይቻል ይመስል ይሆናል፡፡ በነቢዩ ኢሳይያስ በኩል እግዚአብሔር አዲስ ነገር እንደሚያደርግ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ፣ ያ አዲስ ነገር የሚበቅለው ምድረ በዳ ውስጥ ነው፡፡ በሌላ አነጋገር የእርሱ ፍላጎት የሆነውን ለመፈጸም የእግዚአብሔርን መንፈስ ስንከተል፤ አንዳንድ ጊዜ የማታልፍ የሚመስል ደረቅ ምድር ውስጥ ራሳችንን እናገኛዋለን፡፡ ሆኖም፣ ብዙዎቻችን እንደምናውቀው በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ ይቻላል (ሉቃስ 18፥27)፡፡ አሁን ካላችሁበት ምድረ በዳ ባሻገር የበዛና የተትረፈረፈ ሕይወት፣ ድልና መልካም ፍጻሜ አለ፡፡

እንደ አሥሩ ሰላዮችና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመቀበል ፈቃደኛ እንዳልሆኑት፣ ከምድረ በዳ ባዶነት ሊያላቅቃቸው የሚችለውን ለውጥ እንደ ተቃወሙ ሌሎች ሰዎች አትሁኑ፡፡ ከዚያ ይልቅ፣ እግዚአብሔር ለእናንተ ወዳዘጋጀው ሰማያዊ ሽልማት ወዳለበት ተስፋ ምድር ገሥግሡ!

# 7

# የእግዚአብሔር አውራ መንገድ

ችግርና አዳጋች ሁኔታ አንድ ዐይነት መሣሪያ ብቻ ሳይሆን... ለመንፈሳዊ ሕይወታችን ዕድገት እጅግ ውጤታማ የእግዚአብሔር መሣሪያ ነው፡፡ እንደ መሰናክል የምናያቸው ሁኔታዎችና ነገሮች ብዙውን ጊዜ ወደ ከፍተኛ መንፈሳዊ ዕድገት የምንመነደግባቸው ወቅቶች ናቸው፡፡ አንድ ጊዜ ይህን ከተረዳንና እንደ አንድ የሕይወት መንፈሳዊ ሐቅ ከተቀበልነው፣ ችግርንና አዳጋች ሁኔታን ማስተናገድ ይህን ያህል ከባድ አይሆንብንም፡፡

- ቻርለስ ስታንሊ

የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፤
<<የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ አዘጋጁ!
ለአምላካችን አውራ ጐዳና በበረሓ አዘጋጁ!>>

- ኢሳይያስ 40፥3

ምንም እንኳ የማይታመን ቢመስልም፣ የእግዚአብሔር አውራ መንገድ የሚገኘው በረሓ ወይም ምድረ በዳ ውስጥ ነው! እርሱ መንገዱን የሚያበጀው ማለትም፣ የላቀ ልዕልና ወዳለው የእግዚአብሔር አመለካከትና አስተሳሰብ የሚመራውን መንገድ የሚያበጀው እዚያ ውስጥ ነው፡፡

በጠቅላላው የሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ይህን አውራ መንገድ የተከተሉ ጥቂቶች ናቸው፡፡ አሁን ግን እግዚአብሔር በዚያ መንገድ እንዲጓዙ ብዙዎችን እያዘጋጀ ነው፡፡ ይህን ከኢሳይያስ 35፥6፣8 መመልከት ይቻላል፤

> **ውሃ ከበረሐ ይወጣል፤ ምንጮችም ከምድረ በዳ ይፈልቃሉ፡፡... በዚያ አውራ ጐዳና ይሆናል፤ <<የተቀደሰ መንገድ>> ተብሎ ይጠራል፡፡**

የእግዚአብሔር አውራ መንገድ ሌላ መጠሪያ የለውም፤ የቅድስና መንገድ ተብሎ ነው የሚጠራው፡፡

ቅድስና ለሚለው ቃል ከተሰጡ ገለጻዎች አንዱ፣ ‹‹ንጹሕ መሆን፤ የጠራ መሆን›› የሚለው ነው፡፡ ኢየሱስ፣ ‹‹ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና›› ብሏል (ማቴዎስ 5፥8)፡፡ ኢየሱስ የሚመለሰው ቅድስና ለሌላት ንጹሕ ያልሆነች ቤተ ክርስቲያንን ሳይሆን፣ እንከን ወይም ነውር የሌለባትን ቤተ ክርስቲያን ወደ ራሱ ለመውሰድ ነው፡፡

ከብዙ ዓመታት በፊት በጣም ወጣት እያለሁ አገልግሎት በጀመርሁ ዘመን አንድ ቀን እየጸለይሁ እያለ እግዚአብሔር ልዩ በሆነ ሁኔታ ሕይወቴን ማንጻት እንደሚጀምር ነገረኝ፡፡ ይህን ስሰማ በጣም ነበር የተገረምሁት፣ ለሊዛም፣ ‹‹እግዚአብሔር’ኮ ማንኛውንም የረከሰ ነገር ከሕይወቴ ሊያስወግድ ነው›› አልኳት፡፡ እግዚአብሔር የማይወዳቸው የማይፈለጉ ነገሮች ሁሉ ጨርሶ ሊጠፉ መሆኑንም

ነገርኃት፡፡ (ምናልባትም እኔ ሳልዘረዝር ያለፍዋቸው ላይ ሌሎች ነገሮችን ሳትጨምር አልቀረችም!)፡፡

ከዚያ ለሚቀጥለው ሦስት ወር ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፡፡ እንዲያውም በሕይወቴ ይበልጥ ነገሮች የተበለሻሹ መሰሉ፤ ከምንጊዜውም ይልቅ፣ መንጻትን የምፈልግበት ሁኔታ ውስጥ ሆንሁ፡፡ ከዚያም በጸሎት ወደ እግዚአብሔር ቀርቤ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ መጥፎ ፀባዮቼ እየተሻሉ ከመሄድ ይልቅ የተባባሱት ለምንድነው?›› በማለት ጠየቅሁት፡፡

እርሱም፣ ‹‹ልጄ፣ አነጻሃለሁ ብየህ ነበር፤ ያንን አንተ በራስህ ብርታት ለማምጣት እየሞከርህ ነበር፤ አሁን ግን እኔ በራሴ መንገድ አደርገዋለሁ›› አለኝ፡፡ ወደ መጀመሪያው የምድረ በዳ ልምምዴ እየገባሁ መሆኑንና ያም ለአሥራ ስምንት ወሮች የሚቀጥል መሆኑን ሐሳቡ እንኳ አልነበረኝም፡፡

## የእርሱ መንገድ እንደ እኛ መንገድ አይደለም

አማኝ በሆንሁበት መጀመሪያዎቹ ዓመታት ስለ ቲ.ኤል. ኦዝቦርን አገልግሎት ሰምቼ ነበር፡፡ ዶክተር ኦዝቦርን ከሚስታቸው ዴይሲ ጋር በጣም ሰፊ የወንጌል አገልግሎትና ለአያሌ አሥርት ዓመታት በመላው ዓለም ተአምራዊ የፈውስ አገልግሎት የነበራቸው በጣም ድንቅ አገልጋይና ደራሲ ነበሩ፡፡ በእነዚህ ባልና ሚስት አገልግሎት በአሥር ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች በክርስቶስ ወደሚገኘው መዳን መጥተዋል፡፡

በቤተ ክርስቲያናችን ለመስበክ ወደ ዳላስ በመጡ ጊዜ ዶክተር ኦዝቦርንን ሳገኝ የተሰማኝን መገመት ትችላላችሁ፡፡ ከዚያም ባለፈ በእንግዳ ሰባኪነት ወደ ቤተ ክርስቲያናችን የሚመጡትን ሰዎች የማስተናገዱ ሥራ የእኔ ስለነበር በግል ከእርሳቸው ጋር የመተዋወቅ ዕድል ነበረኝ፡፡ ቲ.ኤል ኦዝቦርን የሚገርሙ ሰው ናቸው፡፡ ከእርሳቸው ጋር በነበርሁ ጊዜ ከኢየሱስ ጋር አብሬ የተቀመጥሁ ያህል ነበር

የተሰማኝ፡፡

ቲ.ኤል ኦዝቦርን ደጋግመው ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ይመጡ ስለ ነበር በጣም መቀራረብ ችለን ነበር፡፡ በወጣትነት ዘመናቸው ለአገልግሎት በሚዘጋጁበት ዘመን ሲያጠኑዋቸው የነበሩትን መጽሐፎች ሁሉ ሰጥተውኝ ነበር፡፡ በሁለት የተለያዩ ጊዜዎች ብዙ ልብሶች ሰጥተውኝም ነበር (መጠናችን በጣም ተመሳሳይ ነበር)፡፡ በዚያ ዘመን እኔና ሊዛ ለልብስ የሚተርፍ በቂ ገንዘብ አልነበረንም፤ ስለዚህም የሰጡኝ ልብሶች በጣም ነበር የጠቀሙኝ፡፡ ከጊዜ በኃላም እርሳቸውና ሚስታቸው ዴይሲ ለእኔና ለሊዛ እንደ አባትና እንደ እናት ሆነውልናል፡፡

ይህ ከሆነ ከዓመታት በኃላ ለኮርፖሬት አሜሪካ በምሠራበት ጊዜ ቲ.ኤል ኦዝቦርን እየሰበኩ እያለ መንፈስ ቅዱስ፣ አንድ ቀን እርሱን ታገለግለዋለህ፤ አንድ ቀን ለእነርሱ ሠራተኛ ትሆናለህ በማለት በለሆሳስ ነገረኝ፡፡ ስለዚህም የቡድናቸው አባል እንደምሆንና ወደ ፊትም የእርሳቸው ዐይነት የወንጌል አገልግሎት እንደምጀምር ይህ ለእኔ እንደ ማረጋገጫ እንደሆነ አሰብሁ፡፡

ያም ሆኖ ግን በወቅቱ ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፤ እኔም ምድረ በዳ ውስጥ እንዳለሁ ነበር፡፡ የቲ.ኤል ኦዝቦርን አገልግሎት ዋናው ጽሕፈት ቤት ያለው በቱልሳ ቢሆንም፣ የሚኖሩት በኦርላንዶ ነበር፡፡ ጊዜ እያለፈ ሲሄድ፣ የራሴን አገልግሎት መጀመር እንዳለብኝ በውስጤ በጣም ይሰማኝ ነበር፤ ስለዚህ የበለጠ ከኦዝቦርን ጋር መቀራረብ እንድችል ወደ ኦርላንዶ ለመሄድ ወሰንሁ፡፡ ይህን ያሰብሁት በሁለት ምክንያት ነበር፡፡ የመጀመሪያው፣ ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ጋር እያገለገልሁ እንዳልነበር እርሳቸው እንዲረዱልኝ ነበር፡፡ እርሳቸው በጣም ታማኝና ጨዋ ሰው ስለ ነበሩ፣ ለነበርሁበት ቤተ ክርስቲያን እየሠራሁ ከሆነ የእርሳቸው አገልግሎት ተቋም ሠራተኛ እንድሆን እንደማቀጥሩኝ አውቃለሁ፡፡ ሁለተኛው ምክንያቴ፣ እኔና ሊዛ የምንኖረው በኦርላንዶ ስለ ነበር ከእርሳቸው ጋር አብሮ ለማገልገል ቀላል ይሆንልናል፡፡ ፍሎሪዳ ውስጥ ከሆንን እርሳቸው በፈለጉ ጊዜ

ሊያገኙን ይችላሉ ማለት ነው፡፡

ይህ ከሚገባው በላይ ርቆ መሄድ እንደ ሆነ አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያን ማድረጌ ወደ እውነተኛ ጥሪዬ እንዲያደርሰኝ እግዚአብሔርን የረዳሁት መስሎኝ ነበር፡፡

ስለዚህም ወደ ፍሎሪዳ ለመሄድ አገልግሎቴን መተው እንደምፈልግ ለእርሱ ለመንገር ዳላስ ከነበረው ፓስተሬ ጋር ቀጠሮ ያዝሁ፡፡ ከቀጠሮዬ በፊት በነበረው ምሽት በተለያዩ ከተሞች ከነበሩ ሦስት ፓስተሮች ስልክ ተደወለልኝ፣ በሚቀጥለው ቀን ቀጠሮ እንዳለኝ አውቀው ስለ ነበር ሦስቱም፣ ‹‹ለመሆኑ፣ ሊዛ ከዕቅድህ ጋር ሙሉ በሙሉ ተስማምታለች ወይ?›› በማለት ጠየቁኝ፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ ሊዛ በሐሳቤ አልተስማማችም ነበር፡፡ እንዲያውም፣ ‹‹ጆን፣ አንተ ለምትሰጠው መመሪያ መገዛት እንዳለብኝ አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ይህ ዕቅድህ ትክክል አይመስለኝም›› በማለት ደጋግማ ነግራኝ ነበር፡፡ እኔ ግን አልተቀበልኋትም፤ የቤተ ሰቡ ራስ እኔ እንደ መሆኔ መጠን እኔ ለምሰጠው መመሪያ መታዘዝ አለባት፤ ሊዛ የእኔን ሐሳብ ገና መረዳት አልቻለችም ማለት ነው የቤተ ሰቡ ራስ እኔ ስለሆንሁ መመሪያዬን ሙሉ በሙሉ መቀበል አለባት በማለት አሰብሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ የተሳሳትሁት እኔ እንጂ እርሷ አልነበረችም፤ ብስለትና ማስተዋል የጐደለኝ እኔ እንጂ እርሷ አልነበረችም፡፡

በዚያው ሌሊት አካባቢ ሦስተኛው ፓስተር ደውሎ ሌሎቹ ሁለት ፓስተሮች ጠይቀውኝ የነበረውን ጥያቄ ሲያቀርብልኝ ውስጤ አንድ ነገር ተሰበረ፡፡ ዐይኖቼ ተከፈቱ፤ ነገሮችን ለእርሱ ከመተው ይልቅ፣ ዕቅዱን በሕይወቴ እንዲፈጽም እግዚአብሔርን ለመርዳት እየሞከርሁ መሆኑን አስተዋልሁ፡፡

በሚቀጥለው ቀን ሊዛና እኔ ከፓስተሩና ከሚስቱ ጋር ተገናኘን፡፡ እንድንገናኝ ስለ ፈለግሁበት ምክንያትና ባለፈው ሌሊት ባገኘሁት ሦስት ጥሪዎች የተነሣ ግን ሐሳቤን እንደ ለወጥሁ ነገርሁት፡፡ ሰዎቹ በጣም ቀናዎች ስለ ነበሩ፣ አሁንም ቢሆን ከእነርሱ

ጋር እንድንሠራ እንደሚፈልጉ ነገሩን፡፡ የነበረኝ ቦታና ኀላፊነት እንደ ተጠበቀ ነበር፡፡

ትልቅ ሸክም ከትከሻዬ የተነሣ ያህል ተሰማኝ፤ እኛን በተመለከተ እግዚአብሔር የሚሠራውን ዝም ብዬ ለማየት አሁን ዝግጁ ሆንሁ፡፡ እኔን የማንጻቱ ሂደት ገና አለመጠናቀቁን ያኔ አልተረዳሁም ነበር፡፡ ገና ሌላ ወጀብ በሕይወቴ ማለፍ ነበረበት፤ ያ የሚጀምረው በዚያው ቀን ነበር፡፡

ከፓስተሩና ከሚስቱ ጋር ከተነጋገርን ልክ ስድስት ሰዓት በኋላ የስፖርት ልብሴን ለብሼ ከሌሎቹ የቤተ ክርስቲያናችን ሠራተኞች ጋር ቤዝቦል ለመጫወት የስፖርት ልብስ ለመቀየር ቤት ውስጥ ነበርሁ፡፡ ስልክ ተደወለ፤ የደወሉት ቲ.ኤል.ኦዝቦርን ነበሩ! ነገሩን ለማሳጠር በጣም ነበር የደነገጥሁት፡፡

ለዘጠና ደቂቃ ያህል በነበረን ንግግር እኔና ሊዛ በአገልግሎት ድርጅታቸው ውስጥ እንድንሠራ እንደሚፈልጉ ነገሩን፡፡ እንግዲህ እኔና ሊዛ የእርሳቸው ረዳት ሆነን ከእርሳቸው ጋር በመላው ዓለም ልንዞር ነው፡፡ ከዚያም ሌላ የኋላ ኋላ ለሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ምሳሌ የሚሆን ቤተ ክርስቲያን በቱልሳ ከተማ ልንመሠርት ነው፡፡ እርሳቸው ትልልቅ ስብሰባዎች በሚያደርጉባቸው በዓለም ዙሪያ ባሉ አገሮች ተመሳሳይ ዐይነት አብያተ ክርስቲያናት መመሥረት ግባችን ይሆናል፡፡

በዚያ ረጅም የስልክ ጥሪ ውስጥ እየደጋገምሁ፤ አባት ሆይ፣ በዚህ ውስጥ የአንተ እጅ መኖሩን እርግጠኛ ነኝ፤ ነገሮችን በዚህ ፍጥነት በማድረግህ በጣም እደነቃለሁ! በማለት  አስብ ነበር፡፡ ከቲ.ኤል ኦዝቦርን ጋር በነበረኝ የስልክ ንግግር የተሰማኝን የደስታ ድንጋጤና መገረም ለመግለጥ ቃላት ያጥሩኛል፤ ያ ጊዜ ከነበርሁበት ምድረ በዳ መውጫ በር እንደሚሆነኝም አስቤ ነበር፡፡ በጣም ደስ ከመሰኘቴ የተነሣ የነበርንበትን አፓርታማ ጣራ ራሴ እስኪነካ ድረስ ወደ ላይ መዝለል ቃጣኝ፡፡ ስልኩ ከተዘጋ በኋላ ግቢው ውስጥ እግዚአብሔርን ለማመስገን ወደ ውጭ መውጣት ፈለግሁ፤ ሆኖም መንፈሴ ውስጥ

ነጻነትም ሆነ መፈታት አልነበረም፡፡ በጥልቅ እኔነቴ ውስጥ ምቾትና ነጻነት አይሰማኝም ነበር፡፡

እኔም፣ የለም የለም፤ ጌታ ሆይ፣ እንዲህማ ሊሆን አይችልም፤ ከቲ.ኤል ኦዝቦርን ጋር እንደምሠራ ከረጅም ጊዜ በፊት ቃል ገብተህልኝ ነበር፤ ስለዚህ አሁን አይሆንም የምትለኝ አይመስለኝም! በማለት አሰብሁ፡፡

ጉዳዩን በተመለከተ ነጻነትና መፈታት እስኪሰማኝ ድረስ ሦስት ቀን ለረጅም ሰዓት አጥብቄ ጸለይሁ፤ ሆኖም፣ መንፈሴ ውስጥ ምንም መፈታት አልነበረም፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ይህን በተመለከተ ደስታ ስጠኝ!›› በማለት ጮኽሁ፡፡ ምንም እንኳ ሊዛ ራሷም ብትሆን፣ ከኦዝቦርን ጋር እንድንሠራ ከልቧ ብትፈልግም፣ እርሷም ራሷም ብትሆን ጨፍጋጋ ስሜት ነበር የሚሰማት፡፡

በመጨረሻም ይህ በውስጤ ያለው ጨፍጋጋ ስሜትና የመንፈስ ነጻነት ማጣት ከእግዚአብሔር እንዳልሆነ ማመንን መረጥሁ (ይህ በእኔ በኩል ሌላው ብስለት የማጣትና አደገኛ እርምጃ ነበር)፡፡ ስለዚህ ኢንተርቪው ለመደረግ እኔና ሊዛ ወደ ኦክላሆማ ሄድን፤ ነገሮች ሁሉ በመልካም ሁኔታ እየሄዱ ያሉ ይመስል ነበር፡፡ ቲ.ኤል ኦዝቦርንና ባለቤታቸው ዴይሲ የሥራ ምድባችንን በሥርዐት አስረከቡን፤ የልደትን በዓል ምክንያት በማድረግ በነበረው ግብዣ ከሌሎች የአገልግሎቱ ሠራተኞችም ጋር አስተዋወቁን፡፡

ወደ ዳላስ ተመልሰን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የነበረንን ቦታ ለቀቅሁ፤ ሆኖም፣ ያኔም ቢሆን ያ ጨፍጋጋ ስሜትና የመንፈስ ነጻነት ማጣት እንዳለ ነበር፡፡ በጸሎት ብዙ ሰዓት አሳለፍሁ፤ ያም ሆኖ ግን፣ ምቾት አልተሰማኝም፡፡ ረጅም ሰዓት በመጸለይ ያንን ምቾት የሚነሣ ስሜት ለማስወገድ ሞከርሁ፤ ግን ምንም አልተለወጠም፡፡

በመጨረሻም ሊዛን፣ ‹‹ምን እንደ ሆነ አላውቅም፤ ግን አንድ ችግር እንዳለ ይሰማኛል›› አልኋት፤ እርሷም በመስማማት፣ ‹‹እኔም አንድ ችግር እንዳለ ይሰማኛል›› አለችኝ፡፡

ለኦዝቦርን ደውዬ እየተሰማኝ ያለውን ነገርኋቸው፡፡

እርሳቸውም፣ ‹‹ሁላችንም በአንድነት ተገናኝተን እስቲ ስለዚህ ጉዳይ እንነጋገር›› አሉኝ፡፡ ስለዚህም ወደ ቱልሳ በረርን፤ ከኦዝቦርን ጋር ሁለት ሰዓት ሙሉ ከተነጋገርን በኋላ፣ ኦዝቦርን፣ ‹‹ይህን የኀላፊነት ቦታ የሰጠናችሁ፣ በጣም ስለምንወዳችሁና እናንተም እንደምትወዱን ስለምናውቅ ነበር፤ አሁን ግን ምናልባት ይህ ውሳኔ ከእግዚአብሔር እንዳይደለ እያሰብን ነው›› አሉን፡፡

እኔም፣ ‹‹ነገሩ ለእኔም ግልጽ አይደለም፤ ግን እርስዎ ትክክል እንደሆኑ አስባለሁ›› አልሁ፡፡ ከቲ.ኤል ኦዝቦርን ጋር አብሬ ለመሥራት የረጅም ጊዜ ሕልሜ ነበር፤ አሁን ግን እንደዚያ ማለቴ እኔን ራሴን ገረመኝ፡፡

በዚያ ዘመን በጣም ማለዳ ላይ ጠዋት ከቤቴ ወጥቼ ለአንድ ሰዓት ተኩል ወይም ለሁለት ሰዓት የመጸለይ ልማድ ነበረኝ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ለእኔ ጀግናዬ የሆኑት ዶክተር ኦዝቦርን ጋር አብሮ መሥራትን በተመለከተ ይህ ተስፋ መቁረጥ ከገጠመኝ ወዲህ በጠዋት ወደ ውጭ ብወጣም፣ ለሁለት ሳምንት ይህን ያህል አልጸለይሁም ነበር፡፡ ሥራዬ ማልቀስ ብቻ ሆነ፡፡ ሥራዬ ባለፉት ጥቂት ወሮች ውስጥ የሆነውን ነገር ማውጣት ማውረድ ብቻ ሆነ፤ የሆነውን ሳስብ ለማመን ይከብደኝ ነበር፡፡ የተሰማኝ ሐዘንና የልብ ስብራት መግለጥ ከሚቻለው በላይ ነበር፡፡ በሞት ለተለየኝ ዘመዴ የማልቀሰ ያህል ነበር ያለቀስሁት፡፡ ይህ ከሆነ ሁለት ሳምንት በኋላ ከቤት ወጪ ማንም ድምፄን መስማት የማይችልበት ቦታ ነበርሁ፤ የሚቻለኝን ያህል ጮኽ ብዬ፣ ‹‹ለምን?! ለምን ይህ ዕድል እንዲያመልጠኝ አደረግህ፤ ከስድስት ዓመት በፊት'ኮ ከእርሳቸው ጋር እንደምሠራ ነግረኸኝ ነበር፤ ግን አሁን ለምን እንዲህ ሆነ?›› አልሁ፡፡

ጌታ የነገረኝን በፍጹም አልረሳውም፤ ‹‹የምታገለግለው እኔን ወይም ዓላማና ዕቅድህን መሆኑን ለማየት ነው›› ነበር ያለኝ፡፡
እጅግ በጣም ተደነቅሁ፡፡

ከዚያም በመቀጠል፣ ‹‹አብርሃም ይስሐቅን መሠዊያ ላይ እንዲያቀርበው ያደረግሁት ከእኔ ይልቅ የሰጠሁትን በረከት ይወድ

እንደ ሆነ ለማየት ነበር። የሚያገለግለው ሕልሙን መሆኑን፣ ወይም እኔን የሚያገለግለው ሕልሙ እንዳሳካለት መሆኑን፣ ወይም የሰጠሁትን ሕልም ለመፈጸም ታማኝ መሆኔን በመረዳት በእኔ መደገፉና እኔን ማገልገሉን ይረጋገጣል።››

ይህ አባባሉ ላለፉት ጥቂት ሳምንቶች ሳብሰለስል ለነበረው ጥያቄ መልስ ሆነኝ። ካለፉት አሥራ ስምንት ወሮች ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ መንፈሴ በደስታ ተሞላ። ሕይወቴ እንደ ገና ወለል ብሎ እንደ ተከፈተ ተሰማኝ፤ በዚያ ቅጽበት ምን ያህል የተባረክሁ መሆኔን አስተዋልሁ። በጣም ቆንጆ ሚስት፣ በጣም የሚያምር ወንድ ልጅ እንዳለኝ በአዲስ ሁኔታ ታየኝ። ሚስቴንና ልጄን ከበፊቱ የበለጠ መውደድ ጀመርሁ። የምንኖርበት አፓርታማ በጣም ከሚያምረው መዋኛ ቦታ ሰላሣ እርምጃዎች ብቻ የራቀ መሆኑና አካባቢውም አብዛኛውን ጊዜ ፀሐያማ መሆኑ በአዲስ መልኩ ደስ አሰኘኝ። ትኩረቴ ሁሉ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል ብዬ የማስበው አገልግሎቴ ሸክም ላይ ስለ ነበር፣ እነዚህን ሁሉ በረከቶቼን ማየት አልቻልሁም ነበር።

አሁን ላይ ሆኜ ወደ ኃላ ዞር ብዬ ስመለከት ከቲ.ኤል ኦዝቦርን ጋር እንደምሠራ እግዚአብሔር የነገረኝ ዳላስ ወደ ነበረው ቤተ ክርስቲያናችን ይመጡ ስለ ነበር እርሳቸውን ብዙ ጊዜ የማገልገል ዕድል ማግኘቴን ማስተዋል ችያለሁ።

### ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 7 ጓደኞችህን በጥንቃቄ መምረጥ

ምናልባት በጣም ይገርማችሁ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ ብዙውን ጊዜ በጣም የሚጐዱን ነቃፊዎችና ተቃዋሚዎቻችን የቅርባችን የምንላቸው ሰዎች ናቸው! አብዛኛውን ጊዜ አሳጃጅና ጠላት የሚሆንብን ጓደኞችን ያልነው ሰው ነው።

በምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ጠንከር ያለ ስደት ሊገጥመን ይችላል፤ ክርስቶስን እስከ ተከተልን ድረስ ስደት እንደሚኖር መጠበቅ አለብን፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ፣ ‹‹በእርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ›› ይላል (2 ጢሞቴዎስ 3፥12)፡፡ ስደቱ እኛን የማጥራቱ ሂደት አካል ነው፡፡ ግን፣ ስደቱ የሚመጣው በማን በኩል ይሆን? ምናልባት ለእግዚአብሔር የሚሆን ልብ ባይኖራቸውም አማኞች መስለው በእግዚአብሔር ሕዝብ መሐል ሾልከው በገቡ ሰዎች በኩል ሊሆን ይችላል፡፡ ሙሴን ስለ ተቃወሙት ኢያኔስና ኢያንበሬስ የተባሉ ሰዎች ጳውሎስ የተናገረው በዚህ ምክንያት ነበር፡፡ እነዚህ ሰዎች ከጌታ ጉባኤ ውጭ ሳይሆን፣ በጌታ ጉባኤ ውስጥ ያሉ ሰዎች ነበሩ፡፡

ጳውሎስ ስለ ደረሰበት ስደትና መከራ ሲዘረዝር አንዳንዶቹ፣ ‹‹በሐሰተኛ ወንድሞች›› በኩል የመጡ ስደትና መከራዎች እንደ ነበሩ ይናገራል (2 ቆሮንቶስ 11፥26)፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ የሚወዱንና የሚያስቡልን፣ ለሕይወታችን የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚነግሩን ሰዎች መኖራቸው በጣም ይጠቅማል፡፡ በዚያ ጊዜ የማነቅፉንና የኢዮብ ሚስትና ጓደኞቹ እንዳደረጉት በእግዚአብሔር ላይ እንድናምፅ የሚያበረታቱን ሰዎች አያስፈልጉንም፡፡ የሚያስፈልገን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ ተግሣጽ እንጂ፣ በባዶ ቃላት የሚሸነግሉን ሐሰተኛ ነቢያት አይደሉም፡፡ በዚያ ወቅት የሚያስፈልጉን በእውነት የሚወዱንና የእግዚአብሔርን ጥበብ የሚነግሩን ሰዎች ናቸው፡፡

ግን ተጠንቀቁ፤ የሚነቅፉችሁና ላለችሁበት ምድረ በዳ ምክንያቱ እናንተው እንደ ሆናችሁ የሚነግራችሁ ሁሉ

በእውነት ጓደኞችሁ ወይም ወዳጆችሁ ላይሆን ይችላል፡፡ እርግጥ ነው፤ መንፈስ ቅዱስ በኀጢአታችን ይወቅሰናል፤ ስሕተታችንን ሊያሳየንና ወደ ንስሓ ሊመራን ብዙ ጊዜ በአንድ ሰው ሊጠቀም ይችላል፡፡ ምንም ተስፋ የማይሰጥ፣ የማያበራ ነቀፋና ትችት ግን ከጠላት ሊሆን ይችላልና፡፡ ተጠንቀቁ!

አሁን ግን ሥራ የለኝም፡፡ ማንም ሳያየኝ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሄጄ እንደ ገና ወደ ሥራዬ ይመልሱኝ እንደሆነ ጠየቅሁ፡፡ ከረዳት ፓስተሮቹ አንዱ የነበረውን ጓደኛዬን ሳገኘው፣ ‹‹በበሩ ሥር መግባት የምችል እስኪመስለኝ ድረስ በጣም ያነስሁ ያህል ነበር የተሰማኝ›› በማለት በወቅቱ መናገሬን አስታውሳለሁ፤ በትክክል እንደዚያ ነበር ያልሁት፡፡ ከቲ.ኤል ኦዝቦርን አገልግሎት ጋር ለመሥራት ወደዚያ እንደምሄድ ተናግሬ ነበር፡፡ ፓስተራችንም ይህንኑ መድረክ ላይ ተናግሮ ነበር – አሁን ግን የተባለው አልሆነም፡፡

እኔን ለመርዳት ተብሎ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የትርፍ ሰዓት ሥራ ተሰጠኝ፡፡ እዚያ ለስምንት ተጨማሪ ወር አገለገልሁ፡፡ ከዚያም እግዚአብሔር እኔን ሲያዘጋጅ የነበረበት የእርሱ ጥሪ ቀጣዩ ገጽታ እውን ሆነ፡፡ በአሜሪካ ውስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያደገ በመሄድ ላይ ያለ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የወጣቶች ፓስተር እንድሆን ተጠየቅሁ፡፡ ነገሩ የሆነው በተአምር ነበር ማለት እችላለሁ፡፡ ሊዛም ሆነች እኔ ይህ እግዚአብሔር የከፈተው በር እንደሆነ እርግጠኞች ነበርን፡፡ በዚህ ጊዜ አዲስ ሕይወትና አዲስ ራእይ ነበረኝ፤ ለአዲሱ ሥራዬ ልክ እንደ አዲስ ወይን ጠጅ መያዣ ለመሆን ተዘጋጅቼ ነበር፡፡

## የመንጻት/የመጥራት መንገድ

ኢየሱስ ከዚህ ምድር ከሄደ ለአያሌ መቶ ዓመታት ተከታዮቹ በገዛ ጥረታቸው ቅድስና ላይ ለመድረስ የተለያየ ጥረት ሲያደርጉ

ነበር፡፡ እንዲያውም አንዳንድ ቤተ ክርስቲያኖች የተመሠረቱት ንጹሕ ሆኖ ለመገኘት በሚደረገው ከንቱ ሙከራ ላይ ነበር፡፡ ሆኖም፣ ቅድስና የእግዚአብሔር ጸጋ ሥራ እንጂ፣ ውጫዊ ሥጋን የመግራት ውጤት ባለ መሆኑ እኛ ያደረግነው ሁሉ የወግ አጥባቂነት ባሪያዎች አድርጎናል፡፡

እግዚአብሐሔር ጸጋ የሚሰጠው ለትሑታን እንጂ፣ ለትዕቢተኞች አይደለም፡፡ ትዕቢተኛ ሰው በጽሑፍ የሰፈሩ መመሪያዎች፣ ሕጎችንና ደንቦችን በመከተል ያለ እግዚአብሔር ጸጋ እርዳታ ቅድስና ላይ መድረስ እንደሚችል ያስባል፡፡ ትሑት ሰው ግን ይህ ከንቱ ሙከራ መሆኑን ስለሚያውቅ፣ በጌታ ጸጋ (ብርታት) ላይ ይደገፋል፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር የምናደርገው ልባዊ ግንኙነት ንጹሕ ነው፤ አንድ ሰው ልቡ ውስጥ የተጻፈውን ሕግ መፈጸም የሚችልበት ኃይል የሚያገኘው ከእንዲህ ዐይነቱ ግንኙነት ነው፡፡

ብዙዎቻችን ለአዲስ ኪዳን ፊደሎች ወይም መጽሐፍ ቅዱሳዊ ላልሆኑ አስተሳሰቦች በመታዘዝ ቅድስና ላይ ለመድረስ ሞክረን አልተሳካልንም፡፡ የሕጉን ፊደል በመጠበቅ ድነት ለማግኘት ቢሞክሩም እንዳልተሳካላቸው አይሁዳውያን ሁሉ፣ እነዚህን ሕጎች በመጠበቅ እኛም በቅድስና መመላለስ አልቻልንም፡፡ ሕግ አክራሪ በመሆናቸው ብዙዎች አንዳንድ ነገሮችን ከማድረግ ይታቀባሉ፡፡ የእነዚህ ውጫዊ ገደቦች ዓላማ ውስጣዊ ንጽሕና ለማግኘት ሲባል ነው፡፡

ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ውጫዊ ቅድስና አይደለም የሚፈልገው፤ እርሱ የሚፈልገው የልብ መለወጥን ነው፤ ልብ ሲለወጥ ሕይወትም ይለወጣል፡፡ ማቴዎስ 23÷26 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹አስቀድመህ የጽዋውንና የወጭቱን ውስጥ አጽዳ፤ ከዚያም ውጪ የጸዳ ይሆናል›› ብሏል፡፡

ልባችሁ ንጹሕ ከሆነ ኢየሱስን በማያከብር መንገድ መኖር አትፈልጉም፡፡ በኢንተርኔት ያሉትን መጥፎ ነገሮችን ታርቃላችሁ፣ ሌሎችን የሚያሳዝን ልብስ አትለብሱም፡፡ አንድ ወንድ ወይም ሴት ፍቺ ባለ መፈጸማቸው ይኩራሩ ይሆናል፤ ሆኖም በልባቸው መሥሪያ

ቤታቸው ካሉ ሰዎች ወይም አልፎ አልፎ በሚያዩት ዌብሳይት ዝሙት ይፈጽሙ ይሆናል፡፡ ታዲያ፣ ይህ ቅድስና ነው?

ልባችሁ ንጹሕ ከሆነ ኮምፒዩተር ወይም ስማርትፎን የማያንጽ ነገር እንድትፈልጉ ሊያደርጋችሁ አይችልም፡፡ በመሠረቱ ሰዎችን የሚያረክስ ቴክኖሎጂው ራሱ አይደለም፡፡ ሰውን የሚያረክስ ልብ ውስጥ ያለው ሐሳብ ነው፡፡ ልባችሁ ንጹሕ ከሆነ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ብቻ ትፈልጋላችሁ፡፡

ምድረ በዳ የእኛን የልብ ዝንባሌና ዓላማ ለማንጻት እግዚአብሔር ከሚጠቀምባቸው የእሳት ወላፈኖች አንዱ ነው፡፡ እርሱ ቤተ ክርስቲያኑን ለመውሰድ ከመመለሱ በፊት እግዚአብሔር ልባችንን ዝግጁ የማድረግ ሂደት ላይ ነው፡፡ እግዚአብሔር የራሳቸውን ሳይሆን የእርሱን ክብር የሚያሳዩ፣ በእርሱ ባሕርይ የሚመላለሱ ትውልዶች እያስነሣ ነው፡፡

> እንግዲህ ማንም ራሱን ከእነዚህ ከጠቀስኋቸው ነገሮች ቢያነጻ ለክብር አገልግሎት የሚውል የተቀደሰ፣ ለጌታው የሚጠቅም፣ ለመልካም ሥራም ሁሉ የተሰናዳ ዕቃ ይሆናል (2 ጢሞቴዎስ 2፥20-21)።

ሁለት ዐይነት ዕቃዎች መኖራቸውን ልብ በሉ፤ ለክብር የሆነና ለክብር ያልሆነ፡፡ ለክብር ያልሆነ የሚለውን የግሪኩ ቃል አቲሚያ (atimia) ይለዋል ‹‹የተዋረደ፤ የተነቀፈ፤ አሳፋሪ፤ ከንቱ›› ማለት ነው፡፡ ክብር ለሚለው የግሪኩ ቃል ቲሜ (time) ሲሆን ‹‹የከበረ፤ የተወደደ›› ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር፣ ‹‹የከበረውን ከማይረባው ለይተህ ብትናገር አፍ ትሆነኛለህ›› ይላል (ኤርምያስ 15፥19)፡፡ የከበረው ከማይረባው የሚለየው ከፍተኛ የማንጻት ወይም ንጹሕ ካልሆነ ነገር የማላቀቅ ሥራ ሲከናወን ነው፡፡

ሚልክያስ የብሉይ ኪዳን ነቢይ ነበር፣ ስለ አዲስ ኪዳን ዘመን በስፋት ትንቢት ተናግሮአል፡፡ የእርሱ ችግር በአዲስ ኪዳን ዘመን የሚሆኑትን ነገሮች በሚገባ ለመግለጽ ቃላት ያልነበሩት መሆኑ ብቻ ነው፡፡ ስለሆነም በመንፈስ ቅዱስ በኩል ክርስቲያኖች ስለሆኑት

ስለ አዲስ ኪዳን ወገኖች ሲናገር፣ ያየውን ወይም የተነገረውን ለይቶ ለማመልከት፣ ‹‹ካህናት›› እና፣ ‹‹ሌዋውያን›› በተሰኙ ቃሎች ተጠቅሟል፡፡

ወደ ቤተ መቅደሱ ከመምጣቱ በፊት ጌታ ቤተ መቅደሱን (ቤተ ክርስቲያንን) እንደሚያነጻ ይኸው ነቢይ አስቀድሞ አመልክቷል፡፡

> ብርን እንደሚያነጥርና እንደሚያነጻ ሰው ይቀመጣል፤ ሌዋውያንንም አንጽቶ እንደ ወርቅና እንደ ብር ያጠራቸዋል፤ ከዚያም እግዚአብሔር ቁርባንን በጽድቅ የሚያቀርቡ ሰዎች ይኖሩታል (ሚልክያስ 3፥3)።

ሌዋውያን የሚለው ወደ ፊት የሚመጡትን፣ ‹‹የንጉሥ ካህናት›› ያመለክታል፤ እነርሱም የክርስቶስ ተከታዮች የሆኑት ክርስቲያኖች ናቸው፡፡ እነዚህ ካህናት የሚነጹበትና የሚጠሩበትን ሁኔታ ወርቅና ብር ከሚነጹበትና ከሚጠሩበት ሁኔታ ጋር እግዚአብሔር እያነጻጸረ ስለሆነ፣ ስለ ወርቅና ስለ ብር ባሕርያትና የሚነጹት እንዴት እንደ ሆነ መረዳት በጣም ይጠቅማል፡፡ ወርቅም ሆነ ብር የሚነጹበት መንገድ ተመሳሳይ በመሆኑ፣ እዚህ ላይ የምናገረው ወርቅ ስለሚነጻበት ሂደት ብቻ ይሆናል፡፡

ወርቅ የሚያምር ቢጫ መልክ ያለው ሲሆን፣ ደብዘዝ ያለ ነጸብራቅ ያመነጫል፡፡ በስፋት የሚገኘው ከተፈጥሮ ውስጥ ቢሆንም አብዛኛውን ጊዜ የሚገኘው በጣም በጥቂቱ ነው፣ ነጽቶ ወይም ጠርቶ የሚገኘው እጅግ በጣም አልፎ አልፎ ነው፡፡ ወርቅ ሲነጻ ለስላሳ፣ ተጣጣፊና ከዝገት ነጻ ይሆናል፡፡ ወርቅ ከሌሎች ነገሮች ማለትም ከመዳብ፣ ከብረት፣ ከኒኬል ጋር ከተቀላቀለ ይጠነክራል፣ ተጣጣፊነቱ ይቀንሳል፤ ይበልጥ ለዝገት ይጋለጣል፡፡ ይህ ድብልቅ ቅይጥ (alloy) ይባላል፡፡ ሌሎች ነገሮች በተቀየጡበት መጠን በዚያው ልክ ወርቁ ይበልጥ እየጠነከረ ይሄዳል፡፡ በሌላ በኩል የቅይጡ መጠን እየቀነሰ ሲሄድ ወርቁ እየለሰለሰና የበለጠ ተጣጣፊ እየሆነ ይሄዳል፡፡

አሁን ንጽጽሩን ማየት ይቻላል፡- በእግዚአብሔር ፊት ንጹሕ የሆነ ልብ፣ እንደ ንጹሕ ወርቅ ነው፡፡ ንጹሕ ልብ ለስላሳ፣ ስስና

ተጣጣፊ ነው፤ ይህን በተመለከተ መንፈስ ቅዱስ እንዲህ ይላል፤

> <<ስለዚህ መንፈስ ቅዱስ እንደሚል ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ፣ በምድረ በዳ በፈተና ቀን በዐመፅ እንዳደረጋችሁት ልባችሁን እንዳታደነድኑ... ከመካከላችሁ ማንም በኀጢአት ተታሎ ልቡ እንዳይደነድንና፣ <<ዛሬ>> እየተባለ ሳለ በየቀኑ እርስ በርሳችሁ ተጽናኑ፡፡ (ዕብራውያን 3፥7-8፤ 13)

ኀጢአት ንጹሑን ወርቃችንን ወደ ቅይጥነት የሚለውጥ፣ ልባችንንም የሚያጠነክር ድብልቅ ነገር ነው፡፡ ግትርነቱ ወይም ጥንካሬው እየጨመረ ሲሄድ መንፈሳዊ ንቁነታችን ይቀንሳል፤ የጌታን ድምፅ የመስማት ችሎታን ያዳክማል፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ዛሬ ብዙዎች ያሉት እንዲህ ዐይነቱ እዚህ ሁኔታ ውስጥ መሆኑ ነው፤ ሃይማኖታዊ ቁመና ሊኖረን ይችላል፤ ለኢየሱስ የሚቀጣጠል ስስ ልብ ግን የለንም፡፡ ያ በእግዚአብሔር ፍቅር ይቀጣጠል የነበረው ልባችን የራሱን ደስታ፣ ምቾትና ጥቅም ብቻ በሚፈልግ እንደ በረዶ በቀዘቀዘ ራስ ወዳድነት ተተክቶአል፡፡ መንፈሳዊነት ግላዊ ጥቅም ማግኛ ስለሚመስላቸው (1 ጢሞቴዎስ 6÷5) ከተስፋ ቃሉ መካከል ለእነርሱ የሚጠቅመውን ብቻ ይወስዳሉ፤ ወሎ አድሮም ባለ ማወቅ ወይም በመታለል ተስፋ የሰጣቸውን ጌታ ራሱን ያገልላሉ፡፡ ከእውነት መንገድ በመሳታቸውም በዚህ ዓለም ነገር ይደሰታሉ፤ መንግሥተ ሰማይ እንደሚገቡም ተስፋ ያደርጋሉ! እግዚአብሔር የሚፈልገው ይህን አይደለም፤

> በእግዚአብሔር አብ ፊት ንጽሕና ነውር የሌለበት ሃይማኖት ይህ ነው... ከዓለም ርኩሰት ራስን መጠበቅ፡፡ (ያዕቆብ 1፥27)

ኢየሱስ የሚመጣው ጉድፍ ወይም እንከን ለሌለባት ለተቀደሰች ቤተ ክርስቲያን፣ ልባቸው በዓለም ነገር ላልረከሰ አማኞች ነው፡፡ (ኤፌሶን 5÷27)

ሌላው የወርቅ ባሕርይ ሻጋታ ነገር ወይም ዝገትን መቋቋሙ ነው፡፡ ምንም እንኳ ሌሎች የብረት ዘሮች በአካባቢያቸው ባለው ሁኔታ ቢበላሹም፣ ንጹሕ ወርቅ ላይ ግን ምንም ተፅዕኖ አይኖረውም፡፡ ነሐስ፣ (ቢጫ መልክ ያለው የመዳብና የዚንክ ድብልቅ) ወርቅ ይመስላል፤ ግን የወርቅ ባሕርይ የለውም፤ ነሐስ በቀላሉ ይወይባል፡፡ እውነተኛ የወርቅ ባሕርይ ባይኖረውም፣ ወርቅ መስሎ ይታያል፡፡ ቤተ ክርስቲያንም ውስጥ የዚህ ዐይነት ሰዎች ሞልተዋል፤ ወርቅ ይመስላሉ ግን አይደሉም፡፡ በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት የሚገልጠው የሚያነጻና የሚያጠራ እሳት ብቻ ነው፡፡ ከመንጻትና ከመጥራት በኋላ ስላለው ጉዳይ ሚልክያስ ሲናገር፡-

> <<በዚያን ጊዜም እንደ ገና በጻድቁና በኀጢአተኛው መካከል፣ እግዚአብሔርን በሚያገለግለውና በማያገለግለው መካከል ያለውን ልዩነት ታያላችሁ ይላል>> (ሚልክያስ 3፥18)።

ስለ ወርቅ መንጻት ሂደት ወደ ጀመርነው እንመለስ፡፡ ከወርቅ ጋር የሚቀላቀል ባዕድ ነገር እየጨመረ በሄደ መጠን፣ ወርቁ ይበልጥ እየጠነከረ ከመሄዱም ሌላ ለሻጋታና ለዝገትም የበለጠ ተጋላጭ ይሆናል፡፡ በቀላሉ በምንኖርበት ዓለም ተፅዕኖ ሥር ይውላል፡፡

በአሁኑ ዘመን የዓለም አመለካከትና አስተሳሰብ ወደ ቤተ ክርስቲያን ሾልኮ እየገባ ነው፡፡ የዓለም ባሕል ሰርጎ ውስጣችን በመግባቱ እውነተኛ መልካችን ጠፍቷል፡፡ የዓለም እሴት መለኪያ የእኛም ጭምር ሆኗል፡፡ ብዙዎች ንቁዎች አይደሉም፤ መንጻት እንደሚያስፈልጋቸውም አልተረዱም፡፡

አንጥረኛ ወርቅ እንደሚያጠራ ኢየሱስም ቤተ ክርስቲያንን ከዓለም ነገር እንደሚያጠራ ሚልክያስ 3፥3 ያመለክታል፡፡ በማጥራቱ ሂደት ወርቁ ይደቆሳል፤ ከዚያም ፍሉክስ ከሚባል ነገር ጋር ይቀላቀላል፡፡ ከዚያም እነዚህ ሁለት ነገሮች ምድጃ ውስጥ በኃይለኛ እሳት ወላፈን እንዲቀልጡ ይደረጋል፡፡ ቅይጡ ወይም የማይረባው ነገር ፍሉክስ ወደ ተባለው ነገር ይሳባል ወደ ላይም ይነሣል፡፡

ክብደት ያለው ወርቁ ግን ከሥር ይቀራል፡፡ መዳብ፣ ብረትና ዚንክን የመሳሰሉ ከፍሉክሱ ጋር የተዋሐዱ ነገሮች ይወገዳሉ፡፡

አሁን እግዚአብሔር እንዴት እንደሚያነጻ ተመልከቱ፡-

> እጄን በአንቺ ላይ አነሣለሁ፤ ዝገትሽን ፈጽሜ አጠራለሁ፤ ጉድፍሽንም ሁሉ አስወግዳለሁ። ፈራጆችሽን እንደ ጥንቱ አማካሪዎችሽንም እንደ ቀድሞው እመልሳለሁ፤ ከዚያም የጽድቅ መዲና፣ የታመነች ከተማ ተብለሽ ትጠሪያለሽ። (ኢሳይያስ 1፥25-26)

እኛን ለማጥራት እግዚአብሔር የሚጠቀምበት እሳት ምንድነው? መልሱ የሚከተለው ምንባብ ውስጥ ይገኛል፡-

> አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ፣ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኋል። እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደ ተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው። (1 ጴጥሮስ 1፥6-7)

እግዚአብሔር ሰውን የሚያጠራበት እሳት ፈተናና መከራ ሲሆን፣ የምድረ በዳ መገለጫም ይኸው ነው፡፡ የእነዚህ ነገሮች ወላፈን ጉድፍ የሆነውን ነገር እኛ ውስጥ ካለው የእግዚአብሔር ባሕርይ ይለያል፡፡ ይህም እኛን ወደ ቅድስና የመምራት ዐቅም ይኖረዋል (ለምን ‹‹ዐቅም›› እንዳልሁ ጥቂት ቆየት ብዬ እገልጻለሁ፡፡)

ንጹሕ በሆነ ይዞታው ሲሆን ወርቅ የሚያሳየው ሌላው ባሕርይ አንጸባራቂ መሆኑ ነው፡፡ (እንደ መስተዋት ውስጡ የሚያሳይ)፡፡ ‹‹የከተማይቱም አውራ መንገድ እንደ መስተዋት ብርሃን የሚያስተላልፍ ንጹሕ ወርቅ ነበር›› (ራእይ 21፥21)፡፡ በመከራና በፈተና እሳት ከነጻን በኋላ ብርሃን የምናስተላልፍ እንሆናለን፡፡! የሚያስተላልፍ ነገር ውስጡ ያለውን እንጂ ራሱን አያከብርም፡፡ ለራሱ ትኩረት አይስብም ልብ ብለን የምናየውም አይደለም፡፡

እኛ ከነጻንና ከጠራን ዓለም እንደ ገና ኢየሱስን ያያል፡፡ ንጹሕ ከሆንን፣ እውነት የምንናገር ከሆንን፣ ቃላችንን የምንጠብቅ ከሆንን፣ ታማኞችና ምንም ወደ ኋላ የምንለው ነገር የሌለን ሰዎች ከሆንን፣ ሌሎችም ይህንኑ ያስተውላሉ፡፡

ኢሳይያስ ይህን በሚገባ ገልጦታል፤

> እነሆ፣ እንደ ብር ባይሆንም አንጥሬሃለሁ፤ በመከራ እቶን ፈትኜሃለሁ፡፡ ስለ ራሴ፣ ስለ ራሴ ስል አድርጋለሁ፤ ራሴን ለውርደት እንዴት አሳልፌ እሰጣለሁ? ክብሬን ለማንም አልሰጥም፡፡ (ኢሳይያስ 48፥10-11)

እሳቱ ወይም ምድጃው የመከራ እቶን እንጂ፣ ብር (ወይም ወርቅ) እንደሚጠራበት በዐይናችን እንደምናየው እሳት አይደለም፤ ‹‹እንደ ብር ባይሆንም›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ የምናልፍበት መከራ የከበረውን ከማይረባው የሚለይ ከባድ ወላፈን ነው፡፡

እግዚአብሔር ወራዳ ነገርን ከሕይወታችን የሚያስወግደው ያለ እኛ ፈቃድ አይደለም፡፡ 2 ጢሞቴዎስ 2፥21 ላይ ጳውሎስ፣ መጥራት የሚፈልግ ሰው፣ ‹‹ራሱን ያነጻል›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ራሳችሁን የምታጸድቁ፣ ወይም ሰበብ የምትፈጥሩና የማይረባ ነገር ወደ ኋላ እንዲጐትታችሁ የምትፈቅዱ ከሆነ፣ እግዚአብሔር በግድ ከእነዚህ ነገሮች አያላቅቃችሁም፡፡ የማንጻቱ ሂደት ብቻውን ምንም ጥቅም የለውም፤ (ቀደም ሲል፣ ‹‹ዐቅም›› በሚል ቃል የተጠቀምሁት ለዚህ ነበር)፡፡ የቅድስና አውራ ጐዳና ቀጣይና የማያቋርጥ ሂደት ሲሆን፣ ብዙ ጊዜ ሕመም አለው፡፡ ሆኖም፣ ጥቅሙን ስለማውቅ በበኩሌ በደስታ እቀበለዋለሁ፡፡

የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ‹‹…ለመቀደስም ፈልጉ፤ ያለ ቅድስና ጌታን ማየት አይቻልም›› ይላል (ዕብራውያን 12፥14)፡፡ ኢየሱስም፣ ‹‹ልባቸው ንጹሕ የሆነ ብፁዓን ናቸው፤ እግዚአብሔርን ያዩታልና›› ብሏል (ማቴዎስ 5፥8)፡፡ እንደ እግዚአብሔር የሆነ ልብ

የነበረው ዳዊትም፣ ‹‹ስሕተቱን ማን ሊያስተውል ይችላል? ከተሰወረ በደል አንጻኝ›› ይላል (መዝሙር 19÷12)፡፡

ይህ የእኛም ጸሎት ይሁን፡፡ ልባችንን እንዲያነጻ እግዚአብሔርን ከለመንነው ከእኛ ዐይን የተሰወሩትን እነዚህን ጉድፎች ያስወግዳል፡፡ እግዚአብሔር ጥልቅ ልቦናችንንና ዝንባሌያችንን ያውቃል፤ እኛ ግን አናውቅም፡፡ የምድረ በዳ መንፈሳዊ ጊዜንና ወቅትን ለይታችሁ ማወቅንና መቀበልን እንድትማሩ እመክራችኋለሁ፡፡ እንደ እሳት የሚፋጅ መከራ ሲደርስባችሁ አትቁጡ፤ ዓላማው ምን እንደ ሆነ ለመረዳት ሞክሩ እንጂ፣ ሌሎችን አትውቀሱ፡፡ ይልቁን ልባችሁን መርምሩ፤ እግዚአብሔር የከበረውን ከማይረባው እንዲለይ ፍቀዱለት፡፡ እርሱ፣ ‹‹እኔ ቅዱስ እንደ ሆንሁ እናንተም ቅዱሳን ሁኑ›› በማለት አዝዞናል (1 ጴጥሮስ 1÷6)፡፡

የሚያነጻውና የሚያጠራው እሳት ቀድሞውኑ መልካም የነበረውን እንደሚያበረታና ደካማውን ወይም የማይረባውን ግን እንደሚያነጻና እንደሚያስወግድ አትርሱ፡፡ ባማረ ሁኔታ የእርሱን ክብር የሚያንጸባርቅ የክብር ዕቃ እንድትሆኑ የእርሱን የማንጻት ሥራ በደስታ ተቀበሉ፡፡

# 8

# የውሃ ጉድጓድ አዘጋጁ

ማንኛውም ኮኮብ ዋልታ አካባቢ ሰማይ ላይ እንዳሉት ከዋክብት አያበራም። ማንኛውም ውሃ ከምድረ በዳ አሸዋ መካከል እንደሚነሣ ምንጭ አይጣፍጥም። ማንኛውም እምነት መከራ ውስጥ ያለውንና አሸንፎ የወጣውን እምነት ያህል ክቡር አይደለም። የተፈተነ እምነት ተመክሮ ወይም ልምድ ያስገኛል። በአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ ባታልፉ ኖሮ፣ የገዛ ራሳችሁን ድካም አታውቁም ነበር። እናንተን በዚያ ውስጥ ለማሳለፍ የእርሱ ብርታት ባያስፈልጋችሁ ኖሮ፣ የእግዚአብሔርን ብርታት አታውቁም ነበር።

- ቻርለስ ኤች ስፐርጂን

እንደ ሥጋ ፈቃድ የሚኖሩ ልባቸውን በሥጋ ፍላጎት ላይ ያሳርፋሉ፤ እንደ መንፈስ ፈቃድ የሚኖሩ ግን ልባቸውን በመንፈስ ፍላጎት ላይ ያደርጋሉ።

- ሮሜ 8፥5



አንድን ወንድ ወይም ሴት የእግዚአብሔር ሰው የሚያደርጋቸው የተለወጠ ባሕርያቸው እንጂ፣ መቀባታቸው አይደለም፡፡ አንድ ሰው የሚነጻውና ፀባዩ የሚቀረጸው ጫና በሚበረታበት፣ ተስፋ መቁረጥ በሚያጋጥምበትና ተስፋ ያደረግነው ነገር እንደ ጉም የበነነ በሚመስልበት ምድረ በዳ ውስጥ ነው፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ እያለሁ አንድ ጊዜ ቁጣን ለማሸነፍ ከፍ ያለ ጥረት አድርጌ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ ይህን በመጀመሪው ምዕራፍም አካፍዬአችሁ ነበር፡፡ ስለዚህም፣ ‹‹በሰው ሁሉ ላይ የምቆጣው ለምንድነው? ያንን ለመቆጣጠር ወይም ከሕይወቴ ለማስወጣት የሚያስፈልገኝ ምንድነው?›› በማለት እግዚአብሔርን ጠየቅሁ፡፡

እርሱም፣ ‹‹ልጄ፣ ሥጋ ይሰቀላል እንጂ እርሱን መግታት ወይም ማስወጣት አትችልም›› አለኝ፡፡

በዚህ ጊዜ ግራ በመጋባት፣ ‹‹ታዲያ፣ ይህ ቁጣ የሚመጣው ከየት ነው? እንዲህ ያለ ነገር ሌላው ቀርቶ፣ ከመዳኔ በፊት እንኳ አልነበረብኝም!›› በማለት ጠየቅሁ፡፡

‹‹ለዓመታት ውስጥህ ነበር›› በማለት ጌታ መለሰ፣ ‹‹ሆኖም፣ ምድጃ ውስጥ ከመንጠሩ በፊት ጣትህ ላይ ያለው ወርቅ ቀለበት ጉድፍ የማይታይ እንደ ነበር ሁሉ፣ ይህም ፀባይ ይፋ አልወጣም ነበር፤ የእሳት ወላፈን ውስጥ ሲሆን ግን ጉድፉ ይገለጣል፡፡ አንተን ወደዚህ የመከራ እቶን በማምጣት፣ ውስጥህ የነበረው ቁጣ አሁን ግልጽ እንዲሆንልህ አድርጌአለሁ፡፡››

እግዚአብሔር እየነገረኝ የነበረውን በተመለከተ፣ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ይህን ያህል እርግጠኛ አልነበርሁም፡፡ ስለዚህም እርሱ በመቀጠል፣ ‹‹ሚስትህን መውቀስ ትችላለህ፤ የሥራ ባልደረቦችህን መውቀስ ትችላለህ፤ ጓደኞችህን መውቀስ ትችላለህ፤ አካባቢህን መውቀስ ትችላለህ፡፡ እንዲህ ካደረግህ ቁጣው ሁሌም አብሮህ

ይኖራል፤ ወላፈኑ በረድ ሲል ተመልሶ ወደ ውስጥህ ይመጣል፤ ሂደቱ እንዲህ እያለ ይቀጥላል፡፡ ወይም ደግሞ፣ ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ በጣም አዝናለሁ፤ ይህን ቁጣ ውሰድልኝ›› በማለት በጸሎት ከተናዘዝህ በትልቁ ጭልፋዬ ያንን ከውስጥህ አወጣዋለሁ አለኝ፡፡

እኔም ያደረግሁት ያንኑ ነበር፡፡ የበረሓው እቶን ወላፈን ውስጤ ተሰውሮ የነበረ ቁጣዬን ግልጽ ሲያደርገው፣ ኀጢአቴን ተናዘዝሁ፤ እግዚአብሔር ያንን ከእኔ እንዲወስደውም ለመንሁት፡፡

የቱንም ያህል ከባድ ቢሆንም፣ ምድረ በዳ በጣም ጠቃሚ፣ እንዲያውም የኃላ ኃላ ወደ ታላቅ ደስታ ያደርሳል ከተባለበት ምክንያት አንዱ ይህ ነው፤

> አሁን በብዙ ዐይነት ፈተና ውስጥ ሆናችሁ ለጥቂት ጊዜ መከራን ብትቀበሉም እንኳ፣ በዚህ እጅግ ደስ ይላችኃል፡፡ እነዚህ ነገሮች በእናንተ ላይ የደረሱት በእሳት ተፈትኖ ቢጠራም፣ ጠፊ ከሆነው ወርቅ ይልቅ እጅግ የከበረው እምነታችሁ እውነተኛ መሆኑ እንደ ተረጋገጠና ኢየሱስ ክርስቶስ በሚገለጥበት ጊዜ ምስጋናን፣ ክብርንና ውዳሴን እንዲያስገኝላችሁ ነው፡፡ (1 ጴጥሮስ 1፥6 - 7)

ምድረ በዳ የምንነጻበትና በውስጣችን መልካም ባሕርይ የሚቀረጽበት ቦታ ነው፡፡ እውነተኛ መንፈሳዊ ሰው የሚበጀው ወይም የሚሠራው በዚህ የመከራና የስደት እቶን ውስጥ ነው፡፡ ሮሜ 5፥3-4፣ ‹‹በዚህ ብቻ ሳይሆን፣ በመከራችንም ሐሤት እናደርጋለን፤ ምክንያቱም መከራ ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ እናውቃለን፡፡ ትዕግሥት ጽናትን፣ ጽናት የተፈተነ ባሕርይን፣ የተፈተነ ባሕርይ ተስፋን›› ያስገኛል ይላል፡፡

እግዚአብሔር ዳዊትን የተቀበለው መንግሥትን ለመያዝ እየተጋደለ ስለ ነበር ሳይሆን፣ እንደ እግዚአብሔር የሆነ ልብ ስለ ነበረው ነው! ንጉሥ ሳኦል በሚያነጻና በሚያጠራ ምድረ በዳ ውስጥ አላለፈም፤ ስለዚህ አልነጻም ልቡ የተረጋጋ ሰው አልነበረም፤ ዳዊት ግን ምድረ በዳ ውስጥ ተፈትኖ ነጽቶአል፤ ዳዊትን ወደዚያ ለመውሰድ

እግዚአብሔር በሳኦል ተጠቅሞአል!

የእግዚአብሔር መንገድ ምስጢራዊና ከአእምሮ በላይ ሊሆን ይችላል፤ ሆኖም፣ ዕቅዶቹ ሁሌም መልካም ናቸው!

## እውን ከመሆን የዘገየ ሕልም?

የመንጻቱ ሂደት ቀላል አይደለም፤ ያምማል፤ ይህን በተመለከተ እንድትሳሳቱ አልፈልግም – ምድረ በዳ ለሽርሽር የምኬድበት ቦታ አይደለም፡፡ መከራ መከራ ነው፤ አንዳንዴ በጣም በሚያሳምም ሁኔታ ሊመታን ይችላል፡፡

ምናልባትም፣ እግዚአብሔር ለእናንተ ስላለው ዓላማ ሕልም ወይም ራእይ ሰጥቷችሁ ይሆናል፡፡ ለሕይወታችሁ ስላለው ዕቅድ በተለያየ መልኩ ነግሮአችሁ ሊሆን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምድረ በዳ ውስጥ በምትሆኑበት ጊዜ ይበልጥ ጌታን በፈለጋችሁ መጠን፣ ይበልጥ ለቃሉ በታዘዛችሁ መጠን፣ እርሱ ልባችሁ ውስጥ አኑሮት የነበረው ሕልም ይበልጥ ከእናንተ ይርቃል፡፡

ዮሴፍን ተመልከቱ፤ መሪ እንደሚሆን – ሌላው ቀርቶ ወንድሞቹና ቤተ ሰቡ በእርሱ ሥልጣን ሥር እንደሚሆኑ ሕልም አይቶ ነበር፡፡ ታዲያ ምን ሆነ? የእርሱ መከታ መሆን በሚገባቸው ታላላቅ ወንድሞቹ ጉድጓድ ውስጥ ተጣሉ፤ በኋላም በባዕድ ምድር ባርያ እንዲሆን ተሸጠ፡፡ የተሰማውን ቁስል፣ ስብራትና ተስፋ መቁረጥ ማሰብ ትችላላችሁ?

እግዚአብሔር በተአምር ጣልቃ ገብቶ ቶሎ ከዚያ እንደሚያወጣው ተስፋ ሳያደርግ አልቀረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ በባርነት የቆየው ጥቂት ወሮች ወይም ጥቂት ዓመታት ሳይሆን፣ ከአሥር ዓመት ለበለጠ ጊዜ በመሆኑ የኃላ ኃላ ይህ ተስፋው እንደ ጉም በንኖአል፡፡ አሥር ዓመት ረጅም ጊዜ ነው! በጣም የሚገርመው ደግሞ ለዚህ ችግር የዳረጉት ሰዎች ተንደላቅቀው በነጻነት እየኖሩ፣ በአባታቸው ሀብት እየተጠቀሙ ነበር፡፡

ታዲያ፣ ዮሴፍ ምን ነበር ያደረገው? በምድረ በዳ ባሳለፈው ወቅት የእርሱ ምላሽ ምን ነበር? በእምነቱ በረታ፤ ባለበት ቦታ እንኳ እግዚአብሔርንና ሰውን በቅንነት አገለገለ፤ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል አልዘነጋም፡፡ እርሱ ታማኝ፣ አስተዋይና ትጉ ሰው ነበር፤ ከዚህም የተነሣ የተባረከ ስኬት መለማመድ ቻለ፡፡

ይሁን እንጂ፣ ሁኔታው ወዲያውኑ ተለውጦ ከበፊቱ የባሰ ሆነ፡፡ የጌታው ሚስት ዮሴፍ ላይ ዐይኗን ጣለችበት፡፡ አንዴ ወይም ሁለቴ ሳይሆን፣ በጣም ብዙ ጊዜ በዝሙት ልታጠምደው ፈለገች፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ዮሴፍ ደጋግሞ ከዝሙት ኀጢአት ሸሸ፡፡ በመጨረሻም ሴትዮዋ በጣም ስለ ተናደደች አንቃ ያዘችው፤ ስለዚህም ዮሴፍ ሮጦ ማምለጥ ነበረበት፡፡ በኋላም እርሱ አጥብቆ ሲሸሽው በነበረው በዝሙት ኀጢአት ከሰሰችው፡፡ በሐሰት እንደ በደለኛ ተቆጥሮ ወደ እስር ቤት ተጣለ፡፡ በመሠረቱ የንጉሡን ሹም ሚስት በመድፈር ወንጀል የተከሰሰ ሰው ይገደላል እንጂ በሕይወት አይኖርም፡፡

እስር ቤት ውስጥ ያለ ሰው ያለፉ ነገሮችን ለማሰብ ሰፊ ያለ ጊዜ ያገኛል፡፡ ደጋግሞ ወደ ዮሴፍ ይመጡ የነበሩ ሐሳቦችን መገመት ትችላላችሁ? *በሕይወት ዘመኔ ሁሉ በታማኝነት እግዚአብሔርን ባገለግልም ያተረፍሁት ምንድነው? ያለ በደሌ ወህኒ ቤት ተጥዬ ሞቴን እየጠበቅሁ ነው፤ ከእንግዲህ አብቅቶልኛል! ወንጀል የፈጸሙ ወንድሞቼ ሁሉም በተትረፈረፈበት ቤት ውስጥ በነጻነት እየኖሩ ነው፡፡ ለመሆኑ፣ በደሌ ምን ነበር? ያደረግሁት፣ ‹‹እግዚአብሔር የሰጠኝ›› የመሰለኝን ሕልም ለወንድሞቼ መናገር ነበር፤ ግን ያተረፍሁት ይህ አሁን ያለሁበትን ስቃይ ነው፡፡ ታዲያ፣ እግዚአብሔርን የማገልገሌ ጥቅም ምንድነው? እንዲያውም ይበልጥ እርሱን ባገለገልሁ መጠን መከራዬም በዚያው ልክ እየጨመረ የሚሄድ ነው የሚመስለው፡፡*

ለመሆኑ፣ እንዲህ ያሉ ሐሳቦችን በማውጣት በማውረዱ ዮሴፍን የሚወቅስ ማን ነው? ያቀረባቸው ምክንያቶችም አሳማኝ ናቸው፡፡

አንድ ቀን ዮሴፍን እስር ቤት ውስጥ ከምድረ በዳ ፈተናዎቹ

ሁሉ የባሰ ፈተና ገጠመው፡፡ እግዚአብሔር ሁለት ሰዎች ወደ እርሱ አመጣ፤ የንጉሡ እንጀራ ቤትና ጠጅ አሳላፊ ነበሩ፤ ሁለቱም ሕልም አይተው ነበር፤ ባዩት ሕልም ግራ ተጋብተው ስለ ነበር የሚተረጉምላቸው ሰው እየፈለጉ ነበር፡፡ ዮሴፍ በእግዚአብሔርና እርሱ በሰጠው ተስፋ ማመኑን ትቶ ቢሆን ኖሮ፤ የራሱን ልምምድ ምክንያት በማድረግ ሁለቱንም ፊት ይነሣቸው ነበር፤ ‹‹ሕልም አየን ነው የምትሉት? ይገርማል! እኔም በአንድ ወቅት እንደ እናንተ ሕልም አይቼ ነበር፡፡ ሕልሙ ከእግዚአብሔር የመጣ መስሎኝ ነበር፡፡ ሕልም እውነት እንዳይደለ ከእኔ ሕይወት መማር ትችላላችሁ፤ ሕልም'ኮ ከንቱ፣ ባዶና አሳሳች ነው፤ ስለዚህ ከእኔ ዞር ለማለት ፈቃደኞች ናችሁ?›› ይላቸው ነበር፡፡

ዮሴፍ እንዲህ አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ለተጨማሪ ሌሎች ዓመቶች ምናልባትም፣ ዕድሜውን በሙሉ እስር ቤት ውስጥ ያሳልፍ ነበር፡፡ ወደ ነጻነት መውጫ ቲኬቱን ያጣ ነበር (በኋላ ላይ የዩሴፍን ሕልም የመፍታት ችሎታ ለንጉሡ የተናገረው ጠጅ አሳላፊው ነበር፤ ለእርሱ ከእስር ቤት መውጣትና የላቀ ደረጃ ላይ መድረስ ምክንያት የሆነው ይኸው ሰው ነበር)፡፡ ዮሴፍ ከሚገባ በላይ ለራሱ በማዘን ቁጭት ተውጦ ቢሆን ኖሮ፣ መራራ፣ ፌዘኛና ተስፋ ቢስ ሆኖ እዚያው እስር ቤት ውስጥ ይሞት ነበር፤ በተለያየ መልኩ፣ ‹‹እግዚአብሔር'ኮ ታማኝ አይደለም፤ እርሱ'ኮ ቃሉን አይጠብቅም!›› በማለት ይናገር ነበር፡፡

ዮሴፍ ያደረገው ግን ይህን አልነበረም፡፡ በግል ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ተስፋ የሚጻረር አስተሳሰብንና ምክንያታዊነትን ችላ በማለት ጠጅ አሳላፊውንና እንጀራ ቤቱን ማገልገልን መረጠ፡፡ ለእግዚአብሔር ከመታዘዝ አላወላወለም፡፡ ታዲያ፣ ውጤቱ ምን ሆነ? የኋላ ኋላ ነጻ ሆነ፤ በአንድ ቀን ውስጥ ከፈርዖን ቀጥሎ ሁለተኛው ባለ ሥልጣን ሆነ!

እርሱ ያንን ሥልጣን ከያዘ ዘጠኝ ዓመት በኋላ፣ የራቡ ዘመን እየከፋ በመሄዱ ወንድሞቹ እህል ፍለጋ ወደ ግብፅ መጥተው እፊቱ ቀረቡ፡፡ ዮሴፍ ብዙዎች እንደሚያደርጉት የበቀልን መንገድ

አልተከተለም፡፡ አሁን እውነተኛ የመንግሥት መሪ ባሕርይ አዳብሮአል፡፡ ክፉ ላደረጉበት መልካም አደረገ፡፡ እምነት፣ ፍቅርና ለዚያ ሁሉ ችግር ለዳረጉት ሰዎች ይቅር ባይነትን የተሞላ እንጂ፣ መራራ አልሆነም፡፡ ዘማሪው ዮሴፍን አስመልከቶ ሲጽፍ እንዲህ ብሏል፡-

> በባርነት የተሸጠውን ሰው፣ ዮሴፍን ከእነርሱ አስቀድሞ [እግዚአብሔር] ላከ። እግሮቹ በእግር ብረት ተላላጡ፤ በዐንገቱም የብረት ማነቆ ገባ። የተናገረው ቃል እስኪፈጸምለት፣ የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው። (መዝሙር 105፥17-19)

ለዮሴፍ የገባለት ተስፋ ቃል የሚፈጸምበትን ጊዜ የሚያውቅ እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ (ሕልሙን ካየ ሃያ ዓመት አልፎት ነበር)፡፡ የምድረ በዳ ልምምዱ የራሱን፣ የቤተ ሰቡንና የኀላፊነት ሥልጣኑን በአግባቡ የሚይዝበትን ባሕርይ ውስጡ ቀርጾ ነበር፡፡ ለዚህ ሁሉ ስኬቱ ዋናው ቁልፍ ነገር ጌታን መፍራቱ ነው፡፡ የነበረበት ሁኔታ የቱንም ያህል አዳጋች ቢሆንም፣ ዮሴፍ የሚናገረውና የሚንቀሳቀሰው እንደ እግዚአብሔር ቃል ነበር፤ ለእግዚአብሔር ቃል ታዘዘ፡፡

እኔና እናንተስ እንዴት ነን? ቀደም ብዬ እንዳልሁት ጥሪያችሁን በተመለከተ እግዚአብሔር ሕልሞችና ራእዮች ሰጥቷችሁ ይሆናል፡፡ ለእናንተ ያለውን ዕቅድ በተመለከተ ተናግሮአችሁ ይሆናል፡፡ ሆኖም፣ እናንተም እንደ ዮሴፍ ያላችሁት ምድረ በዳ ውስጥ ሊሆን ይችላል፤ እግዚአብሔርን በፈለጋችሁና ለቃሉም በታዘዛችሁ መጠን እርሱ ልባችሁ ውስጥ ካኖረው ሕልም ይበልጥ እየራቃችሁ የምትሄዱ ይመስል ይሆናል፡፡

እናንተ እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ሕልም በተቃራኒ አቅጣጫ ቁልቁል እየሄዳችሁ እያለ፣ እናንተ የቆማችሁለትን ዓላማ የሚጻረሩ ሰዎች ግን፣ በአገልግሎት ወይም በሌሎች የሕይወት መስኮች ይበልጥ ከፍ እያሉ ሲሄዱ እየተመለከታችሁ ይሆናል፡፡ ማድረግ ያለባችሁን ሁሉ ብታደርጉም፣ የተሰጣችሁ ራእይ ግን ሲፈጸም አታዩም፡፡

ሥጋውያን የሆኑና እግዚአብሔርን የማይፈልጉ ሰዎች በአካባቢያችሁ ይኖሩ ይሆናል፤ ያም ሆኖ ግን ከፍ ከፍ እያሉ ሲሄዱና ነገር ሁሉ ሲሳካላቸው ትመለከቱ ይሆናል፡፡ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ፣ ‹‹በረከቶች›› የሚቀበሉ እነርሱ ናቸው፡፡ ሰዎችን በመሸንገላቸው ወይም ሌሎች ላይ በሚያሳድሩት ጫና እየተሳካላቸው የሚሄዱ ሰዎች ይኖራሉ፡፡ በሚያደርጉትና በሚናገሩት እውነት የሌላቸው ውሸታሞችና አታላይ ሰዎች፣ ‹‹የተባረኩ›› ሲመስሉ እናንተ ግን እንደ ዮሴፍ ወህኒ ቤት ውስጥ በሰንሰለት ታስራችሁ ይሆናል፡፡

ታዲያ፣ እንዲህ ሲሆን ምንድነው የምታደርጉት? ታማርራላችሁ? ወይስ ትነጫነጫላችሁ? እግዚአብሔር የሚናገረውን ስሙ፡-

> <<በእኔ ላይ የድፍረት ቃል ተናግራችኃል>> ይላል እግዚአብሔር፤እናንተ ግን፣ <<በአንተ ላይ የተናገርነው ምንድነው?>> ትላላችሁ። እንዲህም ብላችኃል፤ እግዚአብሔርን ማገልገል ከንቱ ነው፤ እርሱየሚፈልገውን ሁሉ በማድረግና በእግዚአብሔር ጸባኦት ፊት ሐዘንተኞች ሆነን በመመላለስ ምን ተጠቀምን? አሁን ግን ትዕቢተኞችን ብሩካን እንላቸዋለን፤ ክፉ አድራጊዎች ይበለጽጋሉ፤ እግዚአብሔርን የሚፈታተኑም ያመልጣሉ፡ ፡›>> (ሚልክያስ 3፥13-15)

እነዚህ አጉረምራሚዎች ምን እያሉ ነው? ‹‹ውጤቱን ስላላየን ለእግዚአብሔር የመታዘዝ ጥቅሙ ምንድነው? ከፍ ሲሉ፣ ሲባረኩ፣ ወይም ሲሳካላቸው የሚታዩት ዐመፀኞቹ፣ ሥጋውያንና ጉረኞቹ ናቸው›› እያሉ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ይህን፣ ‹‹የድፍረት ቃል›› ብሎታል፤ በቀጥታ እርሱን እንደ መጻረር ነው የተመለከተው፡፡ በግልጽ አነጋገር እነዚህ ሰዎች እያማረሩና እየተነጫነጩ ነበር፡፡

የእስራኤል ልጆች ተስፋ ወደ ተገባላቸው ምድር እንዳይገቡ ያደረገ ማጉረምረም ነበር፡፡ ማጉረምረም በእግዚአብሔር ላይ የድፍረት ቃል የሆነውና ከባድ ቅጣት የሚያስከትለው ለምንድነው? በቀጥታም ባይሆን በተዘዋዋሪ እግዚአብሔርን፣ ‹‹በሕይወቴ እያደረግህ ያለውን አልወደውም፤ እኔ አንተን ብሆን ኖሮ፣ ከዚህ የተለየ ነገር አደርግ

ነበር›› የማለት ያህል ነው፡፡ ይህ ደግሞ እግዚአብሔርን መዳፈር ነው፡፡

ማን እርሱን እየፈለገ፣ ማን ጥቅማ ጥቅም እየፈለገ መሆኑን እግዚአብሔር ይፈትናል፡፡ የመጀመሪያዎቹ እግዚአብሔርን ለማግኘት ቆራጦች ናቸው፤ ሁለተኞቹ ግን ነገሮች መልካም መስለው ካልታዩዋቸው፣ ሁሌም ያጉረመርማሉ፡፡ አንዳንዶች፣ ‹‹በረከት›› የሚሉዋቸውና በእውነት በረከት የሆኑ ሁለት የተለያዩ ነገሮች ናቸው፡፡ የልባችሁ ዝንባሌ ትክክል ካልሆነ፣ አንዳንድ በረከቶች ዘላቂ ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ራስ ወዳዶችና አጉረምራሚዎችን በተመለከተ፣ እነርሱና በረከቶቻቸው ላይ ምን እንደሚያደርግ እግዚአብሔር እየተናገረ ያለውን ተመልከቱ፡-

> <<አሁንም ካህናት ሆይ [አጉረምራሚ አማኞች] ይህ ማስጠንቀቂያ ለእናንተ የተሰጠ ነው፤ ባትሰሙ፣ ልባችሁንም ስሜን ለማክበር ባታዘጋጁ፣ ርግማን እሰድባችኋለሁ፤ በረከታችሁንም ወደ መርገም እለውጠዋለሁ፤ ልታከብሩኝ ልባችሁን አላዘጋጃችሁምና ረግሜዋለሁ ይላል እግዚአብሔር ጸባኦት፡፡>> (ሚልክያስ 2፥1-2)

ሽልማታችን ወይም ውርሳችን በዋነኛነት ደረጃ ቁሳዊ ነገሮች ወይም ሹመት ሳይሆን፣ ጌታ ራሱ ነው!

ሕዝቅኤል 44፥28፣ ‹‹ለካህናቱ ርስታቸው እኔ ብቻ ነኝ፤ … እኔ ርስታቸው እሆናለሁ›› ይላል፡፡

በዚህ ዘመን ብዙ ክርስቲያኖች ዐይኖቻቸውን ከእውነተኛው ርስት ላይ አንሥተው ቁሳዊ ነገሮች ላይ – ምናልባትም፣ እግዚአብሔር ራሱ በሰጣቸው መልካም ነገሮች ላይ አድርገዋል፡፡ ከአባቱ ጋር ካለው ግንኙነት ይልቅ ከአባቱ የሚያገኘውን መልካም ነገር ብቻ እንደሚፈልግ ልጅ ሆነናል፡፡ አራት ወንዶች ልጆች አሉኝ፤ መልካሙን ሁሉ ለእነርሱ መስጠት ደስ ያሰኘኛል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እኔን የሚፈልጉኝ ከእኔ ስለሚያገኙት ነገር ብቻ ከሆነ፣ ልቤን ይሰብረዋል፡፡ ነቢዩ ሚልክያስ እየተናገረ ያለውን ስሙ፡-

> በዚያን ጊዜ እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሰዎች እርስ በርሳቸው ተነጋገሩ፤ እግዚአብሔር አዳመጠ፤ ሰማቸውም፤ እግዚአብሔርን ለሚፈሩና ስሙን ለሚያከብሩ በእርሱ ፊት የመታሰቢያ መጽሐፍ ተጻፈ። (ሚልክያስ 3፥16)

እነዚህ ሰዎች እንደ፣ ‹‹አጉረምራሚዎቹ›› ሁሉ ተመሳሳይ በሆነ ምድረ በዳ ውስጥ እያለፉ የነበሩ ናቸው፤ ሆኖም፣ እነርሱ ቅድሚያ የሚሰጡት ለደረጃ፣ ለታዋቂነት ወይም ለቁሳዊ ነገሮች አይደለም፡፡ እነርሱ የእግዚአብሔርን ልብ እየፈለጉ ነው! እርሱን የማግኘት ፍላጐታቸው ውስጣቸው እየተቀጣጠለ ነው፡፡ ስለ ማኅበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ልታናግሩዋቸው ትችላላችሁ፤ ጌታን ወይም የእርሱን ቃል በተመለከተ ስታናግሩዋቸው ግን ልባቸው ይቀጣጠላል፡፡ እነዚህ፣ ‹‹እነርሱም፣ ‹በመንገድ ላይ ሳለን፣ እያነጋገረን ቅዱሳት መጻሕፍትንም ገልጦ ሲያስረዳን፣ ልባችን እንደ እሳት ይቃጠልብን አልነበረምን ተባባሉ››› በማለት ሉቃስ የሚናገርላቸውን ሰዎች ይመስላሉ፡፡ (ሉቃስ 24፥32)፡፡ ምኞታቸው ሁሉ የመንፈስ ነገሮች ላይ ነበር፡፡ ‹‹እኔ ጌታን ማወቅ እፈልጋለሁ፤ እርሱን ደስ ማሰኘት እፈልጋለሁ፤ የእግዚአብሔርን ቃል ተርቤአለሁ፤ ተጠምቻለሁ፤ እርሱ የደስታዬ ምንጭ በመሆኑ በእኔ ደስ እንዲለው እፈልጋለሁ›› ይላሉ፡፡ ከሁሉም የበለጠው ይኸው ነው፡፡ የመጀመሪያ ፍቅራቸው ኢየሱስ እንጂ ሥልጣን፣ ታዋቂነት ወይም ንብረት አይደለም፡፡

በምድረ በዳ ውስጥ ቢሆኑም፣ ወይም ያማረ መድረክ ላይ ቆመው ለሚሊዮኖች እየሰበኩ ቢሆኑም ባሕርያቸው አይለዋወጥም፡፡

> እኛ ከእግዚአብሔር ጋር አብረን የምንሠራ ነንና፤ እናንተም የእግዚአብሔር ዕርሻ ናችሁ፤ የእግዚአብሔር ሕንፃ ናችሁ። ከእግዚአብሔር በተሰጠኝ ጸጋ መጠን፣ እንደ አንድ ብልኅ ግንበኛ መሠረትን ጣልሁ፤ ሌላውም በላዩ ላይ ይገነባል፤ ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለበት። (1 ቆሮንቶስ 3፥9-10)

ሕይወታችንን እንዴት እንደምንገነባ መጠንቀቅ አለብን! በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፣ ‹‹ሕንፃ መገንባት›› የሕይወታችንና የመንግሥቱ መገንባት ምሳሌ ነው፡፡ የእርሱ ሕንፃ ስለሆንን እኛ የእግዚአብሔር ነን፡፡

> ...ሙሴ በእግዚአብሔር ቤት ሁሉ ላይ ታማኝ እንደ ነበር እርሱም (ክርስቶስ) ለሾመው ታማኝ ነበር። ቤትን የሚሠራ ከቤቱ ይልቅ የሚበልጥ ክብር እንዳለው ኢየሱስም ከሙሴ የሚበልጥ ክብር የተገባው ሆኖ ተገኝቶአል፤ እያንዳንዱ ቤት የራሱ መሪ አለው፤ ነገር ግን ሁሉን የሠራ እግዚአብሔር ነው። (ዕብራውያን 3፥1-4)

ቤቱን የሠራ ጌታ ራሱ መሆኑን ልብ በሉ፡፡ ያን የሚያደርግ የሥጋችን ብርታት አይደለም፡፡ እግዚአብሔር የሚገነባው ይዘልቃል፤ እኛ የምንገነባው አይዘልቅም፡፡ ‹‹እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ›› (መዝሙር 127፥1)፡፡ አንድ ሰው የገዛ ራሱን ሕይወት ወይም ቤት፣ ሌላው ቀርቶ አገልግሎት እንኳ ቢሆን፣ ከእግዚአብሔር ውጪ የሚገነባው አይዘልቅም፡፡

ዘፍጥረት 11፥4 ላይ ለዚህ ምሳሌ የሚሆነንን እናገኛለን፤ ‹‹ለስማችን መጠሪያ እንዲሆንና በምድር ላይ እንዳንበተን፣ ኑ ከተማና ሰማይ የሚደርስ ግንብ ለራሳችን እንሥራ አሉ፡፡››

የባቢሎንን ግንብ የሠሩ ሰዎች ዓላማ ምን ነበር? የራሳቸውን ሕልም ማሳካት፣ ለክብራቸው የሚሆን ሕንፃ መገንባት ነበር፡፡ እንደ እግዚአብሔር መሆን ፈልገዋል፡፡ ሥራቸውና ጥረታቸው ሁሉ የእነርሱን ፍላጎት ማሳካት እንጂ፣ የእግዚአብሔር አልነበረም፡፡ ያለ እግዚአብሔር የተገነባ አይዘልቅም፤ ዓላማችን የቱንም ያህል የከበረ ቢሆን እንኳ፣ እግዚአብሔር ከሌለበት ከንቱ ነው፡፡ ቀጥሎ ያለው ማስጠንቀቂያ የተሰጠን በዚህ ምክንያት ነው፡፡

> ነገር ግን እያንዳንዱ እንዴት እንደሚገነባ መጠንቀቅ አለበት። ... ማንም በዚህ መሠረት ላይ [ክርስቶስ ኢየሱስ] በወርቅ ወይም በብር፣ በከበረ ድንጋይ ወይም በዕንጨት፣ በሣር ወይም በአገዳ

ቢያንጽ ሥራው እንዴት እንደ ሆነ ይታያል። (1 ቆሮንቶስ 3፥10-13)

ወርቅ፣ ብር፣ የከበረ ድንጋይ፣ በእግዚአብሔር መንገድና ፈቃድ መገንባትን ይወክላሉ፡፡ ዕንጨት፣ ሣርና አገዳ በዓለም ዕቅድ መሠረት የእኛን ግንባታ ዘዴ ይወክላሉ፡፡ እነዚህ ጥቅሶች በሰማይ ስለሚኖረው ፍርድ ብቻ እየተናገሩ ነውን? አይደለም! ጥቅሶቹ ወደ ቤተ መቅደሱ ሲመጣ ስለሚሆነው ጉዳይ ነው የሚናገሩት (ሚልክያስ 3÷16- 4÷1 እና 1 ቆሮንቶስ 3÷16-17)፡፡ እርሱ እንደ እሳት ይመጣል፤ እሳት ዕንጨት፣ ሣርንና አገዳን ያቃጥላል፤ ወርቅና ብርን ግን ያነጻል፤ ያጠራል፡፡ ‹‹ሥራው የተቃጠለበት ግን ሽልማት ይቀርበታል፤ እርሱ ራሱ ግን ይድናል፤ ይሁን እንጂ፣ የሚድነው በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚልፍ ሆኖ ነው›› የሚለው በዚህ ምክንያት ነው (ቁ. 15)፡፡

የራሳችሁን ሕይወት፣ ሥራ ወይም አገልግሎት በሰብዕናችሁ ብርታት ወይም ዓለማዊ ፕሮግራም ወይም ዘዴ ከሆነ… የምትገነቡት ሰዎችን መጠቀሚያ በማድረግ ወይም በማስፈራራት ከሆነ.. አንድ ደረጃ ላይ ለመድረስ በአንደበታችሁ የምትሸነግሉና የምታታልሉ ከሆነ… የራሳችሁን ለመገንባት ስትሉ የሌሎችን በነቀፋ ወይም በሐሜት የምታፈርሱ ከሆነ… በእንዲህ ባሉ መንገዶች የምትገነቡት ሁሉ ተቃጥሎ ይወድምባችኋል፡፡

ብዙዎች በአታላይነት ወይም በድፍረት በመዋሸት ራሳቸውን ያሳድጋሉ፡፡ ይህም ቢሆን ተቃጥሎ ይጠፋል! ‹‹ማንም ራሱን አያታልል፤ ከእናንተ ማንም በዚህ ዓለም ጥበበኛ የሆነ ቢመስለው፣ ጥበበኛ ይሆን ዘንድ ራሱን እንደ ሞኝ ይቁጠር፡፡ የዚህ ዓለም ጥበብ በእግዚአብሔር ፊት ሞኝነት ነውና›› (1 ቆሮንቶስ 3÷18-19)፡፡

ራስ ወዳድነትን መሠረት ያደረገ ማንኛውም የሕይወታችን ገጽታ በእግዚአብሔር ፊት እንደ ዕንጨት፣ ሣርና አገዳ ይቆጠራል፡፡ የቱንም ያህል ሌሎችን የመርዳት ፍላጎት ቢኖረው ወይም በጌታ ስም የሚንቀሳቀስ ቢሆን፣ ጊዜውንና ገንዘቡን መሥዋዕት ያደረገም

ቢሆን፣ ያ ሁሉ ተቃጥሎ ይጠፋል፡፡

የዚህ ዓለም ጥበብ ትኩረት እኔነት ነው፡፡ ‹‹ነገር ግን መራራ ቅንዓትና ራስ ወዳድነት በልባችሁ ቢኖር… እንዲህ ያለችዋ ጥበብ ከላይ አይደለችም፤ ነገር ግን ከምድር፣ ከሥጋና ከአጋንንት ናት›› (ያዕቆብ 3፥14-15)፡፡ ቅንዓት፣ ፉክክርና ጥርጥርን ይወልዳል፡፡ ያለንበት ደረጃ ወይም ይዞታችን እንዳይነካብን በሥልጣናችን እንጠቀም ይሆናል፤ ይህ ደግሞ ጓደኞቻችንና፣ ታማኝነታችንን ያሳጣናል፤ ከሁሉም በላይ ከጌታ ጋር ያለንን ኅብረት ያበላሻል፡፡ ፓስተሮችና አገልግሎት ውስጥ ያሉ ሌሎች ሰዎች ወደ እግዚአብሔር ልብ ጠጋ ብሎ መኖርን ችላ በማለት ለቦታቸው፣ ለመጠሪያቸው፣ ለደመወዛቸው በመቆርቆር ስሜት ይነዳሉ፡፡

በአንጻሩ ደግሞ በእውነት የእግዚአብሔርን ልብ የሚፈልጉ ብዙዎች፣ አብልጠው እርሱን በፈልጉ መጠን፣ በዚያው ልክ ከእርሱ እየራቁ የሚሄዱ ሊመስላቸው ይችላል፤ በዚህ ጊዜ ግራ በመጋባት፤

‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ ይበልጥ አንተን በፈለግሁ መጠን ቁልቁል የምሄድ እንጂ ከፍ የምል አይመስለኝም፡፡›› ይላሉ፡፡

እግዚአብሔር ግን፣ ‹‹አጥልቃችሁ ቆፍሩ!›› ይላቸዋል፡፡

> ‹‹ወደ እኔ የሚመጣ፣ ቃሌንም ሰምቶ የሚፈጽም ሁሉ፣ ማንን እንደሚመስል ላሳያችሁ፤ ቤትን ለመሥራት አጥልቆ የቆፈረና መሠረቱን የመሠረተ ሰው ይመስላል…›› (ሉቃስ 6፥47-48)

በዳላስ እንኖር በነበረ ዘመን ገንቢዎች ረጃጅም ፎቆችን ሲሠሩ እመለከት ነበር፡፡ ዐለቱን በመስበር፣ ለመሠረቱ የሚሆን ጥልቅ ጉድጓድ ለመቆፈር ወሮች ስለሚወስድ መጀመሪያ ላይ ዕድገቱ በጣም ዝግ ይላል፡፡ ሕንፃው ትልቅ እንዲሆን ከተፈለገ የመሠረቱ ጉድጓዱም ጥልቅ ይሆናል፡፡ ግንበኞቹ ከመሬት ከፍ ሲሉ አይታይም አካሄዳቸውም አዝጋሚ በመሆኑ የግንባታው ሥራ ቀርፋፋ ይመስላል፡፡ በድንገት ግን ረጅሙ ሕንፃ በፍጥነት ወደ

ላይ ከፍ ከፍ እያለ ሲሄድ ይታያል፡፡ ዝግጅቱ ከወሰደው ጊዜ ጋር ሲነጻጸር ዕድገቱ በየቀኑ እየጨመረ በፍጥነት የሚሄድ ይመስላል፡፡ ታች ከሚደረገው ዝግጅት ጋር ሲነጻጸር፣ ወደ ላይ ሲወጣ የሚታየው ዕድገት ይህን ያህል አይደለም፡፡

በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ብዙዎች በተለይም በወጣቱ ትውልድ መካከል ያሉት በጣም ወደ ታች ወርደው መሠረትን የመሥራት ሂደት ውስጥ እንዳሉ አምናለሁ፡፡ ለዚያም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ! እነዚህ ወገኖች ለአገልግሎት ወይም እግዚአብሔር የሰጣቸውን ሕልምና ራእይ ለመፈጸም ተጠርተው ይሆናል፤ አሁን ግን በጣም ወደ ታች ወርደው እየሠሩ ነው፡፡ ነገሮች በፍጥነት እየሄዱ ያሉ አይመስሉም፤ ይሁን እንጂ፣ ምድረ በዳ ውስጥ እግዚአብሔር በጥንቃቄ እያዘጋጃቸው እንደ ሆነ አምናለሁ፡፡ መሠረቱ እየተጣለ ነው፤ የክርስቶስ ባሕርይ እየተቀረጸ ነው፡፡ በሚመጡት ዓመታት ክርስቶስንና መንግሥቱን በትጋት የሚያገለግሉትን እንዲህ ዐይነቱ ባሕርይ ብርታት ይሆናቸዋል፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ ሕይወት ያልሆኑት ሌሎች ሰዎች በፖለቲካም ሆነ በሌላ መንገድ በፍጥነት እያደጉ ያሉ ይመስላል፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ ያሉት ወገኖች ግን ጉዞአቸው ቀጥ ብሎ የቆመ ይመስላቸዋል፤ ሌላ ፈጣንና ቀላል አማራጭ መንገድ ለመያዝም ይፈተኑ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እንዲህ ያለው መንገድ፣ ዘላቂ ባሕርይ እንደማያስገኝና ቀድሞኑ ከነበራቸው ባሕርይ ጋር የማይጣጣም መሆኑን ስለሚያውቁ የኋላ ኋላ ከባድ ዋጋ እንደሚያስከፍላቸው ይረዳሉ፡፡ የፈለገው ያህል ጊዜ ቢወስድም እግዚአብሔርን በመጠበቅ የግንበኞቹ አለቃ ዐለቱ ላይ መሠረቱን እንዲሠራ ይፈቅዳሉ፡፡

በአሁኑ ጊዜ አጥብቀው እግዚአብሔርን በመፈለግ ላይ ያሉ ፓስተሮች አሉ፤ ሆኖም፣ ምንም ሲሆን አይታይም፤ አሁን ያሉት በደረቅና የተራቆተ ቦታ ነው፡፡ ራስን በማስተዋወቅ ገበያ ሌሎች ሲያድጉና ሲሳካላቸው ያያሉ፡፡ ማኅበራዊ ሚዲያ ውስጥ እንደ ጉም የማይጨበጥ ደስታና ስኬት ይፈጥራሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ እርሱ

ጠንካራና ዘላቂ መሠረት እያዘጋጀላቸው በመሆኑ፣ ምድረ በዳ ውስጥ ያሉ ወገኖቻችን በእንዲህ ያሉ ዘዴዎች እንዲገነቡ እግዚአብሔር አይፈቅድም፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ እግዚአብሔር ሕልም ቢሰጣቸውም፣ የተለየ ደረጃቸውን ወይም ቦታቸውን ያላሳያቸው ሰዎች አሉ፡፡ እንዴት ሊፈጸም እንደሚችል ይጠይቃሉ፤ የሕልማቸው እውን መሆን ጨርሶ የማይደረስበት ይመስላቸዋል፡፡

**በጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች**

#8 ኢያሱ በትክክል ተረድቶአል

በምድረ በዳ የምናልፍበት ዓላማ ለራሳችን ዘላቂ ጥቅም ከሆነ፣ መጥፎውን እያስወገድን መልካሙን አጥብቀን የምንይዘው እንዴት ነው?

ኢያሱ፣ ምድረ በዳ ውስጥ ቀና ልብ የሚኖራቸው ሰዎች ትክክለኛ ምሳሌ ነው፡፡ ሙሴ ወደ ሲና ተራራ በወጣ ጊዜ ኢያሱ ተራራው ግርጌ ነበር፡፡ በተቻለው መጠን ወደ እግዚአብሔር ሓልዎት መቅረብ ይፈልጋል፡፡ መገናኛው ድንኳን ውስጥ ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር በሚገናኝበትም ጊዜ፣ ወደ ጌታ ሓልዎት ለመጠጋት በማሰብ ኢያሱ እዚያ ነበር፡፡ ሙሴ ነገሩን ከጨረሰ በኃላ እንኳ ኢያሱ ከመገናኛው ድንኳን አልተለየም ነበር (ዘፀአት 33፥11)፡፡

ከመጽሐፉ ኢያሱ በወላጆቻቸው ዘመን (ያለፈው ትውልድ) ሕዝቡን ያስጨነቁ አምስት ኀጢአቶች ምድረ በዳ ውስጥ በነበረው በሁለተኛው ትውልድ ዘመን (አዲሱ ትውልድ) አለመታየታቸውን እንመለከታለን፡፡ አንድ ጊዜ ብቻ አካን በሚሉት ሰው በኩል ተከስቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ አመራሩና ሕዝቡ ወዲያውኑ አንድ ነገር እንዲያደርግ

የእግዚአብሔርን ፊት ፈለጉ፡፡ የመጀመሪያውን ትውልድ ውድቀት – ማለት የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል ሲፈጸም ሳያዩ በምድረ በዳ ስለሞቱት አባቶቻቸው በማስተዋሉ ሁለተኛው ትውልድ መልካም ነገር አድርጎአል፡፡

ኢያሱና የእርሱ ትውልድ ትኩረታቸውን ፈጣሪ ላይ ስላደረጉ፣ ወደ ተስፋው ምድር ገቡ፡፡ የእግዚአብሔርን ቃል ለመጠበቅ የጨከኑና ከማንኛውም ዐይነት ተስፋ መቁረጥ የራቁ ነበሩ፡፡ ማጉረምረምን እንቢ ያሉ፣ በእግዚአብሔር ለመታመን ግን የተዘጋጁ ነበሩ፡፡

በዚህ ደረቅ ምድረ በዳ ወቅት በመታዘዝ እርሱን የሚጠብቁትን በማጭበርበር ከሚገነቡት፣ ራሳቸውን ለማስተዋወቅ ወይም ሌሎች ላይ ተፅዕኖ ለማድረግ የተለያዩ ሐሳቦችን ከሚያወጡ ከሚያወርዱት ሰዎች እግዚአብሔር ይለያቸዋል፡፡ እውነት ነው፣ እግዚአብሔር ወደ ቤተ መቅደሱ እስኪመጣ ለሚጠብቁና ለሚታገሡ፣ እንደ እርሱ ፈቃድ የሆነ ዕድገትና ከምድረ በዳ መውጫ መንገድ ይመጣላቸዋል፡፡ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤

‹‹ለይቼ በወሰንኋት ሰዓት፣ በቅን የምፈርድ እኔ ነኝ፡፡›› … ክብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ ወይም ከምድረ በዳ አይመጣምና፡፡ ነገር ግን የሚፈርድ እግዚአብሔር ነው፤ እርሱ አንዱን ዝቅ፣ ሌላውን ከፍ ያደርጋል፡፡›› (መዝሙር 75፥2-7)

## የሥጋ ከንቱ ድካም

በሥጋና በመንፈስ መካከል የሚደረገው ትግል አገልግሎትን ብቻ ሳይሆን፣ ማንኛውንም የሕይወት ገጽታ ይመለከታል፡፡ ሥጋ የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል እንዲፈጸም ማድረግ እንደማይችል

አስታውሱ! ከሥጋ አንዳች ነገር ከተገኘ ጥሩ ነገር ነው፤ ከሆነ ግን፣ ያ መቀጠል የሚችለው በሥጋ ብርታት ብቻ ነው፡፡ ያ ነገር ከመንፈስ ከተወለደ ግን እግዚአብሔር ማንኛውንም ኀላፊነት ይወስዳል፡፡

ብዙ ጊዜ ሥጋ ሌሎች ላይ ጫና በማድረግና በመቆጣጠር ይጠቀማል፡፡ የሚፈልጉትን ለማግኘት መሪዎች ሥልጣናቸውን ይጠቀማሉ፤ በሰዎችም ስሜት ይጫወታሉ፡፡ አንተም ከተከታዮቻቸው አንዱ ከሆንህ ከእነርሱ ባገኘኸው መመሪያ መሠረት በምትሰጠው ምላሽ ለስኬታቸው ወይም ለውድቀታቸው ተጠያቂ ትሆናለህ፡፡ እንዲህ ባለው ሁኔታ ውስጥ ከባድ ጫና ማሳደር፣ ፈላጭ ቆራጭነት፣ ገዢነትና ሁሉን ለቆጣጠር ባይነት ይኖራል፡፡

ምንም እንኳ በዋናነት እየተናገርሁ ያለሁት አገልግሎትን በተመለከተ ቢሆንም፣ ጉዳዩ የአገልግሎት ብቻ አለመሆኑን አጠንክሬ መናገር እፈልጋለሁ፤ ማንኛውንም የሥጋ የሆነ ውጤት ይመለከታል፡፡ ስለሆነም ይህ ጉዳይ ሥራችንን፣ ትምህርታችንን፣ ጤናችንን፣ መንግሥትን፣ መከላከያን፣ ስፖርትንና እርሱን እንድናገለግል እግዚአብሔር የጠራን ሌሎች ሁኔታዎች ሁሉ ይመለከታል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ከመንፈስ የተወለደ ነገሮችን በራሱ መንገድ የማስተናገድ ኀላፊነት የእርሱ እንዳይደለ ይረዳል፤ በራሱ ችሎታ ዕድገት ማምጣት ወይም ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ እንደማይችል ያውቃል፡፡ እርሱ ለፈጠረው (ለገነባው) የሚያስፈልገውን ሁሉ ማድረግ የእግዚአብሔር ኀላፊነት ይሆናል፡፡

ይስሐቅ በተወለደ ጊዜ እስማኤል ተቀባይነት ካገኘ ዋል አደር ብሎ ነበር፡፡ (ዘፍጥት 16-21)፡፡ የይስሐቅ ሕልም እውን ከመሆኑ በፊት ሁሌም እስማኤልን የማስገኘት ሙከራ እንደሚኖር በግል ልምምዴ ተረድቻለሁ፡፡ እናንተ ግን እግዚአብሔር የገባላችሁን ተስፋ ቃል በራሳችሁ መንገድ እንዲፈጸም የማድረግ ፈተናን መቃወም አለባችሁ፡፡ ‹‹ይህችን ባርያ ከነልጇ አባርልኝ! ምንም ቢሆን የዚህች ባርያ ልጅ፣ ከልጄ ከይስሐቅ ጋር ውርስ አይካፈልም!›› የሚለውን ጥቅስ አስታውሱ (ዘፍጥረት 21፥10)፡፡

አንድ ቀን እግዚአብሔር፣ ‹‹እንደ ሥጋ የሆነው ልጅ እንደ ተስፋ ቃሉ ከተወለደው ጋር ውርስ ስለሌለው እስማኤልን ለማስገኘት የምታደርጉትን ሙከራ አስወግዱ›› በማለት ለሕዝቡ የሚናገርበት ጊዜ ይመጣል፡፡ ምንም እንኳ ውጤት ያለው ቢመስልም፣ በእርሱ ፊት ሥጋ ክብሩን እንዳይወስድ እግዚአብሔር፣ ‹‹አባርልኝ!›› ይላል፡፡

የእግዚአብሔር ፍርድ በሚገለጥበት ጊዜ በራስህ ችሎታ የተገነባ ማንኛውም የሕይወት ገጽታህ የሚያጠራውን እሳት ወላፈን መቋቋም አይችልም፡፡ ጠቅላላ ሕይወትህን የገነባኸው ራስን በማስቀጠልና ራስን በማሳደግ ሙከራ ላይ ከሆነም፣ ሙሉ በሙሉ ይቃጠላል፤ አንተ ራስህ ግን፣ ‹‹በእሳት ውስጥ በጭንቅ እንደሚያልፍ ሰው›› ትድናለህ (1 ቆሮንቶስ 3÷15)

ጸንቶ መቆም የሚችለው በተስፋ ቃሉ የተገኘው፣ ከእግዚአብሔር መንፈስና ጸጋ የተፀነሰና የተወለደው ብቻ ነው፡፡

# 9

# ብርቱ ሆኖ ለመገኘት አስቀድሞ መሠልጠን

እግዚአብሔር ምርጥ ወታደሮቹን የሚያገኘው ከደረሰባቸው ከመከራ… ነው።

- ቻርለስ ኤች. ስፐርጂን

ሕፃኑም አደገ፤ በመንፈስም ጠነከረ፤ ለእስራኤል ሕዝብ በይፋ እስከ ታየበት ቀን ድረስ በበረሓ ኖረ።

- ሉቃስ 1፥80



ከጥቂት ዓመቶች በፊት እንደ የኢየሱስ ተከታዮች በእምነት ስፋትና ጥንካሬ ለማግኘት ለሚያስፈልገን የዝግጅት ጊዜ ምሳሌ የሚሆን የተለየ ዐይነት ፈተና ደርሶብኝ ነበር፡፡ ይህ ፈተና የገጠመኝ በደረቅና የተራቆተ ምድረ በዳ ሳይሆን፣ በስፖርት ማዘውተሪያና ጤና ክለብ ውስጥ ነበር፡፡

የሰላሣ ዓመት ወጣት በነበርሁ ጊዜ በአትላንታ ጆርጂያ በነበረ አንድ ቤተ ክርስቲያን ከሰበክሁ በኃላ መድረክ ላይ ለመውደቅ ደርሼ ነበር፤ የ አካሌ ሁኔታ ጥሩ እንዳልነበረና በአገልግሎት መቀጠል ከፈለግሁ ጠንካራ ሰውነት ሊኖረኝ እንደሚገባ ተረድቼ ነበር፡፡

ከጆርጂያ ወደ ቤት ስመለስ የሆነውን ለሊዛ ነገርኃት፤ ‹‹ወደ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ መሄድ አለብኝ›› አልኃት፡፡

የሰጠችኝ መልስ፣ ‹‹እግዚአብሔር ይመስገን! እኔም ያንኑ እንድታደርግ እየጸለይሁ ነበር›› የሚል በመሆኑ በጣም ገረመኝ፡፡ በዚህ ዘመን ለባልዋ መጸለይ እንዳለባት የምታውቅ ሚስት ማግኘት መታደል ነው!

በዚያ ጊዜ እንኖር የነበረው በፍሎሪዳ ሲሆን፣ ከእኛ ቤት ቀጥሎ ባለው ሁለተኛ ቤት ውስጥ ኪፕ የሚሉት የWWF ስፖርተኛ ይኖር ነበር፡፡ የሁለታችንም ልጆች በተመሳሳይ ዕድሜ ስለ ነበሩ ቤተ ሰቦቻችን መቀራረብ ጀምረው ነበር፡፡ ይህ ሰው ወደ ስፖርት ማዘውተሪያ ቦታ ወስዶ ሊያሠለጥነኝ ደጋግሞ ጠይቆኝ ነበር፣ እኔ ግን፣ ‹‹አልችልም፤ ጊዜ የለኝም›› በማለት ነበር የምመልስለት፡፡ እውነት ነው ሥራ ይበዛብኝ ነበር፤ ከዚያ ባለፈ ግን እርሱን በመሰለ ታዋቂነት ባተረፈ ስፖርተኛ መሠልጠን አሳፍሮኝ ነበር፡፡

ኪፕ ስድስት ጫማ አራት ኢንች ቁመት፣ 240 ፓውንድ ክብደት ያለው፣ ግዙፍ ሰው ነበር፤ በጣም የሚማርክ ቁመና ነበረው፤ ብዙ ጊዜ ልጆቻችንን ይዘን ከእርሱ ጋር የተለያዩ ስፖርታዊ

ጫወታዎች እንጫወት ነበር፡፡ በድንገት ከእርሱ ጋር ከተጋጨሁ፤ እርሱ ምንም ባይሆን እንኳ፣ እኔ ግን ወደ ኃላ ተስፈንጥሬ መውደቄ እንደማይቀር ይገባኝ ነበር፡፡

ከአትላንታ ከተመለስሁ በኃላ በቀጥታ ወደ ቤቱ በመሄድ፣ ‹‹ኪፕ ወደ ስፖርት ማዘውተሪያው ቦታ መሄድ እፈልጋለሁ፤ ልታሠለጥነኝ እንደምትፈልግ ብዙ ጊዜ ነግረኸኝ ነበር - አሁንስ ያንን ለማድረግ ፈቃደኛ ነህ?›› አልሁት፡፡

እርሱም ወዲያውኑ፣ ‹‹አዎን፣ ወደ ስፖርት ማዘውተሪያው እወስድሃለሁ›› አለኝ፤ ፊት ለፊቴ የሚጠብቀኝን ባውቅ ኖሮ ጥሩ ነበር፤ ያኔ ግን ሐሳቡ እንኳ አልነበረኝም!

በሚቀጥለው ጠዋት ወደ ስፖርት ማዘውተሪያው ቦታ (ስዊት ቦክስ) ሄድን፤ እንዲህ ባለው ቦታ የሚሠለጥኑ ከልባቸው የወሰኑ ሰዎች ብቻ መሆን እንዳለባቸው የተረዳሁት ወዲያውኑ ነበር፡፡ በየቦታው ላባቸው የሚንቆረቆር ሰዎች ይታያሉ፤ የሰውነት ጠረን አየሩን ሞልቶት ነበር፡፡ በስፖርት ማዘወተሪያው ቦታ በዚያው ቀን የተረዳሁት አንድ ሰው ቀላል ሸክም ዘንጉ ላይ በማድረግ ሃያ ወይም ሰላሳ ጊዜ ማንሣት ማውረድ ስለ ሠራ ብቻ ጡንቻ እንደማይኖረው ነው፡፡ ባለ ጡንቻ መሆን የሚቻለው ከባድ ሸክም ዘንጉ ላይ በማድረግ ሦስቴ ወይም አራቴ ማንሳት ማውረድ በመሥራት ነው፡፡

ጡንቻችሁ መዳበር የሚጀምረው ከባዱን ሸክም ዘንጉ ላይ አድርጋችሁ ሦስቴ ወይም አራቴ ደጋግማችሁ ስትሠሩ ነው፡፡ በዚያ ጊዜ ውስጣችሁ ያለ ነገር በሙሉ፣ ‹‹ከእንግዲህስ አልችልም›› ይላል፤ ዙሪያችሁ ያሉ ሰዎችም፣ ‹‹አዎን፣ ትንሽ ግፋ! ትንፋሽህን ዋጥ አድርገህ አንዴ ግፋ!›› ሲሉዋችሁ ኀይላችሁን ሁሉ ታሰባስቡና አራቴ ወይም አምስቴ መግፋት ትጀምራላችሁ፡፡ እውነተኛ ጡንቻ መዳበር የሚጀምረው እንዲህ ሲሆን ነው፡፡

በዚያ የመጀመሪያ ቀን አግዳሚው ወንበር ላይ በጀርባዬ ተጋድሜ ማንሣት የቻልሁት 95 ፓውንድ ብቻ ነበር፡፡ ጉረቤቴ ኪፕ ገና ብዙ እንደሚቀረኝ የተረዳው በዚያው ቀን ሳይሆን እንዳልቀረ

አስባለሁ፡፡ ስፖርት ማዘውተሪያው ውስጥ ጥቂት ሳምንቶች ካሳለፍሁ በኋላ እስከ 105 ፓውንድ ድረስ ማንሣት ቻልሁ፡፡ ከጥቂት ሳምንቶች በኋላ 115 ደረስሁ፤ ከዚያም 125 ደረስሁ፡፡ መጨረሻ ላይ 135 ስደርስ ዘንጉ ግራና ቀኝ ላይ 45 ፓውንድ የተጫነበት ክብደት ማንሣት በመቻሌ ኩራት ብጤ ተሰማኝ፡፡ ከዚያ በኋላ እስከ ዛሬ ድረስ ክብደት ለማንሣት ምንም እፍረት አይሰማኝም፡፡

ይህን በተመለከተ እዚሁ ምዕራፍ በኋላ ላይ የማካፍላችሁ ይኖረኛል፤ ይሁን እንጂ፣ አካላዊ ብርታት ለማግኘት ያለፍሁበት አዝጋሚ ሂደት፣ በምድረ በዳ ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ መንፈሳዊ ጡንቻ እንድናዳብር እግዚአብሔር በራሱ መንገድ ሲያሳልፈን የሚሆነውን በተመለከተ ጥሩ ንጽጽር ሊሆን እንደሚችል አስባለሁ፡፡

መንፈሳችን ብርቱ የሚሆነው ምድረ በዳ ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም ምድረ በዳ የድርቅና ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ የት ነው ያለኸው?›› በማለት የምንጮኸበት ብቻ ሳይሆን፣ የፈተናና በአዳጋች ሁኔታዎችም ውስጥ የምናልፍበት ቦታ በመሆኑ ነው፡፡ ምንም እንኳ፣ ምድረ በዳ አስቸጋሪና ተግዳሮት የሞላበት ቦታ ቢሆንም፣ መንፈሳዊ ጥንካሬ ለማግኘት በምናልፍበት ሥልጠና ሸክሙን የሚያነሣልን ማን መሆኑን ማስታወስ አለብን፤ መልካሙ ዜና ይኸው ነው፡፡

> እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሆነ ማን ሊቃወመን ይችላል? (ሮሜ 8፥31)

እርሱ ከእኛ ጋር መሆኑና ሸክሙን ለማንሣት የሚረዳንም እርሱ መሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የሚከተለውንም ቃል ገብቶልናል፡-

> እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፡፡ (1 ቆሮንቶስ 10፥13)

ስለዚህ የምትጋፈጡት ፈተና የቱንም ያህል ከባድ ወይም ጨለማ ወይም ደረቅ ቦታ ቢሆን፣ በተሳካ ሁኔታ በዚያ ውስጥ ማለፍ

የምንችልበትን ዐቅም ሳይሰጠን እዚያ እንደማይተወን እግዚአብሔር ቃል ገብቶልናል፡፡ ይህን ማሰቡ ራሱ አስደናቂ ነው፡፡

የተለያዩ ፈተናዎች ሲገጥሟችሁ ማን መሆናችሁን አትርሱ፡፡ እንደ ተወደዱ የእግዚአብሔር ልጆች ኢየሱስ፣ ‹‹እንግዲህ… በጠላት ኀይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ፤ የሚጐዳችሁም አንዳች ነገር አይኖርም›› ብሏችኋል (ሉቃስ 10፥19)፡፡ ስለዚህ ጠላት የቱንም ያህል ከባድ ሁኔታዎችን ቢያመጣ እናሸንፈዋለን እንጂ አንሸነፍለትም፡፡ እንደዚያ ባይሆን ኖሮ፣ መጀመሪያውኑ እግዚአብሔር አይፈቅድለትም ነበር!

ይሁን እንጂ፣ ችግሩ ያለው እዚያ ላይ ነው! ብዙ ሰዎች ትልልቅ ፈተናዎችን ለማስተናገድ ባላቸው ችሎታ አያድጉም፡፡ መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ማሳደግ የሚችል ፈተናን ይሸሻሉ፤ እንዲህ ያለ ሁኔታ ሲገጥማቸው ያጉረመርማሉ፤ ይነጫነጫሉ፡፡ ጳውሎስ የሚነግረን ግን ከዚህ ፍጹም ልዩ ስለሆነ ዝንባሌ ነው፡፡ እርሱ እንዲህ በማለት ይጽፋል፡-

> <<በክርስቶስ እንድታምኑ ብቻ ሳይሆን፣ ስለ እርሱ መከራ እንድትቀበሉም ይህ ጸጋ ተሰጥቶአችኋል፡፡>> (ፊልጵስዩስ 1፥29)

መከራ ለመቀበል ጸጋ፣ ‹‹ተሰጥቶአችኋል›› የሚለውን ስታነቡ ግራ ይገባችሁ ይሆን? ለመሆኑ፣ ይህ ምን ማለት ነው? አንድ ሰው ተነሥቶ አንድ ነገር፣ ‹‹ተሰጥቶሃል›› ካለኝ፣ ቶሎ ወደ አእምሮዬ የሚመጣው አንዳች በረከት ወይም መልካም ነገር ወደ እኔ እየመጣ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህም በመጓጓት፣ ያ የምቀበለው ነገር ምን ይሆን በማለት አስባለሁ፡፡

‹‹ተሰጥቶአችኋል›› ከተባለ ወዲያውኑ ትዝ የሚለን መልካም ነገር ነው፤ ታዲያ እንዴት፣ ‹‹መከራ›› ተሰጥቶአችኋል ይባላል?፡፡ በዚህ ዘመን ምቾትና ተደላድሎ መኖርን ስለ ለመድን ዐረፍተ ነገሩ ምንም ትርጕም ላይሰጠን ይችላል፡፡ መከራ ተሰጥቶአችኋል የሚለውን ዐረፍተ ነገር አእምሮአችን ሊቀበለው አይችልም፡፡ ችግርና አዳጋች

ሁኔታዎች ሲገጥሟቸው ብዙ ሰዎች፣

‹‹ይህ ለእኔ ይገባኛል ብዬ አላስብም፡፡››

‹‹ግን፣ ለምን እኔ ላይ ሆነ?››

‹‹በፍጹም ይህን መቀበል አልችልም፡፡››

‹‹እያለፍሁ ያለሁበትን ሁኔታ ማንም ሊረዳልኝ አይችልም!››

‹‹ለመሆኑ፣ እንደ ሌሎች የተለመደ ዐይነት ሕይወት ለምን አልኖርም?››

‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ እባክህን ይህን ወዲያ ውሰድልኝ!››

‹‹ለምን ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርጌ አልተወውም…››

ይላሉ፡፡

የተለያዩ ውጣ ውረዶች ሲገጥሙን ማንኛችንም ብንሆን፣ እንዲህ አስበናል ወይም እንዲህ ተናግረናል ብዬ እገምታለሁ፡፡ ይህን የምለው እያዘንሁ ነው፤ ብዙ ጊዜ ፈተና ወይም መከራ (ምድረ በዳ) የሚመጣበትን ዓላማ አንረዳም፡፡

ነገር ግን እንደ ሁልጊዜው እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን ያውቃል፤ በእርሱ መንግሥት ውስጥ በሚኖረን ድርሻ የበለጠ ውጤታማ ለመሆን የሚያስፈልገንን ብርታት እርሱ ያውቃል፡፡ ስለዚህ የእምነት ጡንቻችንን ለማዳበር፣ እግዚአብሔር መከራና ፈተናዎችን እንደሚሰጠን ጳውሎስ የሚናገረው ይህን በማሰብ ነው፡፡

## የፈተና ድርሻ

ቀደም ሲል እንዳልሁት በምናልፍበት ምድረ በዳ ብርታት የምናገኝበት ሥልጠና ፈተናን ለይተን በማወቅና ያንን በማስወገድ ችሎታ ማደግንም ይጨምራል፡፡ አገልግሎቱ መጀመሪያ ላይ በምድረ በዳ በዲያብሎስ እንዲፈተን እግዚአብሔር አባቱ ሲፈቅድ፣ ኢየሱስ ይህን ተለማምዶ ነበር፡፡ ‹‹ኢየሱስ በመንፈስ ቅዱስ ተሞልቶ ከዮርዳኖስ እንደ ተመለሰ መንፈስ ወደ ምድረ በዳ ወሰደው፤ በዚያም አርባ ቀን በዲያብሎስ ተፈተነ›› (ሉቃስ 4፥1-2)፡፡

በመሠረቱ፣ እግዚአብሔር የፈተና ምንጭ አይደለም፤ ‹‹ፈቀደ›› የሚለውን ቃል በጥንቃቄ የመረጥሁት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ‹‹ማንም ሲፈተን፣ ‹እግዚአብሔር ፈተነኝ› አይበል፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር በክፉ አይፈተንም፤ እርሱም ማንንም አይፈትንም›› (ያዕቆብ 1፥13)፡፡

ታዲያ፣ ፈተና ሲገጥመን እኛ ላይ የሚሆነው ምንድነው? የሰይጣን ፍላጎት በኀጢአት እንድንወድቅና ከዚህም የተነሣ ለእግዚአብሔር በመታዘዝ ከነበረን ደስ የሚል ሕይወት እንድንወጣ ማድረግ መሆኑን እናውቃለን፡፡ እንግዲህ በሚያመጣው ፈተና ሰይጣን የሚፈልገው ይህን ከሆነ፣ እግዚአብሔርስ እንድንፈተን ሲፈቅድ የሚፈልገው ምንድነው? ሐዋርያው ጴጥሮስ እንዲህ ይላል፤ ‹‹እንግዲህ ክርስቶስ በሥጋው መከራን ስለ ተቀበለ እናንተም በዚሁ ዐላማ ታጥቃችሁ ተነሡ፤ ምክንያቱም በሥጋው መከራን የሚቀበል ሰው ኀጢአትን ትቶአል›› (1 ጴጥሮስ 4፥1)፡፡

በሌላ አነጋገር በመከራው አማካይነት የሚገጥመን ፈተና፣ ኀጢአትንና በምድረ በዳ የሚገጥሙንን ሌሎች ነገሮች ማሸነፋችን መንፈሳዊ ጡንቻችንን እንድናዳብርና በሕይወታችንም የበለጠ በሳሎች እንድንሆን ይረዳናል ማለት ነው፡፡ እዚህ ጥቅስ ውስጥ ቁልፍ የሆነው ቃል፣ ‹‹ታጥቃችሁ ተነሡ›› የሚለው ነው፡፡

አንድ ወታደር ተገቢውን ትጥቅ ሳይዝ ወደ ጦር ወደ ሜዳ የሚሄድ ይመስላችኋል? እንዲህ ማድረግ በራስ ላይ ጉዳት መጋበዝ ነው የሚሆነው፡፡ መከራ ለመቀበል ታጥቀው የማይነሡ የክርስቶስ ተከታዮችን የሚገጥማቸው ጉዳት ይህን ይመስላል፡፡

የሚመጣውን ፈተና በመወጣት ረገድ፣ የአውሮፕላን ፓይለቶች ጥሩ ምሳሌ ሊሆኑን ይችላሉ፡፡ በየስድስት ወሩ አየር መንገዱ ወደ ሥልጠና ይልካቸዋል፡፡ እነዚህ ፓይለቶች ምስለ በረራው (ሲሙሌተር) ውስጥ ገብተው ሊገጥማቸው የሚችለውን ማንኛውንም ፈተና እንዴት መቋቋም እንደሚችሉ ይለማመዳሉ፡፡ የዚህ ልምምድ ዓላማ ለድንገተኛ አደጋ ፓይለቶቹን ማዘጋጀት ነው፡፡ የአውሮፕላን አደጋ በሚኖርበት ጊዜ ዝግጅት ያላደረጉት መንገደኞቹ በድንጋጤ

ሲርበተበቱ ፓይለቶቹ ግን ችግሩን ለመቆጣጠር እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ ፓይለቶቹ ዝግጅት የሚያደርጉት ለዚሁ ጉዳይ ነው፡፡

የምድረ በዳ ጉዞ አንድ ታዛዥ ክርስቲያን ላይ የሚያመጣው ውጤት ይህን ይመስላል፡፡ የሚገጥሙን የተለያዩ ውጣ ውረዶች ወደ ፊት ለሚመጣው ድል ያዘጋጁናል፡፡ አዳጋች ሁኔታ ማለትም የምድረ በዳ ሕይወት እያንዳንዳችንንም ይገጥመናል፡፡ በዚህ ዓለም መከራና ችግር እንደሚገጥመንና እርሱ ማሸነፍ እንድንችል እንደሚረዳን ኢየሱስ ነግሮናል፡፡ በዚህ ሂደት ብርታታችን እያደገና እየጐለበተ ይሄዳል፡፡

## ታላቅ ዕድል

ለምድረ በዳ ያለን አመለካከት እግዚአብሔር ለሚሰጠን ነገር ብርቱዎች ሆነን እንድንገኝ መንፈሳዊ ጡንቻችንን የምናዳብርበት መልካም ዕድል መሆኑን መቀበል ሊሆን ይገባል፡፡ ሐዋርያው ያዕቆብ እንዲህ ይላል፡-

> ወንድሞች ሆይ፣ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት... (ያዕቆብ 1፥2)

### ጉዞውን በድል ለመውጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 9 የራሳችሁን እስማኤል አትፍጠሩ

ምድረ በዳ ውስጥ ስንሆንና እዚያ ውስጥ ከሚገባው በላይ ረጅም ጊዜ እንደኖርን ስናስብ፣ የተሰጠን ተስፋ እውን እንዲሆን፣ ‹‹አንዳች ነገር›› የማድረግ ፈተና ይገጥመናል፡፡ ይህን ሁኔታ የእስማኤል መፀነስ እለዋለሁ፤ እንዲህ የሚሆነው እግዚአብሔር አደርጋለሁ ያለንን በራሳችን ጥረት ለማድረግ ስንሞክር ነው፡፡ እስማኤልን

የመሳሰሉ ነገሮች የሚወለዱት ተገቢ በሆነ ችግር ውስጥ ቢሆንም፣ የሚወለዱት እንደ እግዚአብሔር ሳይሆን እንደ ሥጋ ፈቃድ ነው፡፡

ይህ ሐሳብ የተወሰደው ወንድ ልጅ እንደሚወልዱ እግዚአብሔር ቃል ገብቶላቸው ከነበሩት ከአብርሃምና ከሣራ ታሪክ መሆኑ እውነት ነው፡፡ የተስፋ ቃሉ እስኪፈጸም ድረስ አሥራ አንድ ዓመት ሙሉ ጠበቁ፤ በዚያ ጊዜ አብርሃም 86 ዓመት ሆኖት ነበር፤ ሣራም ልጅ የመውለጃ ጊዜ አልፎባት ነበር፡፡ ስለዚህ ሌላ ዕቅድ አወጡ - አብርሃም ከአጋር ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት እንዲያደርግና ቃል የተገባለትን ወንድ ልጅ ከእርሷ እንዲወልድ ሣራ ሐሳብ አቀረበች፡፡ ይህ በጣም መጥፎ ሐሳብ ነው፡፡ የቱንም ያህል መልካምና አሳማኝ ቢመስልም፣ እስማኤልን የመሰለ ማንኛውም አማራጭ መንገድ ጥሩ አይደለም፡፡ ምንጊዜም ቢሆን በሥጋችሁ ብርታት የምትወልዱትን ማንኛውንም ነገር፣ በሥጋችሁ ብርታት ማሳደግ ወይም ማስቀጠል ያለባችሁ መሆኑን አትርሱ!

በአንዳንዶቹ የምድረ በዳ ቆይታዎቼ፣ ሌላ አማራጭ መንገድ ለመያዝ ሞክሬ ነበር፡፡ አንድ ቀን መላውን ዓለም የሚያደርስ አገልግሎት እንደሚኖረኝ እግዚአብሔር ቃል ገብቶልኝ እንደ ነበር አውቃለሁ፡፡ ያ እስኪፈጸም ረጅም ጊዜ ጠበቅሁ፤ ግን የተገባልኝ ቃል እውን አልሆነም፤ አገልግሎቴ በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ዙሪያ፣ ‹‹ተገድቦ›› ነበር፡፡ ስለዚህም በራሴ ጥረት ከነበርሁበት ምድረ በዳ ለማምለጥ ሞከርሁ፡፡ ያደረግሁት ከንቱ መከራ ከባድ ዋጋ ቢያስከፍለኝም፣ ምንም ጠብ ያለ ነገር አልነበረም፡፡ የኋላ ኋላ እግዚአብሔር ካደረገው የተነሣ ግን ነገሮች ተለወጡ፡፡

ወገኖቼ፣ የራሳችሁን እስማኤል አትፍጠሩ፤ እንደዚያ ባለማድረግ ከብዙ የልብ ስብራት ትድናላችሁ፡፡

ቃል የገባላችሁን እግዚአብሔር እስኪያመጣው በትዕግሥት ጠብቁ።

በተገኘው ዕድል መጠቀም አለብን፤ ባገኙት አጋጣሚ ተጠቅመው ታላቅ ነገር ያደረጉ ሰዎችን ማንኛችንም ብንሆን እናከብራለን። ለምሳሌ ሥራችንን በተመለከተ የሚገጥመን መልካም ዕድል ዕድገት፣ ስኬትና ብልጽግና ያስገኝልናል። አድማሳችንን ያሰፋልናል። መከራን በተመለከተ ያለን አመለካከትም ይህን መምሰል አለበት፤ ቀጥሎ ባለው ክፍል ያዕቆብ እንዲህ ይላል፤ ‹‹ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉአን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም›› (ያዕቆብ 1፥3-4)።

ምድረ በዳ ውስጥ ስንሆን ትዕግሥታችንን ወይም ጽናታችንን የምናሳድግበት መልካም ዕድል ይኖረናል። በዚህ ዘመን፣ ‹‹ትዕግሥት›› ወይም ጽናት የሚለውን ቃል እንዴት ነው የምንጠቀምበት? ብዙ ጊዜ ይህ ቃል ወኔን ለማጐልበት ጥርስን ንክስ አድርጐ ችግሮችን ከመቋቋም ጋር ተያይዞ ሲነገር ነው የምሰማው። በቀላል አቀራረብ ትዕግሥት ወደ ፊት ለሚገጥም ተግዳሮት ዐቅምን ማሳደግ ወይም ማስፋት ማለት ነው።

እግዚአብሔር መከራ ወይም ችግር እንዲደርስብን የሚፈቅደው በዓላማ ነው፤ ያ ዓላማ ደግሞ ዐቅም መፍጠር ነው። እግዚአብሔር ወደ ፊት የሚገጥመንን ያውቃል፤ ወደ ፊት ለሚገጥመን ነገር የሚያዘጋጁን ፈተናዎች አሁን እንዲደርሱብን ይፈቅዳል ‹‹ይፈቅዳል›› የሚለውን ቃል አጽንዖት ሰጥቼ መጠቀሜን ልብ እንድትሉ እፈልጋለሁ። (ሲሙሌተሩ ውስጥ የበረራ ልምምድ ስለሚያደርገው ፓይለት የተናገርሁትን ምሳሌ አስታውሱ)። ብዙ ጊዜ ፈተና አሁን ካለን ዝግጁነት ወይም ኀላፊነት የገዘፈ መስሎ የሚታየን በዚህ ምክንያት ነው። ስለሆነም ዋናው ነገር ወደ ፊት ለሚጠብቀን የላቀ ድል ብርታት እንዲሰጠን እግዚአብሔር አሁን የሚገጥሙንን ተግዳሮቶች የሚጠቀምባቸው መሆኑ ነው።

አሁን ወደ ጀመርሁት ክብደት የማንሣት ስፖርት እንመለስ፡፡ ቀደም ሲል እንዳልሁት ኪፕ 135 ፓውንድ ማንሣት ደረጃ አድርሶኝ ነበር፡፡ ምንም እንኳ፣ ለእኔ ይህ ትልቅ ስኬት ቢሆንም፣ ከዚህ የበለጠ ማንሣት እችል ይሆን? በማለት ራሴን መጠየቄ አልቀረም፡፡ ክብደት የማንሣት ሥልጠናዬን ከመንፈሳዊ ዝግጁነትና ብርታት ጋር ሳነጻጽር ምናልባት 135 ፓውንድ ከማንሣት የበለጠ ብርታት የሚጠይቅ ሥራ እግዚአብሔር ለእኔ አዘጋጅቶ ይሆን ወይ? እላለሁ፡፡

ወደ ስፖርት ማዘወተሪያው ቦታ መሄዴን ቀጠልሁ፡፡ በመጨረሻ 205 ፓውንድ ማንሣት ብችልም፣ ለተወሰኑ ዓመቶች ከዚያ ንቅንቅ አላልሁም ነበር፡፡ በዚያው ሰሞን ካሊፎርንያ ውስጥ እያገለገልሁ እያለ እዚያ የነበሩ አንዳንድ ወዳጆቼ፣ ‹‹ጆን አንተ'ኮ 225 ፓውንድ አንሥተህ አታውቅም፤ ታውቃለህ እንዴ?›› አሉኝ፡፡

እኔም፣ ‹‹ከአምስት ዓመት ለበለጠ ጊዜ ብሞክርም ያንን አንሥቼ አላውቅም›› አልሁ፤ ጥቂት ዕፍረት ብጤ እየተሰማኝ፡፡

‹‹ያንን ማድረግ እንድትችል እንረዳሃለን›› አሉኝ፡፡ እውነትም በእነርሱ እገዛ በዚያው ቀን 225 ፓውንድ ማንሣት ማውረድ ቻልሁ፤ በዚህ ስኬት በጣም ነበር የተነቃቃሁት!

ይህ ከሆነ ጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ አዲስ ሰው ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል የተሰኘውን አገልግሎታችንን ተቀለቀለ፡፡ ይህ ሰው ክብደት የማንሣት ስፖርት ውስጥ ውድድር የሚያደርግ ሲሆን፣ እኔና እርሱ አብረን መሥራት ጀመርን፡፡ በዚህ ሰው እርዳታ 235 ፓውንድ ማንሣት ችዬ ነበር፤ እንዲያውም አንድ ጊዜ 245 ማንሣቴንም አስታውሳለሁ፡፡ ግን ከዚያ የበለጠ ማንሣትስ እችል ይሆን?

ከአንድ ዓመት በኋላ ዲትሮይት አንድ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሰብኬ ነበር፡፡ እሑድ ከአገልግሎት በኋላ ፓስተሩ፣ ‹‹ጆን፣ አንድ በጣም የታወቀ ክብደት የማንሣት አሠልጣኝ ሰው አለ፤ ወደ ቤተ ክርስቲያናችን ይመጣል፤ ነገ ጠዋት ከእርሱ ጋር ቀጠሮ አለኝ አብረኸኝ ለመምጣት ፈቃደኛ ነህ?›› አለኝ፡፡

‹‹አዎን፣ በጣም እንጂ!›› አልሁ ከልቤ በመጓጓት፡፡

በሚቀጥለው ቀን አብረን ሄድን፡፡ አሠልጣኙም፣ ‹‹እስከ ዛሬ ድረስ ያነሣኸው 245 ብቻ ነው አይደል?›› አለኝ፡፡
‹‹አዎን፣ ግን ያ የሆነው አንዴ ብቻ ነው፡፡››
‹‹ዛሬ ግን ከዚያ የበለጠ እናደርጋለን፡፡››

ሰውየ፣ በጣም ሞኝ መሆን አለብህ፤ በፍጹም እንደዚያ ሊሆን አይችልም! በማለት አሰብሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከተወሰነ ሥልጠናና ልምምድ በኋላ በማይታመን ሁኔታ እስከ 265 ፓውንድ ድረስ ማንሣት እንድችል አደረገኝ፡፡

በጣም ነበር የተገረምሁት፡፡ እኔና አብረውኝ የነበሩ ሰዎች ወደ ክሎራዶ ተመለስን፤ ነገር ግን ይህ አሠልጣኝ በየሳምንቱ በኢሜል ሥልጠና ይሰጠን ነበር፡፡ በጣም በርትተን ነበር የምንሠራው፤ በሚቀጥለው ዓመት ወደዚያው ዲትሮይት ወዳለው ቤተ ክርስቲያን ተመለስሁ፡፡ በዚህ ጊዜ 42 ዓመት ሆኖኝ ነበር፡፡

በዚያ እሑድ ስለ መንፈስ ቅዱስ አስገራሚ ባሕርያት ነበር የሰበክሁት፡፡ ሰኞ ቀን ሁላችንም ወደ ስፖርት ማዘውተሪያው ቦታ ሄድን፡፡ አሠልጣኙ፣ ‹‹ጆን፣ ትናንት ሌሊት 300 ፓውንድ ስታነሣ በሕልሜ አይቻለሁ›› አለኝ፡፡

‹‹በፍጹም፣ የማይታሰብ ነው!›› አልሁት፡፡ ምናልባትም በልቤ – የፈለግኸውን ማለት ትችላለህ፤ እኔ ግን እንደዚያ ያለ ሕልም አላለምሁም! ሳልል አልቀረሁም፡፡

‹‹ጆን፣ ትናንትና ስለ መንፈስ ቅዱስ ኃይል ሰብከህ ነበር፡፡ ጌታ ሕልሙን የሰጠኝ ትናንት ሌሊት ነበር! ይልቅስ፣ አሁን አግዳሚ ላይ በጀርባህ ተኛ፤ ያልሁህን አሁን እናደርጋለን!›› አለኝ፡፡

ስለዚህ ሰውነታችንን ከሚሟቅን በኋላ ዘንጉ ላይ ከባድ ብረቶች ተደረጉ፤ እንደ ምንም ጥርሴን ነክሼ 325 ፓውንድ አነሣሁ!
በጣም ነበር የደነቀኝ፤ የዚያኑ ዕለት ከዲትሮይት አውሮፕላን ማረፊያ ደውየ የሆነውን ለሊዛ ነገርኋት፡፡

በዚያ 325 ፓውንድ ባነሣሁ ቀን ብዙውን ጊዜ 225 ፓውንድ ነበር ደጋግሜ የማነሣው፡፡ ምናልባትም በተደጋጋሚ አሥር ጊዜ

ስላነሣ አልቀረሁም፡፡ ግን ሰባት ዓመት ቀደም ብዬ ጀምሬ ቢሆን ኖሮ ምን አደርግ እንደ ነበር አስቡ፡፡ የ35 ዓመት ሰው እያለሁ ከ95 ፓውንድ ይልቅ ኪጥ 225 ፓውንድ እንዳነሣ አድርጎ ቢሆን ኖሮ፣ ምን ይሆን ነበር? ምናልባት እሞት ነበር! ያን ሁሉ ክብደት የያዘው ዘንግ እላዬ ወድቆ ያደቅቀኝ ነበር! አሁን ያለኝን ብርታት ለማግኘት ለዓመታት ያልተቋረጠ ጥረት ማድረግ ነበረብኝ፡፡ ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ እንደ ተራ ክብደት የምገምተው ከሰባት ዓመት በፊት ቢሆን ኖሮ መጨረሻዬ ይሆን ነበር!

የምናልፍባቸው ፈተናዎች፣ ምናልባትም በተለያዩ ጊዜዎች ለረጅም ጊዜ የምናልፍባቸው ፈተናዎች ወደ ፊት ለሚኖረው የበለጡ ፈተናዎች እንድንዘጋጅ የሚረዱን መንፈሳዊ ብርታት የምናገኝባቸው ሥልጠናዎች ናቸው፡፡ በጌታ እየበረታን ስንሄድ፣ የእግዚአብሔርን መንግሥት በማገልገል ረገድ የበለጠ ዐቅም ይኖረናል፡፡

በጣም የሚያሳዝነው ግን በፍርድ ወንበር ፊት ሲቀርቡ ኢየሱስ እያዘነ፣ ‹‹እናንተ እንድታደርጉ የምፈልገው ሌሎች ብዙ ተጨማሪ ነገሮች ነበሩኝ፤ ይሁን እንጂ፣ ከእነርሱ ጋር የሚመጣውን ተግዳሮት ለማስተናገድ የሚያስችል ዐቅም አልነበራችሁም›› የሚላቸው በጣም ብዙ ሰዎች መኖራቸው ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛ ማስተናገድ ከምንችለው በላይ እንደማይሰጠን እናውቃለን፣ ነገሩን የበለጠ አሳዛኝ የሚያደርገውም ይኸው ነው፡፡ እርሱ ተስፋ ቃል ሰጥቶናል!

ስለሆነም ጥሩ ንጽጽር እንዲሆናችሁ የእኔን ክብደት የማንሣት ታሪክ አስታውሱ፡፡ እናንተ ማንሣት የምትችሉት 135 ፓውንድ መንፈሳዊ ተግዳሮት ከሆነ፣ ምናልባት 185 ፓውንድ የሚሆን ተቃውሞ፣ ስደት፣ ፈተና ወይም መከራ ወደ እናንተ እንዲመጣ እግዚአብሔር አይፈቅድም፤ ምክንያቱም ለዚያ በቂ የሚሆን ጥንካሬ የላችሁም፡፡ ይልቁን፣ ለዚያ ብቁ የሚያደርጋችሁ ሥልጠና ወይም ልምምድ ውስጥ ያገባችኋል፡፡ ምናልባት 155 ፓውንድ ፈተና ወደ እናንተ እንዲመጣ ይፈቅድ ይሆናል (እግዚአብሔር የፈተና ምንጭ አይደለም) ፈተናው የሚመጣው ይበልጥ ሊያዘጋጃችሁ እንጂ፣ ከዐቅማችሁ በላይ ሆኖ

ሊደፈጥጣችሁ አይደለም፡፡

ለምሳሌ አንድ ሰው ስለ እናንተ ሐሜትና ሐሰተኛ ወሬ ያሰራጭ ይሆናል፡፡ ለራሳችሁ ለመከላከልና ለጥቃቱ ምላሽ ለመስጠት በዚያ ሰው ላይ ሐሜት ከማሰራጨት ይልቅ፣ ለእግዚአብሔር ቃል ለመታዘዝ ዝም ትላላችሁ ወይም ያንን ሰው ትባርኩታላችሁ፡፡ ይህ ትልቅ ነገር ነው፤ 155 ፓውንድ የሚመዝን ፈተና ማንሣት ችላችኋል ማለት ነው! አሁን ደግሞ ወደ ቀጣዩ ደረጃ ስትሸጋገሩ 165 ፓውንድ ማንሣት ትችላላችሁ፡፡ በምታልፉባቸው ፈተናዎች ውስጥ ሁሉ ለቃሉ ከታዘዛችሁ፣ 185 ፓውንድ ላይ እስክትደርሱ ድረስ ሥልጠናው ይቀጥላል፡፡ በዚህ ጊዜ በመንግሥቱ ውስጥ ለከፍተኛው ዕቅድ ወይም አዲስ ደረጃ ዝግጁ ትሆናላችሁ፤ እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ያለው ዕቅድ ያ እንዲሆን ነው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቅር በመሰኘት በሚወራባችሁ ሐሜት ከተሰናከላችሁና እዚያ ሰው ላይ የመልስ ምት ከሰነዘራችሁ ምን እንደሚሆን መገመት ትችላላችሁ፤ ጌታ ያዝናል፤ ‹‹እንደ ገና ወደ ኋላ ተመልሳችሁ 145 ፓውንድ የሚመዝን ተግዳሮት አንሡ›› ይላችኋል፡፡ አሁንም ያላችሁት፣ ‹‹ስፖርት ማዘውተሪያው›› ውስጥ ቢሆንም ከዚያ የሚገኘውን ጥቅም ገና በሚገባ አላገኛችሁም፡፡

ሥልጠናው ባላችሁበት ደረጃ ይቀጥላል፡፡ ቀጥሎ 155 ፓውንድ የሚመዝን የገንዘብ ችግር ወደ እናንተ እንዲመጣ ይፈቅዳል፡፡ የእግዚአብሔርን መፍትሔ ከመጠበቅ ይልቅ ወዲያውኑ፣ ‹‹ምንም ችግር የለም፤ ብድር መጠየቂያ ካርዴን እጠቀማለሁ!›› ትላላችሁ እግዚአብሔርም ተጨማሪውን ክብደት ያነሣና፣ ‹‹ወደ 145 ተመለሱ›› ይላችኋል፡፡

ውሎ አድሮ እግዚአብሔር ለዚያ የመንግሥቱ ሥራ ወይም ኀላፊነት የሚያበቃችሁ 185 ፓውንድ ተቃውሞ ወደ ሕይወታችሁ ያመጣል፡፡ በምድረ በዳ ፈተና፣ ክብደት በማንሣቱ ልምምድ ደጋግማችሁ ከወደቃችሁ፣ ለሁኔታው ወይም ለቦታው የሚሆን መንፈሳዊ ጡንቻ ስለሌላችሁ እግዚአብሔር ጥሪ አያደርግላችሁም፡፡

በዚህ ጊዜ ያንን ሥራ ወይም ያንን ኀላፊነት መውጣት የሚችል ሰው መፈለግ ይኖርበታል፡፡

## ታላቅ ሥልጣንና ኃይል

ምድረ በዳ በጣም ጠቃሚ የሆነው ብርታትና ጥንካሬ ስለሚሰጠን ነው፡፡ መጥምቁ ዮሐንስ በመንፈስ የበረታው ምድረ በዳ ውስጥ ነበር፡፡

ኢየሱስ በመንፈስ የበረታው ምድረ በዳ ውስጥ ነበር፡፡

መንፈሳዊ ጡንቻቸው የዳበረው በአዳጋች ሁኔታ ጊዜ፣ እምነታቸው በተፈተነ ጊዜ እንጂ፣ ሁሉም በተስተካከለበት የምቾት ጊዜ አልነበረም፡፡

ያዕቆብ ይህን የምሥራች ይነግረናል... በአዳጋች ሁኔታዎች ውስጥ በምታልፉበት ጊዜ ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ ካስተናገዳችሁ፣ ቀጥሎ እግዚአብሔር ለእናንተ ላለው ነገር በአስደናቂ ሁኔታ ዝግጁና ብርቱ ትሆናላችሁ፡፡

> *የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉአን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም።* (ያዕቆብ 1፥3-4)

ያዕቆብ፣ ‹‹ሥራውን ይፈጽም›› ሲል ይፈጽም የሚለው ዐቅማችንን ወይም ትዕግሥታችንን ነው፡፡ የምድረ በዳ ሕይወትን በተገቢው መንገድ የምናስተናግድ ከሆነ፣ የሚከተለውንም እንድንጠብቅ ያዕቆብ ይነግረናል፤ ‹‹በፈተና የሚጸና ሰው የተባረከ ነው፤ ምክንያቱም ፈተናን ሲቋቋም እግዚአብሔር ለሚወዱት የሚሰጠውን ተስፋ የሕይወትን አክሊል ያገኛል›› (ያዕቆብ 1፥12)፡፡

‹‹አክሊል›› የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሥልጣንን ነው፤ ከሥልጣን ጋር አብሮ ኀይል ይመጣል፡፡ በዲያብሎስ እንዲፈተን ኢየሱስ ወደ ምድ በዳ በሄደ ጊዜ በመታዘዙና ባለ ማወላወሉ በበለጠ

ሥልጣንና ኀይል እንደ ተመለሰ ሁሉ (ሉቃስ 4፥1፤14 ይመ.) እኛም ምድረ በዳ ውስጥ ከምናሳልፈው ወቅት በበለጠ ሥልጣንና ኀይል እንወጣለን፡፡

የእናንተን ባላውቅም በበኩሌ እግዚአብሔር ያዘጋጀልኝን ነገር በአግባቡ ለማከናወን መንፈሳዊ ጡንቻ እንዳለኝ ወይም እንደሌለኝ እርግጠኛ መሆን እፈልጋለሁ፡፡

# 10

# ውሃ በምድረ በዳ ውስጥ

ነገሮችና ሁኔታዎች ሲጠምሙባችሁ በእግዚአብሔር የማታምኑ ከሆነ መጀመሪያውኑም አለመናችሁበትም ነበር ማለት ነው።
- ቻርለስ ኤች ስፐርጂን

<<ከዚህ ውሃ የሚጠጣ እንደ ገና ይጠማል፤ እኔ ከምሰጠው ውሃ የሚጠጣ ግን ከቶ አይጠማም፤ እኔ የምሰጠው ውሃ በውስጡ የሚፈልቅ የዘላለም ሕይወት ውሃ ምንጭ ይሆናል።>>
- ዮሐንስ 4፥13-14



ምድረ በዳ ውስጥ ውሃ የሚገኘው በጣም በጥቂቱ ነው፡፡ እዚያ ውሃ በቀላሉ አይገኝም፤ ቢገኝ እንኳ የሚቀዳው ከጉድጓድ ወይም ከምንጭ ነው፡፡ ምድረ በዳ ደረቅና ውሃ የተጠማ ምድር ነው (መዝሙር 63÷1)፡፡ ስለሆነም ኢየሱስ እንዲህ የሚል ጥሪ ያቀርብልናል፡-

> ‹‹ማንም የተጠማ ቢኖር ወደ እኔ ይምጣና ይጠጣ፤ በእኔ የሚያምን መጽሐፍ እንዳለ የሕይወት ውሃ ምንጭ ከውስጡ ይፈልቃል። … ይህን ያለው ስለ መንፈስ ነበር (ዮሐንስ 7፥37-39)።

ደረቅ ወቅት ውስጥ በነበርሁ ጊዜ በተለያየ ጊዜ ለመጸለይ ሞክሬ እንዳቃተኝ፣ የሚያረካ የሕይወት ውሃ ምንጭ ማግኘትም አስቸጋሪ ሆኖብኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ ከእነዚህ በአንዱ ቀን ጌታን እየፈለግሁ እያለ፣ ምሽቱንና የሚቀጥለውን ቀን ጠዋት በዚያ ለማሳለፍ ድንኳኔን አንድ የመንግሥት አትክልት ቦታ ተከልሁ፡፡ በዚያ ምሽት አጥብቄ ጸለይሁ፤ ከዚያም አነበብሁ፤ የምስጋና መዝሙሮችን መዘመር ጀመርሁ፡፡ እንዲህ በማድረግ ሦስት ሰዓት ያህል አሳለፍሁ፤ ግን ምንም የሆነ ነገር አልነበረም፡፡ አሁንም ሕይወቴ እንደ ደረቀ ነበር፡፡ በጣም ተስፋ ቆርጬ መጨረሻ ላይ ለመተኛት መኝታው ውስጥ ገብቼ እንቅልፍ እስኪወስደኝ እገላበጥ ጀመር፡፡

ጥሩ እንቅልፍ አልተኛሁም፤ በዚያ ሌሊት አጋንንት ደስ ሳይሰኙ እንዳልቀረ አስባለሁ፡፡ መኝታው ላይ ወዲያ ወዲህ ተገላበጥሁ፤ እግዚአብሔር ለምን ራሱን ለእኔ መግለጥ እንዳልፈለገ ጥያቄ አደረብኝ፡፡ በማግሥቱ ጠዋት ወደ ውጭ ወጥቼ በመንፈስ እየጸለይሁ በመንግሥት አትክልት ቦታው እየተመላለስሁ ነበር፤ ያም ሆኖ ሕይወቴ እንደ ደረቀ ነበር፡፡ ለአንድ ሰዓት ተኩል ያህል በዚያው ሁኔታ ቀጠለ፡፡ በመጨረሻም ወደ ላይ ቀና ብዬ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ ምድረ

በዳ ውስጥ ሳልሆን እንዳልቀረ አስባለሁ›› አልሁ፡፡ ስለዚህም ወደ ቤት መሄድና እርሱን መፈለጌን መተው አለብኝ፤ መጀመሪያውኑ እዚህ ደረቅ ቦታ ያመጣኝ እርሱ ነው፤ እርሱ ራሱ ከዚያ እስኪያወጣኝ ድረስ ምንም ለውጥ አይኖርም›› በማለት አሰብሁ፡፡

ይህ የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው! እግዚአብሔር እንዲህ ወዳለው ጊዜ የሚያመጣን ተስፋ ሊያስቆርጠንና እርሱ በሉዓላዊነቱ ያለንበትን ሁኔታ እስኪለውጥ ድረስ ሁሉንም ነገር እርግፍ አድርገን እንድንተው አይደለም፡፡ የእርሱ ዓላማ ምድረ በዳ የውድቀት ሳይሆን፣ የድል ቦታ እንዲሆንልን ነው፡፡ ወዲያውኑ፣ ‹‹ተዋጋ!›› የሚል አንድ ለስለስ ያለ ቃል ሰማሁ፤ ያ አንድ ቃል ለእኔ የሚያስፈልገኝ የእሳትና የሕይወት ፍንጣቂ ሆነ፡፡ ወዲያውኑ፣ ‹‹የእግዚአብሔር ስጦታ በውስጤ ተቀጣጠል፤ የሕይወት ውሃ ወንዝ ሆይ ፍለቅ! አንተ ምንጭ ሆይ፣ ውስጤ ፍለቅ›› ማለት ጀመርሁ፡፡ እስራኤላውያን ምድረ በዳ ውስጥ በነበሩ ጊዜ የሆነውን አስታወስሁ፤

> ከዚያም እግዚአብሔር ለሙሴ ሰዎቹን በአንድነት ሰብስባቸውና ውሃ እሰጣችኋለሁ ወዳለበት ብኤር ወደ ተባለው የውሃ ጉድጓድ ጉዞአቸውን ቀጠሉ። ከዚያም እስራኤል ይህን መዝሙር ዘመረ፣ <<አንተ ምንጭ ሆይ ፍለቅ!>> (ዘኁልቁ 21፥16-17)

ይህን የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ስደጋግም ጸሎቴ የበለጠና የበለጠ ኀይል አገኘ፤ በመንገዱ ላይ ታች እያልሁ ጸለይሁ፤ የጌታን ቃል በታላቅ ብርታትና ግለት ተናገርሁ፡፡ ሁሉም ነገር አዲስ ሆነ፤ እኔም እንደ ሌላ ሰው ሆንሁ! ሓልዎቱ በብርታት ከእኔ ጋር ነበረ፡፡ ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት ከብዶኝ ነበር፤ ድካም ተሰምቶኝ ነበር፤ አሁን ለውጊያ ተነሣሁ፤ በጌታ ቃል ጠላትን ለመግጠም ዝግጁ ሆንሁ!

ይህ የሆነው በሃያ አምስት ደቂቃ ውስጥ ቢሆንም፣ አምስት ደቂቃ ብቻ ነበር የመሰለኝ፡፡ አሁን ታደስሁ፤ ቃሉን ለዓለም ለማድረስም ዝግጁ እንደ ሆንሁ አሰብሁ!

ወደ እርሱ መጥተው በሚጠጡ ሰዎች ልብ ውስጥ የሕይወት

ውሃ ወንዝ ወይም ምንጭ እንደሚፈልቅ ኢየሱስ ይናገራል፡፡ በምድረ በዳ የምንለማመደው የእግዚአብሔርን መንፈስ መፍሰስ (ዝናብ) አይደለም፡፡ በዚህ ደረቅ ቦታ የምናገኘው ጥምን የሚቆርጥ የሕይወት ውሃ በጥልቅ ልባችን ውስጥ ካለው ከእግዚአብሔር ምንጭ ወይም ጉድጓድ የሚቀዳ መሆን አለበት፡፡

ኢየሱስ እየተናገረ ያለው ስለ የጌታ መንፈስ (ዮሐንስ 7፥39) እንደ ነበርና ወንዞቹ (‹‹ወንዝ›› አይደለም) ከአማኙ ልብ ውስጥ የሚፈልቅ መሆኑን ልብ በሉ፡፡

የጌታ መንፈስ ከልባችን እንደ ወንዞች የሚፈልቀው እንዴት ነው? ነቢዩ ኢሳይያስ የመንፈስን አሠራር ባሕርይ ይገልጻል፤ ‹‹የእግዚአብሔር መንፈስ፣ የጥበብና የማስተዋል መንፈስ፣ የምክርና የኀይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ያርፍበታል›› (ኢሳይያስ 11፥2)፡፡

መንፈስ ቅዱስ የጥበብ መንፈስ፣ የማስተዋል መንፈስ፣ የምክር መንፈስ፣ የኀይል መንፈስ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት መንፈስ ተብሏል፡፡ ኢየሱስ መንፈስ እንደ ወንዞች እንደሚሆን ሲናገር፣ የጥበብ ወንዝ፣ የማስተዋል ወንዝ፣ የምክር ወንዝ፣ የኀይል ወንዝ፣ የዕውቀትና እግዚአብሔርን የመፍራት ወንዝ ማለቱ ነበር ማለት ነው፡፡ ስለዚህም ልቤ በእሳት መቀጣጠሉ የሚገርም አልነበረም ማለት ነው፡፡

ቀጥሎ ያሉት ለዚህ ድጋፍ የሚሆኑ እውነቶች ናቸው፡-

- ምሳሌ 18፥4፣ ‹‹ከሰው አፍ የሚወጡ ቃላት ጥልቅ ውሆች ናቸው፤ የጥበብም ምንጭ እንደሚንዶለዶል ፏፏቴ ነው›› ይላል፡፡
- ምሳሌ 16፥22፣ ‹‹ማስተዋልን ገንዘብ ላደረጋት የሕይወት ምንጭ ናት›› ይላል፡፡
- ምሳሌ 20፥5፣ ‹‹የሰው ልብ ሐሳብ እንደ ጥልቅ ውሃ ነው፤ አስተዋይ ሰው ግን ከዚያ ቀድቶ ያወጣዋል›› ይላል፡፡

እነዚህ የውሃ ጉድጓዶች ያሉት አማኙ ልብ ውስጥ ነው፤ ምክንያቱም

መንፈስ የሚያድረው እዚያ በመሆኑ ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከጉድጓዱ ውሃ መቅዳት የሚችለው የጌታን መንገድ የሚያስተውል ሰው ብቻ ነው፡፡ እዚህ ላይ ቁልፉ ቃል፣ ‹‹መቅዳት›› የሚለው ነው፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ የምናገኘው ጥም የሚቆርጥ ውሃ ከልብ የሚቀዳ እንጂ፣ ከመንፈስ ዝናብ የሚወርድ አለመሆኑን በድጋሚ ልብ ማለት በጣም ይጠቅማል፡፡

- ምሳሌ 10፥11፣ ‹‹የጻድቅ አንደበት የሕይወት ምንጭ ናት›› ይላል፡፡
- ምሳሌ 15፥23፣ ‹‹ሰው ተገቢ መልስ በመስጠት ደስታን ያገኛል...›› ይላል፡፡

‹‹እኔም ወደ ቤቴ እሄዳለሁ፤ እርሱን መፈለግ እተዋለሁ፤ መጀመሪያውኑ እዚህ ደረቅ ቦታ ያደረገኝ እርሱ ነው፤ እርሱ ከዚህ ካላወጣኝ ምንም ለውጥ አይኖርም›› በማለት የነበርሁበትን ቦታ ትቼ ሄጄ ቢሆን ኖሮ፣ የነበረኝን የልብ ክብደት እንደያዝሁ ነበር የምሄደው፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ልቤ ውስጥ ያኖረውን ቃል በመናገሬ፣ ከጥልቁ ጉድጓድ የሚያስፈልገውን ጥም የሚቆርጥ ውሃ ሰጠኝ፡፡ ጥልቁ ልቤ ውስጥ የነበረውን የመዳን ኩሬ ከፈትሁ፤ እርካታ የሚሰጠውን ውሃ ቀዳሁ፡፡ ነገሩ ምድረ በዳ መካከል ካለው ቀዝቃዛ ውሃ ምንጭ እንደ መጠጣት ነበር!

እንዲህ ያሉ ደረቅ ወቅቶች ሲመጡ ብዙዎች ተስፋ ይቆርጣሉ፤ እግዚአብሔር ግን፣ ‹‹ወደ ፊት መገሥገሥ ቀጥሉ፤ ወደ ፊት ተራመዱ፤ በፍጹም አታቁሙ!›› ይላል፡፡ የእርሱ ፈቃድ በሕይወታችን እስኪፈጸም ድረስ፣ በፍጹም ተስፋ የማይቆርጥና ወደ ኃላ የማይል ብርቱ ተነሣሽነት ሊኖረን ይገባል፡፡

ድርቀት ሲሰማቸው ብዙዎች መጸለይ ያቆማሉ፤ መጸለይ የሚያቆሙት ከጉድጓዱ ውሃ ስለማያገኙ ነው፤ ከእንግዲህም በፍጹም ማግኘት የማይቻል መስሎ ይታያቸዋል፡፡ እነዚህ ወገኖች በተለያየ ምክንያት ደክመዋል፤ እግዚአብሔር ግን ወደ ፊት ለሚገጥማቸው ውጊያ ጉልበታቸውን ማበርታት ይፈልጋል፡፡

የምንቀዳበት ጉልበት የምናገኘው ከየት ነው? ከደስታ ነው! ኢሳይያስ 12÷3፣ ‹‹ከድነቴ ምንጮች ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ›› ይላል፤ እንዲህ የሆነው፣ ‹‹የእግዚአብሔር ደስታ ኀይላችን›› ስለሆነ ነው (ነህምያ 8÷10)፡፡ ደስታ ብርታት የሚሰጥ መንፈሳዊ ኀይል ነው፡፡

የእግዚአብሔር ደስታ ምንድነው? የእግዚአብሔር ደስታ እርሱ ያለውን ዐይነት ደስታ ማግኘት ማለት እንደሆነ ለዓመታት ሳስብ ነበር፡፡ ያን ደግሞ ለሕይወቴ ተግባራዊ ማድረግ ከባድ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ እርሱ የሚለው እንዲህ አይደለም፡፡ ለመሆኑ፣ ሰዎች፣ ‹‹ምግብ የማብሰል ደስታ›› በማለት ሲናገሩ ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? ምግብ ማብሰል በራሱ ደስታ የለውም፡፡ እንዲህ ሲሉ ምግብ በማብሰል ስለሚገኝ ደስታ መናገራቸው ነው፡፡ ‹‹የእግዚአብሔር ደስታ›› ከእርሱ ጋር ካለን ቀረቤታ የተነሣ የምንለማመደው ደስታ ነው፡፡ እርሱ ደስታ ይሰጠናል፡፡

በጸሎት ተንበርክከን ባለንበት ጊዜ የእርሱ ሓልዎት አልተሰማንም ማለት እርሱ ትቶናል ማለት አይደለም፡፡ ስለሆነም ደስታችን የተመሠረተው የሚሰማን ስሜት ላይ አይደለም፡፡ ደስታችን የተመሠረተው በእርሱ ማንነትና ከእርሱ ጋር ለመገናኘት ያለን መብት ላይ ነው፡፡ ስለሆነም እርሱ ትቶናል ከሚለው ሐሰት ባሻገር፣ ወደ ጥልቁ ምንጭ እየቀረብን መሆኑን እንገነዘባለን!

## የማይደርቁ ጉድጓዶች

አብርሃም በተአምር ያገኘው ልጁ ይስሐቅ አንድ ጊዜ ደረቅ ወቅት ገጥሞት ነበር፡-

> ቀድሞ በአብርሃም ዘመን ከደረሰው ራብ ሌላ በአገሩ ላይ ራብ ሆነ… እግዚአብሔርም ለይስሐቅ ተገልጦ እንዲህ አለው፤ ‹‹እኔ በምነግርህ ምድር ተቀመጥ እንጂ፣ ወደ ግብፅ አትውረድ፤ ለጥቂት ጊዜ እዚሁ አገር ተቀመጥ፤ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ፤ እባርክሃለሁም፡፤›› (ዘፍጥረት 26፥1-3)

እርሱ ባስቀመጠው ስፍራ እንዲቆይ እንጂ፣ ወደ ግብፅ መውረድ እንደሌለበት እግዚአብሔር አጠንክሮ ለይስሐቅ ነገረው፡፡ ደረቅ ቦታ ውስጥ ስንሆን ብዙዎቻችን የምናስበው የመጀመሪያው ነገር፣ ‹‹እንደ ምንም ብዬ ከዚህ ውስጥ መውጣት አለብኝ!›› ማለትን ነው፡፡ በማለዳው ጸሎታችን የእግዚአብሔር ሓልዎት ካልተሰማን በቀኑ ውሎአችን የምናደርጋቸው ነገሮችን በማውጣት በማውረድ አእምሮአችን ወዲያ ወዲህ ይባክናል፡፡ ቶሎ የጸሎት ጊዜያችንን እንጨርስና የምናደርጋቸውን ነገሮች ዝርዝር ቅደም ተከተል ማስያዝ እንጀምራለን፡፡

የምንሄድበት ቤተ ክርስቲያን ለእኛ የደረቀ ከመሰለን፣ መጀመሪያ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ከመጠየቃችን በፊት፣ ጥሩ ጥሩ የምንላቸው ሰባኪዎችና ብዙ ሰዎች ወዳሉበት ቤተ ክርስቲያን እንሄዳለን፡፡

ወይም ደግሞ ማኅበራዊ ሕይወታችን ወይም ሥራችን ደረቅ የሆነብን ከመሰለን፣ በራሳችን ሐሳብ ተነሥተን ኢኮኖሚው እያደገ ወዳለበት ከተማ መሄድ እንፈልጋለን፡፡ ‹‹እዚህ ከቆየሁ እኔም ራሴ መድረቄ ነው፤ እንደዚያ ከሆነ የእግዚአብሔር ዓላማ በሕይወቴ ሲፈጸም አላይም›› እንላለን፡፡

በሀገራችን እንዲህ የሚያስቡ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ፤ ደረቅ ያልሆነ ቦታ ፍለጋ፣ ከአንዱ ቦታ ወደ ሌላው ቦታ፣ ከአንዱ ቤተ ክርስቲያን ወደ ሌላው ቤተ ክርስቲያን፣ ከአንዱ የሥራ መስክ ወደ ሌለው የሥራ መስክ፣ ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላው ከተማ ይንከራተታሉ፡፡ ጉድጓዱን ከመቆፈርና እነርሱ ላሉበት ደረቅ ቦታ የሚያረካ ውሃ ለማግኘት እግዚአብሔር እንዲጠቀምባቸው ከመፍቀድ ይልቅ ምቾትና የተደለደለ ኑሮ ፍለጋ፣ ‹‹ወደ ግብፅ›› ይመለሳሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ያልተረዱት ከእነዚህ ደረቅ ቦታዎች በአብዛኞቹ እርሱ የሰጣቸውን ራእይ እውን የማድረግ ዓላማ እግዚአብሔር ያለው መሆኑን ነው፡፡ ይህ ሁልጊዜ እውነት እንዳልሆነ አውቃለሁ፤ ምክንያቱም እግዚአብሔር አሮጌው ምንጭ እንዲደርቅ ካደረገ በኋላ፣ ወደ አዲስ ቦታ ሊወስደን እኛን

የሚያዘጋጅበትም ጊዜ አለ፡፡ ዋናው ቁልፍ ነገር በእግዚአብሔር መንፈስ መመራት ነው! እግዚአብሔር ዝም ካለ ባለንበት ቦታ ሆነን መዋጋት ይኖርብናል!

ይስሐቅ ለእግዚአብሔር በመታዘዙና ራብ በነበረበት ምድር በመቆየቱ የሆነውን ተመልከቱ፡-

> ይስሐቅ በዚያ ምድር ዘር ዘራ፤ እግዚአብሔርም ባረከለትና በዚያኑ ዓመት መቶ ዕጥፍ አመረተ። ሰውየውም እጅግ ባለጠጋ እስኪሆን ድረስ፣ ሀብት በሀብት ላይ እየተጨመረለት ሄደ። ብዙ የበግና የፍየል መንጋ፣ ብዙ ከብት፣ ብዙ አገልጋዮችም ስለ ነበሩት ፍልስጥኤማውያን ተመቀኙት። ከዚህ የተነሣ ፍልስጥኤማውያን አባቱ አብርሃም በሕይወት በነበረበት ጊዜ የአብርሃም አገልጋዮች የቆፈሩአቸውን የውሃ ጉድጓዶች በሙሉ ዐፈር ሞልተው ደፈኑዋቸው… ይስሐቅም በአባቱ በአብርሃም ጊዜ ተቆፍረው የነበሩትን አባቱ ከሞተ በኋላ ፍልስጥኤማውያን የደፈኑአቸውን የውሃ ጉድጓዶች እንደ ገና እንዲከፈቱ አደረገ፤ አባቱ ቀድሞ ባወጣላቸው ስምም ጠራቸው። (ዘፍጥረት 26፥12-15፣18)

## ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

#10 ደስታ የሚገኝበት ምስጢር

ምድረ በዳ ውስጥ ስንሆን ዐይኖቻችን በቀላሉ አካባቢያችን ባሉ ነገሮች ይጋረዳሉ፡፡ በበኩሌ አንድ የልቤን ትንሽ ምስጢር ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፣ ይህ እኔ በምድረ በዳ በነበርሁ ጊዜ አቁሞኛል ደግሞም አለምልሞኛል፡፡ ይህን ደስታ የሚገኝበት ምስጢር ብየዋለሁ፡፡

በዐይን የሚታይ ብዙ ማራኪ ነገር ሲጠፋ፣ ምንም የሚሆን ነገር የሌለ ሲመስለኝ፣ አብዝቼ ብጸልይ እንኳ ውጤት ማየት ሲሳነኝ፣ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ኢየሱስ ያደረገውን አስባለሁ፡፡ እርሱ እሳቱ ከማይጠፋ፣ የድኚው

> ሽታ ከሚያውድበት ገሃነም እንዳዳነኝ አስታውሳለሁ፡፡ በዚያ ያለው ስቃይ አያባራም፡፡ ገሃነም የተፈጠረው ለዲያብሎስ እንጂ፣ ለእኔ አልነበረም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ዲያብሎስ የሰው ልጆችን በማሳሳት ብዙዎች ከእርሱ ጋር ወደዚያ እንዲመጡ አድርጓል፡፡ ኢየሱስ ግን እኔን ለማዳን የእርሱን ሕይወት ሰጠ፤ እኔን ከዚያ አዳነኝ፡፡
>
> እኔ እንዲህ ሳደርግ፣ ዓይኖቼን እርሱ ላይ ሳሳርፍ፣ ምስጋናን መሠረት ወዳደረገ ዕይታ ስሸጋገር፣ ሕይወትን ከዘላለም አንጻር ማየት ስጀምር፣ በወቅቱ እኔ ያለሁበት ሁኔታ ወይም ስፍራ ይህን ያህል ፋይዳ እንዳሌለው እረዳለሁ፡፡ እኔ ደስታ የማገኝበት ምስጢር ይህ ነው፤ እንዳመሰግን ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ማሰብና ዓይኖቼን ኢየሱስ ላይ ማድረግ፡፡

የዘራው ዘር የሚያድግበትን ውሃ ይስሐቅ ያገኘው ፍልስጥኤማውያን ዘግተውት የነበረውን የአባቱን ጉድጓድ በመቆፈር ነበር፡፡ እንደ ይስሐቅ ሁሉ ልባችን ውስጥ የተዘራው የማይጠፋ ዘር እንዲያድግ የሚያስፈልገው ውሃ ብዙውን ጊዜ መገኘት ያለበት ከተደፈነው ጉድጓድ ነው፡፡ ፍልስጥኤማውያን የዚህ ዓለምና የሥርዐቱ ወገኖች ናቸው፡፡ ብዙውን ጊዜ ከሚገባ በላይ ከዚህ ዓለም ሥርዐት ጋር በጣም ከመቀራረባችን የተነሣ ጉድጓዳችን ይደፈናል፤ ነፍሳችንን ለማጠጣት የሚያስፈልገውን ውሃ ለማግኘት ጉድጓዶቻችን መከፈት አለባቸው፡፡

በዚህ ዘመን የክርስቶስን አካል (ቤተ ክርስቲያን) የወረሩ ባሕላዊ እሴቶች ብዙ ጉድጓዶችን እንደ ደፈኑ እምነቴ ነው፡፡ ጉድጓዶቹን ለመድፈን ጠላት እንዲያሳስታት በመፍቀድ፣ የወራጅ ውሃ ምንጭ መሆን ይገባት የነበረች ቤተ ክርስቲያን ደረቅ ቦታ ሆና ይሆን?

እዚህ ላይ ማንሣት ያለብን ጥያቄ፣ ትኩሱን ውሃ ማመንጨት እንድትችል እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንን ሊመልሳት ይችላልን?

የሚል መሆን አለበት፡፡ መልሱ፡- አዎን፣ በሚገባ ይችላል! የሚል ነው፡፡ ይህን ነቢዩ ኢሳይያስ በጣም በሚማርኩ ቃሎች ገልጦታል፡-

> እግዚአብሔር ሁልጊዜ ይመራሃል፤ ፀሐይ ባቃጠለው ምድር ፍላጐትህን ያሟላል፤ ዐጥንትህን ያበረታል፤ በውሃ እንደረካ የአትክልት ቦታ፣ እንደማያቋርጥም ምንጭ ትሆናለህ። ወገኖችህ የቀድሞ ፍርስራሾችን መልሰው ይሠራሉ፤ የጥንቱንም መሠረት ያቆማሉ፤ አንተም የተናዱ ቅጥሮችን አዳሽ፣ ባለ አውራ መንገድ ከተሞችን ጠጋኝ ትባላለህ። (ኢሳይያስ 58፥11-12)

ምቾት ወዳለበት ምድር በመሄድ ይስሐቅ የራሱን መንገድ ወይም ደስታ እንዳልፈለገ ሁሉ፣ እኛም የራሳችንን መንገድና ደስታ ባለ መፈለግ እግዚአብሔርን ብናከብር በውሃ እንደ ረካ የአትክልት ቦታ፣ ውሃው እንደማያቋርጥ ምንጭ እንሆናለን! የእርሱን ፈቃድ ብናደርግ፣ የእርሱን የሕይወት ውሃ ወደ ተጠሙና ወደ ደረቁ ሰዎች እግዚአብሔር ያመጣል፡፡

እግዚአብሔር ዓለም የደፈናቸውን የውሃ ጉድጓዶች መልሰን እንድንከፍት ይመራናል፡፡ ይህ ትጋት ይጠይቃል፤ ከጥቂት ሰዓቶች፣ ቀኖች፣ ሳምንቶች፣ ወሮች እንዲያውም ዓመታት እንኳ የበለጠ ጊዜ ሊወስድ ይችላል፡፡

## የተነሳሽነት መጥፋት

ምድረ በዳ የተለያዩ አዳጋች ሁኔታዎችን ለመግለጥ ጥቅም ላይ የዋለ ምሳሌያዊ ዘይቤ መሆኑን በዚህ መጽሐፍ ግልጽ እንዳደረግሁ አምናለሁ፡፡ ለሁላችንም የጋራ የሆነ ነገር ቢኖር፣ ማንኛችንም ብንሆን በተለያዩ ጊዜ ደስ የማይል ወቅትና ቦታ ወይም ድርቀት ይገጥመናል፡፡ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ምድረ በዳ ውስጥ የመሆናችን ምልክት ለጥሪያችን የነበረን ስሜትና ተነሳሽነት መጥፋት ወይም ከእግዚአብሔር ጋር ላለን ግንኙነት እንኳ ደንታ ቢስ መሆን ነው፡፡

የወጣቶች ፓስተር በነበርሁበት ዘመን የገጠመኝን ሁለተኛውን

ሁነኛ የምድረ በዳ ሕይወት ልምምድ በአጭሩ ላካፍላችሁ፡፡

በፍሎሪዳ ቤተ ክርስቲያን የነበሩኝ የመጀመሪያዎቹ ዘጠኝ ወሮች በጣም ደስ የሚሉ ነበሩ - አገልግሎቱ እየሰፋ፣ የሰዎችም ቁጥር እያደገ ነበር፡፡ በጣም የተነቃቃሁ፣ ኀይልና ተነሣሽነት የሞላብኝ ሰው እንደ ሆንሁ ነበር ይሰማኝ የነበረው፡፡ ሆኖም፣ በድንገት መስመሩ ተቋረጠ፤ ተነሳሽነቴና ብርታቴ ሁሉ ብን ብሎ ጠፋ፡፡

ቀድሞ አደርግ ከነበረው የበለጠ ጊዜ በጸሎት ባሳልፍም፣ ከነበርሁበት ንቅንቅ አላልሁም፡፡ ያም ብቻ ሳይሆን፣ ለወጣቱ ቡድን የነበረኝ ራእይ እየደበዘዘ ሄደ፡፡ (አሮጌው ወይን ጠጅ ከእኔ ወጥቶ እየፈሰሰ ነበር)፡፡ ብዙ በጸለይሁ መጠን፣ ራእዩም በዚያው ልክ እየራቀኝ የሚሄድ መሰለ፡፡ ከውጭ ሲታይ ምንም የተለወጠ ነገር ባይኖርም፣ በውስጥ ግን ነገሮች እየተለወጡ ነበር፡፡

በዚህ ሁሉ ላይ ተጨምሮ፣ በዚህ ሁሉ መካከል ከዚያ በፊት ባልነበሩ ውጫዊ ፈተናዎች ውስጥ እያለፍን ነበር፡፡ ለመሆኑ ከባዱ ፈተና ምን ነበር? የቅርብ አለቃዬ የነበረው ሰው ከቦታዬ ሊያፈናቅለኝ ነገር እየሠራብኝ ነበር፡፡ የዚህ ሰውየ ልጅ እኛ ቡድን ውስጥ ነበር፤ አንድ ምሽት የወጣቶች አገልግሎት ካበቃ በኋላ ወደ ሚስቴ ይመጣና፣ ‹‹እኅት ሊዛ፣ ወላጆቼ ቤት ውስጥ… እያደረጉ እኔ እንዴት ጆን የሚሰብከውን ዓይነት ሕይወት መኖር እችላለሁ?›› ይላታል፡፡ (ወላጆቹ እያደረጉ የነበረው ጥሩ አልነበረም ከማለት ውጪ፣ ምን እንደ ነበር መናገሩ አስፈላጊ አይደለም)፡፡

ሊዛ በሰማችሁ በጣም ደነገጠች፤ ይሁን እንጂ፣ ማስተዋል በሞላበት ሁኔታ፣ ‹‹አንተ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ ሁን፤ የወላጆችህን ሁኔታ ግን ለእግዚአብሔር ተወው›› በማለት መከረችው፡፡ ከዚያ ቀን ወዲህ የቅርብ አለቃዬ የነበረው ሰው ስሜን ለማጥፋትና እኔን ከዚያ ለማባረር ሴራ መጐንጐን ጀመረ፡፡ በእኔና በዋናው ፓስተር መካከል መግባባት እንዳይኖር አደረገ፡፡ ከፓስተሬ ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት ወይም ንግግር ሳላደርግ አሥራ ስድስት ሳምንቶች ያህል አሳለፍሁ፡፡

ይህ ሰው ሴራ መጎንጎን ከጀመረ ጥቂት ወሮች በኋላ፣ ዋናው ፓስተር እኔን ለማባረር ወሰነ፡፡ የወጣቶች ቡድን ውስጥ አንድ ትልቅ ለውጥ እንደሚኖር በእሑዱ ጠዋት አገልግሎት ተናገረ፡፡ እኔ ሰኞ ለት እንደምባረር የፓስተሩ ሁለት ወንድሞች ነገሩኝ፡፡

በዚህ መሐል ግን እግዚአብሔር ተአምር አደረገ፤ ዋናው ፓስተር ሐሳቡን ለወጠ፡፡ በእሑድ ጠዋት አገልግሎትና ሰኞ ለት ከእኔ ጋር በያዘው ቀጠሮ መሓል አንድ ቦታ ላይ እግዚአብሔር ተናገረው፡፡ በቀጠሮአችን መሠረት ሰኞ ዕለት ስንገናኝ፣ ‹‹ጆን ወደ እኛ የላከህ እግዚአብሔር ነው፤ የምትሄድበት ጊዜ መድረሱን እርሱ እስካልተናገረ ድረስ አንተ ከዚህ የትም መሄድ የለብህም›› አለኝ፡፡

ይህ ከሆነ ስድስት ወር በኋላ፣ የቅርብ አለቃየ ማንነት ተጋለጠ፤ ወዲያውኑ ከቤተ ክርስቲያኑ አገልግሎት ታገደ፡፡ እያደረገ የነበረው ብዙዎቻችን ከምናስበው በላይ በጣም አደገኛ ነበር፡፡

በዚህ ወቅት እኔ ይህን በመሰለና ሌሎች ውጫዊ ውጊያዎች ውስጥ ማለፍ ብቻ ሳይሆን፣ ከዚያ በፊት ገጥመውኝ የማያውቁ አያሌ ውስጣዊ ውጊያዎችም ነበሩብኝ፡፡ ምናልባት እኔ ሳላውቅ ያደረግሁ ኀጢአት ይኖር እንደሁ አሰብሁ፤ የማስታውሳቸውን ሁሉ ተናዘዝሁ፤ ይሁን እንጂ፣ ጥቃቱም ሆነ መንፈሳዊ ድርቀቱ ከእኔ አልተወገደም ነበር፡፡

አንድ ቀን ኀጢአቴ ምን ሊሆን እንደሚችል ለማስታወስ እየሞከርሁ እያለ ጌታ፣ ‹‹ምድረ በዳ ውስጥ ያለኸው ኀጢአት ስላደረግህ አይደለም፤ ፊት ለፊትህ ላለው ለውጥ እያዘጋጀሁህ ነው›› አለኝ፡፡ ይህ ምዕራፍ 5 ላይ ያብራራሁት፣ ‹‹አዲስ ወይን ጠጅ›› መሆኑ ነው፡፡

በዚህ ምድረ በዳ ውስጥ አንድ ዓመት ያህል ካለሳለፍሁ በኋላ፣ ጌታ መጾም እንዳለብኝ ለልቤ ተናገረ፡፡ በዚህ ጾም ውስጥ ጥቂት ቀን እንደ ቆየሁ፤ አንድ ጸሎት ከአፌ ወጣ፤ ልብ ያልሁት አፌ ከተናገረው በኋላ ነበር፡፡ ከጥልቅ ልቤ የወጣው መቃተት፣ አእምሮየ ማሰብ ከሚችለው በላይ ነበር፡፡ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አንድ ሰው እንኳ

በሌለበት ምድረ በዳ ውስጥ ብሆን፣ ወይም ለሚሊዮኖች እየሰበክሁ ቢሆን፣ ግድ የለኝም፤ በሁለቱም ቦታዎች በማደርገው መካከል ምንም ልዩነት አይኖርም፤ በፍጹም ልቤ የአንተን ልብ ሐሳብ መረዳት እፈልጋለሁ!›› በማለት ከልቤ ጮኽሁ፡፡

በድንገት ውስጤ የደውል ዐይነት ድምፅ ሰማሁ፤ እያደረገ የነበረውንም አየሁ! ‹‹እግዚአብሔር ሆይ፣ አንተ እኔ ውስጥ ስታደርግ የነበረው ይህንኑ ነበር፤ አገልግሎት ወይም ሌላ ነገር ሳይሆን፣ አንተ ርስቴና የመጀመሪያ ፍቅሬ መሆንህን ማየት ወደምችልበት ወደዚህ ቦታ አምጥተኸኛል፡፡ ስለዚህ ያ ለውጥ ሲመጣ ጣዖት አላደርገውም፤ የመጀመሪያ ፍቅሬ የሆንኸው አንተን ትቼ አገልግሎትን አልወድም፡፡ ልቤ ከአንተ ጋር ይሆናል›› አልሁ፡፡

ከዚያም እግዚአብሔር ስለ ዳዊት የተናገረውን አስታወስሁ፡-

> ሳኦልንም ከሻረው በኋላ ዳዊትን አነገሠላቸው፤ ስለ እርሱም፣ ‹እንደ ልቤ የሆነና እኔ የምሻውን ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ› ሲል መሰከረለት። (የሐዋርያት ሥራ 13፥22)

ይህን በጣም ጠቃሚ እውነት እንደ ገና ላብራራላችሁ - ንጉሥ ሳኦል በምድረ በዳ ልምምድ ውስጥ አላለፈም፡፡ ንግሥናን በተቀበለ ጊዜ፣ ከነቢዩ ሸሽቶ ዕቃዎች መካከል ሲደበቅ ከውጭ ሲታይ ትሑት ይመስል ነበር፡፡ ጥቂት ተከታታይ ስኬት እያገኘ ሲሄድ ግን ንጹሕ ያልነበረው ነገሩ መውጣት ጀመረ፡፡ ባደረገው ከባድ ውጊያ ድል ተቀዳጅቶ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ያንን ያደረገው በራሱ መንገድ በመሆኑ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ላይ ዐመፀ፡፡ ይህ አልበቃ ብሎት ለራሱ መታሰቢያ ሐውልት አቆመ፡፡ ይህ ወደ ፊት ለሚገለጠው ክፉ ባሕርዩ ገና የመጀመሪውያ ደረጃ ነበር፡፡ የኋላ ኋላም እነዚያ ንስሐ ያላደረገባቸው ክፉ ነገሮቹ አጠፉት፡፡

ውስጣችሁ የተደበቀውን የሚገልጡ ሁለት ሁኔታዎች አሉ፡፡ ቀደም ሲል የተነጋገርነው የሚያነጻ ወይም የሚያጠራ እሳት አንዱ ነው፡፡ ሁለተኛው ስኬት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፣ ምንም እንኳ ስኬት

በዙሪያችሁ ያሉ ሰዎችን መጥፎ ነገር ይፋ ቢያወጣም፣ እናንተ ያንን ላታስተውሉ ትችላላችሁ፡፡ በቀደመው ዘመናቸው ብዙ አገልግሎቶች የሚያጠራውና የሚያነጻው እሳት እንዲነካቸው አልፈለጉም፡፡ ያም ሆኖ ግን፣ ከንጉሥ ሳኦል በተለየ መልኩ ለአገልግሎት ተጠርተዋል፡፡ ውለው አድረው ወደ አገልግሎት ደረጃ ገብተዋል፡፡ በጣም የሚያሳዝነው፣ እነዚህ ወገኖች ተገቢ ዝግጅት አልነበራቸውም፡፡ ስለዚህ ስኬት ንጹሕ ያልሆነ ነገራቸውን ወደ ውጭ ሲያወጣው የኃላ ኃላ፣ ይኸው ስኬት የተቀበሉት ጥሪ ወደሚከሽፍበት ደረጃ አደረሳቸው፡፡

ሳኦል፣ ‹‹አገልግሎት›› ይወድ ነበር፤ ለአገልግሎቱ ሲል ሰው እስከ መግደል እንኳ ርቆ ሄዶ ነበር፡፡ ዳዊት ዙፋንን ሳይሆን፣ የእግዚአብሔርን ልብ የሚፈልግ ሰው ነበር፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ በነበረ ጊዜ ዳዊት እውነተኛ የደስታውን ምንጭ አገኘ፤ ይህ ምንጭ ራሱ እግዚአብሔር እንጂ፣ ሌላ አልነበረም፡፡ ዳዊት ሳኦልን ገድሎ ዙፋን ለመያዝ ሁለት ዕድል ገጥሞት ነበር፤ አብረውት የነበሩ ሰዎች ያንን እንዲያደርግ አበረታትተውት ነበር፡፡ የዳዊት ልብ ፍላጐት እንደ ሳኦል ዐይነት ቢሆን ኖሮ፣ በነቢዩ ሳሙኤል በኩል እግዚአብሔር ለእርሱ ለገባለትን ተስፋ ቃል እውን ለማድረግ ሲል ሰው ይገድል ነበር፡፡

በዚህ ዘመን እግዚአብሔር የገባላቸውን ተስፋ እውን የሚያደርጉ እየመሰላቸው ስም የሚያጠፉ፣ የሚያሙ፣ ወይም የሚዋሹ ብዙ ወንዶችና ሴቶች አሉ - ምንኛ ስላቅ እንደ ሆነ ይታያችሁ! እነዚህ ሰዎች ርስታቸውን ለማግኘት ወይም ከእጃቸው እንዳይወጣ ለመከላከል ማንኛውም ነገር ከማድረግ ወደ ኃላ የማይሉ ናቸው፡፡ እግዚአብሔር ደረጃን፣ ተፅዕኖ ፈጣሪነትን፣ ገንዘብን ወይም ዝናን ሳይሆን የእርሱን ልብ የሚፈልጉ ‹‹ዳዊቶች›› ይፈልጋል፡፡ የአሮጌው ወይን ጠጅ አቁማዳ መለወጥ፣ እኔና እናንተ ውስጥ ወዳለው የእግዚአብሔር ባሕርይ ጠልቆ መግባት ማለት ነው፡፡ የአዲሱን የመንፈስ ወይን ጠጅ ጫና የሚደግፈው የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፡፡ (ሓልዎቱና ቅባቱ)፡፡ ምንጊዜም ቢሆን እውነተኛ ባሕርይ የሚዳብረው መከተል

የምንፈልገውን ጌታ አጥብቆ በመፈለግ ነው፡፡

ምናልባትም፣ ‹‹ታዲያ፣ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?›› በማለት ትጠይቁ ይሆናል፡፡

የምሰጣችሁ መልስ፣ ‹‹የሚያስፈልገው ጊዜ ይህን ያህል ሊያሳስባችሁ አይገባም፤ እናንተ ግን ውሃ እስኪገኝ ድረስ መቆፈር ቀጥሉ›› የሚል ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ መልሱ በአንድ የጸሎት ጊዜ ብቻ ላይመጣ ይችላል፡፡ በሚቀጥለው የጸሎት ጊዜ ያንኑ ማንሣት፣ ምናልባትም ከዚያ በኋላም ብዙ ጊዜ መጸለይ ሊያስፈልግ ይችላል፡፡

ዳላስ እያለሁ ዋናውን ፓስተርና ሚስቱን በመርዳት እያገለገልሁ በነበረ ጊዜ፣ ቤተ ክርስቲያኑ ውስጥ የነበረ ቡድን ረዳት ፓስተር ከነበረ ከአንድ በጣም ከምወደው ጓደኛዬ ጋር በየጠዋቱ አብረን እንጸልይ ነበር፡፡ ጠዋት 1ሰዓት ላይ ወደዚያ ክፍል ገብተን ስንጸልይ ብዙውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሓልዎትና የእኛን ጉዳይ አስመልክቶ ሲንቀሳቀስ ይሰማን ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ግን ሳናውቀው ሥራ የሚጀመርበት ሁለት ሰዓት ተኩል ይሆንና ወደ ቢሮ እንሄዳለን፡፡ ነገራችን መፍትሔ ባለ ማግኘቱ... የሚያረካ ውሃ ባለ መፍለቁ ቅር ይለን ነበር፡፡ የውሃው ጉድጓዶች ገና አልተከፈቱም ነበር!

በማግሥቱ ጠዋት እንመጣና ካቆምንበት ቦታ እንጀምራለን፡፡ ይህ ሁኔታ አንዳንዴ ሁለት ቀን፣ ሌላ ጊዜ ሦስት ቀን ይወስድብን ነበር፤ እንዲያውም አንድ ጊዜ የውሃ ጠብታ ለማግኘት አንድ ሳምንት ያህል ወስዶብን እንደ ነበር አስታውሳለሁ! ይሁን እንጂ፣ ምንጩ በሚነደልበት ጊዜ ሲመጣ ግን የሚያረካውን ውሃ ኀይል እንለማመዳለን፡፡

በተለያዩ አገሮች ወዳሉ አብያተ ክርስቲያናት እየሄድሁ ሳገለግል፣ ጉድጓዶቻቸው እንዲደፈኑ የፈቀዱና በዚያ ሁኔታ ተደላድለው የሚኖሩ ብዙ ክርስቲያኖችን አገኛለሁ፡፡ አስደንጋጩ ነገር፣ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ውስጥ ያሉት ጥቂቶቹ ሳይሆኑ ብዙዎቹ መሆናቸው ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ውስጣቸው ያለውን ሰማያዊውን ስጦታ ቢያቀጣጥሉና እንዲንቀሳቀስ ቢፈቅዱ ኖሮ ምን ይሆን ነበር? የሰዎች ሕይወት ይለወጥ ነበር፤ የተናጋ ቤተ ሰብ ይስተካከል ነበር፤

አብያተ ክርስቲያናት ይለወጡ ነበር፤ የአገራችን ሁኔታ ይስተካከል ነበር!

ብዙ ሰዎች ውስጥ የእግዚአብሔር ስጦታ ያ ገና እንደ ተዳፈነ ነው፡፡ የውሃ ጉድጓዶቹ እንደ ተደፈኑ ቢሆኑም፣ መንፈስ ግን እስኪከፈቱ ድረስ በትዕግሥት ይጠብቃል፡፡

መቆፈር ቀጥሉ! ምድረ በዳ ውስጥ ንጹሕና ትኩስ ውሃ ታገኛላችሁ!

# 11

# የጌታን መንገድ አዘጋጁ

ምንጊዜም ቢሆን ችግር በደስታ አይጠበቅም፤ መልካም አቀባበልም አይደረግለትም። ሳይታሰብ በሕይወታችን መካከል ጣልቃ ቢገባም ሁሌም በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው። ችግርና አዳጋች ሁኔታ ልዕለ ተፈጥሮአዊ የእግዚአብሔር ኀይል የሚገለጥበት መንገድ ነው።

- ቻርለስ ስታንሊ

<<እውነት እላችኋለሁ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ፣ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም።>>

- ዮሐንስ 5፥19



ምድረ በዳ ወይም በረሓ የጌታ መንገድ የሚዘጋጅበት፣ ተራራው ዝቅ የሚልበት፣ ሸለቆው ከፍ የሚልበት ስፍራ ነው፡፡ ነቢዩ ኢሳይያስ በጣም ታዋቂ በሆነው ምንባቡ ይህን እውነት በዚህ አስገራሚ መንገድ ይገልጸዋል፡-

> የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፤ የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ አዘጋጁ፤ ለአምላካችን አውራ ጎዳና በበረሓ አስተካክሉ፡፡ ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፤ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ወጣ ገባው ምድረ በዳ ይስተካከላል፤ ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል፡፡ የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል፤ ሰው ሁሉ በአንድነት ያየዋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና፡፡
>
> ድምፅም፣ <<ጩኸ>> አለኝ፤ እኔም፣ <<ምን ብዬ ልጩኸ? አልሁ፡፡ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው፡፡ ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል፤ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ነፍሶበታልና፤ ሕዝቡ በእርግጥ ሣር ነው፡፡ ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል፡፡>> (ኢሳይያስ 40፥3-8)

ምድረ በዳ ወይም በረሓ ውስጥ ላለነው ሰዎች ይህ በትክክል ምን እያለን ነው?

በክርስቶስ አካል ውስጥ ላለነው ለሁላችንም ጌታ ሥራ ሰጥቶናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያንን ሥራ ከመጀመራችን በፊት ሥጋችን በሚሰቀልበት ምድረ በዳ ውስጥ የፈተና ወይም የሥልጠና ጊዜ ሊኖረን ይገባል፡፡ የእርሱን ድምፅ እስክንሰማና በታዛዥነት ፈቃዱን መፈጸም እንድንችል፣ እርሱ እያደረገ ያለውን መረዳት እንድንችል፣ ጌታን መጠበቅን የምንማረውም እዚያ ነው፡፡

አንዳንድ ግራ የሚያጋቡ አቋራጮችንና ያልጠበቅናቸው የዕረፍት ቆይታዎችን ጨምሮ፣ የምድረ በዳ ጉዞው ከመነሻው እስከ

መድረሻው ያለውን ጠመዝማዛ መንገድ በተመለከተ ጥቂት የግል ልምምዴን ላካፍላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ዳግም የተወለድሁት ፑርዱ ዩኒቨርስቲ ውስጥ የኮሌጅ ተማሪ እያለሁ በ1979 ዓ.ም ነበር፡፡ ከአራት ወር በኃላ በመንፈስ ቅዱስ ተሞላሁ፤ እግዚአብሔርም እርሱን ስለ ማገልገል ሐሳቦችን ወደ ልቤ ማምጣት ጀመረ፡፡ እውነቱን ልንገራችሁ – ወደ አገልግሎት የመግባት ምንም ዐይነት ፍላጎት አልነበረኝም፡፡ በክርስትና ሕይወቴ እያደግሁ እያለ ከገጠሙኝ አገልጋዮች እንደ አንዱ መሆን አልፈልግም፡፡ አባባሌ በሌሎች ላይ መፍረድ እንደነበር አውቃለሁ፤ አኗኗራቸው ለእኔ የሚያጓጓ አልነበረም፤ ብዙዎቹ ጐስቋላ ቤቶች ውስጥ ነበር የሚኖሩት፡፡ የልጆቻቸው ሕይወትም ድህነት ያጠላበት መሆኑ ያስታውቅ ነበር፡፡ በኃላ ግን ግምቴ ትክክል እንዳልነበር ተረድቻለሁ፤ ጥሩ ጥሩ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩና በመልካም ሁኔታ የተያዙ ልጆች ያሉዋቸው በጣም የተማሩ ብዙ አገልጋዮች መኖራቸውን አይቻለሁ! ይሁን እንጂ፣ እንደ አንድ ወጣት አማኝ አንድ ሰው አገልጋይ ለመሆን ያልተለመደ ዐይነት ሕይወት መኖር እንዳለበት ወይም ወደ አፍሪካ ሄዶ ደሳሳ ጐጆ ውስጥ መኖርና ቢያስፈልግ ያለ ጫማ እንኳ መኖር እንዳለበት ነበር የማስበው፡፡

ያደግሁት 3,000 ሰዎች በሚኖሩበት አንድ ትንሽ ከተማ ውስጥ ነበር፡፡ በቅርብ የማውቃቸው አገልጋዮች ጥቂት የካቶሊክ ቄሶችና የአንዲት ትንሽ ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ የነበረ አንድ ፓስተር ብቻ ነበር፡፡ የካቶሊክ ቄሶች ሚስት ስለማያገቡ እንደ እነርሱ መሆን አልፈልግም፡፡ ፓስተሩ የእኔ ዕድሜ ዕኩዮች የሆኑ ሁለት ለየት ያሉ ልጆች ነበሩት፤ ወደ ቤታቸው ስሄድ ውስጡ ምንም ደስ የሚል ነገር አይታይም ነበር፤ ስለዚህም እዚያ ላለመቆየት ምክንያት ፈልጌ ቶሎ ከዚያ እወጣ ነበር! እንግዲህ ከዚህ አንጻር አገልግሎትን ለምን እንዳልፈለግሁ ትረዳላችሁ ብዬ አስባለሁ፡፡ የካቶሊክ ቄስ መሆን አልፈልግም፤ እንደነዚያ ደስ የማይሉ ቤቶች ውስጥ እንደሚኖሩ ልጆች መሆንም አልፈልግም፡፡ ወደ አፍሪካ ሄጄ ደሳሳ ጐጆ ውስጥ

መኖርም አልፈልግም፡፡

በዚያ ዘመን የነበረኝ ዕቅድ ከፑርዱ ዩኒቨርስቲ የሜካኒካል ኢንጂነሪንግ ትምህርቴን ካጠናቀቅሁ በኋላ፣ ወደ ሐርቫርድ ሄጄ ማስትሬት ዲግሪዬን መያዝ ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ኮርፓሬት አሜሪካ የሚባል ካምፓኒ ውስጥ እቀጠርና ዋና ሥራ አስኪያጅ እስክሆን ድረስ አድጋለሁ፤ ብዙ ገንዘብ አገኝና ከዚያ የተወሰነውን ለቤተ ክርስቲያን እሰጣለሁ፡፡ የእኔ ዕቅድ እንዲህ ነበር፤ አገልግሎትን በተመለከተ የእግዚአብሔርን ሐሳብ መቀበል አልፈልግም ነበር፡፡ በመሠረቱ ይህ ዕቅድ መጥፎ እንዳልነበር አውቃለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር ለእኔ ሕይወት የነበረው ዕቅድ እንዲህ እንዲሆን አልነበረም፡፡

ከአራት ወር በኋላ አንድ እሑድ ጠዋት ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የፓስተሩን ስብከት እየሰማሁ እያለ፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ጠንከር ያለ መልእክት ወደ ልቤ አመጣ፤ ‹‹እኔ የጠራሁህ እንድትሰብክ ነው፤ ያንን በተመለከተ ምን ማድረግ አስበሃል?›› አለኝ፡፡

በዚህ ጊዜ በጣም ግልጽ በሆነ ሁኔታ ነበር የሰማሁት፣ ወዲያውኑ፣ ‹‹ጌታ ሆይ፣ አፍሪካ ውስጥ ያለ ጫማ በባዶ እግር መሄድ ቢያስፈልግ፣ ደሳሳ የሣር ጐጆ ውስጥ መኖር ቢያስፈልግ እንኳ፣ ለአንተ እታዘዛለሁ፤ ወንጌልንም እሰብካለሁ!›› የሚል ምላሽ ሰጠሁ፡፡ እግዚአብሔር በትክክል የእኛን ትኩረት የሚያገኝበት የራሱ መንገድ አለው፤ ከዚህ በፊት በነበሩት ወሮች በትናንሽ ጉትጐታዎች ለልቤ ቢናገርም፣ የእኔ ዋናው ትኩረት የሚያስከፍለው ዋጋ ላይ ነበር፡፡ አሁን ግን ምን ማለቴ እንደ ነበር በትክክል ተረዳሁ፤ የቱንም ያህል ትልቅ ዋጋ ቢያስከፍለኝ እንኳ እርሱን ደስ ለማሰኘት ተዘጋጀሁ!

ጌታም ያዘጋጀኝ ጀመር፡፡ ውስጤ ያለው እሳት መቀጣጠል ጀመረ፤ ለትምህርት ቤት ጓደኞቼ ስለ ኢየሱስ አዳኝነት እናገር ነበር፡፡ ብዙዎችም ድነት አገኙ፡፡ ይህ ከሆነ አንድ ዓመት ተኩል በኋላ፣ እዚያው ዩኒቨርስቲ ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጀመርሁ፤ በየካምፓሱ ከነበሩ ተማሪዎች አንዳንዶቹ ይካፈሉ ጀመር፡፡ በየሳምንቱ አዳዲስ ሰዎች ሕይወታቸውን ለክርስቶስ ሰጡ፤ ተፈወሱ፤ በተለያየ

የሕይወት ገጽታዎቻቸው ነጻነትን አገኙ፡፡

ከዚያ በፊት ቅድሚያ እሰጣቸው የነበሩ ነገሮች ቀስ በቀስ ከልቤ መውጣት ጀመሩ፤ በዚያ ጊዜ ወንጌል የመስበክ ፍላጐቴ በጣም እያየለ በመምጣቱ ፑርዱ ዩኒቨርስቲ እየተማርሁ የነበረውን ሜካኒካል ኢንጂነሪንግ አቋርጬ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት ፈለግሁ፡፡ ይህን ያደረግሁት በምን ምክንያት ነበር? እኔ የተጠራሁት ወንጌል እንድሰብክ በመሆኑ ካሊኩለስና ፊዚክስ የማጠናበት ምክንያት ምንድነው? ሰዎች ወደ ገሃነም እየሄዱ ነው፤ ኢየሱስ በቅርቡ ይመለሳል፤ ስለዚህ እኔ በተቻለ መጠን በፍጥነት ወደ አገልግሎት መስክ መግባትና ሰዎችን ወደ እርሱ መመለስ አለብኝ በሚል ሐሳብ ነበር፡፡

አንድ ምሽት አሁን ችላ ያልሁትን ትምህርት የቤት ሥራ እየሠራሁ እያለ፣ ዐይኔን ከኢንጂነሪንጉ መጽሐፍ ላይ አንሥቼ መደርደሪያው ላይ የነበረውን መጽሐፍ ቅዱስ ተመለከትሁ፡፡ በዚያ ቅጽበት ሐሳቤን ለወጥሁ! የዩኒቨርስቲውን መጽሐፍ ወደ ጐን ገፋሁት፡፡ ቁርጥ ውሳኔ አደረግሁ፤ ከእንግዲህ ጊዜ ማባከን የለብኝም! ትምህርቴን አቋርጬ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ መሄድ አለብኝ፡፡

በክርስትና ሕይወቴ እንዳድግ እየረዳኝ የነበረው ሰው ጋ ስልክ ደወልሁ፤ ይህ ሰው ፑርዱ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ምርምር እያደረገ የነበረ ሲሆን፣ የቅርብ ወዳጄም ነበር፡፡ በልበ ሙሉነት፣ ‹‹ከዚህ ለቅቄ መጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት መግባት አለብኝ!›› አልሁት፡፡

ያ ወዳጄም በማስተዋል፣ ‹‹ዛሬ ማታ ለምን የእግር ጉዞ እያደረግን በጉዳዩ ላይ አንጸልይም?›› አለኝ! ያንን በማድረግ ላይ እያለን እግዚአብሔር ተናገረኝ፤ ‹‹እኔ በወሰንሁ ጊዜ ታገለግላለህ… አሁን ግን ትምህርትህን ፈጽም›› አለኝ፡፡

ከጥቂት ጊዜ በኋላ አንድ ቀን፣ እግዚአብሔር ከአንዲት ትንሽ ከተማ የተገኘ ወጣት የዓለምን ሕዝብ እንዲያገለግል እንዴት ይልካል? በማለት እያሰላሰልሁ እያለ፣ በድንገት፣ ‹‹የአገልግሎትህን ጥሪ ያቀደውና የወሰነው ማነው፤ አንተ ወይስ እኔ›› ሲለኝ ሰማሁ፡፡

‹‹አንተ ነህ›› በማለት መለስሁ፡፡
‹‹የወደ ፊቱ አገልግሎትህን በተመለከተ ከአንተ ከራስህ እንኳ የበለጠ እኔ ለአንተ የማስብ አይመስልህም?›› አለኝ ያ ቃል ሙሉ ትኩረቴን ያዘ፡፡

ስለዚህ የኢንጀነሪንግ ዲግሪዬን እስክይዝ ድረስ ተረጋግቼ ማጥናት ጀመርሁ፡፡ ከዚያ ስመረቅ ሮክዌል ኢንተርናሽናል ውስጥ የአሜሪካ ባሕር ኀይል በነበረው ፕሮጀክት በሜካኒካል ኢንጂነርነት ተቀጠርሁ፡፡ እዚያ እየሠራሁ እያለ የአንድ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆንሁ፤ በዓመቱ እኔና ሊዛ ተጋባን፡፡

የቤተ ክርስቲያኑ አባል የሆንሁት ከማግባቴ በፊት ሲሆን፣ አስፈላጊ ሆኖ በተገኘው ቦታ ሁሉ አገለግል ነበር፤ ይህም ከተጋባን በኋላም ቀጥሎ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ አስተናግድ ነበር፤ በእስር ቤት አገልግሎት እሳተፍ ነበር፤ የፓስተሮቹን ልጆች ቴኒስ አስተምር ነበር፤ በተለያዩ ዘርፎች የሚቻለኝን ሁሉ እያደረግሁ ነበር፡፡ ቤተ ክርስቲያኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት ስለ ነበረው በምሽቱ ክፍለ ጊዜ መማር ጀመርሁ፡፡

ከሁለት ዓመት በኋላ የዋናው ፓስተርና የቤተ ሰቡ ረዳት እንድሆን ቤተ ክርስቲያኑ ቀጠረኝ፡፡ እኔ የተጠራሁት ሰባኪ እንድሆን በመሆኑ እዚያ የምቆየው ለአንድ ዓመት ብቻ እንደ ሆነ ለፓስተሩና ለሌሎቹም መሪዎች ተናግሬ ነበር፡፡ በወቅቱ ግን የእኔ ሥራ መኪናቸውን ማጠብና ጋዝ መሙላት፣ የፓስተሩን ጫማ መጥረግ፣ ለተለያየ ሥራ መላላክ፤ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት መውሰድና መመለስ፣ ትንንሽ ልጆቻቸውን ዋና ማስተማር፣ ለአገልግሎት ወደ ቤተ ክርስቲያኑ የሚመጡ ሰዎችን ማስተናገድ፣ ከዚያም በላይ ሌሎች ብዙ ነገሮችን ማከናወን ነበር፡፡ እዚያ አንድ ዓመት ብቻ ሳይሆን፣ አራት ዓመት ተከቤል ቆየሁ፡፡

ለእግዚአብሔር ጥሪ፣ ‹‹እሺ›› የሚል መልስ ከሰጠሁ ሰባት ዓመት አልፎ ነበር፡፡ ኮሌጅ እያለሁ ተማሪዎች ሲድኑ፣ ሲፈወሱና ከተለያየ እስራት ነጻ ሲወጡ፣ ከእንግዲህ ከትንሽ ቀኖች በኋላ የሙሉ

ጊዜ አገልጋይ እንደምሆን አስቤ ነበር፡፡ እግዚአብሔር በእንዲህ ዓይነት ሂደት ውስጥ እንደሚያሳልፈኝ ምንም ያሰብሁት አልነበረም!

ቤተ ክርስቲያኑን እያገለገልሁ በነበረ ዘመን፣ ወደ ሙሉ የስብከት አገልግሎት ለመግባት ሦስት ጊዜ ሞክሬ አልተሳካልኝም ነበር፡፡ ምናልባት እግዚአብሔር እዚያ እንዳገለግለው ይፈልግ ይሆናል በማለት ወደ እስያ ሄጄ ነበር፤ ይህ ሦስተኛ ሙከራዬ ነበር፡፡ ከእስያ ወደ ዳላስ በመመለስ ላይ እያለሁ የዮሐንስን ወንጌል እያነበብሁ ነበር፤ በድንገት አንድ ቃል ልቤ ውስጥ ተተከለ፤ ቃሉ፣ ‹‹ከእግዚአብሔር የተላከ ዮሐንስ የተባለ አንድ ሰው ነበረ›› የሚል ነበር (ዮሐንስ 1፥6)፡፡ ወዲያውኑ እግዚአብሔር፣
‹‹በጆን ቢቨሬ የተላከ ሰው መሆን ነው የምትፈልገው ወይስ በእኔ የተላከ ሰው መሆን?›› ሲለኝ ሰማሁ፡፡
‹‹በአንተ የተላከ ሰው መሆን ነው የምፈልገው፡፡››

ጌታም፣ ‹‹መልካም፣ የተላክኸው በጆን ቢቨሬ ከሆነ፣ የምታገለግለውም በጆን ቢቨሬ ሥልጣን ይሆናል፤ በእኔ ከተላክህ ግን በእኔ ሥልጣን ታገለግላለህ!›› አለኝ፡፡

ከዚህ በኋላ ተረጋግቼ ትኩረቴን ሁሉ እግዚአብሔር እኔን ያኖረበት ቦታ ላይ አደረግሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ቀበጥባጣነቴ እንደ ገና ተመለሰ፡፡ በዚያ ጊዜ የምድረ በዳ ሥልጠናዬ ሂደት ላይ ነበር እንጂ፣ ገና አላበቃም ነበር፡፡

አንድ የአገልግሎት መስክ እስኪከፈት ድረስ፣ ያለፉት ሰባት ዓመታት በከንቱ ያለፉ ነበሩ ማለት ይቻላልን? በፍጹም እንደዚያ ማለት አይቻልም! ወደዚያ ምድረ በዳ የመጣሁት መንፈሳዊ ባሕርይ እንዳዳብር ነበር… በሕይወቴ የእርሱ መንገድ እንዲስተካከል ነበር፡፡ በተጠራሁበት አገልግሎት የሚገባኝን እንድፈጽም በሕይወቴ መብሰል ነበረብኝ፡፡ ከእያንዳንዱ መንፈሳዊ ዕድገት አስቀድሞ ለዚያ ደረጃ ብቁ ለመሆን የዝግጅት ጊዜ እንደሚኖር የኋላ ኋላ ተምሬአለሁ፡፡

## በራሳችሁ ብርታት አታገልግሉ

ዓላማችሁ የቱንም ያህል መልካም ቢሆን፣ የኢየሱስን ስም እየጠራችሁ እንኳ ቢሆን፣ ያለ እግዚአብሔር አንድም ዘላለማዊ እሴት ያለው ነገር ማከናወን አትችሉም! ጌታ ራሱ እንዲህ ብሏል፣ ‹‹እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ፣ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና›› (ዮሐንስ 5፥19)፡፡ እንዴት የሚገርም ቃል ነው! በሥጋ የተገለጠው የእግዚአብሔር ልጅ በራሱ መንገድ አንዳችም ዘላቂ ዋጋ ያለው ነገር ማድረግ እንደማይችል ተናግሮአል፡፡ ይህን ስል ምን ማለቴ እንደ ሆነ ጥቂት ምሳሌዎች አካፍላችኋለሁ፡-

ኢየሱስ በቢታንያ ከተማ የነበሩትን አልዓዛር፣ ማርታና ማርያም የተባሉትን ሁለት እኅቶቹን ይወዳቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን አልዓዛር ታመመ፤ ቀጥሎ የሆነውን ተመልከቱ፤

> እኅትማማቾቹም፣ <<ጌታ ሆይ፣ የምትወደው ሰው ታሞአል>> ብለው መልእክት ላኩበት። ኢየሱስ ይህን በሰማ ጊዜ፣ <<ይህ ሕመም የእግዚአብሔር ልጅ በእርሱ ይከብር ዘንድ ለእግዚአብሔር ክብር ነው እንጂ፣ ለሞት የሚያደርስ አይደለም>> አለ። ኢየሱስም ማርታን፣ እኅቷንና አልዓዛርን ይወዳቸው ነበር። ሆኖም አልዓዛር መታመሙን በሰማ ጊዜ በነበረበት ስፍራ ሁለት ቀን ቈየ። (ዮሐንስ 11፥3-6)

ምንም እንኳ፣ ኢየሱስ መሲሕ ቢሆንም፣ የቅርብ ወዳጆች ነበሩት፡፡ አልዓዛርን ይወደውና ከቤተ ሰቡም ጋር ጊዜ ያሳልፍ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ፣ የወዳጁን መታመም ከሰማ በኋላ ለሁለት ቀን ኢየሱስ ምንም አለማድረጉን እንመለከታለን፡፡ ወዲያውኑ ወደ ቢታንያ ያልሄደው ለምንድነው? ምክንያቱ ከአባቱ ትእዛዝ ስላልተቀበለ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ እንዲሄድ እስኪነግረው ድረስ በመታዘዝ በነበረበት ቦታ ቈየ፤ ከዚያ ኢየሱስ ሄደ፡፡

አልዓዛር ከቅርብ ወዳጆቹ አንዱ ቢሆን ኖሮ፣ ምሪት እንዲሰጠኝ

መንፈስን ለመጠየቅ እንኳ ሳላስብ፣ ወዲያውኑ መኪናዬን ወደ እርሱ ቤት እየነዳሁ ሄጄ፣ እጄን እጭንበት እንደ ነበር ጌታ በአንድ ወቅት ተናግሮኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ በጣም የሚያሳዝነው ብዙዎቻችን የዚህ ዓይነት ዝንባሌ ነው ያለን፡፡ እግዚአብሔር ሁሌም ከእኛ ጋር በመሆኑ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙን የእርሱን ምሪት መጠየቅ እንዳለብን አናስብም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ቆም ማለትና ለመንፈስ ምሪት ንቁ መሆን አለብን፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልገውን ያውቃል፤ ጉዳዩን በተመለከተ የእርሱን ምሪት ወይም የእርሱን ፈቃድ ብንጠብቅ እርሱ ማድረግ የሚገባንን ይነግረናል፡፡

ምንም እንኳ የመንፈስ ቅዱስ ምሪት ባይኖረንም፣ እጆቻችንን የታመመ ሰው ላይ ብንጭን እግዚአብሔር ወዲያውኑ የመፈወስ ግዴታ እንዳለበት እናስብ ይሆናል፡፡ ይህ እውነት ቢሆን ኖሮ፣ ወደ ሆስፒታሎች እየሄድን ባዶ እናደርጋቸው ነበር!

አንዳንድ ቦታ ኢየሱስ፣ ‹‹ሁሉንም ፈወሳቸው›› በማለት መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል፤ ይሁን እንጂ፣ ሁሌ እንደዚያ አይሆንም፡፡ ኢየሱስ በቤተ ሳይዳ የነበረውን ለሰላሣ ስምንት ዓመት ሽባ የነበረውን ሰው ብቻ ቢፈውስም፣ እዚያ የነበሩትን ዐይነ ስውሮች፣ አንካሶችና ሽባዎች ጨምሮ በሽተኞችን ሁሉ ያልፈወሰው ለምንድነው (ዮሐንስ 5)? ምናልባት ሌሎችንም እንዲፈውስ የእግዚአብሔር መንፈስ ስላልመራው ይሆን?

ሌላ ጊዜ ደግሞ፣ ሰዎች በየቀኑ እያመጡ ቤተ መቅደሱ ደጃፍ የሚያኖሩት ከእናቱ ማሕፀን ጀምሮ ሽባ የነበረ አንድ ሰው ነበር፡፡ ኢየሱስ ወደ ቤተ መቅደስ ሲገባ ብዙ ጊዜ ሳያልፈው እንዳልቀረ ግልጽ ነው፤ ታዲያ፣ ኢየሱስ ያልፈወሰው ለምንድነው? እግዚአብሔር አባቱ ያንን እንዲያደርግ ስላልነገረው ነው፡፡

ኢየሱስ ወደ ሰማይ ካረገ በኋላ ጴጥሮስና ዮሐንስ ወደ ቤተ መቅደስ እየሄዱ እያለ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ይህንኑ ሰው ፈወሱት፤ ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ መነቃቃት (ሪቫይቫል) ሆነ (የሐዋርያት ሥራ 3)፡፡

ኢየሱስ እያገለገለ በነበረ ጊዜ ሁሌም አንድ ዐይነት አሠራር አልነበረም የሚከተለው፤ አንዳንዶቹን ምራቅ ቀባ፣ ሌሎች ላይ እጁን ጫነ፣ ሌሎች ላይ እንዲሁ ቃል ብቻ ተናገረ፡፡ ሌላ ጊዜ ጭቃ አላቁጦ የዐይነ ስውሩን ዐይን ቀባ፡፡ ወደ ካህናት እንዲሄድ የነገረውም ሰው ነበር – ዝርዝሩ ብዙ ነው፡፡ እንዲህ ያሉ የተለያዩ አሠራሮች ሊኖሩ የቻሉት ኢየሱስ ያደርግ የነበረው አባቱ ሲያደርግ ያየውን ብቻ በመሆኑ ነው! እያንዳንዱ ሰው የሚፈወስበትን ትክክለኛ ጊዜና በምን መንገድ መፈወስ እንዳለበት እግዚአብሔር ያውቃል፡፡

እግዚአብሔር አገልጋዮቹ እንዲያደርጉ የሚፈልገው ይህን ነው… እኛ የምናስበውንና እንዲሆን የምንፈልገውን ሳይሆን፣ ኢየሱስ ሲያደርግ ያየነውን እንድናደርግና የእርሱን ምሪት መረዳት እንድንችል ይፈልጋል፡፡ ዮሐንስ 20፥21 ላይ ኢየሱስ፣ ‹‹አብ እኔን እንደ ላከኝ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ›› ይላል፡፡ ከአባቱ ምሪት ውጪ ኢየሱስ ምንም አያደርግም ነበር፡፡ በተመሳሳይ መንገድ እኛም የኢየሱስን ምሳሌ መከተል አለብን፡፡ በመንፈስ ቅዱስ በመመራት፣ እርሱ ሲመራን ብቻ በመንቀሳቀስ፣ እርሱን መምሰል ይኖርብናል፡፡ ይህ ደግሞ የሥጋችን ለእግዚአብሔር መንፈስ – ለክርስቶስ መንፈስ መገዛትን ይጠይቃል፡፡ በመንፈስ የሚመራ ሕይወትን በተመለከተ ትክክለኛው የሥልጠና ቦታ ምድረ በዳ ነው፡፡ የጌታ መንገድ የሚስተካከለው እንዲህ ዐይነት ተግዳሮት በሚያጋጥምበት ሁኔታ ነው፡፡

አርባ ዓመት በምድረ በዳ ካሠለጠነው በኋላ እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፡-

> <<በል እንግዲህ ና! ሕዝቤን የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ ምድር እንድታወጣቸው ወደ ፈርዖን እልክሃለሁ። ሙሴ እግዚአብሔርን፣ <ወደ ፈርዖን የምሄድና የእስራኤልን ልጆች ከግብፅ የሚወጣ እኔ ማን ነኝ?> አለው። እግዚአብሔርም፣ እኔ ከአንተ ጋር እሆናለሁ…>> አለው።>> (ዘፀአት 3፥10-12)

ይህን ማንም ሳይልካቸው ራሳቸውን ከላኩ ሰዎች ጋር በማነጻጸር እንመልከት፣

> <<እኔ እነዚህን ነቢያት አልላክኋቸውም፤ እነርሱ ግን ለራሳቸው መልእክታቸውን ይዘው ሮጡ፤ ሳልናገራቸውም ትንቢት ተናገሩ… እነሆ ሐሰተኛ ሕልም ተመርኩዘው ትንቢት የሚናገሩትን ነቢያት እቃወማለሁ ይላል እግዚአብሔር፤ እኔ ሳልልካቸው ወይም ሳልሾማቸው ደፍረው ውሸት ይናገራሉ፤ ሕዝቤንም ያስታሉ፤ ለዚህም ሕዝብ አንዳች አይረቡትም> ይላል እግዚአብሔር።>> (ኤርምያስ 23፥21፣32)

ብዙዎቻችን ከጌታ እንዲህ ያለ መልእክት መስማት አንፈልግም፡፡

የአርባ ዓመት ሰው እያለ በመጀመሪያ ነጻ ሊያወጣቸው የሞከረ ጊዜ ሙሴ የእስራኤልን ልጆች መርዳትም ሆነ እነርሱን መጥቀም አልቻለም፤ ምክንያቱም ገና እግዚአብሔር አልላከውም ነበር፡፡ ከፍተኛ ትምህርት፣ የመሪነት ችሎታ፣ ከግብፅ ያገኘው ጥበብ ቢኖረውም፣ ያለ እግዚአብሔር እርዳታና ትክክለኛ ጊዜ፣ እግዚአብሔር እንደ ጠራው ቢያውቅም ሙሴ ያንን መፈጸም አልቻለም ነበር፡፡ የእርሱ ከንቱ ሙከራ አንድ ጨቋኝ ግብፃዊ ከመግደል ውጪ የፈየደው አልነበረም፡፡ ምንም እንኳ ዓላማው ትክክል ቢሆንም፣ ተልዕኮውን ለመፈጸም ያደረገው የመጀመሪያ ሙከራ ከጥቅሙ ጉዳቱ ነበር የበለጠው፡፡ ከአርባ ዓመት የበረሓ ሥልጠና በኃላ ግን፣ እግዚአብሔር የነገረውን ብቻ እንጂ የራሱን ፈቃድ የማያደርግ አዲስ ሙሴ ተገኘ፡፡ አሁን በሙሴ መሪነት፣ እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ አንድ ግዙፍ ሰራዊት ሙሉ በሙሉ ቀይ ባሕር ውስጥ ሰጠመ፡፡ በእግዚአብሔርና በእኛ ብርታት መካከል ያለው ልዩነት ይህን ይመስላል – አንድ ወታደርን ሙሉ ሰራዊት በማነጻጸር ልዩነት ማየት ይቻላል፡፡

መጥምቁ ዮሐንስ ሰላሣ ዓመት ሙሉ የሠለጠነው ለስድስት ወር አገልግሎት ብቻ ነበር፤ ያም ሆኖ ግን፣ ከሴት ከተወለዱት ታላቁ

ነቢይ እርሱ እንደ ነበር ኢየሱስ ተናግሮለታል፡፡

አሁን ልዩነቱን አይታችኋል! በራሱ ብርታት ስድሳ ዓመት ከሚያገለግል ሰው ይልቅ፣ እርሱ በላከው ወንድ ወይም ሴት እግዚአብሔር በስድስት ወር ውስጥ የበለጠ ነገር ማድረግ ይችላል፡፡

‹‹እውነት እላችኋለሁ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ፣ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋል›› በማለት ኢየሱስ የተናገረው ይህን ነው የሚያመለክተው (ዮሐንስ 5፥19)፡፡

እንደ ገና ኢሳይያስ የተናገረውን እንመልከት፡-

የዐዋጅ ነጋሪ ድምፅ እንዲህ ይላል፣
የእግዚአብሔርን መንገድ በምድረ በዳ አዘጋጁ፤ ለአምላካችን አውራ ጐዳና በበረሓ አስተካክሉ። ሸለቆው ሁሉ ከፍ ይላል፤ ተራራውና ኮረብታው ሁሉ ዝቅ ይላል፤ ወጣ ገባው ምድር ይስተካከላል፤ ስርጓጉጡም ሜዳ ይሆናል። የእግዚአብሔርም ክብር ይገለጣል፤ ሰው ሁሉ በአንድነት ያየዋል፤ የእግዚአብሔር አፍ ይህን ተናግሮአልና።>

ድምፅም፣ <<ጩኽ>> አለኝ፤ እኔም፣ <<ምን ብዬ ልጩኽ? አልሁ።

<<ሰው ሁሉ እንደ ሣር ነው፤ ክብሩም ሁሉ እንደ ሜዳ አበባ ነው። ሣሩ ይደርቃል፤ አበባውም ይረግፋል፤ የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንቶ ይኖራል።>> (ኢሳይያስ 40፥3-8)

የጌታ መንገድ የሚያስተካክለው በበረሓ (በምድረ በዳ) መሆኑን እግዚአብሔር ይናገራል፡፡ የጌታ መንገድ የሰው ብርታት አይደለም፡፡ የሰው ትዕቢት ዝቅ እንደሚል፣ እርሱን የሚጠባበቁ ትሑታን ግን ከፍ እንደሚሉ፣ ወጣ ገባው (ኢታላዩ፣ ትክክል ያልሆነውና ቅንነት የጐደለው) ቦታ እንደሚስተካከል፣ ስርጓጉጡም (ፍቅር የሌለው፣ ደፋርና ወራዳው) እንደሚለሰልስ ይናገራል፡፡

እንደ አንድ በቅርቡ ኢየሱስን መከተል እንደ ጀመረ የኮሌጅ

ተማሪ ብዙ በረከቶች ተቀብዬ ነበር፤ ሌሎችን በማገልገልም፣ ‹‹ስኬት›› አግኝቼ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ በሕይወቴ ዝቅ ማለት የነበረባቸው ተራሮች፣ መለስለስና መስተካከል የነበረባቸው ሻካራና ወጣ ገባ ቦታዎች ነበሩ፡፡ እንዲህ ያሉት ጉድለቶች እንዲለሰልሱ ጥቂት ጊዜ በምድረ በዳ ማሳለፍ እንደሚያስፈልገኝ እግዚአብሔር ያውቅ ነበር፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ እግዚአብሔር በሕይወታችን የራሱ መንገድ እንዲኖረው መፍቀድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በዳላስ ፓስተሬን እያገለገልሁ በነበረ ዘመን፣ አንድ ቀን እግዚአብሔር፣ ‹‹ጆን፣ ዐይኖችህን የነገው ስብከት አገልግሎትህ ላይ ብቻ በማድረግ፣ ዛሬ በሕይወትህ መሥራት የምፈልገው አያምልጥህ›› በማለት ተናግሮኝ ነበር፡፡ እውነቱን ለመናገር ለመስበክ በጣም እፈልግ ስለ ነበር፣ እንዲህ ያለውን የሕይወት ገጽታዬን እንደ ጊዜ ማባከን ነበር የምመለከተው፡፡

እናንተ ግን፣ እንዲህ ያለው ወጥመድ ውስጥ መውደቅ የለባችሁም! እግዚአብሔር ጊዜ እንደማያባክን ዕወቁ! ጊዜን የሚዋጅ እርሱ ነው! ዛሬ ያላችሁበት ቦታ፣ ነገ ለምትሄዱበት እጅግ በጣም ወሳኝ መሆኑን ልብ በሉ፡፡ ይህ የምትሠለጥኑበት ጊዜ ነው፡፡ ከተቀበላችሁት ተስፋ ቃል፣ ወደ ከፍታ – ማለትም ወደ ፍጻሜው የምትሸጋገሩበት ሂደት ነው፡፡ ነገር ሁሉ ተያይዞ እንዲሠራ ማድረግን ለእርሱ ተውላት፤ …እናንተ ከእርሱ ጋር ተንቀሳቀሱ! እርሱ እግዚአብሔር ነው፤ ጀማሪውና ፈጻሚው እርሱ ነው፡፡ እኛ ማድረግ ያለብን በእርሱ መተማመንና ዛሬ ለሚያሳየን መታዘዝ ብቻ ነው!

እግዚአብሔር እኔን ወደ ስብከት አገልግሎቴ የሚያመጣበት በመሰለኝ ነገር ሁሉ ከታላቅ ትዕግሥቱ የተነሣ እርሱ፣ ‹‹ጆን አሁንም ሌላ ስሕተት ውስጥ እየገባህ ነው!›› ይለኛል፡፡ ይህ ሙሉ በሙሉ እውነት ነው፤ ምክንያቱም ወደ አገልግሎት ያመጣኝ እኔ በጠበቅሁት ሳይሆን፣ በፍጹም ባልጠበቅሁት መንገድ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ወደ እርካታ ቦታ (እኛ ወደምንፈልገው ሳይሆን) የሚያመጣን፣ አሁን ባለንበት ሁኔታ በሙላት እንድንኖር ነው፡፡

## ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 11 ሁሌም ተዘጋጅተህ ኑር

ምንም እንኳ እኔ ያንን ባልመክራችሁም፣ የምድረ በዳ ቆይታችሁ ረጅም ጊዜ ሲወስድና ለዘላለም የሚዘልቅ ሲመስላችሁ ትጥቃችሁን ፈትታችሁ እዚያ ለመኖር ትወስኑ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጂ፣ እግዚአብሔር መንቀሳቀስ ከፈለገ በቅጽበት ያደርገዋል – ይህን ስነግራችሁ እመኑኝ፡፡ ዮሴፍን ተመልከቱ፤ ዕድሜ ዘመኑን ሁሉ እስር ቤት ውስጥ የሚያሳልፍ ይመስል ነበር፤ ሆኖም፣ ያለ ምንም ማስጠንቀቂያ በአንድ ቀን! እግዚአብሔር የሰጠው ሕልም ወደሚፈጸምበት ደረጃ ደረሰ! አዎን፣ በአንድ ቀን!

ምድረ በዳ ውስጥ በነበርሁ ጊዜ አርባ ዓመት ሙሉ እዚያ እንዳሳለፍሁ ነበር የተሰማኝ፡፡ ከዚያም ጊዜው ሲደርስ የነበርሁበትን ቦታ ትቼ ከአገር አገር እየተዘዋወርሁ እንድሰብክ በድንገት ጌታ ተናገረኝ፡፡ ብዙ ጊዜ ለውጥ ወዲያውኑ አይመጣም፤ እንደዚያ ሆኖ ከተገኘ ግን ፍጥነቱ የዐውሎ ነፋስ ያህል ሊሆን ይችላል፡፡ እኔም ወደ ቀጣዩ የጥሪዬ ወቅት ለመንቀሳቀስ ዝግጁ ነበርሁ፡፡ ትጥቄም እንደ ተዘጋጀ ነበር፡፡

## ነገሮችን በእግዚአብሔር መንገድ አድርጉ

እግዚአብሔር ለአንድ ሰው ሥልጣንና ኀይል ከሰጠ፣ ለጌታ መንፈስ አለመታዘዙ የተቀበለውን ሥልጣንና ኀይል ታላቅነት ያህል የሚጠበቀውም ፍርድ ከባድ ይሆናል፡፡ ነገሮችን እያደረገ የነበረው በራሱ መንገድ ቢሆንም፣ የአርባ ዓመት ሰው እያለ አልነበረም እግዚአብሔር ሙሴ ላይ የፈረደው፤ ምክንያቱም በዚያ ወቅት

የእግዚአብሔርን ሥልጣንና ኀይል ገና አልተቀበለም ነበር፡፡ በኋላ ግን በዚህ አልዘለቀም፡፡ ምድረ በዳ ውስጥ እያሉ የነበሩበትን ቦታ በተመለከተ ሕዝቡ ከሙሴ ጋር ተከራከሩ፤ በእርሱም ላይ አጉረመረሙ፡፡ ተጠምተው ስለ ነበር የሚጠጡት ውሃ ፈለጉ፤ ስለዚህም ምን ማድረግ እንዳለበት እግዚአብሔር ለሙሴ ነገረው፡-

> እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ አለው፤ በትሪቱን ውሰድ፤ አንተና ወንድምህ አሮን ማኅበሩን በአንድነት ሰብስቡ፤ እነርሱም እያዩ ዐለቱን ተናገሩት። ዐለቱም ውሃ ያወጣል። አንተም ለማኅበረ ሰቡ ከዐለቱ ውሃ ታወጣላቸዋለህ፤ እነርሱና ከብቶቻቸውም ይጠጣሉ።›› (ዘኁልቁ 20፥7-8)

ለዐለቱ እንዲናገርና ዐለቱም ውሃ እንደሚሰጥ ነበር እግዚአብሔር ለሙሴ የነገረው፡፡ ሙሴ ግን ያደረገውን አንብቡ፡-

> ከዚያም ሙሴ እጁን ዘርግቶ በበትሩ ዐለቱን ሁለት ጊዜ መታው፤ ውሃውም ተንዶለዶለ፤ ማኅበረ ሰቡና ከብቶቻቸው ጠጡ። ነገር ግን እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን፣ ‹‹በእስራኤላውያን ፊት እኔን ቅዱስ አድርጋችሁ ለማክበር ስላልታመናችሁብኝ ይህን ማኅበረ ሰብ ወደምሰጠው ምድር ይዛችሁ አትገቡም›› አላቸው (ዘኁልቁ 20፥11-12)

እግዚአብሔር ውሃውን የሰጠው እዚያ ለነበሩ በሚሊዮኖች ለሚቆጠሩ ሰዎች እንደ ነበር ልብ በሉ፡፡ ውሃ ከዐለት ሲወጣ ይገርማል! - ለመሆኑ በዚህ በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን እንዲህ ያለ ታላቅ ተአምር ማን ሰምቶ ያውቃል? ምንም እንኳ፣ ከዐለቱ ውሃ ለማውጣት የተሰጠውን መመሪያ ሙሴ በሚገባ ባይከተልም፣ ተአምሩ ግን ሆኖአል፡፡ ለነበሩበት ችግር መፍትሔ እንዲሆን ውሃው የተሰጠው ለሕዝቡ ነበር፤ ሙሴን ለመቅጣት ሲል እግዚአብሔር ለሕዝቡ ውሃ እንዳይወጣ አላደረገም፡፡ ይሁን እንጂ፣ ያስከተለው ውጤት ነበር - ሕዝቡን እየመራ ወደ ተስፋው ምድር እንዳይገባ እግዚአብሔር ሙሴን አገደው፡፡

የእግዚአብሔር ልዕለ ተፈጥሮአዊ ቅባት ለሕዝቡ ችግር መፍትሔ ማስገኘት እንጂ፣ ስጦታውን የተቀበለውን ሰው ገናና ማድረግ እንዳልነበር ይህ ትክክለኛ ምሳሌ ሊሆነን ይችላል! ሙሴ በሕዝቡ ሳይበሳጭ አልቀረም፤ የእንዲህ ያሉ አስቸጋሪ ሰዎች መሪ ስላደረገው በእግዚአብሔርም ሳይበሳጭ አልቀረም፡፡ ቀደም ሲል በጺን ምድረ በዳ እንዳደረገው ሙሴ ዐለቱን መታው (ዘፀአት 17፥1-7)፡፡ ምናልባትም፣ ሙሴ በመሪነት ችሎታው ልበ ሙሉነት ስለ ተሰማው ለእርሱ ትክክል የመሰለውን ሁሉ እግዚአብሔር እንደሚያከብርለት ተሰምቶት ይሆናል፡፡ በድጋሚ ነገርን በራሱ መንገድ አደረገ፤ በዚህ ጊዜ ግን ያስከተው ውጤት በጣም ከባድ ነበር፡፡ ሙሴ በእግዚአብሔር ኀይልና ብርታት እየተመላለሰ ነበር፤ ብርታቱን የሚያገኘውም በእግዚአብሔር በመተማመን ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ሙሴ በሕዝቡ ፊት ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ በመንቀሳቀሱ ፈጣን ፍርድ በራሱ ላይ አመጣ፡፡

ያዕቆብ 3፥1፣ ‹‹ወንድሞቼ ሆይ፣ ከእናንተ ብዙዎች አስተማሪዎች አይሁኑ፤ ምክንያቱም እኛ አስተማሪዎች የሆንን የባሰ ፍርድ እንደምንቀበል ታውቃላችሁ›› የሚለው ከዚህ የተነሣ ነው፡፡ ኀላፊነቱ ወይም ክብሩ ታላቅ የመሆኑን ያህል ፍርዱም እንደዚያው ታላቅ ይሆናል፡፡

ምድረ በዳ፣ አለመታዘዝን ተከትሎ የሚመጣው ፍርድ ሳያገኘን፣ በጌታ ኀይልና ክብር እንድንመላለስ ያዘጋጀናል፡፡ በደረቁ በረሓ ልምምድ ውስጥ ትዕቢት ዝቅ ይላል፤ ትሕትና ከፍ ይላል፡፡ እውነተኛ ትሑት ሰው ኢየሱስ እንዳደረገው ሁሉ፣ ‹‹የጌታ መንፈስ ሲያደርግ ካላየሁ እኔ በራሴ ምንም አላደርግም፤ በራሴ ብርታትና ችሎታ እኔ ምንም አይደለሁም›› ይላል፡፡

በዚህ ዘመን ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ላሉት ብዙዎች እግዚአብሔር የክብሩንና የኀይሉን መገለጥ የያዘባቸው ምናልባት የባሰ ፍርድ እንዳይመጣብን ይሆን? ምድረ በዳ ውስጥ ሥጋን ከመንፈስ የሚያራቁተው ወደ እርሱ እንድንጮኽና ከእርሱ እንድንሰማ ለማድረግ

ሊሆን እንደሚችል አምናለሁ፡፡ በዚያ ሁኔታ ክብሩ ሲገለጥ ነገሮችን በእርሱ መንገድ ብቻ በማድረግ ለእርሱ ስም ክብር እናመጣለን!

የመንፈስን ድምፅ ስሙ፡፡ እርሱ የሰጣችሁን ሥራ እንዴት እንደምታከናውኑ እርሱ ራሱ እንዲያሳያችሁ ጊዜ ስጡ፡፡ ጌታ እያደረገና እየተናገረ ያለውን ተመልከቱ፤ ስሙም፡፡

> በመጠበቂያዬ ላይ እቆማለሁ፤ በምሽጉ ቅጥር ላይ ወጥቼ እቆያለሁ። ምን እንደሚለኝ፣ ለክርክሩም የምሰጠውን መልስ ለማወቅ እጠባበቃለሁ። እግዚአብሔርም እንዲህ ሲል መለሰ፤ <በቀላሉ እንዲነበብ፣ ራእዩን ጻፈው፤ በሰሌዳም ላይ ቅረጸው። ራእዩ የተወሰነለትን ጊዜ ይጠብቃልና ስለ መጨረሻውም ይናገራል፤ እርሱም አይዋሽም፤ የሚዘገይ ቢመስልም ጠብቀው፤ በእርግጥ ይመጣል፤ ከቶም አይዘገይም። እነሆ እርሱ ታብዮአል፤ ምኞቱ ቀና አይደለም፤ ጻድቅ ግን በእምነት ይኖራል።>> (ዕንባቆም 2፥1-4)

ነቢዩ፣ ‹‹እግዚአብሔር የሚለኝን ለመስማት እጠባበቃለሁ›› ይላል፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ከሚናገርበት መንገድ አንዱ ራእይ ነው፡፡ ኢየሱስ አብ ሲያደርግ ያየውን ብቻ እንደሚያደርግ ተናግሮአል፡፡ ዕንባቆም ያየውን እንደሚጽፍና የተወሰነለትን ጊዜ እንደሚጠብቅ ይናገራል፡፡ ትዕቢተኛ የሆነች ነፍስ (ከፍ ከፍ ያለች) ቀና እንዳልሆነች (ያ ማለት እግዚአብሔር የሚለውን በተመለከተ ራእይ ሳይኖረው የጌታን ቃል የማይጠብቅ ሰው) ይናገራል፡፡ ጻድቅ በሌለው ሰው እምነት ሳይሆን፣ በእምነቱ ይኖራል!

እምነት የሚመጣው እግዚአብሔር የሚለውን በመስማትና በመታዘዝ ነው፡፡ እግዚአብሔር የእስራኤልን ልጆች ወደ ምድረ በዳ ያመጣቸው፣ ‹‹ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣው በእያንዳንዱ ቃል እንጂ፣ በእንጀራ ብቻ እንደማይኖር ሊያስተምርህ አስራበህ›› (ዘዳግም 8፥3)፡፡ ‹‹በሚወጣው›› እንጂ፣ ቀድሞ ‹‹በወጣው›› አለማለቱን ልብ በሉ፡፡

‹‹የሚናገረውን እርሱን እምቢ እንዳትሉ ተጠንቀቁ፡፡ እነዚያ

ከምድር ሆኖ ሲያስጠነቅቃቸው የነበረውን እምቢ ባሉ ጊዜ ካላመለጡ፣ እኛ ከሰማይ የመጣው ሲያስጠነቅቀን ከእርሱ ብንርቅ እንዴት ልናመልጥ እንችላለን›› የሚል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል (ዕብራውያን 12÷25)፡፡ እርሱ የሚናገረው፤ ምንጊዜም ቢሆን ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋር እንደሚስማማ አትርሱ፡፡

ይሁን እንጂ፣ እናንተ መደረግ አለበት ለምትሉት ድጋፍ የሚሆናችሁን ሐሳብ ለማግኘት መጽሐፍ ቅዱስን መመርመር የእግዚአብሔር መንገድ አይደለም፡፡ እንደዚያ ቢሆን ኖሮ ኢየሱስ፣ ‹‹ሕመምተኞችን እንድፈውስ ተቀብቻለሁ፤ ስለዚህ ከዚህ በፊት እንዳደረግሁት አሁኑኑ ተነሥቼ እጄን አልዓዛር ላይ እጭናለሁ›› ይል ነበር፡፡ ይልቁን ለመንቀሳቀስ የእግዚአብሔርን መንፈስ ጠበቀ፤ ከዚያም ተንቀሳቀሰ፡፡

የእርሱን ምሪትና ብርታት ሳንቀበል ለእርሱ አንዳች ነገር ለማድረግ መሞከር ከንቱ ልፋት መሆኑን ሊያስተምረን እግዚአብሔር ወደ ምድረ በዳ ያመጣናል፡፡ ሥጋ ዘላለማዊ እሴት ያለው መልካም ነገር ማድረግ እንደማይችል በእውነት ስንማር፣ እግዚአብሔር የሰጠንን ሕልሞችና ዕቅዶች እውን ለማድረግ ዝግጁ እንሆናለን፡፡ ምድረ በዳ የዝግጅት ቦታ ነው - ተስፋው የሚፈጸምበት ሂደት ነው፡፡ ነገሮችን በራሳችን ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ምሪት ለማድረግ የኢየሱስን ምሳሌ እንከተል፡፡

# 12

# ድል በምድረ በዳ ውስጥ

ሐዘኖቻችን እንደ እኛው ሁሉ ሟች ናቸው። የማትሞት ነፍስ እንጂ፣ የማይሞት ሐዘን የለም። ሐዘን ይመጣል፤ እግዚአብሔር ቡሩክ ይሁን፤ ሐዘን ይሄዳል። አየር ውስጥ እንደሚበሩ ወፎች ከራሳችን በላይ ይበርራል። ሆኖም፣ ነፍሳችን ውስጥ መኖሪያውን አያደርግም። ዛሬ መከራ ይደርስብናል፤ ነገ ግን ደስ ይለናል።

- ቻርለስ ኤች . ስፐርጂን

ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፤
ሕግን የሚጠብቅ ግን የተባረከ ነው።

- ምሳሌ 29፥18



ምድረ በዳ የምናልፍበት እንጂ፣ ዘላቂ መኖሪያችን አይደለም! በማስተዋል ከተጠቀምንበት ምድረ በዳ ውስጥ ድል እናገኛለን፣ ድንበሩንም ተሻግረን እንሄዳለን!

ወጣት ፓስተር በነበርሁ ዘመን እያለፍሁ የነበርሁበት የምድረ በዳ ጉዞ ከመጠን ያለፈ ረጅም ስለ መሰለኝ ወኔዬ ሁሉ ተሟጥጦ ነበር፡፡ የነበርሁበት አስቸጋሪ ሁኔታ ይለወጥ ይሆን ወይ? በማለት ራሴን እጠይቅ ነበር፡፡ የቅርብ አለቃዬ ከነበረው ሰው ጋር የገጠመኝ ችግር ከመጀመሩ ጥቂት ቀደም ሲል፣ የእግዚአብሔር መንፈስ ለውጥ እንደሚመጣ አሳየኝ፡፡ ‹‹ወደ አብያተ ክርስቲያናትና ከተሞች፣ ከአሜሪካ ምሥራቅ ባሕር ዳርቻ እስከ ምዕራብ ዳርቻ፣ ከካናዳ ድንበር እስከ ሜክሲኮ ድንበር፣ ወደ አላስካና ሐዋይ... እየሄድሁ እንደማገለግል እግዚአብሔር የገለጠልኝ በዚያ ዘመን ነበር፡፡

ይሁን እንጂ፣ ቀደም ሲል እንደ ተባለው ይህ በሚቀጥለው ቀን ወይም ሳምንት እውን አልሆነም! እንዲያውም ተጨማሪ ማረጋገጫ ለማግኘት ስድስት ወር መቆየት ነበረብኝ፡፡ ከዚያም አንድ ቀን ዋናው ፓስተር ወደ ስብሰባ በመምጣት ከረዳት ፓስተሮቹ አንዱ (ያኔ አሥራ አንድ ፓስተሮች ነበርን) በቅርቡ ሙሉ ጊዜውን ከአገር አገር እየተዘዋወረ እንደሚያገለግልና ከእንግዲህ ከዚያ ቤተ ክርስቲያን ጋር እንደማይሆን ጌታ እንዳሳየው ተናገረ፡፡ በመቀጠልም፣ ‹‹ጆን ቢቨሬ ያ ሰው አንተ ራስህ ነህ›› አለ፡፡

ያም ሆኖ ግን፣ ተጨማሪ ጊዜ እያለፈ ነበር፤ እርግጠኛ ለመሆን ለስድስት ተጨማሪ ወር ምድረ በዳ ውስጥ ነበርሁ፡፡ ከዚያም ከሦስት ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደዚያ ሄጄ እንድሰብክ ከሰባት የተለያየ ቦታዎች ግብዣ ደረሰኝ — አንዱ ከካናዳ ድንበር አንድ ሰዓት ርቀት ላይ ነበር፤ አንዱ የፍሎሪዳ ምሥራቅ የባሕር ዳርቻ ላይ ነበር፤ ሌላው ከፓስፊክ ውቅያኖስ በመኪና የአንድ ሰዓት ርቀት ላይ ነበር፤ ሌላው

የሜክሲኮ ድንበር ላይ ነበር! ወደ ፓስተሬ ቢሮ ሄድሁና የመጣልኝን ግብዣ በተመለከተ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ጠየቅሁት፤ እርሱም እየሳቀ፣ ‹‹ጆን፣ እንዲህ እንደሚሆን ጌታ እንዳሳየኝ ነግሬህ ነበር፤ አሁን ጊዜው የደረሰ ይመስላል›› አለኝ፡፡

ከዚያ ብዙ ሳይቆይ (ጥር 1990 ላይ) ለዚሁ ጉዳይ በተዘጋጀው ልዩ ፕሮግራም ፓስተሩ እኔና ሊዛ ላይ እጆቹን ጭኖ ጸለየልን፤ እኛም ከቦታ ቦታ እየተዘዋወርን እስከዚህ ጊዜ ድረስ እያገለገልን ነው! ዝግጁ የሆንሁ በመሰለኝ ጊዜ የራሳችንን ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ፣ የእግዚአብሔር ጊዜ በመጠበቃችን ብዙ መልካም ነገር አየን፤ በሕይወታችን ብዙ ፍሬ አገኘን፡፡

እናንተም በተቀበላችሁት ጥሪ እንዲህ እንዲሆንላችሁ እናፍቃለሁ፡፡ የእግዚአብሔርን ሕዝብ በጣም እንደሚወድ የስድሳ ዓመት ሽማግሌ ይህን የምነግራችሁና በሚቻለኝ ሁሉ ግልጽ ልሆንላችሁ የምፈልገው በዚህ ምክንያት ነው፡፡ ፍጻሜያችሁ የተሳካ እንዲሆን እፈልጋለሁ! ስለዚህ ጥቂት የመጨረሻ ሐሳቦች አካፍላችኃለሁ፡፡

## ትክክለኛ ዓላማና ፍጻሜ

ትኩረታችን ወደ ፊት እንዳንገሠግሥ የሚቃወሙን ነገሮች ላይ ሳይሆን፤ የእግዚአብሔር ዓላማ ላይ ይሁን፡፡ ወደ ትክክለኛው ፍጻሜ እንድንደርስ ከፈለግን፣ እፊታችን ትክክለኛ ራእይ መኖር አለበት! አንድ ራጭ በተሳሳተ አቅጣጫ ሮጦ፣ የተሳሳተ ግብ ላይ ቢደርስ በጣም አሳዛኝ ነው የሚሆነው! አንድ ተኳሽ የተሳሳተ ዒላማ ላይ አነጣጥሮ ያንን ቢመታ አሳዛኝ ነው የሚሆነው!

ፈሪሳውያን ለሃይማኖታቸው ቀናዒና ትጉሐን ቢሆኑም፣ ዓላማቸው የራሳቸውን መፈለግ ላይ ነበር፡፡ ቀድሞውኑ ትክክለኛ ራእይ ስላልነበራቸው ዒላማውን ሳቱ፡፡

እግዚአብሔር ለእኛ ለሕዝቡ ያለው ፍጻሜና ዓላማ ምንድነው? ኤፌሶን 1፥11፣ ‹‹ሁሉን በፈቃዱ ምክር መሠረት እንደሚሠራው እንደ

እርሱ ዕቅድ አስቀድሞ የተወሰንን እኛ ደግሞ በእርሱ ተመርጠናል›› ይላል፡፡

‹‹አስቀድሞ የተወሰንን›› ወይም፣ ‹‹አስቀድሞ መወሰን›› የሚለውን ሲሰሙ ብዙዎች ግራ ይጋባሉ፡፡ ይህን ሐሳብ መረዳት እንድንችል ቃሉን መከፋፈልና ሥርወ ቃሉን እንዲሁም መነሻ ቃሉን መመልከት አለብን፡፡ ‹‹አስቀድሞ›› ማለት ‹‹በፊት›› ወይም፣ ‹‹ከመጀመሪያው በፊት›› ማለት ነው፡፡ ‹‹መወሰን›› የሚለው ሥርወ ቃል፣ ‹‹መድረሻ›› ወይም፣ ‹‹መጨረሻ መስመር›› ማለት ነው፡፡ እንግዲህ ሁለቱን በአንድነት ስናደርጋቸው፣ ‹‹ገና ከመነሻው በፊት፣ መድረሻው ነጥብ ላይ እንዲደርስ ማድረግ›› ማለት መሆኑን ማየት እንችላለን፡፡ ስለዚህ ኤፌሶን 1፥11 እኛን ከመፍጠሩ አስቀድሞ እግዚአብሔር ለሰው ልጅ ፍጻሜ ማዘጋጀቱንና ያም ዓላማውን እንደሚፈጽም ያመለክታል ማለት ነው፡፡

ሮሜ 8፥28-29 እንዲህ ይላል፦

> እግዚአብሔርን ለሚወዱትና እንደ ሐሳቡ ለተጠሩት፣ ነገር ሁሉ ተያይዞ ለበጎ እንዲሠራ እንደሚያደርግላቸው እውቃለን፡፡ እግዘአብሔር አስቀድሞ ያወቃቸውን የልጁን መልክ እንዲመስሉ አስቀድሞ ወሰናቸው፤ ይኸውም ከብዙ ወንድሞች መካከል እርሱ በኩር እንዲሆን ነው፡፡

ዘመን ከመጀመሩ በፊት፣ ለእኛ እግዚአብሔርን ለምንወድ እርሱ ያቀደው ፍጻሜያችን የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ እንድንመስል ነው፡፡ በሕይወታችን ወይም በአገልግሎታችን የምናደርገው ማንኛውም ነገር፣ እዚህ ግብ ወይም ፍጻሜ ላይ ማነጣጠር አለበት፡፡ እግዚአብሔር እኛን የፈጠረበት ቁጥር አንድ ዓላማ የተሳካ አገልግሎት ቡድን አባል እንድንሆን፣ ለመንግሥቱ ሥራ በሚሊዮን የሚቆጠር ብር እንድንሰጥ፣ የታወቅን አርቲስቶች እንድንሆን ወይም የሌሎች ችሎታዎች ባለቤት እንድንሆን አይደለም፡፡ ሌላው ቀርቶ ሕሙማንን እንድንፈውስ፣ የበጎ ሥራ ማኅበር እንድናቋቁም፣ ሰዎችን በማስተላለፍ

የሚነግዱትን እንድናስቆም፣ በተለያዩ ሱሶች የተጠመዱ ሰዎችን ነጻ እንድናወጣ ወይም የጠፉ ሰዎችን ወደ ክርስቶስ እንድንመልስ አይደለም። ምንም እንኳ እነዚህ ሁሉ ተገቢና ትክክል ቢሆኑም፤ እነዚህን ነገሮች ቢያደርጉም መጨረሻው መስመር ላይ ያልደረሱ ብዙዎች መኖራቸውን መገንዘብ አለብን። እነዚህ ወገኖች በሚገባ ያልፈጸሙት ትኩረታቸውን የአገልግሎቱ ግብ ወይም ዓላማ ላይ ሳይሆን፣ ራሱ አገልግሎቱ ላይ በማድረጋቸው ነው!

እንግዲህ እዚህ ላይ አንድ ጥያቄ መነሣት አለበት፤ ‹‹የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ እንድንመስል አስቀድሞ እኛን ሲወስን የእግዚአብሔር ዓላማ ምን ነበር?›› መልሱ ቀላል ነው – ‹‹በሚመጣው ዘመን በክርስቶስ ኢየሱስ በቸርነቱ የገለጠልንን ወደር የሌለውን የጸጋውን ባለጠግነት›› እንድናይ እኛን በወደዱና ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግ በመፈለጉ ነው (ኤፌሶን 2፥7)።

ሊዛና እኔ ሌክሲ የምትባል ውሻ አለችን፤ ደስ የምትል ተጫዋችና አስቂኝ ናት። ይሁን እንጂ፣ ከእርሷ ጋር ግንኙነት ማድረግ የምንችለው በተወሰነ ደረጃ ብቻ ነው። ከእርሷ ጋር የምፈልገውን ያህል በሐሳብ መግባባት አለ መቻል ቅር ያሰኛል። ልጆቼን በተመለከተ ግን፣ ነገሩ ፍጹም ሌላ ነው። በዕድሜና በዕውቀት እያደጉ ሲመጡ፣ አስገራሚ የሐሳብ ልውውጥ እናደርጋለን። በሕይወታችን ብዙ መልካም ነገሮች ጨምረዋል። እግዚአብሔር የፈጠረን ለዚህ ነው። ሌክሲ በምትባለው ውሻዬ እኔን እንደ ገጠመኝ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ ያለ ኅብረት እንዲኖረን አይደለም የእርሱ ፍላጎት፤ ወንዶችና ሴቶች ልጆቹ ልብ ለልብ ከእርሱ ጋር እንዲግባቡ እግዚአብሔር ይፈልጋል።

ገና ከመጀመሪያው አንሥቶ የእርሱ ዓላማ ይህ ነበር። ሰውን ፈጥሮ በአትክልቱ ቦታ ባኖረው ጊዜ ለአዳም ከነበረው ፍቅር የተነሣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ኅብረት ያደርግ ነበር። ከአዳም ዝርያዎች አንዱ በዚህ ዓላማ በጣም በመመሰጡ እርሱን በተመለከተ፣ ‹‹ሄኖክ አካሄዱን ከእግዚአብሔር ጋር አደረገ፤ እግዚአብሔር ስለ ወሰደውም

አልተገኘም›› የሚል ተጽፎአል (ዘፍጥረት 5፥24)፡፡ የዕብራውያን መልእክት ጸሐፊ፣ ‹‹…እርሱ [ሄኖክ] እግዚአብሔርን ደስ እንዳሰኘ ተመስክሮለታልና›› ይላል (ዕብራውያን 11፥5)፡፡ ሄኖክ እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው እንዴት ነበር? አንድ ትልቅ አገልግሎት ስለ ነበረው ነውን? አይደለም፤ ከእግዚአብሔር ጋር በመላለሱና ከእርሱ ጋር የቀረበ ኅብረት በማድረጉ ነው፡፡

ባለፈው ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገው፣ አሁንና ወደ ፊትም የሚያደርገው ሁሉ ይህን ዓላማ ለማሳካት ነው፡፡ ስለሆነም የምድረ በዳ ልምምድ ዓላማ የኢየሱስ ክርስቶስን መልክ የምንመስልበትን አቅጣጫ ለእኛ ማመልከት ነው፡፡

እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ዓላማ ማየት ከተሳነን መረን እንሆናለን፤ መንፈሳዊ ማሽቆልቆልም ይደርስብናል፡፡ እንደ ቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ዓላማ ከጠፋብን በመንፈሳዊ ሕይወታችን እንደርቃለን፣ በዚህ ዓለም ነገሮች የሚመራ ተቋም ወደ መሆን ደረጃ ዝቅ እንላለን፡፡ የክርስቶስን መልክ የሚመስሉ ደቀ መዛሙርት ከማፍራት ይልቅ፣ አጽንዖት የምንሰጠው ለውጤቶች ማለትም - ለቁጥር ብዛትና ለትልልቅ ሕንፃዎች ይሆናል (ማቴዎስ 28፥19)፡፡

እንደ ገና ምሳሌ 29፥18 እንመልከት፤ ‹‹ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል፡፡››

እግዚአብሔር መረን እንድንሆን አይፈልግም፤ ምክንያቱም ጥሪያችን የእርሱን መልክ እንድንመስል እንጂ፣ ከዚያ ዝቅ ያለ ሌላ ነገር አይደለም፡፡ የእርሱን መልክ እንድንመስልና እርሱን ፊት ለፊት እንድናይና ክብሩ እስኪገለጥ ድረስ በደረስንበት ደረጃ እንድንወሰንና መረን እንድንሆን አይፈልግም፡፡ መረን ከሆንን የእርሱ ፍጹም ፈቃድ ያልሆነ ነገር እንቀበላለን፡፡ መረን ከሆንን ነገርን ዓለም በሚያደርግበት መንገድ እናደርጋለን፤ የሥጋን መንገድ እንከተላለን፡፡

ራእይን በተመለከተ ኢየሱስ ሲናገር፣ ‹‹ዐይን የሰውነት መብራት ነው፤ ስለዚህ ዐይንህ ጤናማ ከሆነ፣ መላው ሰውነትህ በብርሃን የተሞላ ይሆናል፡፡ ዐይንህ ታማሚ ከሆነ ግን፣ መላው ሰውነትህ በጨለማ

የተሞላ ይሆናል›› አለ (ማቴዎስ 6፥22-23)፡፡ እየተናገረ ያለው ስለ ሥጋዊ ዐይኖችን ሳይሆን፣ ስለ ልብ ዐይን ወይም ነገሮችን በትክክል መገንዘብ ስለምንችልበት ዐይን ነው፡፡

‹‹በልቡ እንዳሰበ እንዲሁ ነውና›› የሚለው የሚያመለክተው ነገሮችን በልብህ ስለምትገነዘብበት መንገድ ነው? (ምሳሌ 23፥7)፡፡

ያለህበትን ሁኔታ የምታይበት መንገድ፣ ከዚያ መውጣት የምትችልበትን ሁኔታ ይወስናል፡፡ የተስፋውን ምድር በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ ሄደው የነበሩ አሥራ ሁለቱ ሰላዮች ተመሳሳይ ነገር ነበር ያዩት፤ ሁሉም ተመሳሳይ የተመሸጉ ከተሞች ነበር ያዩት፤ ሁሉም ተመሳሳይ ግዙፍ ሰዎች ነበር ያዩት፤ ሁሉም ተመሳሳይ የከነዓናውያንን ወታደሮች ነበር ያዩት፡፡ ይሁን እንጂ፣ ከእነርሱ መካከል ሁለቱ ማለት ኢያሱና ካሌብ ከተቀሩት አሥሩ ሰዎች ፍጹም የተለየ ነገር አይተዋል፡፡ ሁለቱ እግዚአብሔር በሚያይበት መንገድ አዩ፤ አሥሩ ግን የተስፋውን ምድር በራሳቸው ተፈጥሮአዊ ልምምድ ዐይን ወይም በራሳቸውን ችሎታና ብርታት ዐይን አዩ፡፡ ዐይናቸው ታማሚ ስለ ነበር፣ ባሕርያቸው ሁሉ (ወይም ኢየሱስ እንዳለው፣ ‹‹መላው›› ሰውነታቸው) ታማሚ ሆነ፡፡ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ተጻራሪ በሆነ ሁኔታ በአንደበታቸው ተናገሩ፤ በድርጊታቸው ምላሽ ሰጡ፤ ወሬያቸው፣ ‹‹መጥፎ›› ወይም፣ ‹‹ክፉ›› እንደ ነበር እግዚአብሔር ተናገረ፤

> ‹‹ስለዚህ እንዲህ በላቸው፤ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እኔ ሕያው ነኝ፤ ስትናገሩ የሰማኋችሁን እነዚያን ነገሮች አደርግባችኃለሁ፤ በተደረገው ቈጠራ መሠረት ሃያ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆናችሁና በእኔም ላይ ያጕረመረማችሁ ሁሉ፣ በድናችሁ በዚህ ምድረ በዳ ይወድቃል፡፡ መኖሪያችሁ እንድትሆን በጽኑ ወደማልሁላችሁ ምድር ከዮፎኒ ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በስተቀር ከእናንተ አንዳችሁም አትገቡባትም፡፡›› (ዘኁልቁ 14፥28-30)

አሥሩ ሰላዮች እግዚአብሔር የሰጣቸውን ተስፋ እንዳያዩ

ያደረጋቸውን ሪፖርት ያቀረቡት ለምን ነበር? ምክንያቱ ፊት ለፊታቸው የነበረውን ነገር በተመለከተ የነበራቸው ግንዛቤ ወይም መረዳት ነበር፤ በመሠረቱ ይህ በተፈጥሮ ዐይን የሚታይ ራእይ እንጂ ትንቢታዊ ራእይ አልነበረም፡፡ ሪፖርት ያደረጉት ሥጋዊ ዐይኖቻቸው ያዩትን ነበር፡፡

ከምድረ በዳ በድል እንድንወጣ ከተፈለገ ነገሮችን ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ማየት አለብን፡፡ እግዚአብሔር ሰላዮቹን ወደ ተስፋው ምድር ከመላኩ በፊት የእስራኤል ልጆች ከአንድ ዓመት የበለጠ ጊዜ እያጉረመረሙ ነበር፡፡ ዕይታቸው ታማሚ ነበር፤ መረን እንዳይሆኑ የሚያግዳቸው ሁሉ ተዛብቶ ነበር፡፡ ስለዚህም ወተትና ማር የምታፈስሰውን ምድር እግዚአብሔር እንዲያዩ ሲያደርግ መልካሙን ነገር ማየት አልፈለጉም፡፡ ይልቁንም ትኩረታቸው በምድሪቱ የነበሩ ግዙፍ ሰዎች ላይ ነበር፡፡

ምድረ በዳውን ብቻ፣ ማለትም ከዚያ ጋር ተያይዞ ያለውን ችግር ብቻ፣ የሚመለከቱ ሁሉ ምድረ በዳ ውስጥ ይሞታሉ፡፡ ዐይናቸውን ተስፋውና እርሱ በፊታቸው ያኖረው ራእይ ላይ የሚያደርጉ ግን፣ ለእርሱ ክብር እንዲሆን የተስፋውን ምድር ለመውረስና በዚያ ለመኖር ብርቱ ጦረኛ ሆነው ከምድረ በዳ ይወጣሉ፡፡

> **ስለዚህ ተስፋ አንቆርጥም [አንዝልም ወይም መረን አንሆንም]፤ ... ምክንያቱም ቀላልና ጊዜያዊ የሆነው መከራችን ወደር የማይገኝለት ዘላለማዊ ክብር ያስገኝልናል። ስለዚህ ዐይናችን የሚያተኩረው በሚታየው ነገር ላይ ሳይሆን፣ በማይታየው ላይ ነው፤ የሚታየው ጊዜያዊ ነውና የማይታየው ግን ዘላለማዊ ነው። (2 ቆሮንቶስ 4፥16-18)**

ምድረ በዳ ውስጥ የምናሳልፈው ጊዜ ርዝመትና የሚደርስብን መከራ ከባድነት ከምናገኘው ጥቅም ጋር ሲነጻጸር፣ እንደ ቀላል ጊዜያዊ ተግዳሮት ይቆጠራል፡፡ እርግጥ ነው፣ ከምድረ በዳ ከወጣችሁ በኋላ የሚመጣውን በተመለከተ ራእይ ከሌላችሁ ምድረ በዳ ውስጥ

በምትሆኑበት ጊዜ የሚደርስባችሁን እንደ ተራ ነገር መቁጠር በጣም ከባድ ይሆንባችኃል፡፡

ባለፈው ዘመኔ ደረቅ ቦታ በነበርሁ ጊዜ ነገሩ፣ ‹‹ጊዜያዊ›› መስሎ አልታየኝም ነበር፤ እንዲያውም፣ ይህ ሁሉ ያበቃ ይሆን? የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል የሚፈጸመው መቼ ይሆን? በማለት የጠየቅሁበት ጊዜ ነበር፡፡ እንዲህ ያሉ ሐሳቦቼን ወዲያውኑ በመተው፣ በጌታ ደስ መሰኘት የነበረብኝ በዚህ ጊዜ ነበር፡፡ እኔን በተመለከተ የተነገሩ ትንቢቶችን አስታወስሁ፤ በዚያ መሠረትም ከባድ መንፈሳዊ ውጊያ አደረግሁ (1 ጢሞቴዎስ 1፥18 ይመ)፡፡ ትንቢቶቹ ለሕይወቴ የእግዚአብሔር ራእይ ነበሩ፤ ያንን በቃሉ በኩል በመንፈሱ ገለጠልኝ፡፡

ምድረ በዳ ውስጥ ስንሆን ነፍስ የውጊያ ሜዳ ትሆናለች፤ ነፍስ አእምሮን፣ ስሜትንና ፈቃድን ትይዛለች፡፡ ፈቃድ የምትመርጡት የእግዚአብሔርን መንገድ ወይም የሥጋን ፈቃድ መሆኑን፣ ነገሮችን የምትመለከቱት ከእግዚአብሔር ዕይታ አንጻር ወይም ከሥጋ አንጻር መሆኑን፣ ትኩረታችሁ ምድረ በዳ ውስጥ የገጠማችሁ ነገር ላይ ወይም እግዚአብሔር ያዘጋጀላችሁ ነገር ላይ መሆኑን፣ የምትወስኑበት የነፍሳችሁ አካል ነው፡፡ ሐዋርያው ጴጥሮስ፣ ‹‹ወዳጆች ሆይ፣ በዚህ ዓለም፣ ‹እንግዶችና መጻተኞች እንደ መሆናችሁ መጠን› ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት እንድትርቁ እለምናችኃለሁ›› ይላል (1 ጴጥሮስ 2፥11)፡፡

ለመሆኑ፣ የትኩረታችሁ ማዕከል ማን ነው - ጌታ ወይስ እናንተ? አእምሮአችሁና ስሜታችሁ ውስጥ የሚዋጋው ሥጋዊ ምኞት ራስ ወዳድ ነገሮች ላይ ያተኩራል፡፡ እነዚህም እግዚአብሔር ከሰጣችሁ ራእይ ወደ ኃላ ይጐትቱዋችኃል፤ የእግዚአብሔር መንገድ የእኔነት መንገድ ሳይሆን፣ ሥጋን የመካድ መንገድ ነው፡፡

በዚህ ዘመን እየተሰበከ ያለውና ብዙዎች የተቀበሉት ወንጌል ለሥጋ ምቾትና እፎይታ የሚሆን ወንጌል ነው፡፡ በዚህ ዘመን የምንሰማቸው መልእክቶች ሥጋን እንድንሰቅል የሚያበረታቱ ሳይሆኑ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የሚመስል ሕይወት እንዳንኖር የሚዋጉ

ምኞቶቻችንን የሚያረኩና እፎይታ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ብዙ ጊዜ ትኩረታችን፣ ‹‹እግዚአብሔር ከእኔ የሚፈልገው ምንድነው?›› ከሚለው፣ ይልቅ፣ ‹‹እግዚአብሔር ምን ያደርግልኝ ይሆን?›› የሚለው ላይ ነው፡፡ የምቾትና የእፎይታ ወንጌል ክርስቶስን ስንከተል ለሚገጥመን መከራ ተገቢነት አጽንዖት አይሰጥም፡፡ ብዙዎች የቸልተኝነት ሕይወት እንዲኖሩ ያደረገው ይኸው ነው፡፡ ይህ ዓይነቱ ወንጌል አማኞች የእግዚአብሔር ወታደሮች እንዲሆኑ አያዘጋጅም፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ ጢሞቴዎስ ለተባለው ደቀ መዝሙሩ በጻፈው መልእክት ይህን ዐቢይ ጉዳይ አንሥቶ ነበር፡-

> እንደ ክርስቶስ ኢየሱስ በጎ ወታደር ከእኛ ጋር መከራን ተቀበል፡፡ በውትድርና የሚያገለግል ሰው አዛዡን ለማስደሰት ይጥራል እንጂ፣ በሌላ ሥራ ራሱን አያጠላልፍም፡፡ (2 ጢሞቴዎስ 2፥3-4)

የምንከተለው፣ ‹‹የምቾት ወንጌል››ን ከሆነ፣ አንዳች ተቃውሞ ወይም አዳጋች ሁኔታ ከገጠመን፣ ችግሩን ከመጋፈጥና ወደ ፊት ከመግፋት ይልቅ ማምለጫ መንገድ እንፈልጋለን፡፡ ከምቾት ወንጌል ትምህርት የምናገኘው ራእይ፣ ‹‹ሰማያዊ ወይም ትንቢታዊ›› ሳይሆን፣ ‹‹የራስ ወዳድነት ራእይ›› ነው የሚሆነው፡፡

ጳውሎስ ይህንንም ጽፎአል፡-

> <<እንግዲህ ንጉሥ አግሪጳ ሆይ፣ ከሰማይ ለታየኝ ራእይ አልታዘዝ አላልሁም፤ ነገር ግን በመጀመሪያ በደማስቆ ለሚኖሩ፣ ቀጥሎም በኢየሩሳሌምና በይሁዳ ላሉት ሁሉ፣ ከዚያም ለአሕዛብ ንስሓ እንዲገቡና ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ፣ የንስሓም ፍሬ እንዲያሳዩ ገልጬ ተናገርሁ፡፡ አይሁድም በመቅደስ ይዘው ሊገድሉኝ የሞከሩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡>> (የሐዋርያት ሥራ 26፥19-21)

በዚህ ዓለም ብዙ ራእዮች አሉ፤ ከሰማይ የመጣ ራእይ ግን አንድ ብቻ ሲሆን፣ ያም የአባት ፈቃድ ነው! ጳውሎስ፣ ‹‹አይሁድ

በመቅደስ ይዘው ሊገድሉኝ የሞከሩት በዚህ ምክንያት ነው›› በማለት መናገሩን ልብ በሉ፡፡ ሰማያዊውን ራእይ ለመፈጸም እየተጋ ቢሆንም፣ ታላቅ ተቃውሞ ገጥሞታል፡፡ በዚህ ዘመን ብዙዎች እንደሚያምኑትና እንደሚሰብኩት የሚያምነው፣ ‹‹የምቾት ወንጌል››ን ቢሆን ኖሮ ራእዩ ሲፈጸም ማየት አይችልም ነበር፡፡ ቀደም ሲል ከመጀመሪያው ከገጠመው ተቃውሞ ሁሉ የሚያመልጥበትን መንገድ ይከተል ስለ ነበር ንጉሥ አግሪጳ ፊት እንኳ አይቆምም ነበር፡፡

ነቢዩ ኤርምያስ ሰማያዊ ራእይን ለመፈጸም የሚተጋ ሌላው የመጽሐፍ ቅዱስ ሰው ነበር፤ ለዚያ ከመታዘዙም የተነሣ አያሌ የአንደበት ዘለፋዎችና አእምሮ ላይ የተቃጣ ጥቃት ደርሶበት ነበር፡፡ በዚህ እጅግ ከማዘኑ የተነሣ አንድ ቀን በመጠኑም ቢሆን፣ እንዲህ በማለት አማርሮ ነበር፡፡ ‹‹የክፉዎች መንገድ ለምን ይሰምራል? የከዳተኞችስ ኑሮ ለምን ይሳካል? (ኤርምያስ 12÷1)

እግዚአብሔር የመለሰለት በመለሳለስ አልነበረም፤ እንዲህ ነበር ያለው፣ ‹‹ከእግረኞች ጋር ሮጠህ እነርሱ ካደከሙህ፣ ከፈረሰኞች ጋር እንዴት ልትወዳደር ትችላለህ?›› (ኤርምያስ 12÷5)፡፡ በሌላ አነጋገር፣ ‹‹ኤርምያስ ሆይ፣ ሰይጣን ያሰማራቸው እግረኛ ወታደሮች ይህን ያህል ካደከሙህ፣ የሰይጣን ፈረሰኞች ሲገጥሙህ ምን ልታደርግ ነው?›› እያለው ነበር፡፡

ጉዞውን በድል ለመወጣት የሚጠቅሙ ምክሮች

# 12 ተገቢ ማስታወሻዎች መያዝ

አሁን ይህን እየጻፍሁ ባለሁበት ጊዜ ስድሳኛ ዓመቴን እየያዝሁ ነው፤ ግን እንዴት እዚህ ደረስሁ? ወደ ኋላ ዞር ብዬ ስመለከት፣ ምንም እንኳ በወቅቱ ወደ ፊት ከመሄድ ይልቅ ወደ ኋላ የተንሸራተትሁ ቢመስለኝም፣ በምድረ በዳ ያሳለፍሁዋቸው ጊዜዎች በከፍተኛ ደረጃ ያደግሁባቸው

ጊዜዎች እንደ ነበሩ እረዳለሁ፡፡ የጥንቱ ወዳጃችን ኢዮብ፣ ‹‹የምሄድበትን መንገድ ያውቃል፤ ከፈተነኝም በኋላ እንደ ወርቅ እወጣለሁ›› ይላል (ኢዮብ 23፥10)

እውነቱን ለመናገር፣ ሃያ በሚሆኑ መጻሕፍቶቼ ውስጥ ከጻፍሁዋቸው እውነቶች ዘጠና እጁን ያህል የተማርሁት ሁሉም በሞላበት ጊዜ ሳይሆን፣ ምድረ በዳ ውስጥ ባሳለፍሁዋቸው ደረቅ ዓመታት ውስጥ እንደ ነበር እገምታለሁ፡፡ ስለዚህ እናንተን የምመክረው በረሓ ውስጥ ስትሆኑ ማስታወሻ እንድትይዙ ነው! በእነዚህ ወቅቶች የምትማሩት ለሌሎች ታላቅ ብርታት ይሆናል (ስታረጁ ለእናንተም ጭምር)፡፡ ማን ያውቃል... ያለፋችሁበት ልምምድ አንድ ቀን በመጽሐፍ ይታተምም ይሆናል!

ወዳጄ፣ አሁኑኑ አንተ ላይ ትንቢት መናገር እፈልጋለሁ! የምነግርህን ልብ ብለህ አድምጠኝ፡- እግዚአብሔር በወሰነው ጊዜ የብዙዎችን ሕይወት የሚነካ አንዳች ነገር በሕይወትህ ያደርጋል፡፡ ያ የሚሆነው በምድረ በዳ ውስጥ ያለህበትን የእርሱን ዓላማ እንዲፈጽም ከፈቀድህለት ነው፡፡ ብዙዎች ይጽናናሉ፤ ይበረታታሉ፤ አንተም የመታዘዝህን ፍሬ ስታይ፣ በዘላለማዊ ዓለም እጅግ ደስ ይልሃል፡፡ ወዳጄ፣ እንደ ወርቅ ተፈትነህ፣ ጠርተህ፣ በርትተህና እውነተኛ ሆነህ ትወጣለህ፡፡

## ግጭት ውስጥ ጦርነት አለ

ያለ ትልቅ ጦርነት ትልቅ ድል እንደሌለ ማስታወስ አለብን፡፡ ኤርምያስ ላይ ውጊያ በርትቶ ነበር፡፡ ከመሰደብ አልፎ እስር ቤት ገብቶ ነበር፤ በኋላም እዚያ እንዲሞት ተብሎ ጉድጓድ ውስጥ ተጥሎ ነበር፡፡ በኋላ ግን እግዚአብሔር ከመከራዎቹና ከስደቶቹ ሁሉ አወጣው፡፡

በዚህ ዘመን በክርስቶስ አካል ውስጥ ብዙዎች እየደረሰባቸው

ያለው ውጊያ፣ ጳውሎስ ላይ እንደ ደረሰው አካላዊ ስደት ሳይሆን፣ አእምሮ ላይ የሚሰነዝር ጥቃት ነው፡፡ ታዲያ፣ ሁኔታው ይበልጥ እየበረታ ሲሄድ ምን ማድረግ ነው ያለብን? አሁን እያለፍንበት ያለው ችግር ወደ ፊት ለሚገጥሙን የበላለጡ ውጊያዎች ሊያዘጋጀን ይገባል፡፡

ምድረ በዳ ለወደ ፊቱ ውጊያ የምንዘጋጅበትና የምንሠለጥንበት ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ዘመን ወታደሮችን ወደ ማሠልጠኛ ካምፕ እንደምንልክ ሁሉ፣ እግዚአብሔርም የእርሱን መንግሥት ለመሥራት ዝግጁ እንዲሆኑ እርሱ የመለመላቸውን ወታደሮች ወደ ምድረ በዳ ይልካቸዋል፡፡ ማሠልጠኛ ካምፕ ውስጥ ወታደሮች ማሸነፍ ያለባቸው ትልልቅ መሰናክሎች ፍርሃት፣ ደካማነትና ተስፋ መቁረጥ ናቸው፡፡ በተመሳሳይ መንገድ ምድረ በዳ ውስጥ የሚገጥመን ትልቁ ፈተና ነፍስ ላይ የሚቃጣው ጥቃት ነው፡፡

ከሚጥሙን ትልልቅ ውጊያዎች አንዱ ተስፋ መቁረጥ ወይም ወኔ ማጣት (discouragement) ነው፡፡ አንድ ቀን ጸሎት ላይ እያለሁ፣ የወኔ ወይም ድፍረት (Courage) ተቃራኒ ምንድነው? በማለት ጌታ ጠየቀኝ፡፡

እኔም፣ ‹‹ፍርሃት ነው›› በማለት መለስሁ፡፡

እርሱ ግን፣ ‹‹ወኔ ቢስነት ወይም ተስፋ መቁረጥ ነው›› (discouragement) ነበር ያለኝ፡፡ ከዚያ በፊት dis-courage የሚለውን ቃል በዚህ መልኩ አይቼው አላውቅም ነበር! በጽሑፍ በሰፈረው ቃል እግዚአብሔር ለኢያሱ፣ ስምንት ጊዜ ያህል፣ ‹‹አይዞህ በርታ አትፍራ›› በማለት የተናገረበት ምክንያት የበለጠ ግልጽ የሆነልኝ ወዲያው ነበር (ዘኁልቁ 13፥20፤ ዘዳግም 31፥6፣ 7፣ 23፤ ኢያሱ 1፥6፣ 7፣ 9፣ 18)፡፡ ይህ ከሚገጥሙት ትልልቅ ተግዳሮቶች አንዱ እንደሚሆን እግዚአብሔር አውቆአል፡፡ ምድረ በዳ ወይም ውጊያ ውስጥ ስንሆን፣ ትኩረታችንን እግዚአብሔርና የተሰጠን ተልዕኮ ላይ ሳይሆን፣ እኛ ራሳችን ላይ ካደረግን ተስፋ መቁረጥ ይገጥመናል፡፡

የጠላት ዓላማ ትኩረታችንን እኛ ራሳችን ላይ እንድናሳርፍ

ማድረግ ነው፤ ምድረ በዳ ውስጥ በነበረ ጊዜ ኢየሱስ ላይ ማድረግ የሞከረው ይህንኑ ነበር፡፡ አርባ ቀን ሙሉ ምንም ስላልበላ ኢየሱስ ርቦት ነበር፤ በዚህ ጊዜ ዲያብሎስ መጥቶ፣ ‹‹የእግዚአብሔር ልጅ ከሆንህ፣ እነዚህን ድንጋዮች እንጀራ እንዲሆኑ እዘዝ›› አለው (ማቴዎስ 4፥1-11)፡፡ የፈተናው ዓላማ ያለ እግዚአብሔር ፈቃድ ሥጋው የሚፈልገውን ለማሟላት የእግዚአብሔርን ኃይል መጠቀም ነበር፡፡ እግዚአብሔር አንዳች ስጦታ የሚሰጠው ከታላቅ ኀላፊነት ጋር መሆኑን ማስታወስ አለብን፤ እርሱ በሚፈልገው መንገድ መጠቀም እንጂ፣ አግባብ ባልሆነ ሁኔታ ልንጠቀምበት አይገባም፡፡ እግዚአብሔር ለኢየሱስ የሚያስፈልገውን ሁሉ እንደሚሰጠው ግልጽ ነው፤ ይሁን እንጂ፣ ያንን የሚያደርገው በእርሱ በራሱ መንገድ ነው፡፡ ዲያብሎስ ትቶት ሲሄድ መላእክት መጥተው ኢየሱስን አገለገሉት፡፡

እዚህም ላይ አገልግሎቱን በተመለከተ ኢየሱስ የተናገረውን ልብ ማለት አለብን፣

> <<እውነት እላችኋለሁ፤ አብ ሲሠራ ያየውን ብቻ እንጂ፣ ወልድ ከራሱ ምንም ሊያደርግ አይችልም፤ አብ የሚያደርገውን ሁሉ ወልድ ደግሞ ያደርጋልና>> (ዮሐንስ 5፥19)

‹‹ያየውን›› የተሰኘውን ቃል ልብ በሉ፤ ኢየሱስ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ውጪ ምንም አያደርግም ነበር፡፡

ደረቅ ወቅት ውስጥ ስንሆን ከሚገጥሙን ፈተናዎች አንዱ፣ የእግዚአብሔርን መንገድ ከመጠበቅ ይልቅ፣ ነገሮችን በራሳችን መንገድ የማድረግ ፈተና ነው፡፡ ይህም የእግዚአብሔር ጊዜ ሳይደርስ ከእርሱ አንዳች ነገር ለመቀበል የእግዚአብሔር ኀይል መጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡ እንደ አለቆቹ ትእዛዝ ሳይሆን፣ በራሱ መንገድ ጦር ሜዳ ውስጥ ውጊያ ላይ ያለ ወታደር ምን እንደሚሆን ማሰብ ትችላላችሁን? ወታደሩም ላይ ሆነ አብረውት የሚዋጉት ላይ ከባድ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡ ወታደራዊ ማሠልጠኛ ካምፕ ውስጥ በጦርነት ጊዜ በራሱም ላይ ሆነ ሌሎች ላይ ጉዳት እንዳያመጣ የሚሰጠውን

ትእዛዝ መፈጸምን ወታደሩ ይማራል፡፡

ሰማይ የገለጠልንን አለመዘንጋት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አሁኑኑ መልስ ማግኘት አለብኝ! ወይም አሁኑኑ መንቀሳቀስ አለብኝ፤ምንም ካላደረግሁ ነገሩ ሁሉ ይበላሽብኛል! በማለት የምናስብበት ጊዜ አለ፡፡ እግዚአብሔር ምንም ያልተናገራችሁ ቢመስላችሁ እንኳ፣ ከእንግዲህ እርሱ በፍጹም አይናገራችሁም! ማለት አይደለም፡፡ በሕይወታችን በሚሆኑ ነገሮች እግዚአብሔር በብዙ የተለያዩ መንገዶች የራሱን ተሳትፎ ያደርጋል፡፡ በዚህ ጊዜ እርሱ እያስተላለፈልን ያለው መልእክት፣ ‹‹አሁን ምንም ማድረግ የለባችሁም›› የሚል ሊሆን ይችላል፡፡ እንዲህ ያሉ ሁኔታዎች ሲገጥሙን በትዕግሥት እግዚአብሔርን መጠበቅ እንጂ፣ ነገሮችን ማስገደድ መሆን የለበትም፡፡

> እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ፤
> አይዞህ በርታ፤ እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።
> (መዝሙር 27፥14)

እግዚአብሔር ላይ ሳይሆን እኛ ላይ ካተኮርን ተስፋ መቁረጥና መደበት ይመጣል፡፡ ዕይታችንን አንሥተን ትኩረታችንን፣ ‹‹ቀላልና ጊዜያዊ›› የሆነው መከራ ላይ ማድረግ የለብንም፡፡ ይልቁንም፣ ወደር የሌለው የሚያስገኝልን ዘላለማዊ ክብር ላይ ይሁን (2 ቆሮንቶስ 4፥17)፡፡

ራእያችን ማረፍ ያለበት በዚህ ፊት ለፊችን ባለው ደስታ ላይ መሆን አለበት፡፡

## ፊት ለፊታችን ያለው ደስታ

> ወንድሞች ሆይ፤ ልዩ ልዩ መከራ ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት፤ ምክንያቱም የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንደሚያስገኝላችሁ ታውቃላችሁ። ምንም የማይጐድላችሁ ፍጹማንና ምሉአን እንድትሆኑ ትዕግሥት ሥራውን ይፈጽም። (ያዕቆብ 1፥2-4)።

ደስታ በመከራችንና በፈተናችን ውስጥ የምንታገሥበትን ብርታት የሚሰጠን መንፈሳዊ ኀይል ነው፡፡ ‹‹እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት›› የሚለውን ቃል ልብ በሉ፤ ‹‹እንደ አንድ ተራ ደስታ ቁጠሩት›› አይደለም የሚለው፡፡ ልባችን ውስጥ ደስታና ሐዘን መቀላቀል የለባቸውም፡፡ ነገሩን እንዲህ ተመልከቱት፡- ዘጠና ዘጠኝ ቀለበቶች ያሉት ሰንሰለት ቢኖራችሁ ከዚያ መካከል አንዱ ሐዘን ነው እንበል፡፡ ሰንሰለቱ ብርቱ የሚሆነው እያንዳንዱ ሰንሰለት ብርቱ ሲሆን ነው፡፡ የተሰጣችሁን ኀላፊነት ለመፈጸም የሚያስችላችሁን ብርታት ለማግኘት አንድ መቶ እጅ ደስታና ዜሮ እጅ ሐዘን ሊኖራችሁ ይገባል፡፡

እኔና እናንተ፣ ‹‹እንደ ሙሉ ደስታ›› የምንቆጥረው ሁሉም ነገር መልካምና ያማረ ሲሆን ብቻ ነው፡፡ ቃሉ ግን እንደዚያ አይደለም የሚለው፡፡ ‹‹እንደ ሙሉ ደስታ›› መቁጠር ያለብን በመከራ፣ በምድረ በዳ፣ በስደት፣ በችግርና በሌሎችም አዳጋች ሁኔታዎች ወቅት ውስጥ ነው፡፡ እግዚአብሔር ይህን የሚለው ‹‹የእግዚአብሔር ደስታ ኀይላችን›› መሆኑን ስለሚያውቅ ነው (ነህምያ 8÷10)፡፡ ይህ ደስታ ብርታት ከሚሰጠን ከእርሱ ጋር በመቀራረብ የሚኖረን ደስታ ነው፡፡

ሚስቴና መላው ቤተ ሰቤ ማለት ወንዶቹ ልጆቼ፣ የልጆቼ ሚስቶችና የልጅ ልጆቼ ታላቅ ደስታ ይሰጡኛል! ከቤት ርቄ የምሄድባቸው ብዙ ጊዜዎች አሉ፤ በእንዲህ ያሉ ጊዜዎች ፎቶዎቻቸውን አውጥቼ አያለሁ፡፡ አንድ ጊዜ እንኳ ለልቤ ደስታ ሳይሰጡኝ ቀርተው አያውቁም፤ ይህም የሚያስፈልገኝን ብርታት ይሰጠኛል፡፡

ነህምያ በዘመኑ ለነበሩ ሰዎች የሚለው ይህንኑ ነበር፡፡ በጣም ከባድ በሆነ ጊዜ ውስጥ እያለፉ ነበር፤ ስለዚህም ነህምያ፣ ‹‹በዚህ መከራ አትዘኑ፤ ዐይኖቻችሁን ጌታ ላይ አድርጉ፤ ምክንያቱም ወደ እርሱ ስትቀርቡ ደስታ ልባችሁን ይሞላዋል፤ ብርታትንም ይሰጣችኋል›› ይላቸዋል፡፡

እግዚአብሔርን ማመስገን ትኩረታችሁ ከእናንተ ተነሥቶ ጌታ ላይ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ ፈተና ውስጥ ስንሆን ከሚደርስብን

ከባድ ጫና የተነሣ በቀላሉ የእግዚአብሔርን ችሎታ እንዘነጋለን፡፡ ዳዊት አብዛኞቹ መዝሙሮቹን የጻፈው ፈተናዎች መካከል ነው፡፡ እግዚአብሔርን በማመስገን በጣም ከባድ በሆኑ ሁኔታዎች ውስጥ በብርታት መዝለቅ ቻለ፡፡

ኢሳይያስ 61÷3 ላይ፣ ‹‹በዐመድ ፈንታ የውበት አክሊል፣ በለቅሶ ፈንታ የደስታ ዘይት›› እንደሚሰጠን እግዚአብሔር ይናገራል፡፡

በጣም ከባድ የድርቅ ወቅት ውስጥ በነበርሁ ጊዜ፣ ይህ ጥቅስ ታላቅ መጽናኛ ሆኖኝ እንደ ነበር አስታውሳለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱሴን አንሥቼ ለማንበብ ሞከርሁ ግን፣ አልቻልሁም፡፡ ስለዚህ መጸለይ ጀመርሁ፤ ያም ቢሆን የባሰ ከባድ ነበር፡፡ ልቤ ውስጥ፣ ‹‹ከምስጋና ሲዲዎች (CDs) አንዱን ክፈት›› በማለት የእግዚአብሔር መንፈስ ሲናገር የሰማሁ መሰለኝ፡፡ ስለዚህ ሳውንድ ሲስተማችን ወደ ነበረበት ክፍል ሄጄ ጥቂት የምስጋና መዝሙሮች ከፍቼ መዘመር ጀመርሁ፡፡ በጌታ ፊት በደስታ ውስጥ ለመሆን መጀመሪያ ላይ ብዙ ጥረት ማድረግ አስፈልጎኝ ነበር፡፡ ያም ሆኖ ደስ ለመሰኘት ሞከርሁ፡፡

ብዙ ሰዎች የሚሳተፉበት የመዝሙሩ ክፍል ሲያበቃ፣ ያንኑ ሲዲ እንደ ገና ለማጫወት ልቤ ፈለገ፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ ስሰማው እየዘመርሁ ያለሁትን በደንብ ማድመጥ ጀመርሁ፡፡ በድንገት ኢየሱስ ዙፋን ላይ ሆኖ የእርሱንም ፍቅር ልቤ ውስጥ በጨረፍታ ማየት ቻልሁ፡፡ ደስታ ወደ ልቤ መጉረፍ ጀመረ፤ እኔም ያለ አንዳች መሰናክል ደስ መሰኘት ቻልሁ፡፡ ዐይኖቼ ከእኔ ላይ ተነሥተው የኢየሱስ ታላቅነት ላይ ማረፋቸውን አስተዋልሁ፡፡ ለቀጣዩ ሰላሣ ደቂቃ ዘመርሁ፤ አሸበሸብሁ፤ ክፍሉ ውስጥ ወዲያ ወዲህ እየተንጐራደድሁ ማመስገን ጀመርሁ፡፡ የከበደኝ ነገር ከላዬ ተነሣ፤ ከሰላሣ ደቂቃ በፊት ምንም ካልነበረው ውስጤ ሕይወትና ብርታት መፍለቅ ጀመረ፡፡

እርሱን ሳመሰግነው ትኩረቴ ወደ እርሱ ተመለሰ፡፡ ‹‹ከድነቴ ምንጮች፣ ውሃ በደስታ ትቀዳላችሁ!›› በማለት ነቢዩ ኢሳይያስ የጻፈውን በግል ሕይወቴ ተለማመድሁ (ኢሳይያስ 12÷3)፤ በጌታ

ደስታ ከድነት ምንጮች ኀይል መቅዳት ጀመርሁ፡፡

ምስጋና ከከበበን ሁኔታ ይልቅ፣ ዐይኖቻችን ፊት ለፊታችን ያለው ደስታ ላይ እንድናደርግ ይረዳናል፡፡

> እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኃጢአት አስወግደን፣ በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ። የእምነታችን ጀማሪና ፍጹም አድራጊ የሆነውን ኢየሱስን እንመልከት፤ እርሱ በፊቱ ስላለው ደስታ መስቀሉን ታግሦ፣ የመስቀሉንም ውርደት ንቆ፤ በእግዚአብሔር ዙፋን ቀኝ ተቀምጦአል። እንግዲህ ዝላችሁ ተስፋ እንዳትቆርጡ፣ ከኀጢአተኞች የደረሰበትን እንዲህ ያለውን ተቃውሞ የታገሠውን እርሱን ዐስቡ። (ዕብራውያን 12፥1-4)

ኢየሱስ ዐይኖቹን ፊት ለፊቱ ያለው ደስታ ላይ በማድረግ፣ ማንም ላይ ደርሶ የማያውቀውን ታላቅ መከራ ተቀበለ፤ ፊት ለፊቱ ያለው ደስታ ስቅለቱን ተከትሎ የሚመጣው ትንሣኤው ነበር፡፡ መከራን ለመቀበል መታዘዙን ተከትሎ የሚመጣ ክብር ነበር፤ የኋላ ኋላም እኔና እናንተን ጨምሮ ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆችን ወደ መንግሥቱ ያመጣል፡፡

ይህ የእርሱን ፈለግ ለምንከተል ለእኛ የተቀመጠ መንገድ ነው፡፡ ራስን ከመካድና ሥጋን ከመስቀል ባሻገር፣ የሕይወት ትንሣኤ ይጠብቀናል፡፡ ሥጋ ላይ ከሚደርስ መከራ ባሻገር፣ ከኢየሱስ ጋር የጠበቀ ኅብረት ለማድረግ የሚያስፈልገው ዕድገት አለ፡፡ ከምድረ በዳ አስቸጋሪ ሁኔታ ባሻገር፣ ታላቅ ክብር አለ! ጳውሎስ፣ ‹‹የአሁኑ ዘመን ስቃያችን ወደ ፊት ሊገለጥ ካለው ለእኛ ከተጠበቀልን ክብር ጋር ሲነጻጸር ምንም እንዳይደለ እቈጥራለሁ›› በማለት ጽፏል (ሮሜ 8፥18)፡፡

እርሱ ከመመለሱ በፊት በቤተ ክርስቲያን የእግዚአብሔር ክብር ይገለጣል፤ ድምቀቱ እጅግ ታላቅ ከመሆኑ የተነሣ የአገሮችና የከተሞች ሰዎችን ወደ ድነት ይስባል፡፡ እግዚአብሔር እንዲያነጻቸው የፈቀዱ የኢየሱስ ተከታዮች ውስጥ የሚገለጠውን ኀይል የመሰለ

ክብር፣ ከዚያ በፊት እንዲህ ያለ ኃይል ሲገለጥ ምድር አይታ አታውቅም፡፡ ይህ ወደ ታላቅ የሰዎች መዳን የሚያደርስ የእርሱ መንፈስ መፍሰስ የሰው ማስታወቂያ እንዲነገር አይፈልግም፡፡ ያንን የሚያደርግ የእግዚአብሔር ኀይልና ክብር ብቻ ነው!

> **ወዳጆች ሆይ፣ እንደ እሳት የሚፈትን ብርቱ መከራ በመቀበላችሁ እንግዳ ነገር እንደ ደረሰባችሁ በመቁጠር አትደነቁ፤ ነገር ግን ክብሩ በሚገለጥበት ጊዜ ደስታችሁ ታላቅ እንዲሆን የክርስቶስ መከራ ተካፋዮች በመሆናችሁ ደስ ይበላችሁ።** (1 ጴጥሮስ 4፥12-13)

በድጋሚ ፊት ለፊታችን ያለው ደስታ ምንድነው? በማለት እጠይቃለሁ፡፡ ለክርስቶስ በመታዘዛችን የእርሱ በሆንነው በእኛ ውስጥ የሚገለጥ የእርሱ ክብር ነው፡፡ ተቃውሞው ከባድ የመሆኑን ያህል፣ ክብሩም ታላቅ እንደሚሆን በመገንዘብ፣ የደስታችሁ ልክ በተቀበላችሁት መከራ መጠን እንደሚሆን ልብ በሉ!

## ለሕይወት እንኳ አለመሳሳት

ወዳጆቼ፣ ተቃውሞ ሲመጣ እግዚአብሔርን መፈለጋችሁን ትተዋላችሁን! የእግዚአብሔር መንግሥትም ሆነ እናንተ የምታገኙት ድል ታላቅ የሚሆነው፣ የጦርነቱን ታላቅነት ያህል በመሆኑ፣ እርሱ ወደ ሕይወት አስቸጋሪ ሁኔታዎች እንደሚመራችሁ አውቃለሁ፡፡ ይሁን እንጂ፣ ጦርነቱ መካከል ምን ጊዜም ይህን ዋስትና ፊታችሁ አኑሩ፡-

> **እግዚአብሔር ታማኝ ነው፤ ስለዚህ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይተዋችሁም፤ ነገር ግን በምትፈተኑበት ጊዜ ፈተናውን መታገሥ እንድትችሉ መውጫ መንገዱን ያዘጋጅላችኋል።** (1 ቆሮንቶስ 10፥13)

እያንገዋበበ ያለው ፈተና ምንም ይሁን ምን፣ በዚያ ውስጥ

በድልና በክብር ማለፍ የምንችልበት ኀይል ይኖረናል፡፡ ያ ባይሆን ኖሮ፣ መጀመሪያውኑ ፈተናው ወደ እናንተ አይመጣም ነበር፤ እግዚአብሔርም አይፈቅድለትም ነበር!

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይልቅ ሕይወታችሁን ወድዳችሁ ቢሆን ኖሮ፣ አዳጋች ሁኔታ ሲገጥማችሁ ውጊያውን ታቋርጡ ነበር፡፡ እግዚአብሔርን መፈለጋችሁን ትታችሁ፣ ፍሬ ቢስ ሕይወት ትኖሩ ነበር፡፡

ራእይ 12፥11፣ ‹‹እነርሱም በበጉ ደም፣ በምስክርነታቸውም ቃል ድል ነሡት፤ እስከ ሞት ድረስ እንኳ ለነፍሳቸው አልሳሱም›› ይላል፡፡

ከእግዚአብሔር ፈቃድ ይበልጥ ለራሳቸው የሚያስቡ ሰዎች፣ ሕይወታቸውን የሚወዱ ናቸው፤ እነርሱን በተመለከተ ኢየሱስ፣ ‹‹ነፍሱን ሊያድን የሚፈልግ ሁሉ ያጠፋታል፤ ነገር ግን ነፍሱን ስለ እኔ የሚያጠፋት ያድናታል›› ይላል (ማቴዎስ 16፥25)፡፡

በሚመጣው ዘመን ፊት ለፊታችን ያለውን በጽናት የምናልፍበት መንገድ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈጸም ሲባል ሕይወታችንን እንኳ ለማጣት ፈቃደኛ በመሆን ነው፡፡ ‹‹መንፈስ ከላይ እስኪፈስልን፣ ምድረ በዳው ለም መሬት፣ ለሙ መሬትም ጫካ እስኪመስል ድረስ›› ወደ ፊት መገሥገሣችሁን እንድትቀጥሉ አበረታታችኋለሁ (ኢሳይያስ 32፥15)፡፡

ምድረ በዳ የጦር መሣሪያችንን በማስቀመጥ ተደላድለን የምንቀመጥበት ቦታ አይደለም! የጌታን ፈቃድ ለማድረግ የምንበረታበት፣ የምንደፍርበትና የምንጠነክርበት ስፍራ ነው፡፡ ራሳችንን ለእግዚአብሔር የምናስገዛበትና አጥብቀን ዲያብሎስን የምንዋጋበት ስፍራ ነው፡፡

አሁን ያላችሁት ምድረ በዳ ውስጥ ከሆነ፣ በልባችሁ ያለውን ለማወቅ ወደዚህ ቦታ ያመጣችሁ እግዚአብሔር መሆኑን እርግጠኞች ሁኑ፡፡ መጀመሪያ ላይ የዲያብሎስ ፈተናዎች ይሆናሉ በማለት ያሰብሁዋቸው ነገሮች፣ ለክርስቶስ መገዛት ያለባቸው የሕይወቴ

ድብቅ ገጽታዎች መሆናቸውን ተረድቻለሁ፡፡ ሰማያዊውን ሽልማት ለማግኘት በምትተጉበት ጊዜ፣ እነዚህን ቃሎች ልብ በሉ፡-

> በክርስቶስ ሁልጊዜ በድል አድራጊነት ለሚያዞረን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን (2 ቆሮንቶስ 2፥14)።
>
> ከክርስቶስ ፍቅር የሚለየን ማን ነው? ችግር ነው ወይስ ሥቃይ፣ ወይስ ስደት፣ ወይስ ረሀብ፣ ወይስ ዕራቁትነት፣ ወይስ አደጋ፣ ወይስ ሰይፍ፤... በዚህ ሁሉ በወደደን በእርሱ ከአሸናፊዎች እንበልጣለን። (ሮሜ 8፥35፣37)
>
> ነገር ግን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ድልን ለሚሰጠን ለእግዚአብሔር ምስጋና ይሁን። (1 ቆሮንቶስ 15፥57)

እርሱን መፈለጋችሁን አትተው፡፡ ተስፋ አትቁረጡ፡፡ ያላችሁበት ሁኔታ ምንም ይሁን ምን፣ እርሱ የሰጣችሁን ራእይ ያዙ፡፡

ዮሴፍ ጉድጓድ ውስጥ፣ በኋላም በባዕድ አገር እስር ቤት በተጣለ ጊዜ የእርሱ ጉዳይ ተስፋ የሌለው ይመስል ነበር፡፡ ሕይወቱ ያበቃ ይመስል ነበር፡፡ ከዚያ ወጥቶ እንዴት የወደ ፊት ሕይወት ሊኖረው ይችላል? የሚያሰኝ ነበር፤ ይሁን እንጂ፣ ‹‹ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን እንዲህ አይደለም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል›› መባሉን አትርሱ (ማርቆስ 10፥27)

እናንተን በተመለከተም ሁኔታው የቱንም ያህል ከባድ ቢሆን፣ ‹‹ለሚያምን ሁሉ ይቻላል›› መባሉን አስታውሱ (ማርቆስ 9፥23)፡፡

ዐይኖቻችሁን ፊት ለፊታችሁ ያለው ደስታ ማለት ለእናንተ የሚገለጠው የእርሱ ክብር ላይ አድርጉ፡፡ ይህ የሚገጥማችሁን ማንኛውንም ፈተና የምታሸንፉበት ብርታት ይሰጣችኋል፡፡ በፍጹም ልባችሁ እርሱን መፈለጋችሁን ቀጥሉ፤ በቃሉ በኩል በመንፈሱ የሚነግራችሁንም እመኑ፡፡ ያን ካደረጋችሁ ምድረ በዳ ውስጥ ድል ትለማመዳላችሁ፡፡

እንዳትወድቁ ሊጠብቃችሁና ያለ ነቀፋና በደስታ በክብሩ ፊት ሊያቀርባችሁ ለሚችለው፤ እርሱ ብቻ አዳኛችን ለሆነው አምላክ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከዘመናት ሁሉ በፊት አሁንና እስከ ዘላለምም ድረስ ክብር፣ ግርማ፣ ኀይልና ሥልጣን ሁሉ ይሁን፤ አሜን። (ይሁዳ 1፥24-25)።

# የውይይት ጥያቄዎች

ይህን መጽሐፍ እያነበብህ ያለኸው የምድረ በዳ ሕይወት ጥናት ወይም ኮርስ ጋር ከሆነ (ይህ ትልቅ ነገር ነው) የእያንዳንዱን ቪዲዮ ትምህርት እንድትመለከትና በቡድን ሆናችሁ ተያይዘው ባሉት ጥያቄዎች እንድትወያዩ እመክራችኋለሁ፡፡ የቪዲዮ ትምህርቶቹ ከዚህ መጽሐፍ ዐቢይ ሐሳብ ጋር ይዛመዳሉ፣ ዐቢይ ሐሳቦቹን አጉልተው ያቀርባሉ፤ ስለሆነም ተሳታፊዎቹ ሁሉ ትምህርቱን ማየታቸውና መጽሐፉን ማንበባቸው በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## ትምህርት 1

*ምዕራፍ 1 አንብብ*

1. በእግዚአብሔር ሁሉ ቦታ መገኘትና እርሱ በፈቀደ ጊዜ ራሱን በመግለጡ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? የሁለቱን ልዩነት መረዳት የሚጠቅመን እንዴት ነው?

2. ምድረ በዳ ውስጥ መሆን አለመሆናችን ለማወቅ ወቅቱን ለይተን መገንዘብ የሚጠቅመው እንዴት ነው?

3. በምድረ በዳ ውስጥ የምንሆንበትን ጊዜ ሆን ብለን ኀጢአት እንድናደርግ ወይም እምነታችንን እንድንተው እኛን ለመፈተን ሰይጣን የሚጠቀምበት ለምን ይመስልሃል?

4. የምድረ በዳ ቆይታችንን እንድናረዝም እግዚአብሔር የሚፈቅደው ለምንድነው?

## ትምህርት 2

*ምዕራፍ 2 እና 3 አንብብ*

1. ምድረ በዳ አያሌ ዓላማዎች አሉት፡፡ በዚህ ትምህርት ከተዘረዘሩት ሰባት ዓላማዎች አንተ ካለህበት ሁኔታ ጋር ይበልጥ የሚስማሙት የትኞቹ ናቸው? ለምን?

2. ምድረ በዳ ውስጥ በምንሆንበት ጊዜ ለእግዚአብሔር መታዘዝ መንፈሳዊ ዕድገት እንደሚያስገኝ የምታስቡት ለምንድነው?

3. ምድረ በዳ ራሳችንን የምናውቅበት ጊዜ ነው፤ ምድረ በዳ ውስጥ በነበራችሁበት ጊዜ ስለ ራሳችሁና ከእግዚአብሔር ጋር ስላላችሁ ግንኙነት የተማራችሁት ጥቂት ነገሮች ምንድናቸው?

4. በዚህ ራሳችሁን ዝቅ በምታደርጉበት ጊዜ፣ እግዚአብሔርን ብርታታችሁ ስለ ማድረግ ምን ተማራችሁ?

## ትምህርት 3

*ምዕራፍ 4 አንብብ*

1. ተስፋው በተሰጠበት ጊዜና ተስፋው በሚፈጸምበት ጊዜ መካከል ሁሌም ሂደት አለ፤ ይህ ሂደት አስፈላጊ የሆነው ለምን ይመስልሃል?

2. የተሰጠህ ተስፋ የሚፈጸምበት ሂደት በሕይወትህ ሲሠራ ያየኸው እንዴት ነበር?

3. ሂደቱ ውስጥ ከመግባታችሁ በፊት እግዚአብሔር አስቀድሞ ተስፋ የሚሰጠው ለምን እንደ ሆነ ታስባለህ?

4. በተለምዶ ከሚደረገው ሰው ሠራሽ ዕቅድ ይልቅ፣ ለሕይወታችሁ ከእግዚአብሔር ተስፋ መቀበል ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?

## ትምህርት 4

*ምዕራፍ 5 እና 6 አንብብ*

1. የሳኦልንና የዳዊትን ሕይወት ማነጻጸር እግዚአብሔር እኛን በምድረ በዳ ውስጥ ማንጻቱ አስፈላጊ መሆኑን ለመረዳት የሚያስችለን እንዴት ነው?

2. ወርቅ በእሳት ሲነጥር ይበልጥ ተጣጣፊ ይሆናል፤ እግዚአብሔር እኛን ሲያነጻ ለእርሱ ይበልጥ ለስላሳ እንሆናለን። ለእግዚአብሔር የበለጠ ለስላሳ መሆን ምን ማለት እንደ ሆነ ግለጽ።

3. የእግዚአብሔር የሚያነጻና የሚያጠራ እሳት በሕይወታችን ውስጥ ተደብቆ ያለውን ኀጢአት ወይም ድካም ሲገልጠው የእኛ ምላሽ ምን መሆን አለበት?

4. የሚያጠራና የሚያነጻ የእግዚአብሔር እሳት የበለጠ ኢየሱስን ማሳየት እንድትችሉ የሚያደርጋችሁ እንዴት ነው?

## ትምህርት 5

*ምዕራፍ 7 አንብብ*

1. እግዚአብሔር ማጉረምረምን የሚጠላው ለምንድነው? በአሁኑ ጊዜ በሕይወትህ የምታጉረመርምበት ነገር ምን ይመስላል?

2. ሚልክያስ ውስጥ ባሉት አጉረምራሚዎችና በነቢዩ ኤርምያስ ማጉረምረም መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው? እግዚአብሔር በእነዚህ ወገኖች ሲቆጣ፣ ለኤርምያስ ማጉረምረም ግን መልስ የሰጠው ለምንድነው?

3. ፍርድ መወሰን እንጂ፣ ውግዘት አይደለም። ፍርድ ከእግዚአብሔር ቤት በሚጀምርበት ጊዜ ማን ለአገልግሎቱ

ተገቢ መሆኑን እርሱ ይወስናል፡፡ እግዚአብሔር ይህን ውሳኔ የሚያደርገው ምን ለመፈለግ ይመስልሃል?

4. እግዚአብሔር ለአገልግሎቱ የሚስማማ ዕቃ ይፈልጋል፡፡ በመጠራትና በመመረጥ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት ትገልጡታላችሁ?

## ምዕራፍ 6

*ምዕራፍ 8 አንብብ*

1. መከራ ስጦታ መሆኑን ስትሰማ መጀመሪያ ላይ ምላሽ ምን ነበር? ይህን ትምህርት ስትጨርስ አመለካከትህ የተለወጠው እንዴት ነበር?

2. እግዚአብሔር መታገሥ ከምትችሉት በላይ እንድትፈተኑ አይፈቅድም፡፡ ይህ እውነት የሚያበረታታችሁ እንዴት ነው?

3. እግዚአብሔር አሁን ባላችሁ ብርታት አይተዋችሁም፡ ፡ ይህ እግዚአብሔር ለሕይወታችሁ ስላለው ዕቅድ ምን ያስተምራችኋል?

4. እግዚአብሔር አሁን መከራ እንዲደርስብን የሚፈቅደው ወደ ፊት ለሚገጥመን ነገር ዝግጁ ሊያደርገን ነው፡፡ አሁን እያለፍህበት ያለው ፈተና ምክንያት ግልጽ እንዲሆንልህ ስለ ወደ ፊቱ ሕይወትህ እግዚአብሔር የገለጠልህ ምንድነው?

## ትምህርት 7

*ምዕራፍ 9 አንብብ*

1. እግዚአብሔርን መከተል አንዳንዴ ትርጒም ላይሰጥ ይችላል፡፡ ከተለመደው የነገሮች ሂደት፣ ‹‹ወጣ ያለ›› ነገር በሚያደርግበት ጊዜ በእግዚአብሔር መተማመን የሚያስቸግረው ለምንድነው?

2. እናንተ በጠበቃችሁበት ጊዜ እግዚአብሔር እርምጃ ሳይወስድ ሲቀር ምን ይሰማችኋል? የእግዚአብሔር ተስፋ ሲዘገይ ምን ዐይነት ፈተናና ጫና ይሰማችኋል?

3. ከሥጋ የተወለደ ማንኛውንም ነገር የሚያድገውም በሥጋ መሆን አለበት የሚለው እውነት በሕይወታችሁ ሲፈጸም ያያችሁት እንዴት ነበር? ይህ እግዚአብሔር ራሱ በሕይወታችሁ እንዲወለድ ከሚያደርገው የሚለየው እንዴት ነው?

4. በሕይወታችሁ የእግዚአብሔርን መንገድ እየተከተላችሁ ለመሆኑ ማረጋገጫችሁ ምንድነው?

## ትምህርት 8

*ምዕራፍ 10 አንብብ*

1. ምድረ በዳ እግዚአብሔር ራሱን የሚገልጥበት ቦታ ነው፡፡ እውነቱ እንዲህ ከሆነ፣ በዚሁ ጊዜ እግዚአብሔር በጣም የራቀ የሚመስለው ለምንድነው?

2. በረከቱን ሳይሆን መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፈለግ ምን ማለት ነው?

3. ከራሱ ከእግዚአብሔር ይልቅ ከእርሱ የተቀበላችሁት ተስፋ ወይም ጥሪ የበለጠ አስፈላጊ ከሆነ አደገኛ የሚሆነው እንዴት ነው?

4. እግዚአብሔር መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ላሉት የእምነት አርበኞች ራሱን የገለጠበትን ምሳሌ ስታዩ፣ በምድረ በዳ ከምታሳልፉት ወቅት ከእርሱ እንድትቀበሉ የምትጠብቁትን የሚለውጠው እንዴት ነው?

## ትምህርት 9

*ምዕራፍ 11 አንብብ*

1. የመንፈሳዊ ድርቀት ጊዜ ሲገጥመን ወዴት መሄድ እንዳለብን ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድነው?
2. ምንም እንኳ ያንን ለማድረግ ስሜቱ ባይኖረንም የጠለቀ የጸሎትና የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቢኖረን መንፈሳዊ ሕይወታችን ሥር እንዲሰድና እንዲበረታ የሚያደርገው እንዴት ነው?
3. የምትሰበስበው መከር ላይ ታላቅ ጥቃት የሚቃጣው መከሩ ገና ከመታየቱ በፊት መሆኑን ማወቅህ የሚያበረታታህ እንዴት ነው?
4. የእግዚአብሔርን ታማኝነት ማሰላሰል የምድረ በዳውን ወቅት የሚለውጠው እንዴት ነው?

## ትምህርት 10

*ምዕራፍ 12 አንብብ*

1. ምድረ በዳ ወቅቱ ለሚጠይቀው ለውጥ ያዘጋጀህ እንዴት ነበር?

2. መለወጥ አስቸጋሪ የሆነው ለምንድነው? ራስህን ከለውጥ ጋር ለማስማማት ብዙውን ጊዜ ትልቅ እንቅፋት የሚሆንብህ ምንድነው?

3. አቁማዳውን የማደስ ሂደትን በተመለከተ ጐላ ብሎ የሚታይህ ምንድነው? ለምን ጐላ ብሎ ታየህ?

4. አዲሱን ለመያዝ አሮጌውን መተው አለብን፡፡ አዲሱን ለመያዝ መተው ያለብህ አሮጌ ነገሮች ምንድናቸው?

# ተጨማሪ

## ለሰው ሁሉ የተሰጠ - ድነት

**ኢየሱስ ጌታ ነው ብለህ በአፍህ ብትመሰክር፣ እግዚአብሔርም ከሙታን እንዳስነሣው በልብህ ብታምን፣ ትድናለህ። የምትጸድቀው በልብህ አምነህ ነው፤ የምትድነውም በአፍህ መስክረህ ነውና።**
**- ሮሜ 10፥9-10**

እግዚአብሔር የበዛና የሞላ ሕይወት እንዲኖርህ ይፈልጋል፡፡ እርሱ ለአንተ ያስባል፤ ለሕይወትህም ዕቅድ አለው፡፡ ይሁን እንጂ ወደ ተዘጋጀልህ በረከት የምትገባባት አንድ መንገድ ብቻ አለ፡- በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ድነት በመቀበል፡፡

በኢየሱስ ሞትና ትንሣኤ በኩል እንደ ተወደዱ ወንዶችና ሴቶች ልጆች፣ ወደ መንግሥቱ የምትገቡበትን መንገድ እግዚአብሔር አዘጋጅቶአል፡፡ የኢየሱስ መስቀል ላይ መሥዋዕት መሆን አንተ ዘላለማዊና የበዛ ሕይወት እንድታገኝ አድርጎአል፡፡ ድነት ለአንተ የተሰጠ የእግዚአብሔር ስጦታ ነው፤ ይህ እንደ ደመወዝ የምታገኙት ወይም የሚገባችሁ ሰዎች ስለሆናችሁ እንደ ሽልማት የምትቀበሉት አይደለም፡፡

ይህን ክቡር ስጦታ ለመቀበል በመጀመሪያ፣ ከፈጣሪ አምላክህ ውጪ በመኖር ኀጢአት ማድረግህን ተቀበል፤ የሌሎች ኀጢአቶችህ ሁሉ ሥረ መሠረት ይኸው ነው፡፡ በእንዲህ ያለ ሁኔታ ንስሓ ማድረግህ ድነትን ለመቀበል ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ ከሐዋርያት ሥራ እንደምንመለከተው አምስት ሺህ ሰዎች በዳኑበት ቀን ጴጥሮስ ይህን በግልጽ ተናግሮአል፡- ‹‹እንግዲህ ኀጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሓ ግቡ፤ ከመንገዳችሁም ተመለሱ›› (የሐዋርያት

ሥራ 3፥19)። እያንዳንዳችን የተወለድነው የኀጢአት ባርያዎች ሆነን እንደ ነበር መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ አድርጓል። ይህ ኀጢአት በገዛ ፈቃዱ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ከጀመረው ከአዳም ኀጢአት የመጣ ነው። ንስሓ ለራሳችሁና የሐሰት ሁሉ አባት ለሆነው ለሰይጣን ከመታዘዝ፣ ሕይወቱን ለእናንተ ለሰጠው ለአዲሱ ጌታችሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ለመታዘዝ መመለስ ማለት ነው።

ኢየሱስን የሕይወታችሁ ጌታ አድርጉት። ኢየሱስን የሕይወታችሁ፣ ‹‹ጌታ›› ማድረግ እርሱ የመላው ሕይወታችሁ (መንፈስ፣ ነፍስና ሥጋችሁ) ባለቤት እንዲሆን፣ ያላችሁንና የሆናችሁትን ሁሉ ለእርሱ መስጠት ማለት ነው። ያኔ እርሱ በሕይወታችሁ ፍጹም ሥልጣን ይኖረዋል። ይህን ስታደርጉ እግዚአብሔር ከጨለማ አውጥቶ ወደ መንግሥቱ ብርሃንና ክብር ያሻግራችኋል። በአጭር ቃል ከሞት ወደ ሕይወት ትሄዳላችሁ - የእርሱ ልጅ ትሆናላችሁ!

በኢየሱስ በኩል ድነት ማግኘት ከፈለጋችሁ እንዲህ በማለት ጸልዩ፡-

*በሰማይ የምትኖር እግዚአብሔር ሆይ፣ ኀጢአተኛ መሆኔንና ከአንተ የጽድቅ ሚዛን መጉደሌን እቀበላለሁ፤ ለኀጢአቴ የዘላለም ፍርድ የሚገባኝ ሰው ነኝ። አንተ ግን ባለሁበት ሁኔታ ስላልተውኸኝ አመሰግንሃለሁ፤ ለእኔ መስቀል ላይ እንዲሞትና ኀጢአቴንም እንዲሸከም ከድንግል ማርያም የተወለደውን የአንተን ብቸኛ ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ላክኸው አምናለሁ። እርሱ ከሞት መነሣቱንና አሁን ጌታዬና አዳኜ በመሆን በአንተ ቀኝ መቀመጡን አምናለሁ። ስለዚህ በዛሬው ቀን ከአንተ ተለይቼ በመኖሬ ንስሐ እገባለሁ፤ ሙሉ በሙሉ ሕይወቴን ለኢየሱስ ጌትነት እሰጣለሁ።*

*ኢየሱስ ሆይ፣ ጌታዬና አዳኜ አድርጌሃለሁ። በመንፈስህ ወደ ሕይወቴ ና፤ እኔንም የእግዚአብሔር ልጅ ወደ መሆን*

*ለውጠኝ፡፡ ከዚህ በፊት ሳደርግ የነበረውን የጨለማ ነገር ሁሉ እክዳለሁ፤ ከእንግዲህም ለራሴ አልኖርም፡፡ ይልቁን፣ በአንተ ጸጋ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረኝ ሕይወትህን ለእኔ ለሰጠኸው ለአንተ እኖራለሁ፡፡*

*ጌታ ሆይ፣ ተመስገን፤ አሁን ሕይወቴ ሙሉ በሙሉ በእጅህ ነው፤ ቃልህ እንደሚናገረው በፍጹም አላፍርም፡፡ በኢየሱስ ስም አሜን፡፡*

እንኳን ወደ እግዚአብሔር ቤተ ሰብ መጣህ! ይህን ድንቅ ዜና ለሌላው አማኝ እንድታካፍል አበረታታሃለሁ፡፡ መጽሐፍ ቅዱስን የሚያምን የአንድ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን አባል እንድትሆንና አዲስ ባገኘኸው እምነት ሊያበረታቱህ ከሚችሉ ሰዎች ጋር እንድትቀራረብም እመክርሃለሁ፡፡ በአካባቢህ ተስማሚ ቤተ ክርስቲያን እንድታገኝ እንድንረዳህ፣ ወደ አገልግሎታችን ለመጻፍ ነጻነት ይሰማህ (Messengerinternational.org ጐብኝ)፡፡

እጅግ በጣም ጠቃሚ ጉዞ ጀምረሃል፡፡ በመገለጥ፣ በጸጋና በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ጋር በምታደርገው ግንኙነት ሕይወትህ ይደግ፡፡

# የሰይጣን ሸንገላ

## *ከአደገኛ የመሰናከል ወጥመድ ነጻ ሆኖ መኖር*




*የሰይጣን ሸንገላ፣ የተሰኘው ይህ መጽሐፍ አማኞችን ከእግዚአብሔር ፈቃድ ለማስወጣት ጠላት ከሚጠቀምበት አሳሳች ወጥመዶች አንዱን ያጋልጣል — ይኸውም መሰናከያ ነው። አብዛኞቹ ሰዎች በዚህ መሰናከያ ተጠምደዋል፣ ያም ሆኖ ግን መጠመዳቸውን እንኳ አላወቁም።*

*አትሞኙ! አለ ክርስቶስ፣ <<ሰዎችን የሚሰናከል መምጣቱ አይቀርም>> (ሉቃስ 17፥1)። መሰናከልን ወይም አለመሰናከልን እናንተ መምረጥ አትችሉም፤ ለዚያ የምትሰጡትን ምላሽ ግን መምረጥ ትችላላችሁ። የሚመጣውን መሰናከያ በአግባቡ ካስተናገዳችሁት ብርቱዎች እንጂ መራራዎች አትሆኑም። ከእግዚአብሔር ጋር የማያቋርጥ ኅብረት ሊኖራችሁ የሚችለው በምትሰጡት ትክክለኛ ምላሽ መሠረት ብቻ ነው።*

*በዚህ መልእክት አማካይነት ጆን ቢ.ቨሬ ከጥርጥርና ካለ መታመን ማነቆ ነጻ ሆናችሁ በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ መሆን የምትችሉበትን ትጥቅ ያካፍላችኃል። ከተጠቂነት ዝንባሌ በማምለጥ ነገሮችን ከሚያባብስና ወደ ተስፋ መቁረጥ ከሚያደርስ ሸክም ነጻ መሆን ትችላላችሁ። በከፍተኛ ደረጃ ለእግዚአብሔር ፈቃድ የመገዛትን ምስጢር ስትረዱ በሕይወታችሁ ይቅር ባይነት፣ ዕርቅና መጠኑ እያደገ የሚሄድ ደስታ ይበዛል።*

**ከ CloudLibrary.org ማግኘት ይቻላል።**




**ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል የሚንቀሳቀሰው ግለ ሰቦች፣ ቤተ ሰቦች፣ አብያተ ክርስቲያናት፣ እና አገሮች ሕይወት ለዋጭ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲገነዘቡና እንዲለማመዱ ለመርዳት ነው። ይህ ግንዛቤ ለሕይወት ኀይል ይሆናል፤ ማኅበረ ሰቦችን ይለውጣል፤ ዓለምን እየናጠ ላለው ፍትሕ አልባነትም መፍትሔ የሚሆን ምላሽ ያስገኛል።**

---

CLOUD LIBRARY

ክላውድ ላይብረሪ ፓስተሮችና በዓለም ዙሪያ ያሉ መሪዎች በገዛ ቋንቋቸው ጠቃሚ ትምህርቶች የሚያገኙበት ቀጥተኛ የኢንተርኔት መድረክ ነው።

ጆንና ሊዛ ቢቨሬ ከ100 ቋንቋዎች በላይ ያዘጋጁቸው ከኢንተርኔት ማውረድ የሚቻሉ ጠቃሚ ነገሮችን ለማግኘት ወደ CloudLibrary.org ሂዱ!

**መጻሕፍት፣ ቪዲዮዎች፣ የድምፅ ትምህርቶች፣ በድምፅ የቀረቡ መጻሕፍት፣ መጽሐፍ ቅዱሶች...**

የበለጠ ትፈልጋለህ? እዚህ እስካን አድርግ

CloudLibrary.org

# እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!

# አጋዥ ጠቃሚ ነገሮች

አሁን በእጅህ ያለው መጽሐፍ *እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* የተሰኘውን መጽሐፍ አስመልክቶ ጆን ቢቨሬ ያዘጋጀው ካሪኩለም አካል ነው። ይህን መጽሐፍ ማንበብ፣ ተያይዞ ካለው DVD ROM እና ከCloudLibrary ማውረድ በሚቻለው አጋዥ የትምህርት *መሣሪያዎች* መጠቀም፣ የዚህን ብርቱና ሕይወት ለዋጭ ተከታታይ ትምህርቶች ማንኛውንም ክፍል ማጥናት ያስችልሃል። ትምህርቱን በአግባቡ ማጥናት የክርስትና ጉዞህን ያጐለብታል፤ የበለጠ እግዚአብሔርን እንድታገለግልም በጐ ተጽዕኖ ያሳድርብሃል።

*እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* የሚከተሉትን ጠቃሚ ነገሮች አካትቶአል። በግል በምትጠቀምባቸው ነገሮች ሁሉንም ማውረድ ይቻላል —

- *እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* ዋናው መጽሐፍ
  ከዚህ ካሪኩለም አካል ታትሞ የሚገኘው ይህ ብቻ ነው። መጽሐፉ በካሪኩለሙ DVD ውስጥ በebook መልክ ይገኛል።
- *እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* ካሪኩለም DVD ROM
  ተያይዞ ያለው ዲስክ የካሪኩለሙ ትምህርቶችን ሁሉ በዲጂታል መልክ አካትቶአል። ይህን DVD ROM ቤትህ ባለው DVD ማጫወቻ መጠቀም አትችልም። ይሁን እንጂ፣ ፋይሎቹን ሁሉ በታብሌት፣ በኮምፒዩተር ወይም በስማርት ፎን ማውረድና ማንበብ ይቻላል።
- *እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* መጽሐፍ በድምፅ
  እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?! መጽሐፍ ክፍሎችን ሁሉ በMP3 በአማርኛ የሚነበቡበት ነው።
- *እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* ቪዲዮ ተከታታይ ትምህርቶች
  11 ተከታታይ የቪዲዮ ትምህርቶች በMP4 ተዘጋጅተዋል።
- ተጨማሪ ነገሮች
  በተጨማሪም ይህ DVD ROM *ተስፋ እንዳትቆርጥ የሚያስፈልግህ ኀይል — ጽናት፤ የጽናት መጽሐፍ ማጥኛና ማሰላሰያ፤ እንስት አንበሶቹ ይነሣሉ፤ መንፈስ ቅዱስ — እንደ መግቢያ፤ የሰይጣን ሽንገላ* የተሰኙ ሌሎች መጻሕፍትንም ይዞአል።

በዚህ ባለ ብዙ ገጽታ አጋዥ የትምህርት ሚዲያ ebooks እና መጽሐፍ ቅዱሶች በነጻ ማግኘት ይቻላል

ከ CloudLibrary.org አውርዱ

# እነዚህ ክፍለ ትምህርቶች ሁሉ
# ለእናንተ የተሰጡ ናቸው !




ይህን DVD ROM ኮፒ ለማድረግ፣ ጽሑፎችን ወይም ሌሎች ነገሮችን ኮፒ ለማድረግና ለወዳጆቻችሁ በኢ.-ሜይል ለመላክ፣ በወርድ ዶኩሜንት ኮፒ ለማድረግና ፔስት አድርጋችሁ ትምህርቶቹን ለቤተ ክርስቲያናችሁ አባሎች ለመላክ፣ እንዲሁም ሌሎች እንዲጠቀሙባቸው በኢንተርኔት ለመጫን ነጻነት ይሰማችሁ። ትክክለኛውን የእግዚአብሔር ቃል ትምህርትና ኀይል ያለው ክርስትና ሕይወትን ለሚራቡ ሁሉ እነዚህን አጋዥ ምንጮች አካፍሉ።

*እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!* መጽሐፍ ትምህርቶችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ፡-



<u>በዚህ DVD ROM ውስጥ ያሉትን ፋይሎች በተለመደው ዐይነት ቪዲዮ ማጫወቻ መጠቀም አይቻልም፤</u> ምክንያቱም፣ የተለያዩ ነገሮችን ማለትም ቪዲዮ፣ ኦዲዮና የጽሑፍ ድብልቅ በመያዙ ነው። ማጫወትና መመልከት የሚቻለው በኮምፒዩተር ወይም በዲጂታል መንገድ ብቻ ነው።

<u>MP4 ቪዲዮ ፋይሎችን፣</u> በታብሌትህ ወይም በኮምፒዩተርህ ማውረድና ማጫወት ይቻላል።

<u>MP3 የድምፅ ፋይሎችን፣</u> በኦዲዮ ሚዲያ ማጫወቻ፣ በስማርት ፎን ወይም በኮምፒዩተር ላይ ማውረድ ይቻላል።

<u>eBooks</u> በስልክህ፣ ታብሌት ወይም ኮምፒዩተር ላይ ማውረድ ይቻላል። በቀላሉ ለማንበብ፣ ለማተምና ለማባዛት ይመቻሉ። አንዳንድ ጽሑፋን ክፍሎች ዶክሜንትህ ላይ ኮፒ አድርግ !

ከሚከተለው ዌብሳይት በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጁ ተጨማሪ ትምህርቶች ማግኘት ይቻላል፡-

ከ CloudLibrary.org አውርዱ

# እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው? !

## አጋዥ ዲስክ

በኮምፒዩተር ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል



ቪዲዮዎችን ተመልከቱ

ክCloudLibrary.org ሌሎች ጠቃሚ ነገሮችን አውርዱ

## ጆን ቢቨሬ

MESSENGER INTERNATIONAL
MessengerInternational.org

ይህን ካሪኩለምና ሌሎች የጆንና ሊዛ ቢቨሬ ትምህርቶች ከሜሴንጀር ኢንተርናሽናል ተከታታይ ነጻ ቪዲዮዎችና አስፈላጊ ነገሮች

ክCloudLibrary.org ዌብሳይት አውርዱ

በብዙ ቋንቋዎች የተዘጋጁ ተጨማሪ ጠቃሚ ነገሮች ክyoutube.com እና youku.com እና ሌሎች ሚዲያዎች መመልከትና ከዚያ ማውረድ ይቻላል፡፡

## አዳጋችና አስቸጋሪ ወቅቶች ሲገጥሙህ ግራ በመጋባት፣ <<እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!>> በማለት እየጠየቅህ ይሆን?

ምናልባት በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ተናግሮህ ይሆናል፤ አሁን ግን፣ ምክንያቱ ባልታወቀ ሁኔታ በፍጹም ድምፁን አጥፍቶብሃል። ምናልባትም፣ የምትችለውን ያህል በእምነት እየተንቀሳቀስህ ይሆናል፤ ይሁን እንጂ፣ በፍጹም ሓልዎቱን መለማመድ አልቻልህም። አሁን ያለህበት ቦታ ወይም ሁኔታ ምድረ በዳ ሊሆን ይችላል፤ ምድረ በዳ የእግዚአብሔርን ተስፋ ቃል በመቀበልና ተስፋ ቃሉ ሲፈጸም በማየት መካከል ያለ ቦታ ነው።

ግን፣ ደስ የሚያሰኝ ዜና አለ፤ አሁን ያለህበት ቦታ፣ ምንም ዓላማ የሌለውና ጠፍ ምድር አይደለም። እግዚአብሔር ምድረ በዳውን እርሱ ላዘጋጀው ፍጻሜ አንተን ለማዘጋጀት ይጠቀምበታል፤ ያ የሚሆነው ግን በትክክል አቅጣጫ ይዘህ ከተጓዝህ ነው። ብዙዎች በስሕተት እንደሚሉት፣ ይህ ቦታ ወይም ወቅት እግዚአብሔርን በትዕግሥት የመጠበቅ ጉዳይ አይደለም። አሁን ባለህበት ምድረ በዳ ውስጥ በድል ለማለፍ የአንተም ትልቅ ድርሻ ይኖራል። ወዲያ ወዲህ በመንከራተት ጊዜህ እንዳይባክን ከፈለግህ፣ የአንተ ድርሻ ምን እንደ ሆነ መረዳቱ በጣም አስፈላጊ ነው።

በዚህ ዐይን ገላጭ መጽሐፍ፣ ከፍተኛ ተነባቢነት ያለው ደራሲ ጆን ቢቨሬ፣ በደረቅና አዳጋች ወቅቶች ውስጥ አልፈህ እግዚአብሔር ለአንተ ወዳዘጋጀው መግባት እንድትችል ሁነኛ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታዎችንና ትምህርት ሰጪ ታሪኮችን ያቀርብልሃል።




**እግዚአብሔር ሆይ፣ ወዴት ነው ያለኸው?!**
**የተሰኘ አጋዥ ዲቪዲ የታከለበት**



**ጆን ቢቨሬ** በእግዚአብሔር ቃል ባለው ድፍረትና የማያወላውል ዐቋሙ የታወቀ ዓለም አቀፍ ተናጋሪና ከፍተኛ ተነባቢነት ያላቸው አያሌ መጻሕፍት ደራሲ ነው። እርሱና ሚስቱ ሊዛ ሜሴንጀር ኢንተርናሽናል የተሰኘ አገልግሎት መሥራቾች ሲሆኑ፣ ይህ አገልግሎት ዓለማችንን መለወጥ የሚችሉ ቆራጥ የክርስቶስ ተከታዮች በማፍራት ረገድ ከፍተኛ እንቅስቃሴ እያደረገ ነው።

በነጻ ለማውረድና ተከታታይ ቪዲዮዎች ለማግኘት
CloudLibrary.org ይጎብኙ


CloudLibrary

MESSENGER INTERNATIONAL
MessengerInternational.org


ይህ መጽሐፍ የደራሲው ስጦታ ነው
አይሸጥም

ሌላም ትፈልጋለህ?
እዚህ እስካን አድርግ